# በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ንጽጽራዊ ጥናት

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ

መርሐ ግብር

ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር የኤም ኤ ዲግሪ ማሟያ

የቀረበ ጥናት

ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

በ

ማናዬ እንግዳወርቅ

መስከረም፣2005 ዓ.ም

## አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ


የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ፣ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር


# በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ንጽጽራዊ ጥናት


በ

ማናዩ እንግዳወርቅ



ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY



መስከረም፣2005 ዓ.ም


## የፈተና ቦርድ አባላት ማረጋገጫ

| | |
|---|---|
| አማካሪ | ፊርማ |
| የውስጥ ፈታኝ | ፊርማ |
| የውጭ ፈታኝ | ፊርማ |


ADDIS ABABA UNIVERSITY
ILS LIBRARY

# ምስጋና


- ውድ ጊዜያቸውን በመሰዋት የጥናት ፅሁፌን ረቂቅ በማረምና በማስተካከል ያላሰለሰ ጥረት ላደረጉልኝ እንዲሁም አስፈላጊ መፃህፍትን በማዋስ ለተባበሩኝ መምህርቴና አማካሪዬ ወ/ሮ ሰላማዊት መካ እጅግ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡
- የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ይህንን ጥናት እንዳካሂድ የገንዘብ ድጋፍ ስላደረገልኝና የትብብር ደብዳቤ ስለጻፈልኝ አመሰግናለሁ፡፡
- ጥናቱን በማካሂድበት ወቅት መረጃዎችን በመስጠት ለተባበሩኝ ለደብረማርቆስ ከተማ የልዩ ልዩ መስሪያ ቤት ሀላፊዎች፣ በዋና መረጃ አቀባይነት ለተባበሩኝና ሌሎች መረጃ አቀባዮችንም በማገናኘት ከፍተኛ ሚና ለነበራቸው በተለይም ለመጋቢ አዕላፍ ጥበቡ የሽታ፣ ለመሪ ጌታ ሊባኖስ የተመኝ፣ ለቄስ ወልደ ትንሳኤ አለማየሁ፣ ለአቶ አህመድ ኑር ያሲን እና ለሼህ ሰይድ ቢላል ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡
- አቶ በላቸው መንግስቴ፣ አቶ እንድሪስ ሰይድ፣ መ/ር አሊ መሀመድ፣ አቶ በትግሉ በላይ፣ መምህር ተስፋው አወቀ፣ ተማሪ ነጃት መንሱር መፃሕፍትንና ልዩ ልዩ ቁሳቁሶችን በማዋስ፣ በሀሳብና በሞራል ድጋፍ ስላደረጋችሁልኝ በጣም አመሰግናችኋለሁ፡፡
- ወንድሜ ማናዬ ሞላ የሁልጊዜ ‹‹ጥናቱ እምን ላይ ደረሰ?›› ጥያቄህና የገንዘብ ድጋፍህ ስላልተለየኝ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው፡፡
- የጥናቱን ረቂቅ (አንዳንዴ ራሴ እንኳ ደግሜ ለማንበብ እቸገርበት የነበረውን ረቂቅ) ያለመታከት እያነበብሽ በኮምፒውተር ለጻፍሽልኝ ወ/ሮ አይናለም ከበደ ከፍ ያለ ምስጋና አቀርባለሁ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት ‹‹በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ንጽጽራዊ ጥናት›› በሚል ርዕስ የተሰራ ነው፡፡ ጥናቱ በተተኳሪው ህብረተሰብ ውስጥ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክንዋኔያቸው ምን ይመስላል? ክዋኔዎቻቸው ከሚመሩባቸው የሀይማኖታዊ መጻህፍት ጋር ያላቸው ግንኙነት እምን ድረስ ነው? የክዋኔዎቹ ትዕምርታዊነት ምንድን ነው? በሁለቱ ሀይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች መካከል አንድነት አለ? ልዩነትስ? የሚሉና የመሳሰሉ ጥያቄዎችን መነሻ አድርጓል፡፡ የጥናቱ አብይ አላማም የሁለቱን ሀይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ በንጽጽር ማሳየት ነው፡፡

ለጥናቱ የሚያስፈልጉ መረጃዎች በተፈጥሯዊ አውድ ውስጥ ተሳትፎአዊ ምልከታ በማድረግና ለጉዳዩ ቅርበት ያላቸውን ልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ቃለመጠይቅ በማድረግ በጽሁፍ፣ በመቅረፀ ድምጽ፣ በፎቶና በቪዲዮ ካሜራዎች ተሰብስበዋል፡፡ የተሰበሰቡት መረጃዎችም በአይነት በአይነት ተደራጅተው ተተንትነዋል፤ ተተርጉመዋል፡፡

በትንታኔው መሰረት በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች አብዛኞቹ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች ከሚመሩባቸው ሃይማኖታዊ አስተምህሮዎች (doctrines) የተቀዱ መሆናቸውን ጥናቱ አሳይቷል፡፡ የተወሰኑት ክዋኔዎች በልማድ የሚፈጸሙ መሆናቸውንም ለመረዳት ተችሏል፡፡ ይህ ጥናት የሁለቱን ሀይማኖት ተከታዮች የሚያመሳስሏቸውንና የሚያለያዩአቸውን የለቅሶ ስነስርአት ክንዋኔዎችንም በግልጽ አሳይቷል፡፡ በዚህ መሰረት በተለይም ከግንዘት፣ ከፍታት፣ አስከሬን አጅቦ ከመሄድ፣ ከአቀባበር አቅጣጫ ምርጫ ወዘተ. ጋር ተያይዘው በሁለቱ ሀይማኖት ተከታዮች መካከል ጎልተው የሚታዩ ልዩነቶች ተለይተው ታውቀዋል፡፡ በእድሜ፣ በጾታና በማህበራዊ ደረጃ ልዩነት ሳቢያ ለየት ያሉ ክዋኔዎች የሚፈጸሙባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉም በጥናቱ ሂደት ለማወቅ ተችሏል፡፡

## የምህጻረ ቃላት ዝርዝር

በዚህ ጥናት በተለይም በሦስተኛው ክፍል ውስጥ በብዛት የሚያጋጥሙ ምህጻረ ቃላት ከነፍቺያቸው እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

በደ/ማ/ከ/አስ/ግብርና ጽ/ቤት፡- በደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ግብርና ጽህፈት ቤት

የምስ/ጎ/ዞ/ገ/ኢ/ል/ቢሮ፡- የምስራቅ ጎጃም ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

የደ/ማ/ከ/አስ/ት/ጽ/ቤት፡- የደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽህፈት ቤት

የደ/ማ/ከ/አስ/መ/ኮ/ጉ/ጽ/ቤት፡- የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት

የደ/ማ/ከ/አስ/ገ/ኢ/ል/ቢሮ፡- የደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ

የደ/ማ/ከ/አስ/ጤ/ጥ/ጽ/ቤት፡- የደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር ጤና ጥበቃ ጽህፈት ቤት

# ማውጫ


ገጽ

ምስጋና ........................................................................ I

አጠቃሎ ........................................................................ II

1.መግቢያ ........................................................................ 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................ 2

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........................................................................ 3

1.3 የምርምር ጥያቄዎች ........................................................................ 4

1.4 የጥናቱ ዓላማዎች ........................................................................ 5

1.5 የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ መንገዶች ........................................................................ 6

1.6 የጥናቱ ወሰን ........................................................................ 7

1.7 የጥናቱ ውጤት ጠቀሜታ ........................................................................ 7

1.8 በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች .......... 8

2. ክለሳ ድርሳን ........................................................................ 11

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ........................................................................ 11

2.2 የፅንሰ ሐሳብ ቅኝት ........................................................................ 34

2.2.1 ሞት እና የለቅሶ ሥነሥርዓት ........................................................................ 34

2.2.2 ክዋኔ ........................................................................ 38

2.2.2.1 የመከወኛ አጋጣሚ ........................................................................ 39

2.2.2.2. ከዋኝ ........................................................................ 40

2.2.2.3. ታዳሚ ........................................................................ 40

2.2.2.4 አውድ ........................................................................ 41

2.2.2.4.1 ተጨባጭ አውድ ........................................................................ 41

2.2.2.4.2 ማህበራዊ አውድ ........................................................................ 42

2.2.2.5 የክዋኔ ጠቋሚዎች ........................................................................ 43

3. ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ዳራ................................................................ 44
3.1 የከተማዋ አመሰራረት.............................................................................. 44
3.2 የከተማዋ መልክዓ ምድራዊ ገፅታ........................................................... 45
3.3 የከተማዋ ህዝብ ቋንቋ፣ ሀይማኖትና አጠቃላይ ሁኔታ.............................. 46
3.3.1 የህዝቡ ቋንቋ........................................................................... 46
3.3.2 የሕዝቡ ሐይማኖት..................................................................... 46
3.4 ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች.......................................................................... 47
3.4.1 ንግድ..................................................................................... 47
3.4.2 መዋዕለ ንዋይ (ኢንቨስትመንት) ............................................... 47
3.4.3 መሠረተ ልማት......................................................................... 48
3.5 ማህበራዊ ሁኔታዎች............................................................................. 48
3.5.1 ትምህርት................................................................................ 48
3.5.1.1 ባህላዊ ትምህርት.............................................................. 48
3.5.1.2 ዘመናዊ ትምህርት............................................................. 49
3.5.2 ጤና........................................................................................ 49
4. በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔ.................................................................................... 51
4.1 የቅድመ ሞት ክዋኔ............................................................................. 52
4.1.1 የቅድመ ሞት ክዋኔ በክርስትና ዕምነት ተከታዮች....................... 53
4.1.2 የቅድመ ሞት ክዋኔ በእስልምና እምነት ተከታዮች....................... 55
4.2. ጊዜ ሞት ክዋኔ..................................................................................... 57
4.2.1 የክርስትና እምነት ተከታዮች የጊዜ ሞት ክዋኔ................................ 57
4.2.1.1 ስርዓተ ግንዘት.................................................................... 60
4.2.1.2 የጉዞ ስነስርአት................................................................... 65
4.2.1.3 ስርዓተ ቀብር..................................................................... 73
4.2.2 የእስልምና እምነት ተከታዮች የጊዜ ሞት ክዋኔ................................ 77
4.2.2.1 ስርአተ ግንዘት..................................................................... 79

4.2.2.2 የጉዞ ስነስርአት ........................................................ 82
4.2.2.3 ስርዓተ ቀብር ........................................................ 84
4.3. ድህረ ቀብር ክዋኔ........................................................ 86
4.3.1 የክርስትና እምነት ተከታዮች ድህረ ቀብር ክዋኔ........................ 86
4.3.2 የእስልምና እምነት ተከታዮች ድህረ ቀብር ክዋኔ........................ 94
5. በሁለቱ የሐይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ውስጥ የታዩ አንድነቶች (ተመሳሳይነቶች) እና ልዩነቶች ........................................97
5.1. አንድነቶች ተመሳሳይነቶች ........................................................ 97
5.2. ልዩነቶች ........................................................ 98
6. ማጠቃለያ እና ይሁንታ........................................................ 101
6.1 ማጠቃለያ........................................................101
6.2 ይሁንታ........................................................102
ዋቢ ጽሁፎች........................................................ 105

አባሪዎች

አባሪ አንድ- የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር ሁኔታ (ፕሮፋይል)

አባሪ ሁለት- ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ መንደርደሪያ ጥያቄዎች

# 1.መግቢያ

የሰው ልጅ በህይወት ዘመኑ የሚያጋጥሙትን ተድላና ደስታ በሳቅ፣ በፈገግታ፣ በጨዋታ፣ በዳንስ፣ በጭፈራ ወዘተ. ያንጸባርቃል፡፡ በአንፃሩ ሐዘኑን፣ ናፍቆት ትዝታውን፣ ረሃብ ጥማቱን፣ እርዛት ጉስቁልናውን፣ ህመሙን፣ ብሶቱን፣ ብቸኝነቱን ወዘተ. በማልቀስ ይገልፃል፡፡ በተለይም ደግሞ ‹የኔ› የሚላቸው ሰዎች-ወዳጅ ዘመዶቹ፣ ቤተሰቦቹና ሌሎች የማህበረሰቡ አባላት በሞት ሲለዩት ያዝናል፤ ያለቅሳል፡፡ ሀዘኑን የሚገልጽባቸው የለቅሶ ስነስርአቶችም እንደየባህሉ የተለያዩ ናቸው፡፡ ሥርዓቶቹ እንደየብሄረሰቡ ወግ፣ ልማድ፣ ባህልና ሀይማኖት ሊለያዩ ይችላሉ፡፡ ከለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች በመነሳት የማህበረሰቡንና የባህሉን ማንነትና ምንነት መናገር ይቻላል፡፡ የየትኛው ሀይማኖት የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ እንደሆነ መግለጽ የሚቻልባቸው አጋጣሚዎችም ይኖራሉ፡፡ ለምሳሌ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት ተከታዮች የራሳቸው የሆነ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ አላቸው፤ የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮችም እንደዚሁ፡፡

በወግ፣ በልማድ፣ በባህልና በሐይማኖት ሳቢያ በተለያዩ ማህበረሰቦች ዘንድ የሚፈፀሙ የለቅሶ ስርዓቶችና ክዋኔዎች በፎክሎር ጥናት ትኩረት ከሚደረግባቸው ጉዳዮች መካከል በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ በዚህ ጥናት በደብረማርቆስ ከተማና በአካባቢዋ የሚገኙ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔያቸው ምን እንደሚመስል እየተተነተነ በንፅፅር ይቀርባል፡፡

የጥናቱ አቀራረብ በስድስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፋፈለ ነው፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ይህ ‹‹መግቢያ›› የሚል ርእስ የተሰጠው ሲሆን በዚህ ክፍል የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የምርምር ጥያቄዎች፣ የጥናቱ አላማዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ መንገዶች፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ውጤት ጠቀሜታ፣ በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

ሁለተኛው ክፍል ‹‹ክለሳ ድርሳን›› የሚል ርእስ ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ ክፍል ‹‹የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት›› እና ‹‹የጽንሰ ሀሳብ ቅኝት›› የሚሉ ሁለት ንኡሳን ርእሶች ይገኛሉ፡፡ በመጀመሪያው ንኡስ ርዕስ ስር ዋነኛ ጉዳያቸውን የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ በማድረግ ለሁለተኛና ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናቶች፣ ከተለያዩ መጻህፍት ላይ የተገኙ ጽሁፎችና ለልዩ ልዩ ሴሚናሮች የቀረቡ ጥናቶች ተቃኝተዋል፡፡ በሁለተኛው ንኡስ ርዕስ

ስር ደግሞ ከለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ ጽንሰ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

ሦስተኛው ክፍል ጥናቱ የተካሄደበትን አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ ለማሳየት የተሞከረበት ነው፡፡ በዚህ ክፍል የከተማዋ አመሰራረት እና መልክዓ ምድራዊ ገጽታ፣ የህዝቡ ቋንቋ፣ ሀይማኖት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

አራተኛው ክፍል በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የክርስትናና የእስልምና እምነት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ የቀረበበት ነው፡፡ የሁለቱ ሀይማኖት ተከታይ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች እየተተነተኑ በንጽጽር ቀርበዋል፡፡

አምስተኛው ክፍል በሁለቱ የሐይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ውስጥ የታዩ አንድነቶች (ተመሳሳይነቶች) እና ልዩነቶች ጠቅለል ተደርገው የቀረቡበት ነው፡፡ ስድስተኛው ክፍል ደግሞ የማጠቃለያ ሀሳብ የቀረበበት ነው፡፡ በዚህ ክፍል ጥናቱ ባለፈባቸው ሂደቶች ውስጥ የተገኙ ውጤቶች ተጠቃለው ቀርበዋል፤ የይሁንታ ሃሳቦችም ተሰንዝረዋል፡፡ በመጨረሻም ዋቢ ጽሁፎችና ልዩ ልዩ አባሪዎች ቀርበዋል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

አንዳንድ መዛግብት እንደሚያመለክቱት በአሁኑ የአማራ ክልል ከ10ኛው ክ/ዘመን መባቻ ጀምሮ የኦርቶዶክስ ክርስትና ሐይማኖት ተከታዮች ይኖሩ ነበር (የአማራ ህዝብ ባህልና ቋንቋ፣ 2001፣ 19)፡፡ በዚሁ ክልል አንዳንድ ክፍሎች ‹‹ከ10ኛው መቶ አመት መጨረሻ ጀምሮ ሙስሊሞች ይኖሩ እንደነበርም ይታወቃል›› (ተመሳሳይ ምንጭ፣ ገጽ 24)፡፡ ከዚያ ወዲህ፣ ከስፍራ ስፍራ ይለያይ እንጂ የሁለቱ ሃይማኖት ተከታዮች በሁሉም የክልሉ ዞኖችና ወረዳዎች መኖር ጀምረዋል፡፡ ደብረማርቆስም እንደሌሎች የክልሉ ዞኖችና ወረዳዎች ሁሉ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች በህብረት የሚኖሩባት ከተማ ናት፡፡ በከተማዋ ውስጥ የሚኖሩ የክርስትናና የእስልምና ሃይማኖት ተከታይ ህብረተሰቦች ህፃናት በእናቶቻቸው ማህፀን ከነበሩበት ጊዜ ጀምሮ ተወልደው ‹ሰው› እስከሚሆኑበት ጊዜ ድረስ የሚፈፅሟቸው (የሚያከናውኗቸው) ልዩ ልዩ ማህበራዊ፣ ባህላዊና ሀይማኖታዊ ድርጊቶች አሉ፡፡ የአወላለድ፣ የአገራረዝ፣ የአመጋገብ፣ የአለባበስ፣ የአስተዳደግ፣ የጋብቻና የመሳሰሉ ስነስርአቶቻቸውን ለአብነት ማንሳት ይቻላል፡፡ እነዚህ ስነስርአቶች ከህብረተሰቡ የአኗኗር

ዘይቤ፣ አመለካከትና ፍልስፍና የሚቀዱ ክዋኔዎች ናቸው፡፡ ሕብረተሰቡ ሰው ሲሞት ሀዘኑን ለመግለጽ የሚጠቀምባቸው ልዩ ልዩ ልማዳዊ ክዋኔዎችና የለቅሶ ስነስርአቶችም ከራሱ መንጭተው እራሱ የሚጠቀምባቸውና ከሌላው ህብረተሰብም ተለይቶ የሚታወቅባቸው መ ለያዎቹ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ሥር አቶች ደግሞ ከየሀይማኖቶቹ አስተምህሮዎች (doctrines) የሚቀዱ ናቸው፡፡ በመሆኑም የስነስርአቶቹ ዋነኛ ምንጮች በአብዛኛው መፅሀፍ ቅዱስ ወይም ቅዱስ ቁርአን ይሆናሉ፡፡ ለምሳሌ አንድ ሰው ከሞተ በኋላ የሚደረጉለት የጸሎት ስነስርአት ክዋኔዎች ለሁለቱም ሀይማኖት ተከታዮች መጽሀፋዊ (መጽሀፍ ቅዱሳዊ /ቅዱስ ቁርአናዊ) መነሻ አላቸው፡፡ ይህም የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች ህብረተሰቡ ይሁነኝ ብሎ ከያዘው (ከሚከተለው) ሀይማኖታዊ ትምህርት ሊቀዱ የሚችሉ መሆናቸውን የሚያስረግጥልን ነው፡፡

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

በደብረማርቆስ ከተማና አካባቢ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎችን የሚመለከቱ ልዩ ልዩ የመጀመሪያና የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች ተደርገዋል፡፡ ለምሳሌ ያህል የልጆች ጨዋታ አይነቶችን፣ አዋቂዎችንና የጥንቆላ ስራዎቻቸውን፣ የሀገረሰባዊ መድሃኒት ቅመማን፣ የገበሬዎችን የሥራ እንቅስቃሴና የመሳሰሉ ጉዳዮችን በሚመለከት በተለያዩ ጊዜያት ጥቂት የማይባሉ ጥናቶች ቀርበዋል (ዝማም ተበጀ፣ 1991፤ የውልሰው ላለለት፣ 1992፤ ደሳለኝ ካሳ፣ 1979፤ ጌትነት ዋለ፣ 1990 ወዘተ.)፡፡ ይሁን እንጂ አንድ ሰው ሲሞት የከተማዋ ህብረተሰብ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ምን እንደሚመስል ለማሳየት የተደረገ ጥናት አላጋጠመኝም፡፡

በአብዛኛው የሀገራችን ህብረተሰብ ዘንድ ሰው ሲሞት በተለያዩ መንገዶች እያለቀሱ የቀብር ስነስርአቱን መፈፀም የተለመደና የሚመሳሰል ጉዳይ ሊሆን ይችላል፡፡ በለቅሶ እያጀቡ የቀብር ስነሰርአትን መፈፀም ያመሳስለው እንጂ እንደየማህበረሰቡ ባህል፣ ወግ፣ ልማድ፣ ሃይማኖት ወዘተ. ደግሞ ልዩነት ይኖራል፡፡ ልዩነቱ በእድሜ፣ በፆታ፣ በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ደረጃ (ደሃ፣ ባለፀጋ፣ የተማረ፣ ያልተማረ...)፣ ወዘተ. ምክንያቶች የሚመጣ ሊሆን ይችላል፡፡

በዚህ ጥናት ተተኳሪ የሆኑት የደብረማርቆስ ከተማና አካባቢ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች እንደሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ሁሉ ተለይተው የሚታወቁበት የራሳቸው የሆነ የለቅሶ

ስነስርአት ክዋኔ አላቸው፡፡ በተለይም የኦርቶዶክስ ክርስትና ሐይማኖት ተከታይ የሆነው የህብረተሰብ ክፍል ወዳጅ ዘመዶቹ፣ ቤተሰቦቹና ሌሎች የህብረተሰቡ አባላት በሞት ሲነጠሉ እንደሁኔታው ሙሾ እየወረደ፣ ደረቱን እየደቃ፣ ፊቱን እየቧጨረ፣ ፀጉሩን እየነጨ ወዘተ. ሐዘኑን ይገልፅ እንደነበረ አውቃለሁ፡፡ የሙስሊሙ ህብረተሰብስ ሐዘኑን እንዴት ይሆን የሚገልጸው? ክዋኔውስ እንዴት ያለ ይሆን? የሚለው የሁልጊዜ ጥያቄዬ ነበር፡፡ በሁለቱ የሐይማኖት ተከታይ ህብረተሰቦች የሚፈፀሙትን የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች ለማወቅ የነበረኝ ፍላጎት ለዚህ ጥናት መደረግ መነሻ ምክንያት ሆኖኛል፡፡

በለቅሶ ስነስርዓት ወቅት የሚደረጉ ልዩ ልዩ ክዋኔዎች ትዕምርታዊነታቸው ምንድን ነው? ለየሐይማኖቶቹ ዋነኛ መሰረት ከሆኑት መፅሐፍ ቅዱስና ቅዱስ ቁርአን ጋር ያላቸው ግንኙነትስ እስከምን ድረስ ነው? በመካከላቸውስ አንድነት ይኖር ይሆን? ልዩነታቸውስ ምን ያህል ነው? እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉት ጥያቄዎችም ለዚህ ጥናት መደረግ እንደመነሻ ከሆኑኝ ምክንያቶች ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው፡፡

በሌላ በኩል የሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች ስለሞትና መለየት ያላቸው አመለካከትና ግንዛቤ ምን ይመስላል? እንዴትስ ይገለፃል? ለሚሉት ጥያቄዎች መልስ በመሻት ይህን ጥናት ለማድረግ ተነሳስቻለሁ፡፡

## 1.3 የምርምር ጥያቄዎች

በደብረማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ቅደም ተከተላዊ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔያቸው ምን ይመስላል? የሚለው በዚህ ጥናት ከሚመለሱ ጥያቄዎች መካከል በዋናነት የሚጠቀስ ነው፡፡ በዚህ አብይ ጥያቄ ስር የሚነሱና ምላሽ የሚሰጣቸው ንዑሳን የምርምር ጥያቄዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ለሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች በሞት መለየት ምንድን ነው? ለሞትና ለመለየት የሚሰጡት ትርጓሜ ምን ይመስላል?
- የሁለቱ ሀይማኖት ተከታዮች በለቅሶ ስነስርዓታቸው የሚከውኗቸው ክዋኔዎች ትእምርታዊነታቸው ምንድን ነው?

- የሁለቱ ሀይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች ከሚመሩባቸው ቅዱሳን መጻሀፍት ( ከመፅሀፍ ቅዱስ ወይም ከቅዱስ ቁርአን ) ጋር ያላቸው ግንኙነ ት እስከምን ድረስ ነው?
- በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች መካከል አንድነት አለ? ልዩነትስ?
- በሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች ዘንድ በእድሜ፣ በጾታ፣ በማእረግ (በደረጃ) ወዘተ. ሳቢያ የተለየ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ የሚደረግላቸው ሰዎች አሉ?

በዚህ ጥናት ለነዚህ የምርምር ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ጥረት ተደርጓል፡፡

## 1.4 የጥናቱ ዓላማዎች

የዚህ ጥናት ዋነኛ ዓላማ በደብረማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች ቅደም ተከተላዊ የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔያቸው ምን እንደሚመስል በንፅፅር ማሳየት ነው፡፡ ጥናቱ የሚከተሉትን ንኡሳን ዓላማዎችንም አካቷል፡፡

- በከተማዋና በአካባቢዋ የሚገኙ የክርስ ትናና የእስልምና ሐይማኖ ት ተከታዮች በክዋኔዎቻቸው አማካይነት ስለ ሞት ያላቸውን አመለካከት መግለፅ
- የሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች በለቅሶ ስነስርአቶቻቸው ውስጥ የሚከውኗቸውን ልዩ ልዩ ክዋኔዎች ትርጉም መግለፅ
- በሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ውስጥ ሀይማኖታዊ ክዋኔዎችን ከባህላዊ(ልማዳዊ) ክዋኔዎች ለይቶ ማሳየት
- በሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች የሚፈፀሙ የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔዎችን በጥልቀት በመመርመር በመካከላቸው ያለውን አንድነትና ልዩነት ማመልከት
- በሁለቱም ሐይማኖት ተከታዮች ዘንድ ለእነማን ሞት ምን አይነት የተለየ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ እንደሚደረግ መግለፅ

## 1.5 የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ መንገዶች

ከፍ ብሎ የተዘረዘሩትን አላማዎች ከግብ ለማድረስ የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም መረጃዎችን መሰብሰብና መተንተን ተገቢም አስፈላጊም ነው፡፡ የመስክ ምርምር በልዩ ልዩ መንገዶች ሊካሄድ ይችላል፡፡ ከነዚህ መንገዶች መካከል ምልከታ፣ ቃለመጠይቅ እና የጽሁፍ መጠይቅ በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው፡፡ የመስክ ምርምር በብዙ ሙያተኞች ዘንድ አስፈላጊና ዋና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ነው (ፈቃደ፣ 1991፣90 ፤ አለም፣1994፣43)፡፡ ይሁን እንጂ የመስክ ስራን የተቃናና የተሳካ እንዲሆን ለማስቻል አስፈላጊ የሚባሉ ቅድመ መስክ ዝግጅቶችን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መሰረት እኔም ወደመስክ ከመሄዴ በፊት ከዚህ የጥናት ርዕስ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ልዩ ልዩ ጥናቶች ከአብያተ መጻህፍት ውስጥ በማንበብ ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን ሰብስቤያለሁ፡፡ ስለአካባቢው የሚያወሱ መጻህፍትንም በማንበብ አስፈላጊ መረጃዎችን ይዣለሁ፡፡ ለቀረጻና ለፎቶግራፍ ማንሻ የሚሆኑኝን መሳሪያዎችና ሌሎች ቁሳቁሶችንም ቀደም ብዬ አዘጋጅቻለሁ፡፡ ከእነዚህ ሁሉ ቅድመ ዝግጅቶች በኋላ ነው እንግዲህ ለመስክ ምርምር ጉዞ የአደረግሁት፡፡

መረጃዎችን የሰበሰብኩት በሁለት ዙር የመስክ ምርምር ነው፡፡ የመጀመሪያውን ዙር የመስክ ምርምር የአደረግኩት ከጥር 15፣2004 ዓ.ም እስከ ጥር 24፣ 2004 ዓ.ም ድረስ ሲሆን፣ የሁለተኛውን ዙር ምርምር ደግሞ ከግንቦት 24፣ 2004 ዓ.ም እስከ ሰኔ 5፣ 2004 ዓ.ም ድረስ አካሂጃለሁ፡፡ መስክ ላይ በቆየሁባቸው በነዚህ ጊዜያት (ከጥር 15፣2004 ዓ.ም እስከ ጥር 24፣ 2004 ዓ.ም እና ከግንቦት 24፣ 2004 ዓ.ም እስከ ሰኔ 5፣ 2004 ዓ.ም) ከመጠይቅ በስተቀር ሌሎቹን የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ተጠቅሚያለሁ፡፡ በጽሁፍ ለመያዝ አመቺ የሆኑ መረጃዎችን በማስታወሻ ደብተሬ በመጻፍ፣ ሌሎች መረጃዎችን ደግሞ በምስልና በድምጽ መቅረጫ መሳሪያዎች (ቪዲዮ ካሜራ፣ መቅረጸ ድምጽ (ቴፕ) እና ፎቶ ካሜራ) በመታገዝ ቀርጬ ይዣለሁ፡፡ መረጃዎችን ተፈጥሯዊውን አውድ በመጠቀም ለመሰብሰብ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ የህብረተሰቡ አባል በመሆኔም ክዋኔዎቹን በተሳትፎአዊ ምልከታ ለመከታተል ችያለሁ፡፡

በተለይም በመጀመሪያው ዙር የመስክ ቆይታዬ በከተማዋ የተለያዩ ቀበሌዎች በመዘዋወርና አላማዬን በማስረዳት ፈቃደኛ የሆኑልኝን ሀያ ሁለት መረጃ አቀባዮች ቃለመጠይቅ አድርጌያለሁ፡፡ ስምንቱ ቁልፍ መረጃ አቀባዮች ሲሆኑ አስራ አራቱ ደግሞ ንኡሳን መረጃ

አቀባዮች ናቸው፡፡ እነዚህን ሃያ ሁለት መረጃ አቀባዮች የመረጥኩት የታላሚ ናሙና (purposive sampling) በመጠቀም ነው፡፡ መረጃ አቀባዮቹ የለቅሶ አፈጻጸም ስነስርአቱን፣ ሀይማኖቱን እና በአጠቃላይም ባህሉን በበቂ ሁኔታ ያውቃሉ የተባሉና ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ናቸው፡፡ ካህናት፣ ኡለማዎች፣ የእድሜ ባለጸጎች፣ መምህራን፣ አርሶአደሮች፣ ነጋዴዎችና የቤት እመቤቶች ቃለመጠይቅ ተደርጎላቸዋል፡፡ ለነዚህ መረጃ አቀባዮች አስቀድሜ ያዘጋጀኋቸውን ጥያቄዎች በመጠየቅ ምላሻቸውን እንዲሰጡኝ አድርጌያለሁ፡፡ አንዳንዴም ለውይይት ይበጃሉ የምላቸውንና በቃለ መጠይቁ ወቅት የሚፈልቁ አዳዲስ ሀሳቦችን በማንሳት መረጃዎችን በበቂ ሁኔታ ለመሰብሰብ ችያለሁ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱትን የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች እያደጋገፍኩና እያስማማሁ ለመጠቀም ሞክሬአለሁ፡፡ የአንደኛውን የመረጃ መሰብሰቢያ መንገድ ክፍተት በሌላኛው በሚሟላት የተሟላ መረጃ ለማግኘት ጥረት አድርጌያለሁ፡፡ የተገኙትንም መረጃዎች ክዋኔን ማእከል ባደረገ ዘዴ ተንትኛለሁ፡፡

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት በደብረማርቆስ ከተማና በአካባቢዋ የሚገኙ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች በሚያደርጉት የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ላይ ትኩረት ሰጥቶ የተካሄደ ነው፡፡ በከተማዋና በአካባቢዋ የሚኖሩ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ክርስትና ሐይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ከእስልምና ሐይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ጋር በማነፃፀር አመለክታለሁ፡፡ ስለዚህ ጥናቱ የሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች በሚያደርጉት የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ላይ ብቻ የተወሰነ ነው፡፡ የሌላ ሐይማኖት ተከታይ የህብረተሰብ ክፍሎች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች በዚህ ጥናት ውስጥ አልተካተቱም፡፡

## 1.7 የጥናቱ ውጤት ጠቀሜታ

የዚህ ጥናት ውጤት የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታመናል፡፡

1. የዚህ ጥናት ዋነኛ ትኩረት በደብረማርቆስ ከተማና በአካባቢዋ የሚገኙ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔያቸው ምን እንደሚመስል ማሳየት ነው፡፡ ይሁን እንጂ ጥናቱ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የአካባቢውን መልክአ

ምድራዊ አቀማመጥ፣ የአየር ንብረት፣ የአስተዳደር ሁኔታና የህብረተሰቡን ልዩ ልዩ እሴቶች በተጓዳኝነት መነካካቱ አይቀርም፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት የተተኳሪውን ህብረተሰብ ማንነት በማስተዋወቅ ረገድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡

2. በከተማዋና አካባቢዋ የሚገኙ የሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔያቸው ምን እንደሚመስል ያሳያል፤ በክዋኔዎቻቸው መካከል ያሉትን አንድነቶችና ልዩነቶች ፍንትው አድርጎ ያሳያል፡፡
3. የሁለቱም ሀይማኖት ተከታዮች ከሚያከናውኗቸው የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች ውስጥ ባህላዊ የሆኑትን ስርአቶች ከሐይማኖታዊ ስርአቶች ነጥሎ በግልፅ ያስገነዝባል፤ የክዋኔዎቹ ትርጉም ምን እንደሆነም ከመፅሀፍ ቅዱስና ከቅዱስ ቁርአን ጋር በማጣቀስ ግንዛቤ ያስጨብጣል፡፡
4. ይህ ጥናት የተተኳሪውን ህብረተሰብ ምሉዕ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ያሳያል የሚል እምነት የለኝም፡፡ ጥናቱ በተለይም የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችን እና የሙስሊሞችን የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ለማሳየት የተደረገ ውጥን ስራ ነው፡፡ በመሆኑም ወደፊት የአካባቢውን ህብረተሰብ የለቅሶ ስነስርአትም ሆነ አጠቃላይ ባህሉን፣ ወጉን፣ ማንነቱን ወዘተ. ሰፋ ባለ ሁኔታ ለሚያጠኑ ተመራማሪዎች የመነሻ ሃሳብ ይሰጣል የሚል እምነት አለ፡፡

## 1.8 በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

ይህን ጥናት በማካሂድበት ወቅት የተለያዩ ችግሮች አጋጥመውኛል፡፡ አብዛኞቹ ችግሮች ከጥናቴ ርእሰ ጉዳይ ጋር የሚያያዙ ናቸው፡፡ የጥናቴ ዋነኛ ትኩረት የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ላይ እንደመሆኑ ትክክለኛ ለቅሶ ማግኘትና ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ድረስ የሚከናወኑ ድርጊቶችን መመልከትና መረጃዎችን መያዝ ይጠበቅብኛል፡፡ ይሁን እንጂ በተለይ በመጀመሪያው ዙር የመስክ ቆታዬ ሙሉ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ለማግኘትና ለመመልከት በጣም ተቸግሬ ነበር፡፡ ምክንያቱም በአካባቢው ህብረተሰብ ዘንድ ለቅሶ መኖሩ የሚታወቀው በዋናነት ንጋት ላይ በሚነፋ ጥሩንባ አማካይነት ነው፡፡ አስከሬንም ወደቀብር ቦታ የሚወሰደው በጠዋት ነው፡፡ በአንድ አካባቢ ላይ ያለን የጥሩንባ ድምጽ ሌላ ቦታ ላይ ሆኖ ማዳመጥ ምን ያህል አስቸጋሪ እንደሚሆን መገመት ይቻላል፡፡ በተለይም ደግሞ የእስልምና እምነት ተከታዮች ሙታቸውን ቶሎ ወደቀብር ቦታ መውሰዳቸው ስራዬን አስቸጋሪ አድርጎት ነበር፡፡ እንደመፍትሄ ለቤተሰቦቼ፣ ለድሮ

ጓደኞቼና ለመረጃ አቀባዮቼ ሰው መሞቱን ሲያውቁ ወዲያውኑ እንዲያሳውቁኝ መንገርና አደራ ማለት ነበረብኝ፡፡ በዚሁ መሰረት ብዙዎቹ ለቅሶ ሲያጋጥማቸው በተለያዩ መንገዶች ቢያሳውቁኝም ከአለሁበት ቦታ ለቅሶ አለ ከተባለበት ቦታ እስከምደርስ ድረስ ብዙ ክዋኔዎች ያመልጡኛል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የምደርሰው አስከሬኑን ይዘው ወደቀብር ቦታ ሲጓዙ ወይም የቀብር ቦታ ላይ ከደረሱ በኋላ ወይም ከተቀበረ በኋላ ነበር፡፡ ያም ሆኖ የደረስኩበትን ክዋኔ እመለከታለሁ፣ መረጃ እሰበስባለሁ፡፡ በመጀመሪያው ዙር የመስክ ቆይታዬ በተለይም በቪዲዮ ካሜራ ቀርጬ የያዝኳቸው የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች ፍሰታቸውን ጠብቀው ከመጀመሪያ እስከመጨረሻ ያለውን ሂደት የሚያሳዩ አይደሉም፡፡የተቆራረጡ ናቸው፡፡

በቃለ መጠይቅ፣ በቪዲዮ ቀረጻ እና በፎቶግራፍ ማንሳት ወቅትም ችግሮች አጋጥመውኝ ነበር፡፡ ቃለመጠይቅ ለማድረግ ያነጋገርኳቸው አንዳንድ መረጃ አቀባዮች ቀጠሮ ከአሲያዙኝ በኋላ የተቃጠርንበትን ሰአት ጠብቀው ያለመምጣት ችግር ሲያጋጥመኝ ነበር፡፡ ይህን ችግር ለመቅረፍ ከወሰድኳቸው እርምጃዎች መካከል አንዱ ከቀጠሮ ሰአቴ ውጭ ለረጅም ሰዓት በመጠበቅ ማግኘትና አላማዬን ማሳካት ነው፡፡ ከአንዳንዶቹ ጋር ደግሞ ተለዋጭ ቀጠሮ ይዤ በዚሁ መሰረት ቃለመጠይቅ አድርጌላቸዋለሁ፡፡ በሌላ በኩል ‹‹አሁን ይሄ ተጠንቶ ምን ይሰራል?›› በሚል ምክንያት አንዳንድ መረጃ ሰጪዎች ለቃለመጠይቅ ፍጹም ፍቃደኛ ያለመሆን ችግርም አጋጥሞኛል፡፡ ስለዚህ በነዚህ ሰዎች ፋንታ ሌሎች መረጃ አቀባዮችን ለመጠቀም ተገድጃለሁ፡፡

በአካባቢው የለቅሶ ስነስርአትን በቪዲዮ መቅረጽም ሆነ በፎቶ ካሜራ ማንሳት ብዙም የተለመደ ባለመሆኑ ምክንያትም ችግሮች አጋጥመውኝ ነበር፡፡ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔን በቪዲዮ መቅረጽ ወይም ፎቶግራፍ ማንሳት ሀዘንተኞችን እንደመናቅና በሀዘናቸውም እንደመደሰት ስለሚቆጠር እንዳልቀርጽ በሟች ቤተሰቦች የምከለከልባቸው አጋጣሚዎች ብዙ ነበሩ፡፡ ሆኖም ተሰሚነት ላላቸው ሽማግሌዎች፣ ለእድሮቹ ሊቃነመናብርት እና ለሟቹ የነፍስ አባት ዩኒቨርስቲው የጻፈልኝን የትብብር ደብዳቤ በማሳየትና አላማዬን በማስረዳት ለችግሮቹ የመፍትሄ አካል እንዲሆኑ አድርጌአቸዋለሁ፡፡ ይህን የመፍትሄ እርምጃ የተጠቀምኩት በክርስትና እምነት ተከታዮች ለአጋጠሙኝ እንቅፋቶች ነው፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮች ‹‹በእኛ እምነት ቪዲዮ መቅረጽም ሆነ ፎቶግራፍ ማንሳት

ሀራም ነው›› የሚል ቁርጥ ያለ መልስ ስለሰጡኝ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔያቸውን በቪዲዮም ሆነ በፎቶ ካሜራ ለመያዝ የአደረግኩት ተደጋጋሚ ሙከራ አልተሳካልኝም፡፡

ለቀረጻ ይገዐው የሄድኩት ቪዲዮ ካሜራ በራሱ አንድ እንቅፋት ሆኖብኝ ነበር፡፡ ካሜራው ትንሿን ዲቪዲ (Mini DVD) የሚቀበል ነው፡፡ ይህን ካሜራ ያዋሰኝ ጓደኛዬ አጠቃቀሙን በደንብ ካሳየኝ በኋላ ሁለት ባዶ ዲቪዲዎችን እንድጠቀምባቸው ሰጠኝ፡፡ ዲቪዲዎቹ እያንዳንዳቸው ሰላሳ ሰላሳ ደቂቃ ብቻ ለመቅረጽ የሚያስችሉ ስለሆኑና እንደማይበቁኝ ስለማውቅ ከዚሁ ከአዲስ አበባ ተመሳሳይ ስድስት ዲቪዲዎችን እያንዳንዱን በብር 90(ዘጠና ብር) ሂሳብ በመግዛት ይገዐ ሄድኩ፡፡ ጓደኛዬ የሰጠኝን ዲቪዲዎች ከቀረጽኩባቸው በኋላ የገዛኋቸውን ዲቪዲ ዎች ለመ ጠቀም ስሞክር ሁሉም ሊሰሩልኝ አልቻሉም፡፡ ባለሙያዎችም ችግሩን ማወቅ አልቻሉም፡፡ ችግሩ ከዲቪዲው ሊሆን እንደሚችል ስለነገሩኝ ሌላ ዲቪዲ በእዚያው በከተማ ውስጥ ብፈልግ ባስፈልግ ማግኘት አልቻልኩም፡፡ ወቅቱ ሰርግ የሚበዛበት ጊዜ ስለነበረ ካሜራ የሚያውሰኝ ሰው አላገኘሁም፡፡ ከፎቶ ቤት ለመከራየትም ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ ጠየቁኝ፡፡ ስለዚህ ለዚህኛውና ለሌሎችም ችግሮች መፍትሄ ለመስጠት ሌላ ጊዜ በድጋሚ የመስክ ጉዞ ለማድረግ ውሳኔ ላይ መድረስ ነበረብኝ፤ ወሰንኩ፡፡ ውሳኔዬ ትክክል ነበር፡፡ ምክንያቱም አንደኛ በቆየሁባቸው ጊዜያት ሙሉ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ለመመልከት እድል አላገኘሁም፡፡ ሁለተኛ በመመላለስ ለትራንስፖርት የማወጣው ገንዘብ ለካሜራ ኪራይ ከተጠየቅሁት አንጻር ሲታይ በጣም ትንሽ ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ እየቆዩ ለሚፈጠሩ ጥያቄዎች መልስ ለመሻት ወደመስክ ተመልሶ መሄዱ ተመራጭ ነበር፡፡ በዚህ መሰረት አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶችን ከአደረግሁ በኋላ ግንቦት 24፣ 2004 ዓ.ም ጠዋት በህዝብ ማመላለሻ አውቶቢስ የመስክ ጉዞዬን ጀመርኩ፡፡ ሆኖም ከአዲስ አበባ ትንሽ እንደወጣን የተሳፈርኩበት መኪና በፊት ለፊቱ ከሚመጣ ከባድ መኪና ጋር ተጋጨ፡፡ በግጭቱ ምክንያት በአንድ ሰው ላይ ቀላል ጉዳት ከመድረሱ በስተቀር በሌሎቻችን ላይ ምንም አይነት ጉዳት ሳይደርስ በሰላም ተርፈናል፡፡ በመትረፌ ፈጣሪዬን እያመሰገንኩ በሌላ መኪና ተሳፍሬ የመስክ ጉዞዬን ቀጠልኩ፡፡

በሁለተኛው ዙር የመስክ ቆይታዬ ስሜንና ስልክ ቁጥሬን የያዙ እንደ “Business Card” ያሉ ትናንሽ ወረቀቶችን አዘጋጅቼ የሰው መሞትን ሲሰሙ ‹‹ምልክት እንዲያደርጉልኝ›› (‹‹Missed call እንዲያደርጉልኝ››) አግባብቻቸው ፍቃደኛ ለሆኑልኝ ብዙ ሰዎች

ሰጠኋቸው፡፡ ይህ ሙከራዬ ተሳክቶ በተለያዩ ጊዜያት በልዩ ልዩ የለቅሶ ስነስርአቶች ላይ አስከሬን ከቤት ሳይወጣ በመድረስ እስከ ቀብር ፍጻሜ ድረስ ያሉ ክዋኔዎችን በመመልከት፣ ቪዲዮ በመቅረጽና ፎቶ በማንሳት መረጃዎችን ልይዝ ችያለሁ፡፡

## 2. ክለሳ ድርሳን

### 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

በዚህ ንኡስ ክፍል ከኔ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር በሐሳብ ተዛማጅ የሆኑ ልዩ ልዩ ፅሁፎችን እቃኛለሁ፡፡ በርግጥ በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ሥነሥርዓት ክዋኔያቸው ምን እንደሚመስል ለማሳየት የተደረገ ጥናት አላጋጠመኝም፡፡ ይሁን እንጂ ትኩረታቸውን በሌሎች አካባቢዎች የለቅሶና የቀብር ስነስርዓት ላይ እንዲሁም በተያያዥነት በለቅሶ ስነስርዓት ጊዜ በሚደረደሩ የቀረርቶ፣ የፉከራና የሙሾ ግጥሞች ላይ ትኩረት ያደረጉ ቁጥራቸው በዛ ያሉ ጥናታዊ ፅሁፎች ተገኝተዋል፡፡ ከነዚህ መካከል ዋነኛ ጉዳያቸውን የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔ ላይ ያደረጉ ጥናታዊ ጽሁፎች ይቃኛሉ፡፡ የቅኝቱ ዋና አላማ ርዕሰ ጉዳዮቹ እንዴት እንደተዘጋጁ፣ የትኩረት አቅጣጫቸው ምን እንደሚመስልና ከዚህ የጥናት ጽሁፍ ጋር ያላቸው ተመሳስሎና ልዩነት ምን እንደሆነ ማመልከት ነው፡፡

በቅድሚያ ትኩረታቸውን የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔ ላይ አድርገው ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተዘጋጁ ጥናታዊ ፅሁፎችን እንቃኛለን፡፡ በመቀጠል በትግራይ፣ በአማራ ክልል ሸዋ ዞን እና በሀረር ክልል የተለያዩ አካባቢዎች የሚኖሩ የህብረተሰብ ክፍሎች የለቅሶና የቀብር ስነስርዓታቸው ምን እንደሚመስል ለማሳየት የተለያዩ ምሁራን ለሴሚናር ያዘጋጇቸውን ፅሁፎች እንመለከታለን፡፡ ከዚያም «የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሎች» ከተሰኘው መጽሐፍ ላይ በለቅሶ ስነስርአት ዙሪያ የተፃፈውን ጽሁፍ እንመለከታለን፡፡ በመጨረሻም ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናታዊ ጽሁፎችን እንቃኛለን፡፡

ሁሉንም ጥናታዊ ፅሁፎች ያቀረብኩት በተዘጋጁበት ዘመን ቅደም ተከተል መሰረት ነው- በቅርብ ዘመን ከተሰሩ ጥናታዊ ጽሁፎች ጀምሬ ወደኋላ በመመለስ፡፡ በተመሳሳይ ዘመን ተሰርተው የተገኙ ጥናታዊ ጽሁፎችን በአጥኚዎቹ ስም ፊደል ተራ ቅደም ተከተል መሠረት እንዲቀዳደሙ አድርጌአቸዋለሁ፡፡

ቅኝታችንን ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ተዘጋጅተው በቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎች እንናስቀድምና እንጀምር፡፡ በዚህ ደረጃ የተገኙ ጥናታዊ ጽሁፎች ሶስት ናቸው፡፡ ሶስቱም ለኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት የቀረቡ ናቸው፡፡

ዘላለም ፋንቱ መስከረም፣ 2004 ዓ.ም ‹‹የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ›› በሚል ርዕስ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቱን አቅርቧል፡፡ ጥናቱ በአምስት ዋና ዋና ክፍሎች የተከፈለ ነው፡፡ መግቢያ የሚል ርዕስ በሰጠው በጥናቱ የመጀመሪያ ክፍል ውስጥ የጥናቱን ዳራ፣ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፣ የምርምር ጥያቄዎቹን፣ የጥናቱን ዓላማዎች፣ የመረጃ መሰብሰቢያና መተንተኛ መንገዶች፣ የጥናቱን ወሰን፣ የጥናቱን ውጤት ጠቀሚታ እና በጥናቱ ሂደት ያጋጠሙትን ችግሮችና የወሰዳቸውን የመፍትሄ እርምጃዎች በዝርዝር አቅርቧል፡፡

‹‹ክለሳ ድርሳን›› የሚል ርዕስ በሰጠው በጥናቱ ሁለተኛ ክፍል ውስጥ ሁለት ዓይነት ቅኝት አካሂዷል-የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት እና የንድፈ ሐሳብ ቅኝት፡፡ ዘላለም የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት ባደረገበት ንኡስ ክፍል ውስጥ ትኩረታቸውን የለቅሶ እና የቀብር ስነስርዓት ላይ ያደረጉ ስምንት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የተዘጋጁ ጥናታዊ ፅሁፎችን፣ አንድ ለሁለተኛ ዲግሪ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፣ አንድ ‹‹ሲዳማ… ሕዝብና ባህል›› በሚል ርዕስ የተዘጋጀ መፅሀፍ እና በ"Ethnological Society Bulletin" የወጡ በተለያዩ ክልሎች የሚደረጉትን የቀብርና የለቅሶ ስነስርአቶች የሚያትቱ አራት ፅሁፎችን ተመልክቷል፡፡ ትኩረታቸውን በዚህ ርዕስ ጉዳይ ዙሪያ ያደረጉ በርከት ያሉ የመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ ፅሁፎች ባሉበት ሁኔታ እነዚህን ብቻ የመረጠበት መስፈርት(ቶች) ምን እንደሆነ(ኑ) አልገለፀም፡፡ ከዚህም በቀር እነዚህ ጥናታዊ ፅሁፎች ለመጀመሪያ ዲግሪ የቀረቡ ፅሁፎች በመሆናቸው ጠንከር ያለ ሂስ መሰንዘር ባልተገባ ነበር፡፡ ፅሁፎቹ በቀረቡበት ዘመን የነበረውን አመለካከት፣ በወቅቱ የተመሩበትን የጥናታዊ ፅሁፍ አደረጃጀት፣ ቅርፅ (Format) እና የቀረቡበትን የትምህርት ደረጃ ከግምት ውስጥ ሳያስገባ ምልዓትና ጉድለታቸው(ጥንካሬና ድክመታቸው) ላይ ከፍተኛ ትኩረት ማድረጉ ተገቢ አልመሰለኝም፡፡

በ"Ethnological Society Bulletin" ውስጥ የወጡ ፅሁፎችን በቃኘበት ክፍል በተለይም አብደላ አብዱራህማን "Harriri funeral custom" የሚል ርዕስ በሰጠው ጽሁፍ ውስጥ

… As common every where, the death of any person is naturally announced primarily by the hue and cries of the relatives, if the deceased person has any. But in the city of Harar it is officially announced by an appointed person, man if the deceased is male, and woman if the deceased is a female

በማለት ያነሳውን ሐሳብ ዘላለም ‹‹በሀረሪ ክልል በገላን እና አርባን አካባቢ.... የመርዶ አነጋገር በፆታ ላይ የተመረኮዘ ሲሆን ወንድ ከሞተ ሴት፤ ሴት ከሞተች ደግሞ ወንድ መርዶ እየዞረ ያረዳል›› ብሎ ተርጉሞታል (አፅንኦት የኔ):: ይሁን እንጂ ፀሀፊው፣ አብደላ አብዱራህማን፣ በፅሁፉ የጠቀሰው ‹ወንድ ከሞተ ወንድ፣ ሴት ከሞተች ደግሞ ሴት ዜና ዕረፍቱን እየዞሩ ይናገራሉ› የሚል ነው:: በፀሀፊውና በተርጓሚው መካከል ከፍተኛ የትርጉም (የይዘት) ልዩነት እንዳለ ልብ ይሏል:: ዋናውን ፅሁፍ (የአብደላ አብዱራህማንን) ሳይመለከቱ፡ የዘላለምን ጥናት እንደ አንድ የመረጃ ምንጭነት ለሚጠቀሙ ሰዎች የአካባቢውን የለቅሶ ባህል በተዛባ መልኩ እንዲገነዘቡ የሚያደርግ በመሆኑ አጥኚው - ዘላለም ፋንቱ- የዚህ ዓይነት ስህተት ላለመስራት ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ ነበረበት::

አጥኚው የንድፈ ሐሳብ ቅኝት ባደረገበት ንኡስ ክፍል ውስጥ ሞት፣ ለቅሶ፣ ክብረ በዓልና ክዋኔ የሚሉትን ፅንሰ ሐሳቦች ዘርዝሯል:: ከዚያም በቀጣዩ ክፍል ጥናቱ፡ የተካሄደበትን አካባቢ ዳራ- የአካባቢውን መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ የብሔረሰብን ታሪካዊ አመጣጥና አሰፋፈር፣ የባህላዊ አስተዳደሩን፣ እሴቶቹንና የበዓላት አከባበሩን ሁኔታ በዝርዝር አንስቷል::

በአራተኛው ክፍል ደግሞ የብሔረሰቡን የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔዎች "የቅድመ ሞት ዝግጅት"፣ "የጊዜ ሞት ዝግጅት"፣ "የድህረ ቀብር ክዋኔዎች" እና "የቀጠሮ ለቅሶ" ብሎ በመከፋፈል ሰፊ ትንተና አድርጓል:: በትንታኔው የበና ብሄረሰብ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ምን እንደሚመስል አሳይቷል:: በእያንዳንዱ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ውስጥ ያለውን ትርጉም ለመግለጽ ያደረገው ጥረትም የሚደነቅ ነው:: ‹‹የቅድመ ሞት ዝግጅት›› በሚለው ንኡስ ርዕስ ስር የብሔረሰቡ አባላት ሞት መቅረቡን ለማረጋገጥ የሚጠቀሙባቸውን ብልሃቶች፣ የኑዛዜ ሥርዓታቸው፣ ለለቅሶ ማስኬጃና ለለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚያደርጓቸውን ዝግጅቶች ዘርዝር አድርጎ ገልጿል:: ‹‹ጊዜ ሞት›› የሚል ርዕስ በሰጠው ንኡስ ክፍል ውስጥ ደግሞ ወደ ቀብር የሚደረገውን ጉዞ እና በቀብር ወቅት የሚፈፀሙ ልዩ ልዩ ድህረ ሞት ሥነስርአቶችን ሰፋ አድርጎ አቅርቧል:: በመቀጠልም የድህረ ቀብር ክዋኔዎችን

አስረድቷል፡፡ ዘላለም በዚህ በትንታኔው ክፍል የበና ብሄረሰብ አባላት የሀዘን ስሜታቸውን ለመግለጽና ለመወጣት የሚያከናውኗቸውን ክንውኖች እና ስለቀሪው አለም ያላቸውን አመለካከት ለመግለጽ የሚጠቀሙባቸውን መንገዶች ዘርዝር አድርጎ አቅርቧል፤ ጥሩ ትንታኔም አድርጓል፡፡ በመጨረሻም ማጠቃለያና ይሁንታውን አስቀምጧል፡፡

ህይወት አበሩ ሀምሌ፣ 2003 ዓ.ም ‹‹የመኢኒት ብሄረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ›› በሚል ርዕስ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቷን አቅርባለች፡፡ ጥናቷ ‹‹መግቢያ››፣ ‹‹ክለሳ ድርሳናት››፣ ‹‹ማህበረ ባህላዊ ዳራ ምልከታ››፣ ‹‹የመኢኒት ብሄረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርአት አከባበር ትንተና›› እና ‹‹ማጠቃለያና ይሁንታ›› በሚሉ ርዕሶች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው፡፡

‹‹መግቢያ›› በሚለው ርዕስ ስር የጥናቷን ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያቷን፣ አላማዋን፣ የአጠናን ዘዴዋን፣ የጥናቷን አስፈላጊነት፣ የጥናቷን ወሰን፣ የመስክ ተሞክሮዋን፣ ያጋጠሟትን ችግሮችና የመፍትሄ እርምጃዎቿን በዝርዝር ገልጻለች፡፡

‹‹ክለሳ ድርሳናት›› በሚለው ክፍል ስር ደግሞ ተዛማጅ ጥናቶች ቃኝታለች፤ ጥሩ ንድፈ ሐሳባዊ ዳራም ሰጥታለች፡፡ ሆኖም አደረጃጀት ላይ መጠነኛ ችግር ይስተዋላል፡፡ ይኸውም ‹‹ክለሳ ድርሳናት›› በሚለው አብይ ርዕስ ስር ‹‹የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት›› እና ‹‹ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ›› የሚሉትን ንኡሳን ርዕሶች ብቻ ተጠቅማ ለአንባቢያን መነሻ ሐሳብ ብትሰጥ ይሻል ነበር፡፡ እርሷ ግን ከእነዚህ ንኡሳን ርዕሶች በተጨማሪ ‹‹የቀብር ስነስርአት›› እና ‹‹ማህበራዊ ደረጃና የለቅሶ ስርአት›› የሚሉ ንኡሳን ርዕሶችን በመጠቀም የትንተና አይነት ቅርጽ ያለውን ጽሁፍ ጽፋለች፡፡ ንኡሳን ርዕሶቹን ‹‹ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ›› በሚለው ርዕስ ከተዘረዘሩት ርዕሶች መካከል አንዱ በሆነው ‹‹ የለቅሶ ስርአትና የለቅሶ ስርአት ክዋኔ›› በሚለው ርዕስ ስር ብታስቀምጣቸው የተሻለ ይሆን ነበር፡፡ ትክክለኛ ቦታቸውም ይሄው ይመስለኛል፡፡ አላደረገችውም፡፡

እንደገና፣ ‹‹ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ›› በሚለው ርዕስ ስር ክዋኔ፣ የመከወኛ ምክንያት፣ የክዋኔ ተሳታፊ፣ የክዋኔ አመላካች፣ ከዋኝ እና የመከወኛ ቁሶች የሚሉ ስድስት ርዕሶች በትይዩነት ዘርዝራለች፡፡ እነዚህን የመጨረሻዎቹን አምስት ርዕሶች ‹‹ክዋኔ›› ከሚለው ከመጀመሪያው ርዕስ ጋር አቻ አድርጋ አስቀምጣቸዋለች፡፡ ከዚህ ይልቅ አምስቱን ርዕሶች በዚህ ርዕስ ስር የሚመጡ ንኡሳን ርዕሶች ብታደርጋቸው ኖሮ የተሻለ ይሆን ነበር፡፡ ምክንያቱም ክዋኔ ከዋኝን፣ የክዋኔ ተሳታፊዎችን፣ የመከወኛ ቁሶችን ወዘተ. በውስጡ ያካትታልና ነው፡፡

‹‹ማህበረ ባህላዊ ዳራ ምልከታ›› በሚለው የጥናቷ ሶስተኛ ክፍል ውስጥ የአካባቢውን መልክዓ ምድራዊ ገጽታ፣ የብሄረሰቡን ታሪካዊ አመጣጥና አሰፋፈር፣ ቋንቋውን፣ የኢኮኖሚ መሰረታቸውን፣ የአለባበስና የአመጋገብ ስርአታቸውን፣ እምነታቸውን፣ ማህበራዊ ህይወታቸውንና ባህላዊ የእርቅ ስርአታቸውን ገልጻለች፡፡ በተጨማሪም ስለ ብሔረሰቡ ባህላዊ የአስተዳደር ስርአት፣ ስለ ዕደ ጥበብ ሙያና ሙያተኞች ዘርዘር አድርጋ አብራርታለች፡፡

የጥናቷ አራተኛ ክፍል ትንተና የተደረገበት ነው፡፡ በዚህ ክፍል የብሄረሰቡን ባህላዊ የለቅሶ ስነስርአት አከዋወን ተንትናለች፡፡ በትንታኔዋም ከዕድሜ አንጻር ከህፃንነት እስከ አቅመ አዳም (ሄዋን) ለደረሱ እና ለዕድሜ ባለፀጋዎች የሚደረጉ ቅድመ ሞት፣ ጊዜ ሞት እና ድህረ ቀብር ዝግጅቶችን አሳይታለች፡፡ እንዲሁም ከባህላዊ ስልጣን አንፃር ለባለቃልቻዎች (‹‹ኔሬይ››) እና ለጎሳ መሪዎች (‹‹ኮሙሩት››) የሚደረጉትን ቅድመ ሞት፣ ጊዜ ሞት እና ድህረ ቀብር ክዋኔዎች አመልክታለች፡፡ በዚህ መሰረት የብሄረሰቡ አባላት ለህጻናት፣ ለወጣቶች እና ለዕድሜ ባለጸጋዎች እንዲሁም ለባለቃልቻዎችና ለጎሳ መሪዎች ያላቸውን አመለካከት አስገንዝባለች፡፡ ከዚህም በቀር የብሔረሰቡ የለቅሶ ስርአት ክዋኔ ታሪክን ከማቆየት፣ ባህላዊና ማህበራዊ ተቋማትን ከማስጠበቅና የማህበረሰቡን አመለካከትና እምነት ከመግለጽ አንጻር ያለውን ፋይዳ ገልጻለች፡፡ በመጨረሻም ማጠቃለያና ይሁንታዋን አስቀምጣለች፡፡

ሞገስ ሚካኤል በ2002 ዓ.ም ‹‹በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ስነስርአት፣ በስርአቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው›› በሚል ርዕስ የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ዕሁፉን አቅርቧል፡፡ጥናቱ አምስት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት፡፡ የመጀመሪያው ክፍል ‹‹መግቢያ›› የሚል ርዕስ ተሰጥቶታል፡፡ በዚህ ርዕስ ስር የጥናቱን ዳራ፣ አነሳሽ ምክንያቶቹን፣ አላማዎቹን፣ የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶቹን፣ የናሙና አወሳሰድ ዘዴዎቹን፣ የጥናቱን ውጤት ጠቀሜታ፣ የጥናቱን ወሰን፣ ያጋጠሙትን ችግሮችና የመፍትሄ እርምጃዎቹን በዝርዝር አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ሁለተኛ ክፍል ክለሳ ድርሳናት የሚል ርዕስ ተሰጥቶታል፡፡ አጥኚው በዚህ ክፍል ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ ተሰጥቶታል-ስለ ቀረርቶ፣ ፉከራ፣ ክዋኔና የቀብር ስነ ስርዓት ምንነት በዝርዝር አስረድቷል፡፡ ተዛማጅ ጥናቶችንም ቃኝቷል፡፡ ተዛማጅ ጥናቶቹን ‹‹የለቅሶ ሥርዓትንና ሙሾን ያጠኑ››፣ ‹‹የለቅሶ ስርዓትን፣ ሙሾን፣ ቀረርቶንና ፉከራን ያጠኑ››፣ ‹‹የለቅሶ ሥርዓትን ብቻ ያጠኑ›› እና ‹‹ቀረርቶንና

ፉክራን ያጠኑ›› ብሎ በመከፋፈል በየምድባቸው ቃኝቷቸዋል፡፡ ከተጠቀመባቸው ተዛማጅ ጥናቶች መካከል አስራ አምስቱ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ተማሪዎች ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የተዘጋጁ ፅሁፎች ሲሆኑ ሦስቱ ደግሞ ለተለያዩ ሴሚናሮች የቀረቡ ጥናቶች ናቸው፡፡ እነዚህን አስራ ስምንት ጥናቶች እንደሚያነሱት ቁም ነገር በየምድብ በየምድባቸው ከፋፍሎ ማየቱ ይበል የሚያሰኝ ጥሩ ስራ ነው፡፡ ይሁን እንጂ በተለይም ለዲግሪ ማሟያ የቀረቡ ጥናታዊ ፅሁፎችን በእርሱ የትምህርት ደረጃ፣ የአመለካከት እና የብስለት መነፅር ተመልክቶ እንከናቸውን (ጉድለታቸውን) አጉልቶ ማሳየቱ ተገቢ አልመሰለኝም፡፡ ጥናቶቹ የቀረቡበትን ዘመንና የትምህርት ደረጃ ከግምት ውስጥ ማስገባት ነበረበት የሚል እምነት አለኝ፡፡

በጥናቱ አራተኛ ክፍል በወረዳው የሚደረ ገውን የቀብር ስ ነስርዓትና በሥርዓቱ ላይ የሚካሄዱ ቀረርቶና ፉክራዎች ላይ ትንተና አድርጎባቸዋል፡፡ በትንተናው የኑዛዜ ሥርዓት አፈፃፀምን፣ ለዋናው ለቅሶና ለለቅስተኛ ማስተናገጃ የሚደረጉ ዝግጅቶችን፣ በምሽትና በንጋት የሚካሄዱ ስነስርዓቶችን፣ የግንዘት አፈፃፀምን፣ በአስከሬን ጉዞ ወቅት የሚከናወኑ ስነስርዓቶችን ወዘተ. በዝርዝር ገልጿል፡፡ በመጨረሻም ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ ሥርዓቶችን አመልክቷል፡፡ ሞገስ በጥናቱ የክዋኔዎችን ትርጉም በማሳየት ረገድ የሰራው ስራ በጥንካሬ ሊነሳለት የሚገባ ነው፡፡ ሆኖም አንዳንድ ጉድለቶችም አሉበት፡፡ ከነዚህም መካከል በዋናነት የሚነሳው ለጥናቱ ደንበኛ ወሰን አለማበጀቱ ነው፡፡ የጥናቱ ወሰን ‹‹ይህ ጥናት በላይ አርማጭሆ ወረዳ በሚደረግ የቀብር ስነ ስርአት፣ በስርአቱ ላይ በሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉክራና ክዋኔው ላይ ትኩረት ሰጥቶ የተካሄደ ነው›› የሚል ነው፡፡ ይሁን እንጂ በጥናቱ ትኩረት ያደረገው ስለ ኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ብቻ ነው፡፡ ስለ ሌላኞዎቹ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ የተናገረው አንድም ነገር የለም፡፡ ይህ ደግሞ ‹‹እውነት የወረዳው ነዋሪዎች በሙሉ የኦርቶዶክስ ክርስትና እምነት ተከታዮች ናቸው?›› የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ አጥኚው በጥናቱ የመጨረሻ ክፍል(በአምስተኛው ክፍል) በጊዜ ሂደት በለቅሶው ስነስርዓት ክዋኔ ላይ የታዩ ለውጦችን በማስታወስ ማጠቃለያውንና ይሁንታውን አስፍሯል፡፡

በመቀጠል የምንመለከተው በተለያዩ ምሁራን ተዘጋጅተው ለሴሚናር የቀረቡ ጽሁፎችን ነው፡፡ ጽሁፎቹ የተገኙት ከ"Ethnological Society Bulletin" (2002) ውስጥ ነው፡፡

አብደላ አብዱራህማን “Harriri Funeral Custom” በሚል ርዕስ በሐረር ከተማ እና በቅርብ ርቀት በሚገኙ ገላን እና አርባን ከተሞች ውስጥ የሚደረገውን የለቅሶና የቀብር ስነስርዓት በሁለት ክፍል ከፍሎ አቅርቧል፡፡ ፅሁፉ የእስልምና ተከታዮች የሚያካሄዱትን የለቅሶ ስነስርዓት ዘርዘር አድርጎ የሚገልፅ ነው፡፡ በእነዚህ ከተሞች በሚኖሩ ህብረተሰቦች ዘንድ ወንድ ከሞተ ወንድ፣ ሴት ከሞተች ሴት ተመድበው ዜና እረፍቱን ለአካባቢው ማህበረሰብ እንዲነግሩ ይደረጋል፡፡ የሟቹ ዜና ዕረፍት ለአካባቢው ሰዎች የሚነገረውና ሌሎች ቀጣይ ክዋኔዎችም የሚደረጉት ሟች የ‹‹አፎቻ›› (አፎቻ እንደ ዕድር ያለ ማህበር ነው) አባል ከሆነ(ች) ብቻ እንደሆነ ፀሀፊው አበክሮ ገልጿል፡፡ አባል ያልሆነ ሰው ከናካቴው ቀባሪ ላያገኝ እንደሚችልም ጠቁሟል፡፡

ተጠርተው ከመጡ የአፎቻ አባላት መካከል በዕድሜ ጠና ያሉና ልምድ ያላቸው ሴቶች ሬሳውን እንዲያጥቡና ቅባት እንዲቀቡት ይደረጋል፡፡ በመቀጠልም ሬሳውን ለቀብር የሚያበቁ አስፈላጊ ዝግጅቶች ሁሉ ይጠናቀቃሉ- ሬሳው ይገነዛል፣ ልብስ ይለብሳል፣ በሬሳ አልጋ ላይ ይታሰራል፡፡ ከዚያም ፀሎት ተደረጎለት ወደቀብር ቦታ ይወሰዳል፡፡ በጉዞ ወቅት ሟችን የሚያውቅም ይሁን የማያውቅ መንገደኛ አክብሮቱን ለመግለፅ የተሸከሙ ሰዎችን ያግዛል፡፡ በዕለተ አርብ የሞተ ሰው ከቀብር በፊት ወደ መስጊድ ተወስዶ ፀሎት ይደረግለታል፡፡

ለመቅበሪያ የሚሆነው ጉድጓድ ወደ ታች ከተቆፈረ በኋላ እንደገና ወደ ውስጥ ዋሻ ነገር ይቆፈራል፡፡ በዋሻው ውስጥ ፊቱ ወደ ሰሜን እንዲሆን ተደርጎ ይቀበራል፡፡ የሰሜን አቅጣጫ የሚመረጠው ፊቱ ወደ መካ እንዲሆን በማሰብ እንደሆነ ፀሀፊው ይገልፃል፡፡

ለቀስተኞች ከቀብር መልስ ከፋራ የተባለ ዳቦ(ቂጣ) ይቀርብላቸዋል፡፡ በዕለቱ የሟች ቤተሰቦች አቅማቸው እንደፈቀደ ፍየል ወይም በሬ ገዝተው በማረድ ድሆችን ይመግባሉ፡፡ በአካባቢው የለቅሶ ስነስርዓት ደንብ መሰረት ወንድ ሐዘንተኛ ነጭ ጥምጣም ጠምጥሞ ከበር አጠገብ የሚቀመጥ በመሆኑ ሐዘንተኛውን በቀላሉ መለየት ይቻላል፡፡ በአራተኛው የለቅሶ ቀን የአፎቻው አባላት ሃያ አምስት ሃያ አምስት ሳንቲም አዋጥተው ስለ ሟቹ(ቿ) ነፍስ ይፀልያሉ፡፡ ይህ ሥርዓት ፋታህ ይባላል፡፡ በአንደኛው ሳምንት የመጨረሻ ቀን ደግሞ የሟች ቤተሰቦች ትልቅ በሬ ገዝተው በማረድ የአፎቻውን አባላት በመጥራት ግብዣ ያደርጋሉ፡፡ ጥሪ የተደረገላቸው ተሳታፊዎች በተዘጋጀላቸው ቅርጫት ውስጥ አቅማቸው የፈቀደውን ብር እያስቀመጡ ይገባሉ፣ ግብዣውንም ይታደማሉ፡፡

በአጠቃላይ አብደላ በፅሁፉ ውስጥ አንድ ሟች ከሞተበት ጊዜ አንስቶ የሚደረጉትን ልዩ ልዩ ስነስርዓቶች ገልጿል፡፡ የአካባቢውን የቀብርና የለቅሶ ስነስርዓት ጠቅለል ባለ ሁኔታ ለማስተዋወቅ ሞክሯል፡፡ ይሁን እንጂ በእስልምና ሐይማኖት ተከታዮች የሚፈፀመው የለቅሶ ስነስርዓት ሁሉን የህብረተሰብ ክፍል ይወክላል ወይ? ለሚለው ጥያቄ ግልጽ የሆነ መልስ መስጠት ነበረበት፡፡

ፋሲካ በለጠ ደግሞ "The death customs among the Amharas of Šäwa" በሚል ርእስ ያጠናውን ጥናት አቅርቧል፡፡ የጥናቱ ትኩረት በዋናነት ሸዋ ውስጥ የሚገኙ የክርስትና ዕምነት ተከታይ አማራዎች ለዘመናት እየከወኑት ያለው የቀብር እና የሐዘን መግለጫ ስነስርዓታቸው ምን እንደሚመስል ማሣየት ነው፡፡ የአንድ ሰው ነፍስ ከስጋው ከተለየች ጊዜ አንስቶ እስኪቀበር ድረስ እና ከተቀበረበት ጊዜ ጀምሮ እስከ ሁለት ዓመት ድረስ (እስከ አስራ አራት ዓመት ሊደርስም ይችላል) የሚኖረውን የሐዘን /የለቅሶ ስነስርዓት ለማሳየት ሞክሯል፡፡

መረጃዎቹን ያሰባሰባቸው የእድሜ ባለፀጋዎችን በመጠየቅ እንደሆነ አበክሮ ጠቁሟል፡፡ አጠቃላይ ስነስርዓቶቹን "The making of the last will", "breaking the news", "the service for the dead", "the funeral procession" እና "the mourning customs" በሚሉ ስድስት ክፍሎች ከፋፍሎ ዘርዘር አድርጎ አቅርቧቸዋል፡፡ በመጀመሪያው ንኡስ ክፍል ውስጥ አንድ ሰው በጣም ከታመመና ይሞታል ተብሎ ከተገመተ የነፍስ አባቱና የአካባቢው ሽማግሌዎች ጊዜያዊ ኮሚቴ አዋቅረው እንደሚያናዝዙት ገልጿል፡፡ ኑዛዜው ወደተቀባዮቹ በምን አይነት ስነስርአት እንደሚተላለፍም አሳይቷል፡፡

በሁለተኛው ንኡስ ክፍል የሟች ህልፈተ ህይወት ለወዳጅ ዘመዶች፣ ለጎረቤቶች እና ለአካባቢው ሰዎች የሚነገርበትን ሁኔታ ገልጿል፡፡ በለቅሶው ላይ መገኘት ላለባቸው ቤተሰቦችና ወዳጅ ዘመዶች መልእክተኞች ይላካሉ፡፡ መልዕክተኞቹም ዜና እረፍቱን ለመንገር እንደ ቦታው ቅርበት እና ርቀት በእግር ወይም በፈረስ ይንቀሳቀሳሉ፡፡ ለሁሉም ሰዎች መልእክቱን ለማድረስ በሚያስቸግሩ በአንዳንድ አካባቢዎች ግን መልዕክተኛው ዳገታማ ቦታ ላይ ሆኖ በቅርብ ርቀት የሚገኝን የአንድ አባወራን ስም ደጋግሞ ይጣራል፡፡ አባወራው ምላሽ ከሰጠ ዜና እረፍቱ ይነገረዋል፡፡ እርሱም በተራው ለሌሎች ሰዎች ይነግራቸዋል፡፡ በዚህ ዓይነት ቅብብሎሽ ሁሉም ሰዎች ይሰማሉ ብሏል፡፡ የግንዘት

ስርዓቱንም በዚሁ ክፍል አንስቷል፡፡ ለቀሳውስት፣ ለመነኮሳት እና ለተራው ህዝብ የሚደረጉት የግንዘት ስነስርአቶች የተለያዩ መሆናቸውን ገልጿል፡፡

ሶስተኛው ክፍል ካህናት (ደባትራን) እና ዲያቆናት ለሚቹ የሚያደርጉትን አገልግሎት የሚያትት ነው፡፡ ለሚች ፀሎት ይደረግለታል፤ ልዩ ልዩ ጥቅሶችም ከመፅሀፍ ቅዱስ ይነበብለታል፡፡ ከመፅሀፍ ቅዱስ የሚነበቡት ጥቅሶች እንደሚቹ ዕድሜና ደረጃ የሚለያዩ እንደሆኑ ጠቁሟል፡፡ ይሁን እንጂ ለማን የትኛው የመፅሀፍ ቅዱስ ጥቅስ እንደሚነበብ አልገለፀም፡፡

አራተኛው ክፍል ሬሳው ወደ ቀብር ቦታ በሚወሰድበት ጊዜ የሚኖረውን የጉዞ ቅደም ተከተል የሚያመለክት ነው፡፡ ካህናት፣ ሬሳውን የተሸከሙ ሰዎች፣ ዋና ሐዘንተኞች (የሚች ሚስት ወይም ባል፣ እናት፣ አባት፣ ከአስራ ስምንት ዓመት በላይ የሆናቸው እህቶችና ወንድሞች) በቅደም ተከተል ይጓዛሉ፡፡ ሌሎች ዘመዶች፣ ጓደኞችና ጎረቤቶች ደግሞ ዋና ሐዘንተኞችን ይከተላሉ፡፡ ሁሉም በእግራቸው ይጓዛሉ፡፡ ነገር ግን በአቅም መድከም ምክንያት በእግራቸው መጓዝ የማይችሉ ሰዎች ከኋላ ሆነው በፈረስ ወይም በበቅሎ ይከተላሉ፡፡ ለካህናቱ የሚሆን ምግብና መጠጥ የተሸከሙ ሰዎችም ለቀስተኞቹን ይከተላሉ፡፡ ምግብና መጠጡ ‹‹እንባ አድርቅ›› እንደሚባል ፀሀፊው ገልጿል፡፡

በአምስተኛው ክፍል የአቀባበር ሥርዓቱን አመልክቷል፡፡ በዚህ ክፍል ማን የትኛው ቦታ ላይ እንደሚቀበር ተመልክቷል፡፡ በህብረተሰቡ ዘንድ መልካም ተብለው የሚታሰቡ የቀብር ቦታዎችና አቅጣጫዎች እንዳሉም ተገልጿል፡፡ በእነዚህ ቦታዎች ለመቀበር ሰዎች በህይወት ዘመናቸው ሳሉ የነበራቸው ማህበራዊ ደረጃ(ማዕረግ) እንዲሁም ለቤተክርስቲያን አገልግሎት የነበራቸው ቀናኢነት ዋነኛ መስፈርቶች ናቸው፡፡

የመጨረሻውን ክፍል በሶስት ክፍሎ ነው ያቀረበው- ለቅሶ/ሀዘን፣ ጌጣጌጥ እና አልባሳት ብሎ፡፡ ለቅሶ ወይም ሐዘን በሚለው ክፍል ውስጥ የግልና የቡድን ለቅሶ እንዳለ ጠቅሷል፡፡ ሐዘንተኞች ከማልቀስ ባሻገር ሐዘናቸውን እንዴት ባለ መንገድ እንደሚገልፁ አብራርቷል፡፡ ለሐዘን የተመረጡ ቀናት/ጊዜያት እንዳሉም ገልጿል፡፡ 3ኛ ቀን፣ 12ኛ ቀን፣ 40ኛ ቀንና 7ኛ ዓመት ከፍተኛ ሐዘን ይደረግባቸዋል፤ ይለቀስባቸዋል፡፡ በአንፃሩ በ40ኛው ቀንና በ7ኛው ዓመት መሀል ባሉት ጊዜያት (በ80ኛ ቀን፣ 6ኛ ወርና 1ኛ ዓመት) ማልቀስ የተለመደ አለመሆኑን ያስገነዝባል፡፡ ምክንያቶቹን ግን በግልፅ አላስቀመጠም፡፡

ጌጣጌጥ አልጋ ላይ አለመተኛትን፣ ጫማ አለማድረግን፣ ቀለበትና ሌሎች ጌጣጌጦችን ማውለቅን፣ ልዩ ልዩ ቀለማት ያላቸው የአንገት ክሮችን በነጭ ክር መተካትን፣ ፀጉር መላጨትን፣ ፂምና ጥፍር አለመቁረጥን ያጠቃልላል፡፡ አልባሳት የሚለው ክፍል ደግሞ ህብረተሰቡ ሀዘኑን ለመግለፅ የሚለብሳቸውን ልብሶች ምንነት፣ የቀለም ምርጫቸውንና የአለባበስ ዘይቤያቸውን የገለፀበት ነው፡፡ የአንዳንድ ክዋኔዎችን ትርጉም ካለመግለፁ በስተቀር ፀሀፊው የለቅሶ ሥነ-ሥርአቱን ዘርዘር አድርጎ በጥሩ ሁኔታ ያቀረበበት ፅሁፍ ነው፡፡

አንዳርጋቸው ተስፋዬ "The funeral customs of the kottu of harar" በሚል ርእስ ያጠናውን ጥናት አቅርቧል፡፡ ቆቱዎች የእስልምና ሐይማኖት ተከታይ መሆናቸውን ፀሀፊው በግርጌ ማስታወሻው ጠቅሷል፡፡ ስለሆነም ፅሁፉ በዚሁ ሐይማኖት ዙሪያ የሚያጠነጥን የለቅሶ ሥነ-ሥርዓትን የሚያሳይ ነው፡፡ ፅሁፉ አንድ ሰው ሊሞት ከተቃረበበት ጊዜ ጀምሮ የሚደረጉ አጠቃላይ ክዋኔዎችን ጠቅለል አድርጎ ለማሳየት ይሞክራል፡፡አንድ ሰው በጠና ሲታመም የጎረቤት ሰዎች ይጠራሉ፡፡ ተጠርተው ከመጡ ሰዎች መካከል በዕድሜ ሽምግል ያለ ሰው ህመምተኛውን ‹‹ሻዳ ቀብዱ›› ይለዋል፡፡ ‹‹አንድ ፈጣሪ ብቻ እንዳለ መስክር›› ማለቱ ነው፡፡ ታማሚውም ከቻለ ‹‹ላዚላህ አላሃ መሐመድ ረሰል አላህ ›› ብሎ ይመልሳል፡፡ ‹‹አንድ ፈጣ ሪ ብቻ አለ፤ መ ሐመድም የእርሱ መልዕክተኛ ነው›› ማለቱ ነው፡፡ እሱ ይህን ማለት ካልቻለ ግን ሌሎች ይሉለታል፡፡ በዚህ ጊዜ ነፍሱ ከስጋው ልትለይ ተቃርባለች ተብሎ ስለሚታሰብ ቤተሰቦቹ ማልቀስ ይጀምራሉ፡፡ መጮህ ግን አይችሉም፤ ፍፁም ክልክል ነው፡፡

በመቀጠል የታማሚው ነፍስ ከስጋው ስትለይ የሚኖረውን የሥራ ክፍፍልና ማህበራዊ ተሳትፎ ገልጿል፡፡ ሶስት በእድሜ ጠና ያሉ ወንዶች ተመርጠው አንደኛው የሞቱን ዜና እየዞረ እንዲናገር ይላካል፡፡ ሁለተኛው ለመገነዣ የሚሆኑ ነገሮችን እንዲገዛ ወደ ገበያ ይላካል፡፡ ሶስተኛው ደግሞ ለሚሰባሰቡ ሰዎች ማስተናገጃነት የሚውሉ ቁሳቁሶችን (ብርጭቆ፣ ሲኒ…) ከአካባቢው ሰዎች እንዲሰበስብ ይላካል፡፡ ወጣት ወንዶች የመቅበሪያ ጉድጓድ(ቀብሪ) እንዲቆፍሩ ይላካሉ፡፡ በዕድሜ ጠና ያሉ ሴቶች ደግሞ ለሬሳ ማጠቢያ የሚሆን ውሃ ያሞቃሉ፡፡ የሴትን ሬሳ በእድሜ ገፋ ያሉ ሴቶች ያጥባሉ፤ ይገንዛሉ፡፡ በአንፃሩ የወንድን ሬሳ በዕድሜ ገፋ ያሉ ወንዶች ያጥባሉ፤ ይገንዛሉ፡፡ ይህ የሆነበት

ምክንያት ከባህል፣ ከእምነት፣ ከፆታ እና ከማህበራዊ ደረጃ አንፃር አልተገለፀም፡፡ ቢገለፅ መልካም ነበር፡፡

ወጣቶቹ የሚቆፍሩት ጉድጓድ ሬሳው ከተቀበረ በኋላ ለመቀመጥ ሲፈልግ የማያስቸግረው መሆን እንዳለበት ፀሀፊው ጠቁሟል፡፡ ምክንያቱንም ገልጿል፡፡ በቆቱዎች ዕምነት ሬሳውን የሚጠይቅ መንፈስ አለ፡፡ መንፈሱ ለሚጠይቀው ጥያቄ ሟች ቁጭ ብሎ መልስ መስጠት አለበት የሚል እምነት ስላላቸው ነው ይለናል፡፡ ሬሳው በቀኝ ጎኑ እንዲተኛ ተደርጎ እንደሚቀበርም ገልጿል፡፡ ሴቶች ሲሞቱ ከነጌጣጌጦቻቸው እንደሚቀበሩም ጠቁሟል፡፡ ምክንያቱን ግን አልገለፀም፡፡ ስለወንዶቹም የጠቀሰው ነገር የለም፡፡ ሠዎች ሲሞቱ ከሰፈር አካባቢ ብዙ ሳይርቁ ይቀበራሉ፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛዎቹ ቆቱዎች በህይወት ዘመናቸው የሚመርጡት ሲሞቱ በመንገድ ዳር ተቀብረው መንገደኛው ሁሉ ሰላማዊ ዕረፍትን እንዲመኝላቸው መሆኑን ጠቅሷል፡፡

ከቀብር መልስ የሟች ቤተሰቦችና ዘመዶች በሐዘን እንዳይጎዱ በማድረግ ረገድ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዙት ወንዶች ናቸው፡፡ ወንዶች እስከ ሰባት ቀን ድረስ እዛው እየዋሉ እዛው እያደሩ ሐዘንተኞቹን ያጽናናሉ፡፡ ይህ ስርዓት ‹‹ታሲያ›› ይባላል፡፡ በዚህ ስርዓት መሳተፍ እያለበት የቀረ ሰው ከባድ ቅጣት ይቀጣል፡፡ የጎሳው አባላት ከቀረው ሰው ከብቶች መካከል አንድ በሬ ይወስዱበትና አርደው በህብረት ይመገባሉ፡፡ ሰባተኛው ቀን የሀዘን መደምደሚያ ተደርጎ ይቆጠራል፡፡ ቀኑም ‹‹ቀበኔይሳ›› ይባላል፡፡ በዚህ ቀን ምን ዓይነት ምግብ ለማን እንደሚዘጋጅ እና አጠቃላይ ስነስርአቱን አብራርቷል፡፡ በአጠቃላይ አንዳርጋቸው የቆቱዎችን የለቅሶ ስነስርዓት ዘርዘር አድርጎ ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ይሁን እንጂ አንዳንድ ጉዳዮችን በተመለከተ ለምን? እንዴት? ተብለው ለሚነሱ ጥያቄዎች በቂ ምላሽ አልሰጠም፡፡

እስከ አሁን ከተመለከትናቸው ጽሁፎች በተጨማሪ የ‹‹Ethnological Society of Addis Ababa›› ማህበር አባላት የሆኑት አበበ አምባቸው፣ አሰፋ ሊበን፣ በቀለ ጋይድ፣ በቀለ ናዲ፣ ቡልቻ ደመቅሳ፣ ኃይሉ ገ/ህይወት እና ኃይሉ ጥላሁን ለጥናት ወደ ወለጋ በተጓዙበት ወቅት በነቀምቴ ያጋጠማቸውን የለቅሶ ስነስርዓት “Funeral and burial” በሚል ርዕስ በዚሁ መጽሄት ውስጥ አስፍረውት እናገኛለን፡፡ ፅሁፉ በዋነኛነት የለቅሶና የቀብር ሥነ-ሥርዓቶችን እንዲሁም ተያያዥ የሆኑ ልማዳዊ ድርጊቶችን ያነሳል፡፡

በነቀምቴ የማንኛውም ሰው ሬሳ በአዲስ ጨርቅ ይሸፈናል። ነገር ግን ሟች ጀግና (አንበሳ የገደለ ወይም ወታደር) ከሆነ ፀጉሩን ቅባት ይቀቡለታል። ዕሁፉ የገዳ ሥርአትን በፈፀመ እና ባልፈፀመ መካከል የአከፋፈን ሥርዓት ልዩነት እንዳለም ይገልፃል። ሬሳ ወደ ቀብር ቦታ በሚወሰድበት ጊዜ የሟች ዘመዶችና ሌሎች በጣም ያዘኑ ሰዎች የ‹‹ቆመኞ›› ዛፍ ቅርንጫፍ (ቅጠል) ይይዛሉ። የ‹‹ቆመኞ›› ቅጠል ለምን ተመረጠ? ትእምርትነቱ ምንድነው? የሚሉትን ጉዳዮች አልገለጿቸውም። እነዚህን ጉዳዮች በቅጡ ቢተረጉሟቸው መልካም ነበር።

ለሟች መቅበሪያ የሚሆነውን ጉድጓድ ዘመድ የሆነ ሰው አይቆፍርም። ይህ የጎረቤቶች ድርሻ ነው። ይሁን እንጂ ብዙ ጊዜ ጉድጓዱን ለመቆፈር የሚጀምር ሰው ይታጣል። ምክንያቱም የሬሳ ጉድጓድ ሲቆፈር ጀማሪ የሆነ ሰው ረጅም ዕድሜ አይኖረውም የሚል ዕምነት በህብረተሰቡ ዘንድ ስላለ ነው።

ሟች ከተቀበረና አፈር ከተመለሰበት በኋላ ለሰው ተብለው ተዘጋጅተው የነበሩ ምግቦች መቃብሩ ላይ ይጣላሉ፤ የሟቹ የግል መጠቀሚያ የሆኑ ቁሳቁሶችም እንዲሁ። ቁሳቁሶቹን ማንም አይነካቸውም፤ ማንም አይወስዳቸውም።

የሟች ቤተሰቦችና ዘመዶች ሐዘናቸውን በተለያዩ ይገልፃሉ። ወንዶችም ሴቶችም ቅቤ አይቀቡም። ሴቶች ፀጉራቸውን ባለማበጠር ሀዘናቸውን ይገልፃሉ፤ ወንዶች ደግሞ ይላጫሉ። ሌላኛው የሐዘን መግለጫ መንገድ ልብስን ሳያጥቡ መልበስ ነው። እንደሁኔታው ለ2 ወር፣ ለ6 ወር ለ1 ዓመት ወዘተ. ልብስን ሳያጥቡ መልበስ የሐዘን መግለጫ ተደርጎ ይቆጠራል።

ሟች በሞተ በአርባኛው ቀን ከፍተኛ ስነስርአት ይደረጋል። ቤተሰቦቹ በሬ ወይም ላም ወይም ፍየል ገዝተው በማረድ ድሆችን ሰብስበው ይመግባሉ- ያበላሉ፤ ያጠጣሉ። ይህ ስነስርዓት ‹‹ሰቀጣጣ›› ይባላል። ለዚህ ስነስርዓት ተብሎ የተዘጋጀውን ምግብና መጠጥ የሟች ቤተሰቦችም ሆኑ ዘመዶች አይበሉም፤ አይጠጡም። ሟች በሞተ በዓመቱም እንደዚሁ ታላቅ ስነስርዓት ይደረጋል። ይሄኛው ስነስርዓት ደግሞ ‹ሚጇ›› ይባላል። ለዚህኛው ስነ ሥርዓት ተብሎ ከተዘጋጀውም ምግብ ቤተሰቦቹና ዘመዶቹ ፈፅሞ አይቀምሱም። በእነዚህ ጊዜያት የተዘጋጀውን ምግብና መጠጥ ድሆች ተመግበው ሲጠግቡና ሲደሰቱ የሟች ነፍስ በገነት ሐሴት ታደርጋለች፤ በአንጻሩ ይህ ስነስርዓት

ካልተፈፀመ የሟች ቤተሰቦችና ዘመዶች በምድር ላይ ሰላም አይኖራቸውም ተብሎ እንደሚታመን ፀሀፊዎቹ ገልፀዋል፡፡

በመቀጠል የምንመለከተው ደግሞ ሀብተማርያም አሰፋ(ዶ/ር) በ1986 ዓ.ም ‹‹የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሎች›› በሚል ርእስ ከአሳተሙት መፅሀፍ የተገኘውን ፅሁፍ ነው፡፡ ፅሁፉ ‹‹የቀብር ስነስርዓት ሁኔታ በአጭሩ›› የሚል ርዕስ የተሰጠው ራሱን የቻለ ምዕራፍ ነው፡፡ በመግቢያው ላይ እንደጠቀሱት የፀሀፊው ዋነኛ ዓላማ ተወልደው ባደጉበት አካባቢ ያዩትንና የሰሙትን የለቅሶ ስነስርዓት በፅሁፍ ለትውልድ ማስተላለፍ ነው፡፡ በአካባቢው በሚኖሩ የክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች የቀብር ባህሎችና ሥርዓቶች ላይ ብቻ ትኩረት አድርገው ነው የፃፉት፡፡ ፅሁፉን ማንበብ ስጀምር የመጀመሪያ ጥያቄዬ ‹‹የየትኛውን አካባቢ የቀብር ስነስርዓት ይሆን የሚያስተዋውቁት?›› የሚል ነበር፡፡ ፀሀፊው የየትኛውን አካባቢ የቀብር ስነስርዓት እያስተዋወቁ እንደሆነ በምዕራፉ ውስጥ አንዳችም ቦታ አልጠቆሙም፡፡ የት ይሆን ተወልደው ያደጉት? ከባድ ጥያቄ ነው፡፡ እንደመፍትሄ የመፅሀፉን መቅድም እና መግቢያ ማንበብ ጀመርኩ፡፡ በሚያስገርም ሁኔታ በመቅድማቸው ውስጥም ‹‹ተወልጄ በአደግሁበት አካባቢ…›› የሚል ሀረግ ተጠቅመዋል (ገፅ 17)፡፡ መቅድማቸውን ሙሉውን አንብቤ ተወልደው ያደጉበትን ቦታ ማወቅ ስላልቻልኩ መግቢያቸውን ማንበብ ቀጠልኩ፡፡ በመግቢያቸው ውስጥም ‹‹እኔ ተወልጄ በአደግሁበት አካባቢ…›› የሚል ሀረግ ተጠቅመው አግኝቻለሁ (ገፅ 28)፡፡ ተወልደው ያደጉበትን አካባቢ ግን እቅጩን አልተናገሩም፡፡ ‹‹የቀብር ስነስርዓት ሁኔታ በአጭሩ›› ከሚለው ምዕራፍ በፊት ‹‹የጋብቻ ስነስርዓት፣ ወጉና አፈጻጸሙ አጭር ታሪክ›› በሚል ርዕስ በፃፉት ፅሁፍ ውስጥ ፀሀፊው ተወልደው ያደጉት በትግራይ ክልል አንደርታ አውራጃ ሳይሆን አይቀርም እንድንል የሚያስችሉ ፍንጭ ሰጪ ሐሳቦች አሉ (ገፅ 552)፡፡ ስለዚህ ፀሀፊው እያስተዋወቁ ያሉት የዚህን አካባቢ የቀብር ስነስርአት ሳይሆን አይቀርም የሚለውን ተሳቢ አድርገን ምን ምን ጉዳዮችን እንዳነሱ እንመልከት፡፡

ፀሀፊው ከቅድመ ሞት እስከ ተዝካር የሚደረጉትን ስነስርዓቶች በአጭር በአጭሩ ለመግለፅ ሞክረዋል፡፡ አንድ ሰው ከሞት አፋፍ ላይ በሚገኝበት ጊዜ የሚደረገውን የኑዛዜ ስነስርአት በመግለፅ ፅሁፋቸውን ጀምረዋል፡፡ በመቀጠልም ህመምተኛው ሲሞት የሚኖረውን የሥራ ክፍፍል ጠቅሰዋል፡፡ አንድ ሰው መሞቱ እንደተረጋገጠ ዘመዶቹና የአካባቢው ሽማግሌዎች ተሰብስበው አስተናባሪዎችን ይመርጣሉ፡፡ እነዚህ አስተናባሪዎች

ኃላፊነታቸው ብዙ ነው፡፡ ‹‹በቅድሚያ ሁለት ሁለት ሰዎች መድበው በየመንደሩ ሄደው እንዲነግሩ ይልካሉ፡፡ መልእክተኞቹ ድርሻቸው ወደ ሆነው መንደር ሄደው ሕዝቡ በሚያውቀውና በተለመደው የመርዶ አባባል ከሁለቱ አንዱ ሁለት ጊዜ ሲጮህ ሁለተኛው እገሌ አርፏልና በእንደዚህ ባለ ቦታና ጊዜ አቃብሩን ብሎ ያስረዳል›› (ገፅ 587)፡፡ ሬሳው እንዲገነዝ የማድረግ ኃላፊነትም በአስተናባሪዎቹ ላይ የተጣለ ነው፡፡ በግንዘት ስነስርዓት ጊዜ የሟቹ ሬሳ እምብርት በጋለ የጥጥ ፍሬ መዳጫ ብረት ሶስት ጊዜ እንደሚተኮስ ጠቅሰዋል፡፡ ፀሀፊው ይህን ጉዳይ ዘርዘር አድርገው ቢያብራሩት መልካም በሆነ ነበር፤‹‹ምናልባት በእውነት መሞቱን ለማረጋገጥ የሚደረግ ሳይሆን አይቀርም›› በሚል መላምት ብቻ ማለፍ አልነበረባቸውም፡፡

ሬሳው በአካባቢው ሥርዓት መሰረት ከተገነዘ በኋላ ወደሚቀበርበት ቤተክርስቲያን እስኪደርስ ድረስ 7 ጊዜ እያረፈ 7 ጊዜ በዕጣን እየታጠነ ፍትሀተ ፀሎት ይደረግለታል፡፡ 7 ቁጥር ለምን እንደተመረጠች ግን አልጠቀሱም፡፡ ሐይማኖታዊ ትእምርትነቷ ምን እንደሆነ ቢጠቅሱ መልካም ነበር፡፡

በጉዞ ወቅት ለቀስተኛው የሚይዛቸው ቁሳቁሶች እንዳሉ ገልፀዋል፡፡ የሚያዙት ቁሳቁሶች እንደሟቾቹ ማህበራዊ ደረጃ (ባለፀጋ፣ ደሃ...) የተለያዩ ናቸው፡፡ የሀዘን መግለጫ መንገዶችንም ጠቅሰዋል፡፡ ወንዶች በለበሱት ሸማ ፊታቸውን በመፈግፈግ፣ ሴቶች ደግሞ ፀጉራቸውን በመንጩት ወይም ደግሞ በመላጩት ሀዘናቸውን ይገልፃሉ፡፡ ጌጣጌጦቻቸውን ያወልቃሉ፡፡ ነጭ ፈትል ወይም ክርም በአንገታቸው ላይ ያስራሉ፡፡

በቀብር ስነስርዓቱ ወቅት ያልተገኙ ሰዎች ወደ ሟች ቤተሰቦች በመሄድ እንዳያስቸግሩ እነሱም እንዳይቸገሩ ሽማግሌዎች የለቅሶ ጊዜና ቦታ ወስነው ለህዝቡ ያውጃሉ፡፡ ለቅሶ ያልደረሱ ሰዎች በተቆረጠው ጊዜና ቦታ ለቅሶ ይደርሳሉ፡፡ የዚህ ዓይነቱ የለቅሶ ስነስርዓት የአኀበር ቀብር ይባላል፡፡ ፀሀፊው የአኀበር ቀብር ጠቅላላ ስነስርዓቱን ዘርዘር አድርገው አቅርበውታል፡፡ በመቀጠልም ሟች እርዳታ የሚያስፈልጋቸው ህፃናትን ትቶ በሚሞትበት ጊዜ ልጆቹን በመንከባከብ ረገድ እነማን ምን አይነት ኃላፊነት እንዳለባቸው አብራርተዋል፡፡ በመጨረሻም፣ ማህበረሰቡ ለሟች መታሰቢያ የሚያደርገውን የተዝካር ድግስ ፉክክር ‹‹ከማን አንሼ የተዝካር ውድድር›› የሚል ርዕስ ሰጥተው ኮንነው አቅርበውታል፡፡

በመቀጠል የምንመለከተው ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረቡ አስራ ስምንት ጥናታዊ ፅሁፎችን ነው፡፡ ጥናታዊ ፅሁፎቹ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ክፍለ ትምህርት የቀረቡ ናቸው፡፡ እነዚህን ጥናታዊ ፅሁፎች በዚህ ክፍል የቃኘኋቸው የትኩረት አቅጣጫቸው ምን እንደሚመስልና ከዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር ያላቸውን አንድነትና ልዩነት ለማመልከት ያህል ብቻ ነው፡፡ በነዚህ ጥናቶች ላይ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች የሰላ ሂስ አላደርግም፡፡ አንደኛው ምክንያ ት ጥናቶቹ ለመ ጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነት የተሰ ሩ እንደመሆናቸው በዚህ ደረጃ ተነስተው የሰላ ሂስ ሊቀርብባቸው አይገባም የሚል እምነት ስላለኝ ነው፡፡ ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በአስራ ስምንቱም ጥናታዊ ጽሁፎች ላይ ሰፋ ያለ ሂስ ማቅረብ ይህን ጥናታዊ ጽሁፍ ከሚገባው በላይ ቦርቃቃ ያደርገዋል የሚል ስጋት ስላደረብኝ ነው፡፡ በመሆኑም በጥናቶቹ ምልዓትና ጉድለት ላይ ሰፋ ያለ ትንተና አላደርግም፡፡ ይህ ማለት ግን ጎላ ብለው የሚታዩ ጥንካሬዎችን አላነሳም ስህተቶችንም ነቅሼ በማውጣት አላሳይም ማለት አይደለም፡፡ ጥናቶቹ በምን ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ እንደሆኑ ከመጠቆሚም ባሻገር ጎልተው የሚታዩ ጥንካሬዎችንና ድክመቶችን የማነሳባቸው አጋጣሚዎች ይኖራሉ፡፡ በመጀመሪያ ሙሉጌታ በላይ ያቀረበውን ጥናታዊ ፅሁፍ እንመልከት፡፡

ሙሉጌታ በላይ በ2002 ዓ.ም ‹‹የሚጫ ወረዳ የለቅሶ ስነስርአት እና የሙሾ ግጥም ይዘት ትንተና ፎክሎራዊ ጥናት›› በሚል ርዕስ ያጠናውን ጥናት አቅርቧል፡፡ ጥናቱ በሶስት ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን፣ ምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ፣ አላማ፣ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የአጠናን ዘዴውና የጥናቱ አደረጃጀት የተጠቀሰበት ነው፡፡ ምዕራፍ ሁለት ተዛማጅ ስራዎች የተቃኙበትና ንድፈ ሐሳባዊ ዳራዎች የተሰጡበት ነው፡፡ በዚህ ምዕራፍ የሙሾ ግጥሞችን ስነቃላዊ ባህርያት ዘርዝሯል፡፡ በሦስተኛው ምዕራፍ ደግሞ ቅድመ ቀብር፣ ጊዜ ቀብርና ድህረ ቀብር የሚከናወኑ ስርዓቶችን በዝርዝር አቅርቧል፡፡ በለቅሶ ጊዜ የሚገጠሙ የሙሾ ግጥሞችንም ለእናት የሚገጠሙ፣ ለአባት የሚደረደሩ፣ ለእህት የሚደረደሩ፣ ለወንድም የሚደረደሩ፣ ጀግና ሲሞት የሚደረደሩ ፣ ለጋስ ሲሞት የሚደረደሩ፣ ለስራ ፍለጋ አገሩን ትቶ የወጣ ሰው ሲሞት የሚደረደሩ፣ ቆንጆ(መልከኛ) ሰው ሲሞት የሚደረደሩ፣ በድሎት ያልኖረ(ደሃ) ሰው ሲሞት የሚደረደሩ ብሎ በመከፋፈል ትንታኔ ሰጥቶባቸዋል፡፡

ጌታመሳይ ግዛው በ2002 ዓ.ም ‹‹የሺናሻ ብሔረሰብ የቀብር ስርዓት ክዋኔ ከፎክሎር ዘውጎች አንፃር›› በሚል ርዕስ ያዘጋጀውን ጥናት አቅርቧል፡፡ የጌታመሳይ ጥናት በሦስት ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ በምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ፣ ዓላማ፣ ጠቀሜታ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴና የጥናቱ አደረጃጀት ተጠቅሰዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት ደግሞ ተዛማጅ ስራዎች ተቃኝተዋል፡፡ ስለቀብር ስርአት ምንነት፣ ስለ ቀብር ስርአት መነሻና አገልግሎት፣ ስለ ቀብር ስርአት አከዋወንና ስለ ፎክሎር ምንነትም በዚሁ ምዕራፍ ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት ተደርጎባቸዋል፡፡ በሶስተኛው ምዕራፍ የሺናሻን ብሔረሰብ የቀብር ስርአት ክዋኔዎች ከቀብር በፊት፣ የቀብር ስርዓት ክዋኔ፣ ድህረ ቀብር ስርዓት ክዋኔ፣ የደም ማጥራት ስርአተ ክዋኔ፣ የተዝካር ስርአተ ክዋኔና የውርስ ስርአት ብሎ በመከፋፈል ትንተና አካሂዶባቸዋል፡፡

አባተ አሰፋ በ 2000 ዓ.ም ‹‹ የአሚባራ ወረዳ አፋሮች የለቅሶ ስርዓት ( አርካ) እና የምሳሌያዊ ንግግሮች ትንታኔ›› በሚል ርዕስ የዲግሪ ማሟያ ፅሁፉን ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነፅሁፍ ክፍል አቅርቧል፡፡ ጥናቱ በአራት ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ በምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣ የጥናቱ አላማ፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ የመረጃ አሰባሰብና አተናተን ዘዴ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሄዎቻቸው ተገልፀዋል፡፡ የጥናቱ ዳራ በሚለው ንዑስ ክፍል ስር የአሚባራ አፋሮች ማንነትና አኗኗር እንዲሁም የወረዳው መልክዓ ምድራዊ ገፅታና የህዝቡ አሰፋፈር ሁኔታዎች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

በምዕራፍ ሁለት በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሰሩ ቀደምት ጥናታዊ ፅሁፎች ተቃኝተዋል፡፡ ሀገረሰባዊ ልማድ (Social Folk custom)ን የሚመለከት ንድፈ ሐሳባዊ ዳራም ተሰጥቷል፡፡

በምዕራፍ ሶስት ከጣዕረ ሞት እስከ ህልፈተ ህይወት፣ ከህልፈተ ህይወት እስከ ግብአተ መሬትና ከግብአተ መሬት እስከ ፍፃሜ ሀዘን ድረስ ያሉት የአሚባራ አፋር የለቅሶ ስርአቶች ቀርበዋል ፣ በወረዳው ውስጥ በሞት ዙሪያ የሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮችም ተተንትነዋል፡፡ በአራተኛው ምዕራፍ የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት ቀርቧል፡፡ በተጨማሪም በለቅሶ ስነስርአቱ የሚታዩ ጠንካራና ደካማ ጎኖችም ተዘርዝረዋል፡፡

ተሾመ ሙሉጌታ በ1998 ዓ.ም ‹‹በቤንሻንጉል ጉሙዝ በድባጤ ወረዳ የለቅሶ ስነ ስርዓት›› በሚል ርዕስ ያዘጋጀውን ጥናታዊ ፅሁፍ አቅርቧል፡፡ ጥናታዊ ፅሁፉ በሶስት ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ ምዕራፍ አንድ የጥናቱ ዳራ፣ ዓ ላማ፣ የ መረጃ አሰባሰብ ዘዴውና የመሳሰሉት ጉዳዮች የተጠቀሱበት ሲሆን፣ ምዕራፍ ሁለት ደግሞ ተዛማጅ ጥናቶች የተቃኙበት፣ የሙሾ ግጥሞች ስነቃላዊ ባህርያት የተዳሰሱበትና ስለ ባህል፣ ልደት፣ ግዝረትና ሰርግ ምንነት ማብራሪያ የተሰጠበት ክፍል ነው፡፡ አጥኚው በምዕራፍ ሶስት ወጣት ሲሞት፣ አዛውንት ሲሞት፣ ሰው የገደለ ሲሞት፣ አውሬ የገደለ ሰው ሲሞትና በጥይት ተመትቶ የሞተ ሰው ሲያጋጥም የሚደረግላቸውን የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔዎች በዝርዝር አቅርቧል፡፡ የቀብር ጉድጓድ እንዴት እንደሚዘጋጅና የአቀባበር ሥርዓቱን አመልክቷል፡፡ የማህበረሰቡ አባላት ለሟቾቹ የሚገጥሟቸውን የጉምዝኛ ግጥሞች ከነአማርኛ ትርጉማቸው አስቀምጧል፡፡ በጥናቱ ማጠቃለያ ደግሞ የወረዳው ነዋሪዎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጅቶች የሚባሉትን ለይቶ እንዲያውቃቸውና እንዲተዋቸው ያሳስባል፡፡

አቡበከር ሀሰን በ1998 ዓ.ም ‹‹የሺናሻ ብሔረሰብ የሐዘንና የተዝካር ስርአት ክዋኔ›› በሚል ርዕስ ያጠናውን ጥናት አቅርቧል፡፡ ጥናቱ በአራት ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ በመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ ዓላማ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ የጥናቱ ወሰን፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ የጥናቱ አደረጃጀት፣ በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና እንደ መፍትሄ የተወሰዱ እርምጃዎች በዝርዝር ቀርበዋል፡፡ ምዕራፍ ሁለት ‹‹የንድፈ ሐሳባዊ ዳራ እና የተዛማጅ ጥናት ቅኝት›› የሚል ርዕስ የተሰጠው ሲሆን ‹‹ንድፈ ሐሳባዊ ዳራ›› በሚለው ንዑስ ክፍል ሥር ስለ ስነቃል ምንነት ተገልጿ፡፡ ‹‹የተዛማጅ ጥናት ቅኝት›› በሚለው ንዑስ ክፍል ውስጥ ደግሞ በተመሳሳይ ርእሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሰሩ ቀደምት ጥናታዊ ፅሁፎች ተዘርዝረዋል፡፡ ጥናታዊ ፅሁፎቹ ከእርሱ ጥናት ጋር ያላቸው ተመሳሳይነትና ልዩነት ምን እንደሆነም ገልጿል፡፡

በምዕራፍ ሦስት በሺናሻ ብሔረሰብ ሰው ሲሞት ከቀብር በፊት፣ በቀብር ጊዜና ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ ስርዓቶች ምን ምን እንደሆኑ፣ የፍትሃት (የሻሮ) እና የተዝካር (የተስካራ) ስርአታቸው ምን እንደሚመስል ተንትኗል፡፡ ለትንታኔ ያመቸው ዘንድ ወጣት ሲሞት፣ ጎልማሳ ሲሞት፣ አዛውንት (ባልቴት) ሲሞቱ እና ጀግና ሲሞት የሚከናወኑ የለቅሶ ስርዓቶችን ከፋፍሎ አቅርቧል፡፡ በለቅሶ ስነስርአቱ በሚገጠሙ የሙሾ ግጥሞች ላይም ይዘታዊ ትንተና አድርጎባቸዋል፡፡ በምዕራፍ አራት የጥናቱን ማጠቃለያ አቅርቧል፡፡

ሽመልስ አክሊሉ በ1997 ዓ.ም ‹‹የቋሪት ወረዳ የለቅሶ ስነስርአትና የለቅሶ ግጥም ይዘት ትንተና›› በሚል ርዕስ ያጠናውን ጥናት አቅርቧል፡፡ ‹የወረዳውን የሙሾ ግጥሞች ተንትኖ መመልከት› እና ‹በቋሪት ወረዳ ውስጥ የሚገኘውን የለቅሶ ሥርዓት ማሳየት› የሚሉት የጥናቱ አበይት ዓላማዎች ናቸው፡፡ ዓላማው አድርጎ ያነሳቸውን ጉዳዮች በጥናት ወረቀቱ ሶስተኛው ምዕራፍ ላይ በተለያየ ርዕሶች ከፋፍሎ ተመልክቷቸዋል፡፡ በተለይ ለሙሾ ግጥሞች የተለየ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ግጥሞቹ የአካባቢውን ማህበረሰብ ልዩ ልዩ ባህላዊ እንቅስቃሴዎችንና ማህበራዊ ጉዳዮችን የሚያሳዩ መሆናቸውን ገልጿል፡፡

አስቴር አንጀሎ በ1997 ዓ.ም ‹‹የጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስርዓት›› በሚል ርዕስ ያጠናችውን ጥናት አቅርባለች፡፡ አስቴር፣ የጋሞ ብሔረሰብ የለቅሶ ስነስርአት ምን እንደሚመስልና ከሌሎች ብሔረሰቦች ጋር ያለውን የባህል ዝምድናና ልዩነት በጥናቷ አሳይታለች፡፡ የብሔረሰቡን የለቅሶ ስርአት ‹‹ከቀብር በፊት››፣ ‹‹በቀብር ጊዜ›› እና ‹‹ከቀብር በኋላ›› ብላ በመከፋፈል ከነክዋኔዎቹ አሳይታለች፡፡ በለቅሶ ስነስርዓቱ ላይ የሚገጠሙ ግጥሞችንም እንደሟች ማህበራዊ ደረጃ፣ ዕድሜና ፆታ ከፋፍላ አቅርባለች፡፡ ግጥሞቹ በእነማን ሊቀርቡ (ሊደረደሩ) እንደሚችሉም ጠቁማለች፡፡ በመጨረሻም የአስከሬን ሳጥን የሚሰራበት እንጨት ሟቹ(ቿ) በማህበረሰቡ ዘንድ እንዳለው ክብርና ተቀባይነት እንደሚለያይ ገልፃለች፡፡

ፊለገሀይወት ዘገየ በ1997 ዓ.ም ‹‹በባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ የቀብር ስነስርአትና ግጥሞች ስብስብ ይዘት ትንተና›› በሚል ርዕስ ጥናት አድርጋለች፡፡ ሴቶችና ወንዶች ሲሞቱ የሚደረደሩ የሙሾ ግጥሞችን ማስተዋወቅ እንዲሁም የህዝቡ መገለጫ የሆነውን ስነቃል በመቀረስ ጠብቆ ማቆየትን አላማዋ በማድረግ ጥናቷን አካሂዳለች፡፡ በጥናቷ ከቀብር በፊት፣ በቀብር ጊዜና ከቀብር በኋላ የሚደረገውን የለቅሶ ስነስርዓት አጠቃላይ ገፅታ፣ የተለያዩ አካላትን ሚና፣ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ስርአቶችን ተንትና አቅርባለች፡፡ በለቅሶ ስነስርአቱ ላይ የሚቀርቡ ናቸው ባለቻቸው የሙሾ ግጥሞች ላይም ስብስብ ይዘታዊ ትንተና አድርጋለች፡፡ የዕድሮችንና የማህበራትን ሚናም ገልፃለች፡፡ በጥናቷ ማጠቃለያ ላይም የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ከሚያሳውቁ ስነቃሎች መካከል የለቅሶ ግጥሞች ግንባር ቀደም ተጠቃሽ መሆናቸውን በመጠቆም ያላቸውን ከፍተኛ ሚና አስረድታለች፡፡

ወርቃየሁ አረጋ በ1995 ዓ.ም ‹‹የአዊ ህብረተሰብ ሴንቲ (የለቅሶ ስርአት) እና የአወኚ ዚንዚምኚ (የሙሾ) ግጥሞች ይዘት ትንተና›› በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዳለች፡፡ ጥናቷ በአራት ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፈለ ሆኖ በምዕራፍ አንድ የጥናቱ አላማና አስፈላጊነት፣

የመረጃ አሰባሰብ ዘዴ፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ እርምጃዎች፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ አቀራረብና ስለ አገው ብሔረሰብ ታሪካዊ ዳራ ገልፃለች፡፡ በምዕራፍ ሁለት ቀደምት ጥናቶችን ቃኝታለች፤ የሙሾ ግጥሞች ስነቃላዊ ባህርያትንም አብራርታለች፡፡

በምእራፍ ሶስት የህብረተሰቡን - የአዊን ህብረተሰብ- የለቅሶ ስርዓት(ሴንቲ) ከቀብር በፊት (ዴወፅዴስፍና)፣ የቀብር ሥርዓት (ዴወፅዊ) እና ከቀብር በኋላ (ዴወጽዴስ) ብላ በመከፋፈል አቅርባለች፡፡ በእነዚህ ጊዜያት የሚኖሩ ክንውኖችን በስፋት ለማሳየት ጥረት አድርጋለች፡፡ የለቅሶ ስነስርአቱ የተሳካ እንዲሆን በማድረግ ረገድ አድሮች የሚጫወቱትንም ከፍተኛ ሚና ገልጻለች፡፡ በምእራፍ አራት የሙሾ ግጥሞችን ለወንዶች (ማለትም አባት ሲሞት፣ ወንድም ሲሞት፣ ልጅ ሲሞት የሚገጠሙ ግጥሞች) እና ለሴቶች (ማለትም እናት ስትሞት፣ እህት ስትሞት) የሚገጠሙ በማለት የይዘት ትንተና አድርጋባቸዋለች፡፡

ዘላለም ኢዮብ በ1995 ዓ.ም ‹‹በኅፋ ብሔረሰብ ባህላዊ ለቅሶ (ዬሆ) ግጥሞች ክዋኔና ስነግጥማዊ ገፅታ›› በሚል ርዕስ ያደረገውን ጥናት አቅርቧል፡፡ የኅፋን ብሔረሰብ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔና በለቅሶ አጋጣሚ የሚባሉትን ግጥሞች ስነግጥማዊ ገፅታቸው ምን እንደሚመስል የተመለከተበት ይህ ጥናት በአምስት ምዕራፎች የተከፈለ ነው፡፡ በምዕራፍ አንድ መግቢያ፣ የጥናቱ አስፈላጊነትና አላማ፣ የጥናቱ ወሰን፣ የመረጃ አሰባሰብ ዘዴና በወቅቱ ያጋጠሙ ችግሮች እንዲሁም የጥናቱ አቀራረብ ተገልፀዋል፡፡ በምዕራፍ ሁለት በተመሳሳይ ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ የተሰሩ ቀደምት ጥናታዊ ፅሁፎች ተቃኝተዋል፡፡ በምዕራፍ ሦስት ስለ ኅፋ መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ ስለ ብሔረሰቡ ጥንተ አመጣጥና ስያሜ፣ ስለ ቋንቋው፣ ስለ ማህበረሰባዊ ስብጥሩ፣ ስለ ማህበረ-ባህላዊ ገፅታዎችና ስለ መሳሰሉት ጉዳዮች ገልጿል፡፡

በምዕራፍ አራት በብሔረሰቡ ለህፃናት፣ ለወጣቶች፣ ለጎልማሶችና ለአዛውንቶች የሚደረገውን ባህላዊ የለቅሶ ስርአት-ለምሳሌ ባህላዊ የአቀማመጥና አቋቋም ስርዓት፣ የለቅሶ ቅዳሚ ዝግጅት ስርአት፣ የመቃብር አዘገጃጀትና የቀብር ስነስርአት ወዘተ.ጉዳዮች- አንስቷል፡፡ በዚህ ክፍል ህጻናትና አዛውንቶች ሲሞቱ ብዙም እንደማይለቀስ በአንፃሩ ወጣቶችና ጎልማሶች ሲሞቱ በጣም እንደሚለቀስ ገልጿል፡፡ አንበሳና ነብር ለገደሉ የማህበረሰቡ አባላት ደግሞ ጦርና ጋሻ ተይዞ እንደሚለቀስላቸው ጠቅሷል፡፡ የለቅሶው ቅድመ ዝግጅት ስነስርአትና የመቃብር አዘገጃጀቱ ምን እንደሚመስልም አሳይቷል፡፡ በተጨማሪም ከቀብር በፊት የሚደረጉትን ‹‹ሚሻዬሆ›› እና ‹‹ባለዬሆ›› የሚባሉትን የለቅሶ

ሂደቶችና ከቀብር በኋላ የሚደረገውን ‹‹ዶቻዬሆ›› የሚባለውን የለቅሶ ሂደት ዘርዘር አድርጎ አቅርቧል፡፡

በምዕራፍ አምስት ስለስነግጥም ምንነትና አበይት ባህርያት ከመግለፁም በላይ የብሔረሰቡ አባላት በልጆች ሞት ጊዜ፣ በወጣቶች ሞት ጊዜ፣ በአዋቂ ሞት ጊዜና በአዛውንት ሞት ጊዜ ለለቅሶ በሚጠቀምባቸው ግጥሞች ላይ የይዘት ትንተና አድርጓል፡፡ በሙሾ ግጥሞች ውስጥ ዘይቤያዊ ንግግሮች እንደሚንፀባረቁና በዋናነት ከሚታዩት የዘይቤ አይነቶች መካከልም አነፃፃሪ ዘይቤ እና ተለዋጭ ዘይቤ ተጠቃሾች እንደሆኑ በትንታኔው አሳይቷል፡፡

ጌጡ ታደሰ በ1989 ዓ.ም ‹‹ክዋኔ በጎንደር ከተማ ለቅሶ ስነስርዓት›› በሚል ርዕስ ጥናት አካሂዷል፡፡ ጥናቱ በሦስት ዋና ዋና ምዕራፎች የተከፈለ ሲሆን በመጀመሪያው ምዕራፍ የእርሱ ጥናታዊ ፅሁፍ ከቀደምት ጥናታዊ ፅሁፎች ጋር ያለውን ዝምድናና ልዩነት ቃኝቷል፡፡ በሁለተኛው ምዕራፍ ስለ ከተማዋ ስለ ጎንደር ህዝብ ወግ፣ ልማድና ባህል እንዲሁም ስለ ለቅሶ አይነትና ባህርያት ገልጧል፡፡ ‹‹ክዋኔ በጎንደር ከተማ የለቅሶ ስነስርአት›› የሚል ርዕስ በሰጠው በሶስተኛው ምዕራፍ ደግሞ ስለ ክዋኔና ከዋኝ አንስቷል፡፡ ከዚህም በቀር አንድ ሰው ከሞተ በኋላ አስከሬኑ ከቤት ሳይወጣ የሚኖረውን የለቅሶ ክዋኔ፣ በጉዞ ፍታት ወቅት የሚኖረውን የለቅሶ ክዋኔ፣ በአፀደ ቤተክርስቲያንና በግብዓተ መሬት ወቅት የሚኖረውን የለቅሶ ክዋኔ እንዲሁም በመርዶና በደመር ጊዜ የሚኖረውን የለቅሶ ክዋኔ አሳይቷል፡፡ ለባላባት፣ ለደሃ፣ ለጀግናና ለመንፈሳዊ ሰው ሞት የሚደረጉ የለቅሶ ክዋኔዎች የተለያዩ እንደሆኑም ጠቁሟል፡፡ አንድ ባላባት ሲሞት በቤት ውስጥ፣ በጉዞ ፍታት፣ በአፀደ ቤተክርስቲያንና በግብአተ መሬት ወቅት የሚደረግለት የለቅሶ ስነ ስርዓት ክዋኔ ደሃ ወይም ጀግና ወይም መንፈሳዊ ሰው ሲሞት ከሚደረግለት የለቅሶ ሥነ ሥርአት ክዋኔ የተለየ እንደሆነ አሳይቷል፡፡ አጥኚው በተለያዩ የማህበራዊ ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚደረጉትን ልዩ ልዩ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች ለማሳየት ያደረገው ጥረት በጠንካራ ጎን የሚነሳለት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በጥናቱ ውስጥ የተገለጸው የለቅሶ ስርአት የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሀይማኖት ተከታዮችን የለቅሶ ስርአት ብቻ ነው፡፡ የጥናቱን ወሰን በደንብ ስላላስቀመጠ እውን ሁሉም የከተማዋ ነዋሪ የአንድ ሀይማኖት ተከታይ ነውን? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡

ወርቁ ማንደፍሮ በ1987 ዓ.ም ‹‹በሊቦ ከምከም ወረዳ የለቅሶ ስነ ስርዓትና የሙሾ ግጥሞች›› በሚል ርዕስ ያካሄደውን ጥናት አቅርቧል፡፡ ወርቁ የየትኛውን ሀይማኖት የለቅሶ

ስነስርአት እንደሚያሳይ ገልጿል፡፡ የጥናቱን ወሰን ጠበብ አድርጎ የአንደኛውን ሀይማኖት (ኦርቶዶክስ ክርስትና ሀይማኖት) ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ብቻ እንደሚመለከት መግለጹ እንደጥንካሬ የሚነሳለት ነው፡፡ በጥናቱ አንድ ሰው ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚቀበርበት ጊዜ ድረስ የሚደረገውን አጠቃላይ የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔና የተወሰኑ የሙሾ ግጥሞችን ከነይዘታዊ ትንታኔያቸው አቅርቧል፡፡ የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔውን በተመለከተበት ክፍል ስነ ስርአቱ እንደየ ሟቹ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ሃይማኖታዊ ሁኔታ እንደሚለያይ አስረድቷል፡፡ የሙሾ ግጥሞችን በተመለከተበት ክፍል ደግሞ ግጥሞቹን ለወጣት፣ ለሽማግሌ፣ ለአባት፣ ለእናት፣ ለወንድም፣ ለእህት ወዘተ. የሚደረደሩ ብሎ በመመደብ ይዘ ታዊ ትንታኔ አድርጎባቸዋል፡፡ የህብረተሰቡ አባላት የለቅሶውን አጋጣሚ በመጠቀም ልዩ ልዩ መልዕክት አዘል የሆኑ የሙሾ ግጥሞችን እንደሚደረድሩም በትንታኔው አመልክቷል፡፡

አጥኚው ወሰንን በመቀንበብ እና መረጃን በማሰባሰብ ረገድ የተወሰኑ ጥንካሬዎች ያሉት ቢሆንም አንዳንድ ጉድለቶችም ታይተውበታል፡፡ ይኸውም ለአብዛኞቹ መረጃዎች ራሱን በዋና የመረጃ ምንጭነት የተጠቀመ መሆኑ ነው፡፡ ራስን በመረጃ ምንጭነት መጥቀስ የሚቻል ቢሆንም አብዝቶ መጠቀም ግን የመረጃዎችን ሚዛናዊነት የሚያዛባ ይሆናል፡፡ የመረጃዎቹን ተአማኒነትም በጥያቄ ምልክት ውስጥ ሊያስገባው ይችላል፡፡

አየለ መሎሪ በ1986 ዓ.ም ‹‹የሀዲያ ህብረተሰብ የለቅሶ ስነስርዓት›› በሚል ርዕስ ያዘጋጀውን ጥናት አቅርቧል፡፡ ጥናቱ የለቅሶ ስነ ስርአትንና የሙሾ ግጥሞችን የያዘ ነው፡፡ የህብረተሰቡን የለቅሶ ስርዓት በተመለከተበት ክፍል የሥርዓቱን ቅደም ተከተላዊ ሂደት ‹‹ቅድመ ቀብር›› እና ‹‹ቀብር›› ብሎ በመለየት ‹‹ከልደት እስከ ሙሽርና ለደረሱ››፣ ‹‹ለአዛውንቶች›› ‹‹ለጀግኖች›› ፣ ‹‹ለሥጋ ደዌ ህመምተኞች›› ወዘተ. የሚደረጉትን ሥርአቶች አሳይቷል፡፡ በዚህ ጥናት ከህጻን ይልቅ ለአረጋዊ የሚደረገው ቅድመ ቀብር ዝግጅት አድካሚ መሆኑ ተወስቷል፡፡ ከሁሉም በላይ የጀግና ሞት ቅድመ ቀብር ዝግጅት የበለጠ አልፌ መሆኑን ያሳየ ስራ ነው፡፡ ከዚህም በቀር የሥጋ ደዌ ህመምተኞች ሲሞቱ በብሔረሰቡ አለመለቀሱን፣ ቢለቀስ ግን የሟች ህመም ወደሌላው ይተላለፋል የሚል ዕምነት እንዳለም አመልክቷል፡፡ ‹‹የቅድመ ቀብር የለቅሶ ስነስርአት›› በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር ከልደት እስከ ሙሽርና ለደረሱ ሟቾች የሚደረጉ ልዩ ልዩ የለቅሶ ሥነስርዓቶችን አመልክቷል፡፡ በቀብር ዕለትና ከቀብር በኋላ የሚኖሩት ባህላዊ ክንዋኔዎች ምን መልክ

እንደሚይዙም አሳይቷል፡፡ እንደዚሁም ለሀብታሞች፣ ለዘረ ብርቱዎችና ጀግንነትን ላሳዩ ሟቾች የሚወጡ የሙሾ ግጥሞችን አካቶ አቅርቧል፡፡

መዓዛ ተስፋይ በ1982 ዓ.ም ‹‹በአጋሜ አውራጃ የቀብር ስነስርዓት አፈፃፀምና የለቅሶ ግጥሞች የይዘት ትንተና›› በሚል ርዕስ ጥናት አድርጋለች፡፡ ጥናት አቅራቢዋ በተላላፊ በሽታ ስለሞተ ሰውና ስለሁለተኛ የቀብር አፈፃፀም ሥርአት አብራርታለች፡፡ ይሁን እንጂ የለቅሶ ስነስርአቱ ለየትኛው የሀይማኖት ተከታይ፣ ለየትኛው ጾታና በየትኛው የእድሜ ክልል ውስጥ ለሞተ ሰው እንደሚፈጸም የጠቆመችው ነገር የለም፡፡ ጥናት በተደረገበት አውራጃ ውስጥ የሚኖሩ ህብረተሰቦች በእድሜ፣ በጾታና በሀይማኖት ልዩነት ሳቢያ የሚያከናውኗቸውን ልዩ ልዩ ድርጊቶች በግልጽ አላሳየችም፡፡ አርባ፣ ሙት ዓመት ወዘተ. ከሚባሉት ጊዜያት ይልቅ በአብዛኛው የመጀመሪያ ቀብርና ሁለተኛ ቀብር በሚባሉት ጊዜያት የሙሾ ግጥሞች እንደሚደረደሩ አስረድታለች፡፡

ወርቁ ወጌ ‹‹በቸሃ ጉራጌ የልደትና የሞት ስርዓት›› በሚል ርዕስ ያጠናውን ጥናት በ1982 ዓ.ም አቅርቧል፡፡ ‹‹ለቅሶ ከህይወተ ሕልፈት እስከ መካነ መቃብር››፣ ‹‹የለቅሶ ማጽናኛዎች››፣ ‹‹የተዝካር አወጣጥ ሥርዓት›› ወዘተ. በማለት በመደባቸው ንኡሳን ርዕሶች ሥር ስለ ለቅሶ አጠቃላይ ሥርዓት አትቷል፡፡ የግጥሞቹን ይዘትና ህብረተሰቡ ምን ጊዜ ምን ዓይነት ግጥም እንደሚገጥምም ገልጧል፡፡ በብሔረሰቡ ህፃን፣ ደሃ፣ ሽማግሌ፣ ሀብታም፣ ጀግና፣ ሰነፍና ብርቱ ገበሬ፣ የአደባባይ ሰው፣ ወዘተ. በሚሞትበት ጊዜ የለቅሶ ደንቡ የተለያየ መሆኑን አመልክቷል፡፡ በዕድሜ እና በማህበራዊ ደረጃ ልዩነት ምክንያት የለቅሶ ስነስርአቱ የሚለያይ መሆኑን ማመልከቱ መልካም ነው፡፡ ይሁን እንጂ እንደሌሎች ጥናት አቅራቢዎች ወርቁም የጾታንና የሀይማኖትን ልዩነት ከግምት ውስጥ አላስገባም፡፡

ጥላሁን ኢ.ቢ.ዶ በ1982 ዓ.ም ‹‹የጌዲኦ ህብረተሰብ የለቅሶ ስርአት›› በሚል ርዕስ ያዘጋጀውን ጥናት አቅርቧል፡፡ ጥናቱ ከህልፈተ ህይወት እስከ ቀብር ፍጻሜ ድረስ ያሉትን ሥርዓቶች ያሳያል፡፡ በጌዲኦ ህብረተሰብ ከህፃን እስከ አረጋዊ ድረስ ያሉ ሰዎች ሲሞቱ የለቅሶ ስነ ስርአት ክዋኔው የተለያየ እንደሆነ ገልጧል፡፡ ለህፃን የሚደረግ፣ ለወጣት የሚደረግ፣ ለጎልማሳ የሚደረግ፣ ለአረጋዊ የሚደረግ ብሎ በመከፋፈል ለእያንዳንዳቸው የሚደረጉ ስነስርአቶችን አመልክቷል፡፡ በጾታ ልዩነት ምክንያት የሚያከናውኗቸውን ልዩ ልዩ ክዋኔዎችም ከግምት ውስጥ በማስገባት ለወንዶችና ለሴቶች የሚደረግ በማለት አንስቷል፡፡

የአንድ ሰው ነፍስ ከስጋው ከተለየችበት ጊዜ ጀምሮ ግብአተ መሬቱ እስከሚፈፀምበት ጊዜ ድረስ ለሟቹ የሚደረጉ ነገሮችንም በዝርዝር አስረድቷል፡፡ የህብረተሰቡ የገዳ ስርአት በለቅሶ ስነስርአት ውስጥ ጉልህ ድርሻ እንዳለው ጠቁሞ ስለ ገዳ ስርአትም አብራርቷል፡፡

ድጋፌ ፈይሳ በ1975 ዓ.ም ‹‹የሲዳማ ብሔረሰብ የለቅሶ ሥርአት›› በሚል ርዕስ ጥናት አድርጓል፡፡ ድጋፌ በግጥሞች ይዘትና ቅርፅ ላይ ብቻ ሳያተኩር የለቅሶ ስነ ስርአቱንም ጭምር ዳስሷል፡፡ ሙሾው ከክዋኔው ጋር ያለውን ዝምድናም በሰፊው አሳይቷል፡፡ ከግርዘት በፊት የሚከበር በአልን(‹‹ሉዋ››ን) አስመልክቶም ማብራሪያ ሰጥቷል፡፡ አንድ አረጋዊ (ጨሚሳ) ሲሞት የሚደረገውን ስርአት (ከሥርአተ ግንዘት እስከ ተዝካር ያለውን ቅደም ተከተላዊ ሂደት) ቅድመ ቀብር፣ ቀብር እና ድህረ ቀብር ብሎ በመከፋፈል አሳይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ለአረጋዊ ሞት የሚደረገውን የለቅሶ ስነስርአት ለምን እንደመረጠ የገለጸው ነገር የለም፡፡ ይህ ስነስርአት የብሄረሰቡን አጠቃላይ የለቅሶ ስነስርአት ይወክላል ብሎ መውሰድ ያስቸግራል፡፡ የሙሾ ግጥሞችን ይዘትና ቅርጽ በተነተነበት ክፍል በሰላም ጊዜ ሙሾ መናገር ሟርት ነው በሚል ዕምነት የሙሾ ግጥሞችን እንዲነግሩት ይጠይቃቸው የነበሩ የዕድሜ ባለፀጋዎች ፍቃደኛ እንዳልነበሩም ጠቁሟል፡፡

ሐረገወይን ድፋባቸው በ1974 ዓ.ም ‹‹የክስታንኛ የለቅሶ ግጥሞች›› በሚል ርዕስ ያዘጋጀችውን ጥናት አቅርባለች፡፡ ጥናቷ ትኩረቱን ያደረገው የክስታኔ ማህበረሰብን የለቅሶ ሁኔታ በማስተዋወቅና የሙሾ ግጥሞችን ይዘት በመተንተን ላይ ነው፡፡ የጨቦና ጉራጌን ከክስታኔ የለቅሶ ስርአት ጋር በማነፃፀር ልዩነቱን አጠር አድርጋ አመልክታለች፡፡ ገለፃዋ አነስ ያለ ይሁን እንጂ ‹‹የለቅሶ ስነስርአት›› በሚለው ንኡስ ክፍል ስር አንድ ሰው ከሞተበት ጊዜ ጀምሮ እስከፍፃሜ ያለውን ስርዓት ዘርዝራለች፡፡ በተጨማሪም በሥርዓቱ ላይ ወንዶችና ሴቶች ያላቸውን ሚና በመግለፅ የቀብር ሥርአቱ እንደሟቹ እድሜ ፣ ፆታና ሙያ እንደሚለያይ ጠቁማለች፡፡ የሙሾ ግጥሞችን የተነተነችበት መንገድ ለሌሎች አጥኚዎች በመነሻነት ሊያገለግል የሚችል ነው፡፡ የግጥሞቹ ይዘት በሟች ዕድሜ፣ ፆታ፣ ማህበራዊ ደረጃ ወዘተ. የተለያየ እንደሚሆን አመልክታለች፡፡ እነዚህ ከፍ ሲል በዝርዝር የተመለከትናቸው ጥናታዊ ፅሁፎች ከኔ ጥናታዊ ፅሁፍ ጋር በብዙ መልኩ የሚመሳሰሉበትም የሚለያዩበትም ሁኔታ አለ፡፡ ሁሉም ጥናቶች በለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ላይ ያተኮሩ መሆናቸው ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስላቸዋል፡፡ የግንዘት ሥርዓትን፣ የአቀባበር ሥርአትን፣ ከቀብር መልስ/በኋላ የሚደረጉ ስነስርዓቶችን ወዘተ. ያብራራሉ፡፡ የእኔም

ጥናት እንደዚሁ፡፡ ይሁን እንጂ ከነዚህ ጥናታዊ ፅሁፎች መካከል ከፊሎቹ በክርስትና ሐይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ላይ ብቻ ትኩረት የሚያደርጉ ናቸው፡፡ ከፊሎቹ ደግሞ በእስልምና ሐይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ ላይ ብቻ፡፡ የሁለቱን ሀይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔ በንፅፅር የሚያቀርቡ ጥናቶች አይደሉም፡፡ የኔ ጥናት የሁለቱን ሀይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት በማነፃፀር በመካከላቸው ያለውን ተመሳሳይነትና ልዩነት የሚያሳይ በመሆኑ ይለያል፡፡ ከዚህም በቀር ለጥናት በተመረጠው ህብረተሰብ ባህል፣ ቋንቋ እና መገኛ ቦታም ይለያል፡፡

## 2.2 የጽንሰ ሐሳብ ቅኝት

### 2.2.1 ሞት እና የለቅሶ ስነስርዓት

በዚህ ንኡስ ክፍል ስለሞት እና ሞትን ተከትለው ስለሚደረጉ የለቅሶ ስነስርአቶች ንድፈ ሀሳባዊ (theoretical) ቅኝት ይደረጋል፡፡ ስለሞትና ስለለቅሶ ከማየታችን በፊት የ‹‹ስነስርአት›ን ምንነት እንመልከት፡፡ የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ያዘጋጀው መዝገበ ቃላት ‹ስነስርዓት› ለሚለው ቃል ‹‹አንድን ድርጊት በተመለከተ የተለመደ ስርአትን ወይም ደንብን ተከትሎ የሚሄድ ክንውን›› የሚል ፍቺ ሰጥቶታል (1993፣138)፡፡ በመዝገበ ቃላቱ ፍቺ መሰረት ሥነስርአት ሁለት ነገሮችን አካቶ ይይዛል- የሚፈፀም ክንውንን (ድርጊትን) እና ድርጊቱ ሲፈፀም ሊከተለው የሚገባውን ስርአት ወይም ደንብ፡፡ ይህ ስርአትና ደንብ በሚፈፅሙት ሰዎች ወይም ማህበረሰቦች ዘንድ የተለመደና የታወቀ ነው፡፡

ስነስርአት የሚለው የአማርኛ ቃል ‹‹ceremony›› እና "rite" የሚሉትን የእንግሊዝኛ ቃላት በመወከል እንዲያገለግል የታሰበ ነው፡፡"ceremony" ለሚለው ቃል Encyclopedia Americana የሚከተለውን ፍቺ ሰጥቶታል፤‹‹a formal act or series of acts conducted with more or less elaborate ritual that marks the sacredness or solemnity of an occasion ›› (vol. 6,

1983, 199)[1]:: ከዚህ መረዳት የሚቻለው ስነስርአት፣ በአንድ አጋጣሚ ወይም በዓል ላይ የሚደረጉ ተከታታይነት ያላቸውን ድርጊቶች የሚያሳይ እንደሆነ ነው:: የሚፈፀሙት ድርጊቶች የተያያዙና ቅደም ተከተላቸውን የጠበቁ መሆን እንዳለባቸውም እንገነዘባለን::

"Rite" ለሚለው ቃል ደግሞ የOxford English Dictionary የሚከተለውን ፍቺ ሰጥቶታል፤ "a formal procedure or act in a religious or other solomn observances" (vol. 13, 1989,990):: እንደመዝገበ ቃላቱ ፍቺ ‹rite› ሃይማኖታዊ ይዘት ባላቸው ወይም በሌሎች በሚታወቁና በሚከበሩ በዓላት ላይ በቅደም ተከተል የሚከናወኑ ድርጊቶችን አካሄድ የሚያመለክት ነው::ስለ ስነስርአት ምንነት ለመንደርደሪያ ያህል ያነሳሁትን ሀሳብ በዚሁ ገታ ላድርግና በመቀጠል ስለሞት እና ሞትን ተከትለው ስለሚደረጉ የለቅሶ ስነስርአቶች ንድፈ ሐሳባዊ ቅኝት አደርጋለሁ::

የተለያዩ መጻህፍት ሞትን በተለያየ መንገድ ገልጸውታል:: World Book Encyclopedia ‹‹ሞት የህይወት ፍጻሜ (ማብቂያ) ነው››ይላል(Vol.5,1992,60):: Encyclopedia of religion and ethics ደግሞ ‹‹ሞት የነፍስ ከስጋ መለየት ነው›› ብሎ ገልጾታል (vol IV,415):: ሞት በማንኛውም ማህበረሰብ የእለት ከእለት እንቅስቃሴ ውስጥ የሚከሰት፣ በሰው ልጅ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ልዩ ስፍራ ያለው የተፈጥሮ ግዴታ ነው:: ሞት በህይወት ኡደት ውስጥ ትልቅ ድርሻ ያለው ነው:: የሰው ልጅ ይወለዳል፤ ያድጋል፤ እድሜው እስከፈቀደለት ጊዜ ድረስ ይኖራል:: በመጨረሻም ጊዜውን ወይም ዘመኑን ጠብቆ ይሞታል:: እንደማንኛውም ህይወት እንዳለው ፍጥረት ሁሉ የሰው ልጅም ስነህይወታዊ ሞትን (biological death) ይሞታል:: ይህ አሟሟቱ ከእንስሳትና ከዕፅዋት ጋር ያመሳስለዋል:: ይሁን እንጂ የእርሱ ሞት በቀሪ ወገኖቹ ላይ ጠንካራ ስሜት የሚያስከትል በመሆኑ ሞቱን ከሌሎቹ ሞት እንዲለይ ያደርገዋል::

ሞት ከሚያስከትላቸው ጠንካራ ስሜቶች መካከል አንዱ ለቅሶ ነው:: የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ባዘጋጀው መዝገበ ቃላት ውስጥ ‹‹ለቅሶ›› የሚለው ቃል ‹‹ሃዘን፤ ሙሾ፣ ዋይ ዋይታ፣ መጮህ፣ ማንባት፤ የእንባ መመንጨት፣ መውረድ፣ መፍሰስ›› የሚል ፍቺ ተሰጥቶታል (1993፣17):: ለቅሶ በተለያዩ ምክንያቶች ይከሰታል:: የሰው ልጅ

1 ከዓመተ ምህረቱ ጎን የተጻፈው ደራሲ ወይም መጽሐፍ በእንግሊዝኛ ቋንቋ በሚሆንበት ጊዜ አመተምህረቱ የጎርጎሮሳውያንን የዘመን አቆጣጠር የሚያሳይ ሲሆን በአማርኛ ከተጻፈ ደግሞ የኢትዮጵያውያንን የዘመን አቆጣጠር የሚያመለክት መሆኑን ልብ ይሏል::

ያሰበው ነገር ሳይሳካለት ሲቀር፣ የመንፈስ ዕናት ሲጎድለው፣ ጥቃት ሲደርስበት፣ ሲከፋ፣ የተለያዩ መጥፎ አጋጣሚዎች (ክስተቶች) ሲከሰትበት ወዘተ. ያለቅሳል፡፡ የማልቀሻ ሰበቦቹ ብዙ ናቸው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን በአምሳሉ የተፈጠረ ወገኑ፣ ዘመዱ፣ የአብራኩ ክፋይ... ሲሞት የሚያለቅሰው ለቅሶ በእጅጉ የተለየ ነው፡፡ የሰው ልጅ ሞት አብሮ የኖረና የተለመደ ቢሆንም ሁሌም ከፍተኛ የሆነ ስሜትን ያጭራል፤ ያስለቅሳል፡፡

አንድ ሰው ሲሞት እንደየባህሉ ሁኔታ የሚከናወኑ ስነስርአቶች ይኖራሉ፡፡ ሟቹ እንደበቀለበት ማህበረሰብ ባህልና እምነት የተለያዩ ክንውኖችና ስርአቶች ይደረጋሉ፡፡ በመሆኑም የለቅሶ ስርዓት አከዋወን ከማህበረሰብ ማህበረሰብ ከባህል ባህል ይለያያል፡፡ በአንዱ ማህበረሰብ ውስጥ ያለው ሁኔታ ከሌላው ፈፅሞ የማይገናኝ ወይም ለዚያ ማህበረሰብ እንግዳ ሊሆን ይችላል፡፡ በማህበረሰቦች መካከል ያለውን የለቅሶ ስነስርአት ልዩነት አስመልክተው ዘሪሁን አስፋው የሚከተለውን ብለዋል፤ ‹‹በአንዱ የለቅሶ ስነስርአት ሙሾ እየተደረደረ ደረት ይደለቃል÷ ይዘለላል፡፡ በሌላው ደግሞ የሟች የቅርብ ዘመዶች ፊታቸውን ይቧጥጣሉ ፀጉራቸውን ይነጫሉ፡፡ በቀረው ደግሞ ከበሮ ይዞ በመጨፈር የለቅሶ ክዋኔ ይደረጋል፡፡ በሆታና በድልቂያ ሙታቸውን የሚሰናበቱም አሉ›› (1996፣ 22)፡፡

ለብዙ ሰዎች የለቅሶ ስነስርአት አጠቃላይ ክዋኔዎች ሟች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ሞተ በሚል እሳቤ ብቻ የሚደረጉ አይደሉም፤ ከዚህኛው ዓለም ወደ ሌላኛው ዓለም ሄደ (ተሸጋገረ) በሚል ዕምነትም ጭምር እንጂ፡፡

> For many people, a funeral symbolizes a passage from one life to another, rather than the end of a person's existence. Such a ceremony, which is associated with the completion of one phase of life and the beginning of another, is called a rite of passage (World Book Encyclopedia, vol.7,1978,483)

ሟች አንደኛውን የህይወት እርከን ጨርሶ ሌላኛውን የህይወት እርከን ጀመረ ተብሎ እንደሚታሰብ ፅሁፉ ይገልፃል::

ከማህበረሰብ ማህበረሰብ የሚለያይ የለቅሶ ስነስርአት ቢኖርም በዓለም ዙሪያ በሚገኙ ሕዝቦች ዘንድ ተመሳሳይ የሆኑ ክንውኖች እንዳሉ ከWorld Book Encyclopedia ላይ የተገኘው የሚከተለው ፅሁፍ ያስረግጥልናል፡፡

> Funeral customs vary from society to society, but many of the same practices are found through out the world. These practices include public announcement of the death; preparation of the body; religious ceremonies or other services; a procession; a burial or other form of disposal; and mourning (vol.7,1978,483)::

ሟች መሞቱን ለሰዎች ማሳወቅ፣ ለሬሳው ሐይማኖታዊ ስነስርአቶችን ወይም ሌሎች አገልግሎቶችን መፈፀም፣ መገነዝ፣ ወደ ቀብር ቦታ ጉዞ ማድረግ፣ ሬሳውን መቅበር እና ለሟች ማልቀስ በሁሉም የዓለም ህዝቦች ዘንድ የሚከናወኑ ድርጊቶች እንደሆኑ ከፅሁፉ እንገነዘባለን፡፡

ቀደም ሲል በ‹የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት› ውስጥ እንደተመለከትነው ለቅሶ እንደየባህሉና ሐይማኖቱ ሁኔታ በተለያዩ መንገዶች ይገለፃል፡፡ ሐዘንተኞች ፀጉራቸውን በመላጨት (አንዳንዶቹ ባለመላጨት)፣ ልብሳቸውን ባለማጠብ፣ ጥፍራቸውን ባለመቆረጥ፣ ሃዘንን ይገልፃሉ የሚባሉ አልባሳትን በመልበስ፣ ጫማን ባለማድረግ፣ ወዘተ. ሐዘናቸውን ይገልፃሉ፡፡

ሞት በለቅሶ፣ በጩኸት፣ በዋይታ፣ በሰቆቃ ወዘተ. ይታጀባል፡፡ ሞትን ተከትሎ ከሚፈፀሙ ልዩ ልዩ ክንውኖች መካከል ደግሞ ቀብር ይጠቀሳል፡፡ ከፍ ብሎ በተጠቀሰው የእንግሊዝኛ ፅሁፍ ውስጥም እንደተጠቀመው ከሞት በኋላ ከሚከናወኑና ሁሉንም የዓለም ህዝቦች ከሚያመሳስሏቸው አበይት የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔዎች መካከል አንዱ ቀብር ነው፡፡ ሞትና ቀብር እጅጉን የተቆራኙ ናቸው፡፡ ትስስራቸው ጥብቅ ነው፡፡ ሰው በህይወት እያለ ይወጣል ይወርዳል፣ ይጥራል ይግራል፣ ይወድቃል ይነሳል፡፡ በመጨረሻም ጊዜውን ጠብቆ የማይቀረውን ሞቱን ይሞታል፣ከዚያም ይቀበራል፡፡ የአንድን ሰው ሞት ክስተት ተከትሎ እያንዳንዱ ማህበረሰብ እንደየራሱ ባህልና እምነት ሊለያይ የሚችል የቀብር ሥነሥርዓትን ይፈፅማል፡፡ የቀብር ስነስርዓት ከጥንት ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ በሰው ልጅ ማህበራዊ ህይወት ውስጥ በየጊዜው የሚታይና በርካታ ሐይማኖታዊና ባህላዊ ክንውኖች የሚፈፀምበት ነው፡፡

የቀብር ስነስርዓት የሟችን ግብዓተ መሬት መፈፀም ብቻ የሚመለከት አይደለም፣ ሟችን ለመቅበር ቀደም ብለው የሚደረጉ ልዩ ልዩ ክዋኔዎችን ጭምር የሚያካትት እንጂ፡፡ በኪዳነ ወልድ ክፍሌ የተዘጋጀው የአማርኛ መዝገበ ቃላት ‹ቀብር› ለሚለው ቃል ‹‹ቀበራ፣ አቀባበር፣ ግንዛት፣ አገናነዝ፣ የሬሳ ህግ፣ ሽቱ መቅባት ማጠን ማጤስ፣ መፍታት ማልቀስ፣

ርግጾ ሙሾ፤ የመሰለው ኹሉ›› የሚል ፍቺ ይሰጠዋል (1948፣781)፡፡ በዚህ ፍቺ መሰረት የአገናነዝ ስርዓቱ፣ አስክሬኑ መጥፎ ሽታ እንዳይፈጥር የሚደረገው ጥንቃቄ ፣ ሽቶ መቀባቱ፣ ማጠኑ፣ ጭስ ማጨሱ፣ ፍትሃቱ እና የመሳሰሉት ሁሉ በቀብር ስነስርዓት ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡

## 2.2.2 ክዋኔ

ማህበራዊ ልማድ፣ ቁሳዊ ባህል፣ ሀገረሰባዊ ትውን ጥበባት እና ስነቃል የፎክሎር ዋና ዋና ዘርፎች ናቸው፡፡ እነዚህ ዋና ዋና ዘርፎችና በነዚህ ስር የሚመጡት ዝርዝር ጉዳዮች በሙሉ ያለ ክዋኔ የሚታሰቡ አይደሉም፡፡ ክዋኔ የጋራ ባህሪያቸው ነው፡፡ በማህበራዊ ልማድ ሥር ከሚጠኑት መካከል አንዱ የሆነው የለቅሶ ስነስርዓትም እንደሌሎቹ የጥናት መስኮች ሁሉ በክዋኔ ይታጀባል፤ ይከወናል፡፡ በለቅሶ ስነስርዓት ጊዜ የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፣ ሁነቶች፣ ሐይማኖታዊና ባህላዊ ክንውኖች (ድርጊቶች)፣ ልዩ ልዩ ድምፆችና የመሳሰሉት ሁሉ በክዋኔ ውስጥ የሚካተቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ጉዳዮች በአንድነት ሆነው ሲመጡ ነው የሠውን ስሜት የሚነኩት፤ የሚያሳዝኑት፤ የሚያስለቅሱት፡፡ ይህን ሐሳብ ፈቃደ አዘዘ እንዲህ ሲሉ ያጠናክሩታል፡፡

> ጠቅላላ ድባቡ፣ የሙሾ አውራጁ ድምፅ ማማር፤ የዜማ አሰባበር አወራረዱ፤ በእጁ በድምጿና በፊቷ የምታደርጋቸው ድርጊቶች፤ ከተቀባዮቹ ጋር የምታደርገው የዜማና ግጥም መለዋወጥ፤ የደረት መምታቱ፣ የዋዬ- ዋዩ፤ በሀዘንተኛው አዕምሮ ውስጥ ስለሚቹ የተቀረፁ ሀሳቦችና ሀዘንተኛ በሀዘንተኛ ላይ ያለው ተፅዕኖ (influence) (የአንዱ ማልቀስ ለሌላው ሰበብ ሊሆን ይችላልና) ወዘተ. እነዚህ ሁሉ በአንድ ህብር ሲገኙ ነው ሰውን የሚያባቡ፣ የሚያሳዝኑ የሚያስለቅሱት፡፡ የአፍአዊ ኪነተ ቃል ዘርፍ የሆነው ሙሾም ምሉእ ክዋኔውን አገኘ የምንለው ይሄኔ ነው (1970፣2)፡፡

ክዋኔ ድርጊቶች የሚፈፀሙበትን ቦታ፣ ጊዜ፣ አጋጣሚ፣ አውድ እና የመሳሰሉትን ሁሉ ያጠቃልላል፡፡ ክዋኔ በግልፅ የሚታወቅ መቼት እና መዋቅሮች እንዳሉት Martha እና Martine በሚከተለው መንገድ ይገልፃሉ፤ “Frequently, performances have clear settings and recognizable structures that indicate to participants that the performance is taking place” (2005,128)

ክዋኔ የሚለው ፅንሰ ሐሳብ በውስጡ በርካታ ነገሮችን የሚይዝና ኪነጥበባዊ ፋይዳ ያለው መሆኑን Richard Bauman እንደሚከተለው ገልፀዋል፤ “the term ‘performance’ has been used to convey a dual sense of artistic action-the doing of folklore- an

artistic event-the performance situation, involving performer, art form, audience, and setting" (1977,4)፡፡ የክዋኔ ኪነጥበባዊነት የሚታወቀው በክዋኔው ሁኔታ፣ በከዋኙ፣ በኪነጥበቡ ቅርፅ፣ በተሳታፊዎቹ እና በመቼቱ እንደሆነም አብራርተዋል፡፡

በአንድ አጋጣሚ የሚደረግን ክዋኔ ለመገንዘብ መዋቅሩን፣ የክዋኔውን ሂደት እና ትዕምርቱን መገንዘብ አስፈላጊ ነው፡፡ የፎክሎርን ጥናት አዳጋች የሚያደርጉት እነዚህ ጉዳዮች ናቸው፡፡ ስለዚህ ፎክሎረኛው እያንዳንዱን እንቅስቃሴና ድርጊት በንቃት በመከታተል የሁነቶችን ቅደም ተከተል፣ ዓላማ፣ ፋይዳ እና ትርጓሜያቸውን ለመረዳት ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡

ለአንድ ክዋኔ መሠረታዊ ነገሮች ናቸው ብለው የተለያዩ ምሁራን በጋራ ከሚያነሷቸው ነጥቦች መካከል የመከወኛ አጋጣሚ (occasion)፣ ከዋኝ (Performer) ፣ ታዳሚ (audience)፣ አውድ(context) እና የክዋኔ ጠቋሚዎች (markers) ይጠቀሳሉ፡፡

### 2.2.2.1 የመከወኛ አጋጣሚ

ቀደም ሲል ለመጠቆም እንደሞከርኩት ክዋኔ ለፎክሎር ዘርፎች የጋራ ባህሪያቸው ነው፡፡ የፎክሎር ዘርፎች ያለ ክዋኔ ህይወት አይኖራቸውም፤ በድን ናቸው፡፡ ለመከወን ደግሞ አጋጣሚን ይሻሉ፡፡ በዘፈቀደ የሚከወን የፎክሎር ዘርፍ የለም፡፡ ‹‹ክዋኔ የሚከወንበት ጊዜና አጋጣሚ ያለው ነው፤ በማንኛውም ጊዜና በየትኛውም ቦታ የሚከወን አይደለም›› (Vansina, 1985, 39)፡፡ የሠርግ ዘፈን በሰርግ አጋጣሚ (ማለትም ሰርግ ባለበት ቦታ እና በሠርግ ጊዜ) ሲዘፈን ያምራል፤ ውበት ይኖረዋል፤ ተቀባይነትም ያገኛል፡፡ ወንዶች ‹‹ሆያ ሆዬ››ን ሴቶች ደግሞ ‹‹አበባይሆሽ››ን ይጨፍሩ ዘንድ የበዓል አጋጣሚ መኖር የግድ ነው፡፡ የለቅሶም ሁኔታ እንደዚሁ ነው፡፡ የሙሾ ግጥሞችን እየደረደሩ ለማልቀስ ወይም ዋይ ዋይ ለማለት አልያም ደግሞ ፀጉርን ለመላጨት፣ የሀዘን ልብስ ለመልበስና የመሳሰሉትን ክዋኔዎች ለመፈፀም የለቅሶ አጋጣሚ ሊኖር ግድ ነው፡፡ ‹‹ለቅሶ ሳይኖር ሙሾ አይወረድም፡፡ ሰርግ ሳይኖር የሰርግ ዘፈን አይዘፈንም፤ ስራ ሳይኖር የስራ መዝሙር አይዘመርም፤ ቡሄ ሳይኖር ቡሄ አይጨፈርም፡፡ ሥርዓቱ በሌለበት ቢለቀስ፣ ቢዘፈን፣ ቢጨፈር ክዋኔው ለዛና ድምቀት ያጣል፡፡በባህሪው የሚያስለቅሰው አያስለቅስም፤ የሚያስቀውም አያስቅም›› (ሞገስ፣2002፣31)፡፡ ያለ አጋጣሚ የሚከወን ክዋኔ ለዛ እና ውበት ከማጣቱም በላይ ‹‹እርክሰትን፣ ውግዘትን እና ተቀባይነት ማጣትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

ለምሳሌ ቀብርን ከተፈቀደለት ስፍራ ውጭ ማከናወን፣ በዓልን ያለጊዜውና ያለ ቦታው ማክበር እንደዚሁም ለቅሶን በጭፈራ ቤት እና ሰርግን በለቅሶ ቤት አልያም በመቃብር ቦታ ማድረግ የሚያስከትለውን ማህበራዊ እና ስነልቦናዊ ጫናን እና ውጤቱን ማጤን ይቻላል›› (ዘላለም፣ 2004፣28)፡፡

## 2.2.2.2. ከዋኝ

ክዋኔን ከከዋኝ ነጥሎ ማሰብ አይቻልም፡፡ ክዋኔና ከዋኝ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታዎች ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ አንድ ነገር ተከወነ ስንል ያንን ነገር የከወነ ከዋኝ አለ ማለታችን ጭምር ነው፡፡ አበባየሆሽን የሚያዜሙት፣ የሰርግ ዘፈኑን የሚያወጡት (የሚዘፍኑት)፣ ሆያ ሆዬውን የሚያቀነቅኑት ከዋኞች ናቸው፡፡ በክዋኔው ውስጥ የመሪነት ሚና ያላቸውን ሰዎች ነው ከዋኝ የምንላቸው፡፡ ተረት ተረቱ፣ ቀረርቶው፣ ፉከራው ወዘተ. ከዋኝ አላቸው፡፡ በለቅሶ ስነስርዓትም እንደየባህሉ ሁኔታ ሙሾ እየደረደረ፣ እየዘለለና ደረት እየደቃ አልቅሶ የሚያስለቅስ ከዋኝ አለ፡፡

ለክዋኔ መሣካት የከዋኙ ሚና ከፍተኛውን ድርሻ ይይዛል፡፡ ከዋኙ የሰውነት እንቅስቃሴውን፣ የድምጽ ቅላፄውን ወዘተ. በመቀያየር መድረኩን በደንብ ከተቆጣጠረና የመሪነት ሀላፊነቱን በአግባቡ ከተወጣ ክዋኔው የሠመረ ይሆናል፡፡ የከዋኙ ማንነት፣ ዕድሜው፣ ማህበራዊ ደረጃው፣ የመናገር ወይም ሐሳቡን የመግለፅ ችሎታውና የመሳሰሉት ጉዳዮችም ለክዋኔ መሳካት የሚኖራቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛ ነው (Finnegan 1992፣90 ፤ Vansina 1985፣34)፡፡

## 2.2.2.3. ታዳሚ

ከከዋኙ ጋር መሳ ለመሳ በመሆን ለክዋኔ መሳካት ከፍተኛ ድርሻ የሚኖራቸው ታዳሚዎች ናቸው፡፡ ታዳሚዎች ከዋኙ ክዋኔውን የሚያቀርብላቸው አካላት ናቸው፡፡ እነሱም በአፀፋው ከዋኙን ያበረታታሉ፤ ያግዛሉ፡፡ እንደሚከወነው የፎክሎር ዘውግ ዓይነትና ባህሪ የታዳሚዎች ሚና ይለያያል፡፡ እንደሚከወነው ክዋኔ ሁኔታ በጥሞና ያዳምጣሉ፣ ልብ ብለው ይመለከታሉ፣ይሳተፋሉ፡፡ የተፈጠረላቸውን አጋጣሚ በመጠቀም ሐሳባቸውን፣ ፍላጎታቸውን፣ ደስታቸውን፣ ሐዘናቸውን ወዘተ. ይገልፃሉ፡፡ ክዋኔ ውጤታማ ሊሆን

የሚችለው ታዳሚዎች ሚናቸውን በአግባቡ ሲወጡ ነው (vansina 1985፣ 34፤ Martha እና Martine 2005፣ 128-130)፡፡

የልቅሶ ስነስርዓት ክዋኔ ሲፈፀም ታዳሚዎች ፀጥ ብለው እንዲያዳምጡ ወይም ደግሞ በጥሞና እንዲመለከቱ ብቻ አይጠበቅም፤ የሙሾ ደርዳሪዋን(ውን) እንቅስቃሴ በመከታተል ዋይ ዋይ እያሉ፣ እየዘለሉ፣ ደረት እየመቱ ፣ እያለቀሱ ወዘተ. እንዲሳተፉም ጭምር እንጂ፡፡ ለቅሶ ያለታዳሚ በአግባቡ ሊከወን አይችልም፡፡ ታዳሚ ከዋኙን ያጅባል፤ ተሳታፊም ይሆናል፡፡ በመሆኑም ታዳሚዎች የሀዘኑን እውነተኛ ድባብ በማምጣትና የለቅሶው ስነስርአት በአግባቡ እንዲከናወን በማድረግ ረገድ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ከከዋኙ (ከከዋኞቹ) ጋር ግንባር ለግንባር በመገናኘት ወጪታውን ያወጣሉ፤ ያንጎራጉራሉ፡፡ ከዋኙ አልቅሶ የማስለቀስ ችሎታና ልምድ ያለው ከሆ ነ ታዳሚ ዎቹን ተን ሰቅስቀው እንዲያለቅሱና ከተሳታፊነት አልፈው ወደ ከዋኝነት እንዲሸጋገሩ ያደርጋቸዋል፡፡ ሚናውን ይነጥቁታል፡፡ በዚህ መንገድ አንደኛው በሌላው በመደገፍና እርስ በእርስ በመተጋገዝ ክዋኔው ላይ ህይወት ይዘሩበታል፡፡

### 2.2.2.4 አውድ

አውድ አንድ የፎክሎር ዘርፍ በሚከወንበት ወቅት የሚኖረውን አጠቃላይ ሁኔታ የሚመለከት እንደሆነ Martha እና Martine በሚከተለው መንገድ ይገልፃሉ "context refers to anything and everything that surrounds a text and performance" (2005፣137)::በመሆኑም አውድ አንድ ክዋኔ የሚከወንበትን ጊዜ እና ቦታ (መቼት)፣ የመከወኛ ቁሳቁሶችን፣ በከዋኙና በታዳሚዎች መካከል ያለውን መስተጋብር፣ አጠቃላይ የክዋኔውን ድባብ ሁሉ የሚያካትት ነው ( Martha እና Martine 2005፣ 137፤ Bauman 1977፣36)፡፡ ያለ አውድ አንድን የፎክሎር ክዋኔ በውል መረዳት አይቻልም፡፡ አውድ ተጨባጭ አውድ (physical context) እና ማህበራዊ አውድ (social context) ተብሎ በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡፡

#### 2.2.2.4.1 ተጨባጭ አውድ

ተጨባጭ አውድ አንድ ክዋኔ የሚካሄድበትን መልክዓምድር፣ የአየሩን ሁኔታ፣ አካላዊ እንቅስቃሴን፣ የድምፅ ከፍታ እና ዝቅታን(ቃናን) እና የክዋኔውን ድግግሞሽ ሁሉ

የሚያጠቃልል ነው፡፡ ተጨባጭ አውድ በአንድ ክዋኔ ላይ የነበሩትን ከዋኝ እና ታዳሚዎችን እንዲሁም ተመልካቾችን (ፎክሎረኛውንም ጭምር) እንደሚያካትት Martha እና Martine እንዲህ ይጠቅሳሉ "The physical environment also includes who is present performers and audience members as well as any observers (of course, that includes the folklorist) (2005, 138):: ተጨባጭ አውዶች የአጠቃላይ የክዋኔው አውድ ግማሽ አካላት ናቸው፡፡ ስለዚህ ፎክሎረኛው ስለ ክዋኔ ትክክለኛ መረጃ ማግኘት እና መፃፍ እንዲቻለው እነኚህን ሁሉ በአንክሮ ማጤን ይኖርበታል፡፡ ይህ ሲሆን ነው ክዋኔው እንዴት እንደተደረገ ብቻ ሳይሆን ለምን እንደተደረገ ጭምር መገንዘብ የሚቻለው፡፡ ቀጣዩ የእነ Martha እና Martine ሀሳብም ይህንን ሃሳብ የሚያስረግጥልን ነው፡፡

> Describing what happens during a performance not only gives us an idea of the action taking place, but also gives us some idea of why the actions occur. It is this interpretive dimension of performance, as well as performer and audience responses, that we consider when we observe relationships and interactions between and among performers and audience members (2005 ፣139)፡፡

### 2.2.2.4.2 ማህበራዊ አውድ

ማህበራዊ አውድ የክዋኔን አጠቃላይ መዋቅር የሚመለከት ነው፡፡ በመሆኑም ማህበራዊ አውድ የከዋኙ ማንነት፣ ማህበራዊ ደረጃና ሐይማኖታዊ ዕውቀት እንዲሁም የታዳሚዎች በዕድሜ፣ በፆታ፣ በጎሳ፣ በሐይማኖት፣ በሙያ ወዘተ. የተሰባጠሩ መሆናቸው በክዋኔው ላይ ያላቸውን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያካትት Martha እና Martine በሚከተለው መንገድ ይገልፃሉ፤

> ...ethnic back ground, religious affiliations, occupation, regional connections, culture- all these are social aspects of performances, audiences and settings that influence the events taking place during a performance.These kinds of social components influence how those present interact, and may reflect assumed roles or expectations within the group or community. (2005፣ 139)፡፡

በአንድ ክዋኔ ተሳታፊ የሚሆኑ ሰዎች (ከዋኝም ይሁን ታዳሚዎች) የተለያዩ እና የተሰባጠሩ መሆናቸውን መገንዘብ የማህበራዊ አውድን አጠቃላይ ድባብ በቀላሉ ለመገንዘብ ያስችላል፡፡

### 2.2.2.5 የክዋኔ ጠቋሚዎች

አንድ የፎክሎር ዘርፍ ሲከወን ክዋኔው የሚከወንበትን ሁኔታ፣ የክዋኔውን አጀማመር፣ ሂደትና አጨራረስ፣ ለክዋኔው የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን፣ ክዋኔው የሚከወንበትን ጊዜና ቦታ የሚያመለክቱ የክዋኔ ጠቋሚዎች አሉት፡፡ የክዋኔ ጠቋሚዎች ከዋኙና ታዳሚዎቹ እርስ በርስ የሐሳብ ልውውጥ እንዲያደርጉ፣ መጠነኛ ዕረፍት እንዲወስዱ፣ ስለክዋኔው አጠቃላይ ሁኔታ አስተያየት እንዲለዋወጡ የሚያስችሉ ናቸው፡፡ ከዚህም በቀር የከዋኙንና የታዳሚዎችን ድምፀት፣ የሰውነት እንቅስቃሴ፣ የፊት መለዋወጥ እና የመከወኛ ቁሳቁሶችን ድምፅ ግምት ውስጥ በማስገባት መረጃ የሚሰጡ ናቸው፡፡ ስለዚህ ፎክሎረኛው ከክዋኔው አጠቃላይ ሁኔታ በመነሳት ተገቢ ማብራሪያና ትንታኔ እንዲሰጥ በማድረግ ረገድ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

እንደ ክዋኔ ጠቋሚዎች ሁሉ የክዋኔ ማዕቀፎችም (Frames) ያላቸው ሚና የሚናቅ አይደለም፡፡ አንድ ክዋኔ ከተፈቀደለት ማዕቀፍ ሊወጣ አይችልም፡፡ ከተፈቀደለት ማዕቀፍ እና የአከዋወን ስልት ከወጣ አጠቃላይ የክዋኔውን ድባብ ያበላሻል፤ ክዋኔው በአግባቡ እንዳይከወን ያደርጋል፡፡ ስለዚህ ክዋኔን በተፈቀደለት ማዕቀፍ ውስጥ መከወን የግድ ነው፡፡

በዚህ ንኡስ ክፍል ከዋኝ፣ ታዳሚ፣ አውድ ወዘተ. እያልን ያነሳናቸው ጽንሰ ሀሳቦች በትንታኔው ውስጥ (በዚህ ጥናት አራተኛው ክፍል) የሚች ቤተሰቦች፣ ወዳጆችና ዘመዶች እጆቻቸውን እያወራጩ፣ አይኖቻቸውን እየጨመቁ፣ እየወደቁና እየተነሱ፣ አንገት ለአንገት እየተቃቀፉ፣ ክብ እየሰሩ ወዘተ. የሚያከናውኗቸውን የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች የሚያመለክቱ ናቸው፡፡

በቀጣዩ ክፍል ለጥናት የተመረጠው አካባቢ አጠቃላይ ገጽታ (የአካባቢውን መልክአ ምድራዊ ገጽታ፣ የህዝቡን ቋንቋ፣ ሀይማኖት ወዘተ.) ይቃኛል፡፡ ቀጥሎ በሚገኘው ክፍል ደግሞ የአካባቢው ህብረተሰብ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ እየተተነተነ ይቀርባል፡፡

# 3. ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ዳራ

የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር በአማራ ክልል ከሚገኙ 11 የዞን ዋና ዋና ከተሞች አንዷ ስትሆን ከክልሉ ርእሰ ከተማ ከባህር ዳር 265 ኪ.ሜ. እና ከመዲናችን ከአዲስ አበባ 300 ኪ.ሜ. ርቀት ላይ ትገኛለች፡፡ ደብረ ማርቆስ በቀድሞ አጠራሩ የጎጃም ጠቅላይ ግዛት ዋና ከተማ በመሆን ለበርካታ ዓመታት አገልግላለች፡፡ ዋና ከተማ እንድትሆን የተመረጠችው ባላት ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ነበር፡፡

ደብረ ማርቆስ በንጉሰ ነገስቱ ዘመን በአንድ ከንቲባና ትላልቅ ሰፈሮች ተከፋፍላ ትተዳደር የነበረች ሲሆን የመጀመሪያው የደብረ ማርቆስ ከተማ ከንቲባ ፊታውራሪ ገላ ጊዮርጊስ እቁቢት ይባላሉ፡፡ ከእርሳቸውም ቀጥሎ የተለያዩ ከንቲባዎችን አስተናግዳለች፡፡ እስከ አሁኑ ከንቲባ አቶ ነብዩ ምናለ ድረስ ከተማዋን 18 ከንቲባዎች በመፈራረቅ አስተዳድረዋታል(የደ/ከ/መ/ኮ/ጉ/ጽ/ቤት፣ 2004፣ 3)፡፡ በአሁኑ ወቅት የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ከገጠር ቀበሌዎች የተካተቱትን ጎጦች (የመቃ፣ ዳሊጋው የህንስ፣ መሀል የብራጌ፣ እንደገም፣ እንግጫ፣ እንድማጣ፣ ዳሊጋው ጊዮርጊስ፣ ጨሞጋ፣ አምቡሳም፣ አጭራ፣ ጠንጠር እና ማቀት) በመጨመር በሰባት ጥምር የቀበሌ አስተዳደር ትመራለች፡፡ በአራቱም ማዕዘናት ከጎዛምን ወረዳ ከሚገኙ የገጠር ቀበሌዎች የምትዋሰን ሲሆን በምስራቅ የጨሞጋ ወንዝ፣ በምዕራብ የወንቃ ቀበሌ፣ በሰሜን የእነራታ ቀበሌ፣ በደቡብ ቀቢ እና የቦ ያዋስኗታል፡፡

## 3.1 የከተማዋ አመሰራረት

የከተማዋ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ በ2003 ዓ.ም ያዘጋጀው መጽሄት እንደሚያመለክተው ደብረ ማርቆስ ከተማ የተቆረቆረችው በ1845 ዓ.ም የጎጃም ገዥ በነበሩት በደጃዝማች ተድላ ጓሉ ሲሆን በዚያን ጊዜ የከተማዋ መጠሪያ መንቆረር ይባል ነበር፡፡ መንቆረር የሰው ስም መጠሪያ ነው፡፡ በጥንት ዘመን ከተማዋን በርስትነት ያስተዳድሯት ከነበሩት የሳርን ልጆች ወንድማማች ዝናና መንቆረር መካከል የአንደኛውን ልጅ ስም መጠሪያዋ አድርጋ አመታትን አሳልፋለች፡፡ በ1872 ዓ.ም ንጉስ ተክለ ሃይማኖት ከነገሱ ከሁለት ዓመት በኋላ መለዕለተ አድባር ደብረ ዐሀይ ቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን በመተከሉ ምክንያት የከተማዋ ስያሜ መንቆረር መባሉ ቀርቶ ደብረ ማርቆስ ተብላ እንድትጠራ ተደነገገ፡፡

ደብረ ማርቆስ የተቆረቆረችው ከአካባቢው የመሬት አቀማመጥ ከፍተኛው ቦታ ላይ ነው፡፡ ለከተማዋ መቆርቆር እንደምክንያት ከሚጠቀሱት ውስጥ አንደኛው ጠላትን ከሩቅ ለመከላከል ታስቦ የተደረገ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በቆላማው ክፍል በዚያን ወቅት ይከሰት ከነበረው ወረርሽኝ በሽታ ለመሸሽ እንደነበረ የተገኘው መረጃ ይጠቁማል፡፡

## 3.2 የከተማዋ መልክዓ ምድራዊ ገፅታ

ደብረ ማርቆስ በምስራቅ ከብቸና፣ በሰሜንና በሰሜን ምስራቅ ከሞጣ፣ በምዕራብና በሰሜን ምዕራብ ከቆላ ደጋ ዳሞት አውራጃ ጋር ትዋሰናለች፡፡ የአባይ ወንዝ የከተማዋን ደቡብ እና ደቡብ ምስራቅ ጠረፍ ይነካል፡፡ በደብረማርቆስ ከተማ እና በአካባቢው ሸለቆዎች፣ ኮረብታማ ቦታዎች፣ አምባዎች፣ ተራራዎች ይገኛሉ፡፡ አራት መከራከር (ሙቄ) ረጅሙ ተራራ ሲሆን ከዚሁ ከፍተኛ ቦታ የሚነሱ ወንዞች ወደ አባይ ወንዝ ይፈሳሉ፡፡

የከተማዋ የቆዳ ስፋት ከ6160 ሄክታር በላይ እንደሚሸፍን ይገመታል፡፡ ደብረ ማርቆስ ከባህር ወለል በላይ አማካይ 2420 ሜትር ከፍታ ያላት ሲሆን እንደ የራባ መናፈሻ እና በቀድሞው ቤተመንግስት አካባቢ ያሉ ቦታዎች 2522 ሜትር ከፍታ አላቸው፡፡ ወይና ደጋ የአየር ፀባይ እንዳላት፣ አማካይ የሙቀት መጠኗ 16 ዲ.ሴ.ግ. እንደሆነና ዓመታዊ የዝናብ መጠኗም በአማካይ 1380 ሚ.ሜ እንደሚደርስ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡

በከተማዋ ውስጥ ካለው መሬት 75% ወይም 4620 ሄክታር ለግንባታ ምቹ የሆነ፣ 20% ወይም 1232 ሄክታር ረግረጋማና ለግንባታ ምቹ ያልሆነ ሲሆን 5% ወይም 308 ሄክታር ደግሞ ገደላማና ወጣ ገባ የሆነ መሬት ነው፡፡ ደብረ ማርቆስ ከተማ ለዓመታዊ ሰብል ልማት ሊውል የሚችል 2346 ሄክታር ሲኖር ከዚህ ውስጥ 60 ሄክታሩ በመስኖ፣ 2256 ሄክታሩ በዝናብ፣ 30 ሄክታሩ በቋሚ ተክል የሚለማ ነው፡፡ 1093 ሄክታር በደንና ቁጥቋጦ የተሸፈነ፣ 1123 ሄክታሩ ለግጦሽ የተተወና 3209 ሄክታር ደግሞ ለተለያዩ ግንባታዎች የዋለና የሚውል ነው፡፡ የአፈር አይነቱም የበለጠውን ድርሻ የያዘው 97% ቀይ አፈር ሲሆን 3% ደግሞ የዋልካ መሬት እንደሆነ የከተማዋ ግብርና ጽ/ቤት በ2003 ዓ.ም ያወጣው አመታዊ ሪፖርት ያመለክታል፡፡

## 3.3 የከተማዋ ህዝብ ቋንቋ፣ ሀይማኖትና አጠቃላይ ሁኔታ

በደብረ ማርቆስ ከተማ (ከገጠር የተካተቱ ቀበሌዎችን ጨምሮ) 58,194 ወንዶች፣ 64,839 ሴቶች በድምሩ 123,033 ህዝብ እንደሚኖር ይገመታል፡፡ የነዋሪው ሕዝብ ስብጥርም 97% አማራ፣ 1.2% ትግራይ፣ 0.7% ኦሮሞ 0.6% አገዋዊ፣ 0.4% ሌሎች ብሔረሰቦች እንደሆነ በ1999 ዓ.ም የተደረገውን የህዝብና ቤቶች ቆጠራና ትንቢት መሰረት አድርጎ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የምስ/ን/ዞ/ገ/ኢ./ል/ ቢሮ በ2003 ዓ.ም ያወጣው ሪፖርት ያመለክታል፡፡

በከተማ ከሚኖረው ህዝብ መካከል 4,235 የሚሆነው የህብረተሰብ ክፍል በመንግስት ስራ የሚተዳደር ሲሆን ቀሪው የከተማ ነዋሪ በንግድ፣ በልዩ ልዩ ሙያ፣ በጡረታ ወዘተ. ህይወቱን የሚመራ ነው፡፡ በከተማ ከሚኖሩት የመንግስት ሰራተኞች፣ ነጋዴዎች እና ልዩ ልዩ ሙያ ካላቸው ሰዎች በስተቀር ደብረ ማርቆስ ከተማና በአካባቢው የሚኖረው አብዛኛው ህዝብ በግብርና ስራ ላይ የተሰማራ ነው፡፡

በግብርና ስራ ላይ የተሰማራው የህብረተሰብ ክፍል ከሚያመርታቸው ሰብሎች መካከል ጤፍ 38% ፣ ስንዴ 24% ፣ ገብስ 5% ፣ እንግዶ 10% ፣ በቆሎ 12% ፣ ባቄላ 7% ፣ አተር 2% ፣ ኑግ 0.9% ፣ ተልባ 0.2% እና የጓሮ አትክልት 1.71% ሆኖ እናገኘዋለን (በደ/ማ/ከ/አስ/ግ/ጽ/ቤት የ2004 ዓ.ም የ3ኛው ሩብ ዓመት ሪፖርት)፡፡

### 3.3.1 የህዝቡ ቋንቋ

ከፍ ብሎ እንደተመለከትነው የደብረ ማርቆስ ከተማ በአመዛኙ የአማራ ብሔር ተወላጆች የሚገኙባት ሲሆን ሌሎች ብሔር ብሔረሰቦችም ይኖሩባታል፡፡ በዚህ መሠረት የከተማዋና የአካባቢው ሕዝብ ዋነኛ የመግባቢያ ቋንቋ አማርኛ ሲሆን በተወሰነ መልኩ ትግርኛ፣ ኦሮምኛና አገውኛ ቋንቋዎች ይነገራሉ፡፡

### 3.3.2 የሕዝቡ ሐይማኖት

ከደ/ማ/ከ/መ/ኮ/ጉ/ጽ/ቤት የ3ኛው ሩብ ዓመት ሪፖርት መግቢያ ላይ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው የከተማዋ የሐይማኖት ስብጥር 97.25% ኦርቶዶክስ፣ 0.81% ፕሮቴስታንት፣ 0.03% ካቶሊክ፣ 1.91% እስልምና ፣ 0.03% ሌሎች የሐይማኖት ተከታዮች ናቸው፡፡ የሙስሊሞች ቁጥር ከኦርቶዶክስ ክርስትና ሐይማኖት ተከታዮች ጋር

ሲነፃፀር በጣም ትንሽ ነው፡፡ ብዙዎቹ ሙስሊሞች በከተማዋ ውስጥ የሚኖሩ ሲሆን ጥቂቶች ደግሞ በገጠር አካባቢ ይኖራሉ፡፡

## 3.4 ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች

በዚህ ንኡስ ርዕስ ስር የከተማዋ የንግድ፣ የኢንቨስትመንትና የመሰረተ ልማት እንቅስቃሴዎች በዝርዝር ቀርቧል፡፡ መረጃዎቹ የተገኙት የምስ/ጎ/ዞ/ገ/ኢ/ል/ቢሮ በ2003 ዓ.ም ካወጣው ሪፖርት ነው፡፡

### 3.4.1 ንግድ

በደብረ ማርቆስ ከተማ ከ1980 ዓ.ም እስከ አሁን ያለውን በንግድ ስራ የሚንቀሳቀሱ ነጋዴዎች በአይነት በአይነታቸው ስናየው 18 በጅምላ፣ 689 በችርቻሮ እና 707 የሚሆኑት ደግሞ በአገልግሎት ሰጪነት ተሰማርተው ይገኛሉ፡፡ ባለፉት አምስት ዓመታት 920,597 ካፒታል ያላቸው 52 አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች የተቋቋሙ ሲሆን ለ300 ሰዎች የሥራ እድል ፈጥረዋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ 50 በመቶ የሚሆኑት በብረታብረትና እንጨት ስራዎች የተሰማሩ ናቸው፡፡

የከተማዋን የንግድ እንቅስቃሴ በካፒታል ደረጃ ለይተን ስንመለከት በከፍተኛ ንግድ 30፣ በመካከለኛ 110 እና በዝቅተኛ ደረጃ 1,800 ነጋዴዎች እንደሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ይህ አሃዝ በጥቃቅን ንግድ ስራዎች (ኢመደበኛ ሴክተር) የተሰማሩትን የሚያጠቃልል ባይሆንም በርካታ የንግድ ሥራዎች የሚመሩት በዚህ ሴክተር እንደሆነ ይታመናል፡፡

### 3.4.2 መዋዕለ ንዋይ (ኢንቨስትመንት)

በከተማ አስተዳደሩ መዋዕለ ንዋያቸውን ለሚያፈሱ ባለሀብቶች የኢንዱስትሪ መንደር ተብሎ የተከለለ 102 ሄክታር ቦታ ሲኖር፣ ከ1985 ዓ.ም እስከ 2003 ዓ.ም ድረስ ከ 2,473,398,164 (ሁለት ቢሊየን አራት መቶ ሰባ ሦስት ሚሊዮን ሦስት መቶ ዘጠና ስምንት ሺህ አንድ መቶ ስልሳ አራት) ብር ካፒታል ያስመዘገቡ 491 ባለሀብቶች ፍቃድ ወስደው ተግባራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ የከተማ አስተዳደሩም 293,775.5 ሄክታር መሬት ለዚሁ ተግባር አውሏል፡፡ በመሆኑም ባለሀብቶቹ ወደ ተግባር በመግባታቸው ለ5,911 ሰዎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ ዕድል ተፈጥሯል፡፡

### 3.4.3 መሠረተ ልማት

ከተማዋ የ24 ሰዓት የመብራት፣ የውሃ፣ የመንገድ፣ የስልክ (የአውቶማቲክ እና የተንቀሳቃሽ ስልክ) ተጠቃሚ ናት፡፡ በከተማዋ 37 የጤና ተቋማትና 59 ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ የንፁህ መጠጥ ውሃ ሽፋኗም ዘጠና በመቶ ደርሷል፡፡ በከተማዋ 12.84 ኪ.ሜ የአስፋልት መንገድ (በግራና ቀኝ ተፋሰስ የተሰራለት)፣ 99.6 ኪ.ሜ ጠጠር መንገድ የለበሰ እና 54 ኪ.ሜ የውስጥ ለውስጥ ጥርጊያ መንገዶች ይገኛሉ፡፡

የጨሞጋ ወንዝ ለደብረ ማርቆስ ከተማ የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ኃይል ምንጭ በመሆን ሲያገለግል የቆየ ሲሆን በአሁኑ ወቅት ከተማዋ የኤሌክትሪክ ሀይል የምታገኘው ከፊንጫ የኃይል ማመንጫ ነው፡፡ ደብረ ማርቆስ ከተማን የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት በተመለከተ የንዑስ ጣቢያው ትራንስፎርመር አቅም 24 ሰዓት አገልግሎት ለከተማዋ የሚሰጥ ሲሆን አጠቃላይ አቅሙ 19.2 ሜጋ ዋት ነው፡፡ ይሁን እንጂ በአሁኑ ሰዓት ጥቅም ላይ የዋለው 9.5 ሜጋ ዋት ብቻ ነው፡፡

## 3.5 ማህበራዊ ሁኔታዎች

በዚህ ንኡስ ርዕስ ስር ከተማዋ በትምህርትና በጤና ረገድ ያላት ገጽታ ምን እንደሚመስል ይቃኛል፡፡

### 3.5.1 ትምህርት

የደ/ማ/ከ/አስ/ትምህርት ጽ/ቤት የ2004 ዓ.ም ሦስተኛው ሩብ አመት ሪፖርት ላይ የተገኙትን መረጃዎች አቀናብሬ በመውሰድ የከተማዋን የትምህርት እንቅስቃሴ እንደሚከተለው አቅርቤዋለሁ፡፡

#### 3.5.1.1 ባህላዊ ትምህርት

ዘመናዊ ትምህርት ወደ አገሪቱ ከገባ ወዲህ የአካባቢው ህብረተሰብ መለያ የሆነው ባህላዊ ትምህርት ቀስ በቀስ እየተዳከመ በመምጣት ላይ ይገኛል፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በከተማዋ የሚኖረው ህብረተሰብ ልጁን የባህላዊ ትምህርት እንዲማር የማድረጉ ሂደት በተዳከመ ሁኔታ ላይ የሚገኝ መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡ የቆሎ ተማሪዎችም ትኩረታቸውን ወደ ዘመናዊ ትምህርት በማድረጋቸው ቁጥራቸው እየተመናመነ በመሄድ ላይ ይገኛል፡፡

### 3.5.1.2 ዘመናዊ ትምህርት

በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ በመንግስትና በግል ተከፍተው አገልግሎት በመስጠት ላይ የሚገኙ የትምህርት ተቋማት 59 ሲሆኑ፣ ተቋማቱ ከአፀደ ህፃናት እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ ተማሪዎችን ተቀብለው በማስተናገድ ላይ ይገኛሉ፡፡

- ቅድመ መደበኛ ትምህርት

በከተማዋ 13 የአፀደ ህፃናት ትምህርት ቤቶች ይገኛሉ፡፡ በእነዚህ ትምህርት ቤቶች 1,200 ህፃናት በ25 መምህራን አማካኝነት ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡

- መደበኛ ትምህርት

በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ በመንግስት 36፣ በግል 23 በድምሩ 59 የትምህርት ተቋማት አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ተቋማት መካከል ዩኒቨርሲቲዎችን፣ ኮሌጆችን፣ የአፀደ ህፃናት ትምህርቶችን፣ የአማራጭና የልዩ ትምህርት መስጫ ተቋማትን እንዲሁም የጎልማሶች ትምህርት ሳይጨምር በከተማዋ ባሉት 5 የመጀመሪያ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ትምህርት፣ 14 የአንደኛ ደረጃ ሁለተኛ ሳይክል ትምህርት፣ 2 የሁለተኛ ደረጃ አንደኛ ሳይክል ትምህርት እና 1 የመሰናዶ ትምህርት ከ25,185 በላይ ተማሪዎች ትምህርታቸውን 1,200 በሚሆኑ መምህራን አማካኝነት በመከታተል ላይ ይገኛሉ፡፡

- የጎልማሶች ትምህርት


በከተማዋ 4 የጎልማሶች ማሰልጠኛ ጣቢያ የሚገኝ ሲሆን፣ 548 ጎልማሶች በ16 መምህራን አማካይነት ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ፡፡

### 3.5.2 ጤና


በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ በመንግስት 20፣ መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች 4፣ በግል 13 በድምሩ 37 የጤና ተቋማት ተገንብተው አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛሉ፡፡ በከተማዋ አንድ ዞናል ሆስፒታል፣ ሦስት ጤና ጣቢያ፣ ሰባት ጤና ኬላ፣ ሦስት ከፍተኛ ክሊኒክ፣ ስምንት መለስተኛ ክሊኒክ፣ ስድስት መካከለኛ ክሊኒክ፣ ሰባት መድሃኒት መደብር እና ሁለት የገጠር መድሐኒት ቤቶች ይገኛሉ፡፡

በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚከሰቱ በሽታዎችን ስንመለከት፣ አጠቃላይ ገፅታው ከሌሎች አካባቢዎች የተለየ ነው ባይባልም በአብዛኛው የሳንባ ነቀርሳ፣ የመተንፈሻ አካላት ህመሞች፣ የአንጀት ትላትሎች፣ የጨጓራ በሽታ፣ የአይን በሽታ፣ የአንጀት ተስቦ፣ የሽንት ቧንቧ በሽታና ከግል ንፅህና አጠባበቅ ችግር ጋር በተያያዘ መልኩ የሚከሰቱ ተላላፊ በሽታዎች መሆናቸውን የፅሁፍ ማስረጃዎች ያሳያሉ (የደ/ማ/ከ/ጤ/ጥ/ጽ/ቤት የ2003 ዓ.ም ዓመታዊ ሪፖርት)፡፡

በከተማዋ በሚገኙ የመንግስት የጤና ተቋማት 105 የህክምና ባለሙያዎች ተቀጥረው በመስራት ላይ ይገኛሉ፡፡ የባለሙያዎች ጥመርታ ከህዝቡ ቁጥር አንፃር ሲታይ አንድ ስፔሻሊስት ሃኪም ለ20,823 ሰዎች፣ አንድ ጠቅላላ ሃኪም ለ4,809 ሰዎች፣ አንድ ጤና መኮንን ለ15,617 ሰዎች ፣ አንድ ነርስ ለ1,452 ሰዎች፣ አንድ ላባራቶሪ ቴክኒሺያን ለ8,924 ሰዎች፣ አንድ ፋርማሲ ቴክኒሺያን ለ6,941 ሰዎች፣ አንድ ጤና ረዳት ለ2,839 ሰዎች እና አንድ የጤና ኤክስቴንሽን ሰራተኛ ለ8,924 ሰዎች አገልግሎት እንደሚሰጡ የከተማዋ ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት በ2003 ዓ.ም ያዘጋጀው ሪፖርት ያመለክታል፡፡




Mota Town Adm
Hulet Iju Enesie
Goncha Siso Enese
Enebse Sar Mider
Bibugn
West Gojjam
Enarji Enawuga
Sinan
Machakel
Debay Telatgin
Inemay
South Wollo
Debre Markos Town Ad
Shebel Berenta
Gozamin
Debre Elias
Awabel
Aneded
Dejen
Oromya Region
Baso Liben
Oromya Region
1;10,000
Source: egzfed,GIS officer




# Map of Gozamin Woreda by Kebele

SOURCE: EGZOFED,GIS OFFICER

# Elivation Map of East Gojjam Zone



## 4. በደብረ ማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔ

በዚህኛው የጥናት ክፍል በደብረማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚኖሩ የእስልምናና የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔያቸው ምን እንደሚመስል እየተተነተነ በንፅፅር ይቀርባል፡፡

የክርስትናና የእስልምና ሐይማኖት ተከታዮች በሰላምና በፍቅር ተከባብረው አንድ ላይ የሚኖሩ ሕዝቦች ናቸው፡፡ ሙስሊም እህቶችና ወንድሞች ከክርስቲያን እህቶችና ወንድሞቻቸው ጋር በደስታም ሆነ በሐዘን ተሳስበውና ተደጋግፈው ይኖራሉ፡፡ በመሆኑም በአብዛኛው ባህላዊ እሴቶቻቸው ላይ ተመሳሳይነት ይታያል፡፡ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔያቸውስ ምን ይመስል ይሆን? ተመሳሳይነት አለው? ልዩነትስ? በዚህ ክፍል ለእነዚህና እነዚህን ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ጥረት ይደረጋል፡፡

የሁለቱ ሀይማኖት ተከታዮች በለቅሶ ስነስርዓቶቻቸው ላይ የሚያከናውኗቸውን ሐይማኖታዊና ባህላዊ ጉዳዮች እየተነተንኩ ለማረቅብ ጥረት አደርጋለሁ፡፡ ማህበራዊ ጉዳዮችንም እንደዚሁ፡፡ ለአቀራረብ ያመቸኝ ዘንድ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎቹን ‹‹የቅድመ ሞት ክዋኔ››፣ ‹‹ጊዜ ሞት ክዋኔ›› እና ‹‹ድህረ ቀብር ክዋኔ›› በማለት በሦስት ንኡሳን ርዕሶች ከፋፍዬ ነው የማቀርባቸው፡፡ የለቅሶ ስነስርአቶቹን በሦስት ንዑሳን ርእሶች ከፋፍዬ ለማቅረብ ውሳኔ ላይ ከደረስኩ በኋላ ግን ሁለት አማራጮች ፊታችኝ ሆነውብኝ ነበር፡፡ አንደኛው አማራጭ ‹‹የክርስትና እምነት ተከታዮችን የለቅሶ ስነስርዓት ሙሉ ክዋኔውን ‹የቅድመ ሞት ክዋኔ›፣ ‹ጊዜ ሞት ክዋኔ› እና ‹ድህረ ቀብር ክዋኔ› በማለት ከፋፍዬ ካቀረብኩ በኋላ የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮችን የለቅሶ ስነስርዓት ሙሉ ክዋኔውን በዚሁ መልክ ማቅረብ ይሻላል›› የሚል ሲሆን ሁለተኛው አማራጭ ደግሞ ‹‹ ‹የቅድመ ሞት ክዋኔ› በሚለው ንኡስ ርእስ ስር የሁለቱን ሀይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ በማነጻጸር ከአቀረብኩ በኋላ ‹ጊዜሞት ክዋኔ› እና ‹ድህረ ቀብር ክዋኔ› በሚሉት ንኡሳን ርዕሶች ስርም እንደዚሁ የሁለቱን ሀይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ በንጽጽር ማቅረብ ይሻላል›› የሚል ነው፡፡ የሆነው ሆኖ በእያንዳንዱ ንኡስ ርዕስ ስር የሁለቱ ሀይማኖት ተከታይ ክዋኔዎች በንጽጽር ቢቀርቡ አንባቢያን አንድነቶችንና ልዩነቶችን በቀላሉ ማስተዋል ይችላሉ ብዬ ስላመንኩ ሁለተኛውን አማራጭ

ተጠቅሚያለሁ፡፡ ስለዚህ ‹የቅድመ ሞት ክዋኔ› በሚለው ንዑስ ርእስ ስር የሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች የሚያከናውኗቸውን ስነስርአቶች በተናጠል አሳያለሁ፡፡ በጊዜ ሞት እና በድህረ ቀብር ወቅት የሚፈፀሙ ክዋኔዎችንም በተመሳሳይ፡፡ ‹የቅድመ ሞት ክዋኔ› በሚለው ርዕስ ስር አንድ ሰው በጠና ሲታመምና ከሞት አፋፍ ላይ መሆኑ ሲጠረጠር በሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች ዙሪያ የሚያጠነጥኑ ሐሳቦች ይነሳሉ፡፡ በዋናነት የኑዛዜ ስነስርዓቶች ትኩረት ይሰጣቸዋል፡፡ ‹ጊዜ ሞት ክዋኔ› በሚለው ክፍል ውስጥ ደግሞ አንድ ሰው ሲሞት ወዲያውኑ የሚደረጉ(ለት) ክዋኔዎች ምን ምን እንደሆኑ ይቃኛሉ፡፡ ሬሳውን ከመገነዝ ጀምሮ እስከ መቅበር ድረስ ያሉት ሂደቶች በዝርዝርና በቅደም ተከተል ይተነተናሉ፤ ይተረጎማሉ፡፡ በመጨረሻም ‹ድህረ ቀብር› በሚለው ንዑስ ርእስ ስር ከቀብር በኋላ የሚከናወኑ ስነስርዓቶች በዝርዝር ይገለፃሉ፡፡

ትንታኔውን ያደረግሁት ጎልማሳ የሆነና ‹ለወግ ለማእረግ የበቃ› ሰው በሚሞትበት ጊዜ የሚደረገውን የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ አገላለጼም ተባእት ጾታን በመጠቀም ይሆናል፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ ስነስርአቶች ላይ የፆታ፣ የእድሜ፣ የደረጃ(የማዕረግ) ወዘተ. ልዩነቶች በሚኖሩበት ጊዜ ጉዳዮቹን አንስቼ በደንብ ለማብራራት ጥረት አደርጋለሁ፡፡ ተባእት ጾታን መምረጤ በወንድነቴ አድልኦ ማድረጌ አይደለም፤ ብዙ ድርሳናት በዚህ መልክ በመጻፋቸውና እኔም የእነርሱ ተጽእኖ ሰለባ በመሆኔ እንጂ!

ከፍ ሲል ለመጠቆም እንደሞከርኩት የለቅሶ ስነስርዓቶቹን ለአቀራረብ አመቺነት ሲባል በሦስት ከፋፍዬ አቀረብኳቸው እንጂ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ የቀረቡት ሁነቶች ራሳቸውን ችለው የሚቆሙ(የሚታዩ) ናቸው ማለት አይደለም፤ እርስ በርስ የተያያዙና የተሰናሰሉ ናቸው እንጂ፡፡ ስነስርዓቶቹ ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው ያለማቋረጥ የሚጓዙ ናቸው፡፡ አንዳንድ ሁነቶችም በተቀነበቡት ክልሎች ውስጥ ተወስነው ሊቀመጡ የሚችሉ አይደሉም፡፡

## 4.1 የቅድመ ሞት ክዋኔ

የሞት መምጫ ጊዜው በሰዎች ዘንድ በውል የማይታወቅ መምጣቱ የማይቀር እውነተኛ ቀጠሮ ነው፡፡ የሰው ልጅ በልዩ ልዩ ምክንያቶች ይህን ዓለም ይሰናበታል፤ ይሞታል፡፡ አሟሟቱ ግን ሳይታሰብ በድንገት እና በቅፅበት፣ ወይም ደግሞ አሳስቦ፣ አስጠንቅቆና አዘጋጅቶ ሊሆን ይችላል፡፡ ሰው በድንገት ሲሞት በቀሪ ወዳጅ ዘመዶቹ ላይ የሚፈጠረው

ስሜት ቀላል አይሆንም፡፡ ሐዘናቸውን ያከብደዋል፤ ለቅሶአቸውንም መሪር ያደርገዋል፡፡ በቀጣይ የሚኖሩ ሥራዎችንም እጅግ ከባድና ውስብስብ ያደርግባቸዋል፡፡ ሟች ታሞ፣ ከዛሬ ነገ ይሻለዋል ሲባል እየባሰው ሄዶ፣ የመሞቱን ጉዳይ አሳስቦና አስጠንቅቆ የሞተ እንደሆነ ደግሞ በቀሪ ዘመዶቹና ወዳጆቹ ላይ የሚፈጠረው ስሜት ያን ያህል የበረታና የከበደ አይሆንም፡፡ ይሄኛው አሟሟት ለቅድመ ሞት ዝግጅቶች ጊዜ ይሰጣል፡፡ ሟቹ ከመሞቱ በፊት ለመናዘዝ ዕድል ያገኛል፤ ነገሮችንም ፈር ለማስያዝ ይቻለዋል፡፡ ወዳጅ ዘመዶቹም እንዲዘጋጁ ምቹ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል፡፡ ቀጣይ ሥራዎችም የተወሳሰቡ አይሆኑም፡፡

በቀጣዩ ንኡስ ክፍል የክርስትና እምነት ተከታዮችን የቅድመ ሞት ክዋኔ ከተመለከትን በኋላ በመቀጠል ደግሞ የእስልምና እምነት ተከታዮችን የቅድመ ሞት ክዋኔ እንመለከታለን፡፡

### 4.1.1 የቅድመ ሞት ክዋኔ በክርስትና እምነት ተከታዮች

በደብረማርቆስ ከተማና አካባቢዋ የሚገኙ የክርስትና እምነት ተከታዮች አንድ ሰው በጠና ታሞ ከማይድንበት ደረጃ ላይ መድረሱን ሲገምቱ ሲሞት ለሚያስፈልጉ ነገሮችና ከሞት በኋላ ለሚኖሩ ጉዳዮች ቅድመ ዝግጅቶችን ያደርጋሉ፡፡ ከሚያደርጓቸው ቅድመ ዝግጅቶች መካከል አንዱና ዋነኛው ታማሚውን ለኑዛዜ እንዲበቃ ማድረግ ነው፡፡ በተለይ ሟች ለአካለ መጠን የደረሰና ትዳር ይዞ ልጆችን የወለደ፣ ሐብት ንብረትንም ያፈራ ከሆነ እንዲናዘዝ ይደረጋል፡፡ ለኑዛዜው ተፈጻሚነት ህመምተኛው የነፍስ አባት ያለው እንደሆነ ለነፍስ አባቱ፣ የነፍስ አባት የሌለው ከሆነ ደግሞ በዛው አካባቢ ለሚኖሩ ካህን የቶሎ ድረሱልን መልእክት ይላካል፡፡ በመካሪነታቸው፣ በአስታራቂነታቸውና በአስተዋይነታቸው ለሚታወቁና ለተመረጡ የአካባቢው ሽማግሌዎችም ‹እገሌ (የታማሚው ስም ተጠቅሶ) በጠና ታሟልና ቶሎ ድረሱልን› የሚል መልዕክት ይላክባቸዋል፡፡ ስልክ ያላቸው ከሆኑም በስልክ ይነገራቸዋል፡፡ በቅርብና በሩቅ ለሚገኙ ዘመዶቹም አመቺ በሆነው መንገድ ሁሉ መልእክቱ እንዲደርሳቸው ጥረት ይደረጋል፡፡ መልዕክቱ ደርሷቸው የመጡት ካህን በቅድሚያ ብቻቸውን ሆነው ህመምተኛውን ያናዝዙታል፡፡ ይሄኛው ኑዛዜ በአብዛኛው በሐጢያት ስርየት ላይ የሚያተኩር ነው የሚሆነው፡፡ ሟች ህሊናው ንጹህ ሆኖ እና ተረጋግቶ እንዲኝዝ ይፈለጋል፡፡ ህመምተኛው ተኝቸ መንገደኛ ነውና ለቀጣይ መንገዱና

ዕጣ ፋንታው ይበጀኛል ይጠቅሙኛል የሚላቸውን ነገሮች ያደርጋል፡፡ በሀሰት በመመስከር፣ ዝሙት በመስራት፣ በመስረቅ፣ በመግደል በአጠቃላይ ሰውንና ፈጣሪውን የሚያሳዝኑ ስራዎችን በመስራት ላይ የነበረ ከሆነ ሐጢአቱን እግዚአብሔር ይቅር እንዲለው በደሉንም እንዲሽርለት በካህኑ ፊት ይናዘዛል፡፡ መንገደኛ ነውና መንገድ እንዲቃናለትና እንዲሳካለት በሄደበትም ቦታ መልካም እንዲያጋጥመው ሽክሙን አራግፎ ንፁህ ሆኖ ይዘጋጃል፡፡ ይሄ በካህኑና በህመምተኛው መካከል ብቻ የሚፈፀም ኑዛዜ ነው፤ በፅሁፍ የሚሰፍርም አይደለም የቃል ኑዛዜ ነው እንጂ፡፡ ከቃለ ኑዛዜው ቀጥሎ የነፍስ አባቱ ወይም ተጠርተው የመጡት ካህን ከሽማግሌዎች ጋር ሆነው ስለ ውርስ ጉዳይ በጠቅላላውም ስለቤተሰቦቹና ስለንብረቱ ሁሉ በቃል ወይም በጽሁፍ ኑዛዜውን እንዲሰጥ ያደርጋሉ፡፡ በዚህኛው ኑዛዜ ህመምተኛው በሐብት ወራሾች ዙሪያ፣ በብድር አከፋፈል (ያበደረው ወይም የተበደረው ገንዘብ ካለ) እና እነዚህን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ ሐሳቡን ይሰጣል፤ እንዲሆን የሚፈልገውን ይናገራል፡፡ ኑዛዜው በቃል ከሆነ ካህኑና ሽማግሌዎቹ በጥሞና እያዳመጡ ይከታተላሉ፤ የጋራ መግባባት እንዲኖር ጥረት ያደርጋሉ፤ ሐሳቡንም በሐሳባቸው ይይዛሉ፡፡ በፅሁፍ እንዲሰፍር የተደረገ ከሆነ ደግሞ የኑዛዜው ቃል በትክክል መስፈሩን እንዲያረጋግጥ ለህመምተኛው ከተነበበለት በኋላ ወረቀቱ ይሁንታ ባገኘ በአንዱ ሽማግሌ ቤት ውስጥ በጥንቃቄ እንዲቀመጥ ይደረጋል፡፡ አንዳንዴ ግን ህመምተኛው ህመሙ ሳይፀናበት በፊት ኑዛዜውን አስቀድሞ ጽፎ የሚገኝበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ይህ ከሆነ ተጠርተው ለሚመጡት የነፍስ አባቱና የአካባቢው ሽማግሌዎች ያዘጋጀውን የኑዛዜ ወረቀት በጥንቃቄ እንዲያስቀምጡት ይሰጣቸዋል፡፡ ከእርሱ ሞት በኋላ በቤተሰቦቹ መካከል ችግር እንዳይፈጠር አደራ ይላቸዋል፡፡ ሽማግሌዎቹ ከህመምተኛው ሞት በኋላ የሚፈጠሩ ችግሮችን ባዳመጡት ወይም በፅሁፍ በያዙት የኑዛዜ ቃል መሰረት የመፍታት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

አንዳንድ ጊዜ ተናዛዡ ለየት ያሉ ሐሳቦችን ሊያነሳ ይችላል- እንዲቀበር የሚፈልግበትን ቦታ (ቤተክርስቲያን) እና የአቀባበሩን ሁኔታ የሚናዘዝበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ ‹‹ስሞት ሬሳዬን በሰሌን ከፍናችሁ እዚህኛው ቤተክርስቲያን (የቤተክርስቲያኑን ስም በመጥቀስ) እንድትቀብሩኝ አደራ፡፡ የሬሳ ሳጥን አልፈልግም፤ በሬሳዬ ላይም ሀውልት እንዳታሰሩብኝ፤ እንዲሁ ቅበሩኝ›› የሚልበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡ ቤተሰቦቹና ወዳጅ ዘመዶቹ የሟቹ ቃል ተግባራዊ እንዲሆን የበኩላቸውን ጥረት ያደርጋሉ፡፡ ተናዛዡ ሐውልት እንዳይሰራና

በሰሌን ብቻ ተከፍኖ ያለ ሬሳ ሳጥን እንዲቀበር የሚፈልገው በተለያዩ ምክንያቶች ነው፡፡ አንድም የኢየሱስ ክርስቶስ ስጋ በተልባ እግር ልብስ ተከፍኖ እንደተቀበረ የእርሱም አቀባበር እንደዚሁ እንዲሆን በመሻት፣ አንድም በህይወት እያለ ለፈፀመው በደል መቀጣጫ ይሆነው ዘንድ በማሰብ ሲሆን ፣አንድም ደግሞ ‹በህይወት እያለሁ ያስቸገርኩት አንሶ ሞቼም ላስቸግር እንዴ?› ከሚል እሳቤ በመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡

ታሞ የነበረው ሰው በአጋጣሚ ከዳነ ይህ መልካም ዕድል ነው፡፡ ‹እድሜው ረጅም ነው› ይባላል፡፡ የቤተሰቦቹም ሆነ የወዳጅ ዘመዶቹ ሐዘን በደስታ ይተካል፡፡ ፌሽታ ይሆናል፡፡ በሀዘን የቆሰለ ህሊናቸው ይጠግጋል፡፡ ኑሯቸውም ይረጋጋል፡፡ ህመምተኛው ከሞተ ደግሞ ሌሎች ክዋኔዎች ይኖራሉ፡፡ ለእነዚያ ክዋኔዎች ራሳቸውን ያዘጋጃሉ፡፡

### 4.1.2 የቅድመ ሞት ክዋኔ በእስልምና እምነት ተከታዮች

እንደ ክርስትና እምነት ተከታዮች ሁሉ የእስልምና እምነት ተከታዮችም አንድ ሰው በጠና ሲታመምና የመሞቱ ነገር አይቀሬ መሆኑን እርግጠኛ ከመሆን ደረጃ ላይ ሲደርሱ አመቺ በሆነው መንገድ ሁሉ በመጠቀም ለቅርብና ለሩቅ ዘመዶቹ መልዕክት ይልካሉ፤ ‹በነፍሱ ድረሱበት› ይላሉ፡፡ ታማሚው ለአካለ መጠን የደረሰና ትዳር የመሰረተ፣ ልጆችንም ወልዶ ሀብት ንብረት ያፈራ ሰው ከሆነ እንዲናዘዝ ይደረጋል፡፡ ሐይማኖቱ ያዛል፤ ያስገድዳል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ሃሳብ የሰጡኝ ሼህ ሰይድ ቢላል የተባሉ መረጃ አቀባይ እንደገለፁት አንድ ሰው ሲታመም ኑሳ(ኑዛዜ) እንዲያስቀምጥ፣ የሰደቃ[2] ገንዘብም እንዲወስን በቅዱስ ቁርአን ታዟል፡፡ ኑሳው (ኑዛዜው) ሰውዬው ከሞተ በኋላ በህይወት በነበረበት ሰዓት ያፈራው ሀብት ንብረቱ እርሱ በሚፈልገው መንገድ ፊር እንዲይዝለት የሚደረግበት፣ ብዙውን ጊዜ የሚፃፍ፣ ኑዛዜ በሚተወው ሰው የሚፈረምበትና በምስክሮች የሚረጋገጥ፣ በህግ ፊትም ተቀባይነት ያለው ሰነድ ነው (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 17፣ 2004 ዓ.ም)፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው በጠና ሲታመም በአስቸኳይ በአቅራቢያ ወደሚገኝ ኡለማ(ዎች) ዘንድ ሰው ይላካል፡፡ ኡለማው(ዎቹ) ተጠርተው እንደመጡ ከሌሎች ሽማግሌዎች ጋር በመሆን ታማሚውን እንዲናዘዝ ያደርጉታል፡፡ የኑዛዜው ቃል በአብዛኛው በሐብት ንብረት ክፍፍል ላይ የሚያተኩር ነው የሚሆነው፡፡ በአደራ መልክ ያስቀመጠው የሌላ ሰው ሀብት ንብረት ካለ ለባለቤቱ እንዲመለስለት፣ የእርሱ የሆነ ሀብትና ንብረትም ሌሎች ሰዎች ላይ

---

[2]ሰደቃ፡- የእስልምና ሀይማኖት ተከታዮች ለድሆች የሚያበሉት ተዝካር ነው፡፡

ካለው ቤተሰቦቹ ያንን እንዲረከቡና እንዲጠቀሙበት ይናዘዛል፡፡ በውርስ ጉዳይ ላይ ያለውን ሐሳብ እንዲገልጽ ይደረጋል፡፡ የሰደቃ ገንዘብም ይወሰናል፡፡ ህመምተኛው ካለው ገንዘብ ላይ አንድ ሶስተኛ በሚሆነው ወይም ከዚያ በሚያንሰው ገንዘብ ላይ ነው ኑዛዜ ማድረግ የሚችለው፤ የሰደቃ ገንዘብም እንዲወስን የሚፈቀድለት፡፡ ይህም የሚሆነው ምናልባት እዳ ያለበት እንደሆነ እዳው ከተከፈለ በኋላ ነው፡፡ ህመምተኛው እዲናዘዝ ከሚፈቀድለት የገንዘብ መጠን ላይ ‹‹ይሄን ያህል ገንዘብ (የገንዘቡን መጠን ጠቅሶ) ወጪ አድርጋችሁ ስሞት ሰደቃ አድርጉልኝ›› ብሎ ይናዘዛል፡፡ ሲሞት ራሱ የወሰነው ገንዘብ ወጪ ተደርጎ አስፈላጊው ነገር ሁሉ ይፈፀማል፤ ሰደቃም ይደረጋል (በዚህ ዙሪያ የሚነሱ ዝርዝር ጉዳዮችን ‹‹ጊዜ ሞት ክዋኔ›› በሚለው ክፍል እንመለከታለን)፡፡

እንደ ሼህ ሰይድ ገለጻ ‹‹ቀሪው ገንዘብ (ሁለት ሶስተኛው ማለታቸው ነው) ታማሚው ከሞተ በኋላ አላህ(ሱ.ወ[3]) በቅዱስ ቁርአን ውስጥ በተናገራቸው የውርስ መደቦች መሰረት ለሚመለከታቸው የሚከፋፈል ይሆናል››፡፡ አላህ(ሱ.ወ) በቅዱስ ቁርአን የተናገራቸው ናቸው ብለው የነገሩኝ የውርስ መደቦች ስድስት ናቸው፡፡ የንብረቱን ግማሽ የሚወርሱ መደቦች አሉ፡፡ ከንብረቱ አንድ አራተኛ የሚወርሱ መደቦች አሉ፡፡ የንብረቱን አንድ ስምንተኛ የሚወርሱ አሉ፡፡ የንብረቱን ሁለት ሶስተኛ የሚወርሱ አሉ፡፡ አንድ ሶስተኛ የሚሰጣቸው አሉ፡፡ አንድ ስድስተኛም የሚደርሳቸው አሉ፡፡ ከሞት በኋላ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮች በዚህ ህግ መሰረት እልባት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ተጠርተው የመጡት ሰዎችም ሆኑ ቤተሰቦቹ ታማሚው ከመሞቱ በፊት እንዲያደርጉት የሚጠበቅባቸው አንድ ሌላ ተግባር አለ-ህመምተኛው ከሊማን[4] እንዲያነብ ማድረግ፡፡ የሚሞትን ሰው የሚጎበኙ ሰዎች ሟች የእምነትን የምስክርነት ቃላት እንዲያነብ ወይም እንዲናገር ማስታወስ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ‹‹የሚሞት ሰው የእምነትን የምስክርነት ቃላት እንዲያነብ ማስታወስ፣ ሐሳብ ማቅረብ፣ እንዲያም ሲል ማዘዝ ሁሉ እንደሚቻል በሱንና በግልፅ ተጠቅሷል፡፡ ህመምተኛው በጣም ተዳክሞ ማንበብ ባይችል እንኳ በአጠገቡ ያሉት ሰዎች ቃላቱን በማንበብ እንዲያዳምጥ ሊያደርጉ ይገባል›› (ሼህ ሰይድ ቢላል፣ቃለመጠይቅ፣ጥር 17፣2004ዓ.ም)፡፡ ህመምተኛው እንዲያነበው የሚጠበቅበት የእምነት የምስክርነት ቃል ‹‹ላ ኢላህ ኢልላ ሏህ›› የሚል ነው፡፡ ትርጉሙም ‹ከአላህ

---

[3] ሱ.ወ፡- “ሱብሀነሁ ወተአላ” ማለት ነው፤ ትርጉሙም ከሁሉ የጠራ እንደማለት ነው፡፡
[4] ከሊማ የሚለው ቃል ትርጉሙ የእምነት የምስክርነት ቃል ማለት እንደሆነ ሼህ ሰይድ ቢላል ተናግረዋል፡፡

በስተቀር ሌላ አምላክ የለም› ማለት ነው፡፡ የዚህን ዓለም ውጣ ውረድ፣ መውደቅና መነሳት፣ ማግኘትና ማጣት ወዘተ. ጨርሶ የሚሰናበት ሰው የመጨረሻ ቃላቱ ‹‹ላ ኢላሀ ኢልላ ሏህ›› የሚል ከሆነ ጀነት ይገባል የሚል ፅኑ ዕምነት አላቸው - ሙስሊሞቹ፡፡ ይህን የምስክርነት ቃል ሳይናገር በድንገት የሚሞት ሰው ዕድለኛ አይደለም፡፡

## 4.2. ጊዜ ሞት ክዋኔ

በቀዳሚው ክፍል አንድ በጠና የታመመ ሰው ከመሞቱ በፊት የሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች የሚያደርጓቸውን ክንዋኔዎች ተመልክተናል፡፡ ‹ጊዜ ሞት ክዋኔ› የሚል ርዕስ በተሠጠው በዚህኛው ክፍል ደግሞ ህመምተኛው ሲሞት የሚያከውኗቸውን ስርአቶች እንመለከታለን፡፡

ህመምተኛው እንደሞተ ወዲያውኑ ከሚከናወኑ ስነስርአቶች መካከል ሥርዓተ ግንዘት፣ ሥርዓተ ጉዞ (የጉዞ ስነስርአት) እና ሥርዓተ ቀብር በዋናነት የሚጠቀሱና የሁለቱም ሐይማኖት ተከታዮች የሚጋሯቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም በቅድሚያ የክርስትና እምነት ተከታዮች የጊዜ ሞት ክዋኔያቸው ምን እንደሚመስል እየተነተንኩና እየተረጎምኩ አቀርባለሁ፡፡ በመቀጠል ደግሞ የእስልምና እምነት ተከታዮችን የጊዜ ሞት ክዋኔ እተነትናለሁ፤ እተረጉማለሁ፡፡

### 4.2.1 የክርስትና እምነት ተከታዮች የጊዜ ሞት ክዋኔ

አይቀሬው ሞት መከሰቱ እውን ሲሆን በቤት ውስጥ ያሉት ሰዎች ሁሉ ለቅሶውን ድብልቅልቅ ያደርጉታል፡፡ የሟች ቤተሰቦች መሪር ሀዘን ያዝናሉ፡፡ ይወድቃሉ፤ ይነሳሉ፤ ይጮሃሉ፤ ያነባሉ፡፡ እሪታው ይቀልጣ ል፤ ዋይታ ና ኡኡታም ይሆናል፡፡ ጩኸቱንና ለቅሶውን የሰሙ የጎረቤትና የአካባቢው ሰዎች ወደ ለቅሶው ቤት በፍጥነት ይመጣሉ፡፡ መንደርተኞች ደጅ ላይ ይሰበሰባሉ፡፡ የሀዘንተኞችን[5] የአለቃቀስ ሁኔታ የሚመለከት ማንኛውም ሰው ዝም ብሎ መቆም ወይም መቀመጥ አይቻለውም፡፡ አብዛኛው ሰው ያለቅሳል፤ ያነባል፡፡

የማስተናበርን ድርሻ የሚወስዱ ሰዎች (አብዛኛውን ጊዜ የሟቹ የቤተሰብ አባላት፤ ዘመዶች፣ ጎረቤቶች ወይም ጓደኞች ሊሆኑ ይችላሉ) ለሟቹ የነፍስ አባት እና ለወዳጅ

[5] ሐዘንተኛ የሚለውን ቃል የምጠቀመው የሟቹን ቤተሰቦች፣ ዘመዶችና ወዳጆችን ለመግለጽ ነው፡፡

ዘመዶቹ መልዕክት ይልካሉ - መሞቱ እንዲነገራቸው ያደርጋሉ፡፡ ሚቹ የነፍስ አባት ከሌለው ለሌላ ለሚታወቁ ካህን ይነገራቸዋል፤ ይመጣሉ፡፡ ቄስ ወልደትንሳኤ አለማየሁ የተባሉ መረጃ አቀባይ አንድ ሰው ሲሞት ካህናት የሚጠሩበትን ምክንያት ተጠይቀው ሲመልሱ፤‹‹ሰው ከሀጢያት የነፃ አይደለም፡፡ በህይወት ዘመኑ ብዙ ሀጢያቶችን ይሰራል፡፡ እናም በሞተ ጊዜ ካህናቱ ‹አምላክ ሆይ የዚህን ሰው ሀጢያት አትቁጠርበት› እያሉ ይማልዳሉ፡፡ መጽሀፉ (መጽሐፍ ቅዱስ ማለታቸው ነው) ‹ ‹በምድር ያሰሩት በሰማይ የታሰረ፣ በምድር የፈቱት በሰማይ የተፈታ ነው› ስለሚል ፍትሀት ያደርጉለታል፤ ለዚህ ነው ካህናት የሚጠሩት›› ብለዋል (ቃለ መጠይቅ፣ ጥር 19፣ 2004 ዓ.ም)፡፡ ሀመምተኛው የሞተው ሌሊት ከሆነ ለነፍስ አባቱ በጠዋት መልእክት ይላክባቸውና ሌሎች ካህናትንና ዲያቆናትን ይዘው ወደሚቹ ቤት ይመጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሀመምተኛው ጠዋት ወይም ከሰአት በኋላ የሞተና በማግስቱ የሚቀበር ከሆነ በሞተበት ቀን ማታ የነፍስ አባቱ ከሌሎች ካህናትና ዲያቆናት ጋር በመሆን ቤተክርስቲያን ውስጥ ግብረ ሌሊት ይቆሙለታል፡፡ እጣን እያጠኑ፣ ኪዳን እያደረሱ ስለሚች ነፍስ ጸሎት ያደርጋሉ፡፡

ሚች በማግስቱ፣ በሁለተኛው ቀን ወይም በሦስተኛው ቀን ወዘተ. የሚቀበርባቸው አጋጣሚዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በእንደነዚህ አይነት አጋጣሚዎች የለቅሶው አስተናባሪዎች ለቀስተኛውን በሙሉ ከማልቀስ እንዲቆጠብ ያደርጋሉ፡፡ በተለይ ቤተሰቦቹና ወዳጅ ዘመዶቹ በሀዘን ብዛት እንዳይጎዱ ይመክራሉ፤ ይገስጻሉ፡፡

አስከሬን አንድ ቀንም ይሁን ሁለት ሦስት ቀናት ሳይቀበር እንዲቆይ የሚደረገው በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች ነው፡፡ የመጀመሪያው፣ መልእክት የተላከባቸው ሩቅ ያሉ ቤተሰቦችና ወዳጅ ዘመዶች እስኪመጡ ለመጠበቅ ሲሆን ሁለተኛው የደመቀና የተሳካ የለቅሶ ስነስርአት ለማካሄድ ነው፡፡ ሩቅ ያሉ የሚች ዘመዶችና ወዳጆች አስከሬኑ ከመቀበሩ በፊት ደርሰው በደንብ እንዲያለቅሱና ሀዘናቸው ከውስጣቸው እንዲወጣላቸው አብዛኛውን ጊዜ የሚች ሬሳ ቢያንስ ለአንድ ቀን እንዲያድር ይደረጋል፡፡

የወንቃ አካባቢ ነዋሪ የሆኑት አቶ ዳኛቸው ቢልልኝ የተባሉ መረጃ አቀባይ መርዶ ለመንገር መልእክተኛ እንዴት እንደሚላክ ሲገልጹ ‹‹አሁን አሁን ይሄ ሞባይል የሚባል ነገር ከመጣ ወዲህ በሱም ይነገራል፡፡ በተለይ የከተሜው ሰው እሱን ይጠቀማል፡፡ አሁን አሁን እየቀነሰ የመጣ ቢሆንም በዚህ በኛ በገጠሩ አካባቢ በተለይ ለሚች የቅርብ ዘመዶች መርዶ እንዲነገራቸው የሚደረገው መልእክተኛውን በሌጣ ፈረስ በመላክ ነው፡፡

መልእክተኛው ፈረሱን ያለ ኮርቻ ሊጣውን እየጋለበው ከመጣ አንዳች መርዶ ይዞ እንደመጣ ይታወቃል›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 21፣ 2004 ዓ.ም)፡፡

አስተናባሪዎቹ ለመግነዝ የሚያስፈልጉ እንደጨርቅ፣ የዘሀ ክር፣ መርፌ፣ ምላጭ፣ ሰሌን፣ የሬሳ ሳጥንና የመሳሰሉ ነገሮች እንዲገዙ ያደርጋሉ፡፡ ከቤተሰቡ አባላት መካከል ሬሳውን ሊገንዝ የሚችል ካለ መልካም ነው፤ ከሌለ ግን በአካባቢው የመገነዝ ልምድ ያላቸው ሰዎችን ያስጠራሉ፤ እንዲመጡ ያደርጋሉ፡፡ በመገነዝ ችሎታቸው ተጠርተው የመጡት ሰዎች ከአሚሚቹ[6] ጋር በመሆን አስከሬኑን ለቀብር ዝግጁ የማድረግ ስራ ይሰራሉ፡፡

የለቅሶ ስነስርአት የተሳካ እንዲሆን ከፍተኛውን ሚና የሚጫወቱት የማስተናበሩን ድርሻ የሚወስዱ ሰዎች ናቸው፡፡ አስተናባሪዎቹ ለለቀስተኛ ማስተናገጃ የሚሆን ስንዴ ወይም ሽንብራ እንዲገዛ ያደርጋሉ፡፡ ቀብሩ የሚፈጸምበት ቀን ጾም ካልሆነና የሟች ቤተሰቦችም ለቀስተኛውን ስጋ በማብላት የመሸኘት ሐሳብ ካላቸው በሬም እንዲገዛ ያደርጋሉ፡፡ ሟቹ ወይም የሟቹ ቤተሰቦች የእድር አባል ከሆኑ አስተናባሪዎቹ ለእድሩ ሊቀመንበር ያሳውቃሉ፡፡ መልእክተኛ ይልኩበታል ወይም ደግሞ በስልክ ይነግሩታል፡፡ የእድሩ ሊቀመንበርም ከእርሱ የሚጠበቁበትን ሀላፊነቶች ይወጣል፡፡ ሰዎችን በማስተባበር መቀመጫ ወንበሮችን ወደ ለቅሶው ቤት እንዲያጓጉዙ ያደርጋል፤ ድንኳን ያስጥላል፤ ስለሟች ማንነት፣ የመቀበሪያ ቦታና ሰዓት ወዘተ. የእድሩ አባላት እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡ አባላቱ የሟቹን ማንነት፣ መቀበሪያ ቦታውንና ሰዓቱን እንዲያውቁ የሚያደርግበት ዋነኛ መንገድ በእድር ጡሩንባ ነፊ አማካይነት ነው፡፡ ጡሩንባ ነፊው ለዚሁ አላማ የሚቀጠርና በእድሩ ደሞዝ የሚከፈለው ነው፡፡ ሟች የሚቀበርበት ቀን ከታወቀ በኋላ ጡሩንባ ነፊው በሌሊት ተነስቶ (በግምት ከሌሊቱ 11 ሰዓት አካባቢ ጀምሮ) በእድርተኞቹ መኖሪያ ቤት አካባቢ ጡሩንባውን እየነፋ ‹እገሌ (የሟቹን ስም በመጥቀስ) ሞቷልና ዛሬ በ-----

6 አሚሚች የሚባለው ህመምተኛው ከመሞቱ በፊት በቅርብ ሆኖ አስፈላጊውን እንክብካቤ የሚያደርግ ነው፡፡ ህመምተኛውን ምን እንዳማረው ይጠይቃል፣ ይመግባል፣ ንጽህናውን ይጠብቃል፣ ልብስ ይቀይርለታል፣ እንዳይበርደው ወይም በጣም ሞቆት እንዳይጨናነቅ ጥንቃቄ ያደርጋል፤ ወዘተ፡፡ ህመምተኛው ሲሞትም አስፈላጊውን እንክብካቤ ሁሉ ያደርግለታል፣ ያሟሙተዋል፡፡ እንደሁኔታው ችሎታና ልምዱ ካላቸው ሌሎች ሰዎች ጋር በመሆን አስክሬኑን ለቀብር ዝግጁ የማድረግ ስራዎችንም አብሮ ይሰራል -ይገንዛል፡፡

ሰዓት(የሚቀበርበትን ሰዓት በመጥቀስ)፣በ------ቤተክርስቲያን (የሚቀበርበትን የቤተክርስቲያን ስም በመጥቀስ) አቃብሩ ተብላችኋል› ይላል፡፡

ብዙ ጊዜ የሚች የቀብር ስነስርአት የሚፈጸመው በጧት ነው፡፡ ጧት 3 ሰዓትና 4 ሰዓት ላይ የቀብር ስነስርአታቸው የተጠናቀቁ ለቅሶዎች አጋጥመውኛል፡፡ እድርተኞቹ በለቅሶ ቤት የመገኘት ደንብ ካላቸው ከለቅሶው ቤት ጀምሮ በመገኘት፣ ደንባቸው ቤተክርስቲያን ተገኝቶ ማቃበር ከሆነም በዚሁ መሰረት ተገኝተው ያቃብራሉ፡፡ አብዛኞቹ ግን ከቤት ጀምሮ በሚኖረው የለቅሶ ስነስርአት ላይ በመገኘትና በመሳተፍ፣ በማልቀስ፣ አሬሳውን በመሸኘት ያቃብራሉ፡፡ ሌቴናል ኮለኔል ያደሳ የተባሉ የእድር ሊቀመንበር ሲገልጹ ‹‹በእኛ እድር ደንብ መሰረት ከለቅሶው ቤት እንዲገኙ የሚገደዱት አስከሬን ለመሸከም ተረኛ የሆኑ ሰዎች ናቸው፡፡ ሌሎች የእድር አባላት ሬሳው በሚቀበርበት ቤተክርስቲያን እንዲገኙ ደንባችን ነው፡፡ ሰዉ ግን እንደፍላጎቱ ከለቅሶ ቤት ጀምሮ ሊገኝና ሊያቃብር ይችላል›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 22፣ 2004 ዓ.ም)፡፡

ለከተማዋ ነዋሪ የሞት ለቅሶ ትልቅ ትርጉም ያለው ማህበራዊ ጉዳይ ነው፡፡ በለቅሶ ቀዛ የለም፡፡ ለቅሶ ለማህበራዊ ግንኙነት መጥበቅና መላላት እንዲሁም ጭራሹን መቋረጥ መሰረታዊ ነገር ነው፡፡ ለቅሶ የማይደርስ፣ የማያዝን - የማያስተዛዝን፣ አስከሬን በመሸከም የማያግዝ፣ የመቃብር ጉድጓድ የማያቋፍር፣ ድንኳን የማያታክል በአጠቃላይ በአንዱም ይሁን በሌላኛው የለቅሶ ስነስርአት ውስጥ የማይሳተፍ የእድር አባልም ይሁን ሌላ ሰው በማህበረሰቡ ይገለላል፤ ከፍተኛ ተጽእኖ ይደርስበታል፡፡ የእድር አባል ከሆነ ይቀጣል፤ ከነአካቴው ከአባልነቱም ሊሰረዝ ይችላል፡፡ በእርሱም ይሁን በቤተሰቦቹ ላይ መከራ ቢመጣ ከቁርጠኛ ወዳጅ ዘመዶቹ እና ከጥቂት ሰዎች በስተቀር የሚደርስለት አይኖርም፡፡

አስተናባሪዎች ለመግነዝ የሚሆኑ ነገሮችን እንዲሟሉ ካደረጉ በኋላ ገናገሮች የግንዘት ስነስርአቱን ይቀጥላሉ፡፡

#### 4.2.1.1 ሥርዓተ ግንዘት

ግንዘት አስከሬንን ለቀብር ዝግጁ የማድረግ ስራ ሲሆን ራሱን የቻለ ስርዓት ያለው ነው፡፡ አሟሟቹ ህመምተኛው እንደሞተ ወዲያውኑ ሬሳው ያለበትን ክፍል በመጋረጃ ወይም ሊከልል በሚችል ሌላ ጨርቅ (ነጠላ ወይም ጋቢ) ይጋርዳል፡፡ በልምዳቸው ተመርጠውና

ተጠርተው ከመጡት ሰዎች ጋር አንድ ላይ በመሆን የሚቹን አይኖች ይከድናሉ፤ ጥርሶቹን ይገጥማሉ፤ አፉን ይዘጋሉ። ከዚያም አስከሬኑን አጥበው በጀርባው ቀጥ ብሎ ተንጋሎ እንዲተኛ ያደርጋሉ። አስከሬን ለምን እንደሚታጠብ የተጠየቁት ቄስ ይትባረክ አለሙ የተባሉ መረጃ አቀባይ

> ይህ የለበስነው ስጋ እንኳን ሞተን በቁም እያለንም ውሃ ካላጠራው ያው ስጋ ነው። በቁም እያለን ራሳችንን በራሳችን ልናፀዳው ይገባል። ስንሞት ደግሞ ሬሳችንን ህያዋን ሊያፀዱት፣ ሊያጥቡት ይገባል። ለምሳሌ ጴጥሮስ ከሞት ያስነሳት ጣቢታ ከሞተች በኋላ በውሃ አጥበዋት እንደነበር መፅሀፉ ላይ (መፅሀፍ ቅዱስ ማለታቸው ነው) ተጠቅሷል። የሚችን አስከሬን በንፁህ ውሃ ማጠብ የቤተክርስቲያናችን ሥርዓት ነው። የሬሳው ንፅህና ተጠብቆ ንፅህት ወደ ሆነችው ቤተክርስቲያን እንዲገባ ነው የሚታጠበው ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 20፣ 2004 ዓ.ም)።

እኚሁ መረጃ አቀባይ አስከሬኑ ተንጋሎ እንዲተኛ የሚደረገው በአፍና በአፍንጫው የተለያየ ፈሳሽ እየወጣ ሰዎችን እንዳያውክ እንደሆነ ነግረውኛል። ገናገሮቹ ሬሳውን አንጋለው ካስተኙት በኋላ አንገቱ እንዳይጣመም ወገቡም እንዳይታጠፍ ቀጥ እንዲሉ ያደርጓቸዋል። እጆቹንና እግሮቹንም ይዘረጓቸዋል። ይህን የሚያደርጉት ወዲያውኑ በትኩሱ ነው። የሬሳው ሰውነት ከቀዘቀዘና ከቆየ ሰውነቱ ድርቅ ብሎ እንደልብ አይታዘዝላቸውም። ‹‹የሁሉንም ሰው ሬሳ ማንኛውም ልምድ ያለው ሰው መገነዝ ይችላልን?›› የሚል ጥያቄ ያቀረብኩላቸው መሪ ጌታ ሊባኖስ የተመኘ ሲመልሱ፤

> የግንዘት ሥርዓት የሚከናወነው የእያንዳንዱን ሚች ምድራዊ ማእረግ መሰረት በማድረግ ነው። ሚች አንድ ማእረግ ካለው የሚገንዘው እንደሱ የሆነ ሰው ነው። ካህኑን ካህን ይገንዘዋል እንጂ ምእመን ሊገንዘው አይችልም፤ አይገንዘውምም። ሚች ማእረግ ያለው ከሆነና አሟሟቹ ምእመን ከሆነ ወዲያውኑ መፈፀም ያለባቸውን (እንደ አይን መክደን፣ ጥርስ መግጠም እና አፍን መክደን ያሉትን) ስራዎች ይሰራል እንጂ ከዚያ ባለፈ ያሉ ተግባራትን የሚመለከታቸው ሰዎች እንዲያከናውኑ ይደረጋል። ሊላውም ሰው ልምድ ስላለው እንዲገንዝ አይደረግም፤ አይገንዝም።

ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 21፣ 2004 ዓ.ም)።

ሬሳው ቀጥ ብሎ እንዲተኛ ከተደረገ በኋላ ሰባት ቦታዎች ላይ በክር ይታሰራል፤ ይገነዛል። የሁለት እግሩ አውራ ጣቶች አንድ ላይ ይታሰራሉ። ሁለት እጆቹም ብልቱ ላይ እንዲያርፉ ከተደረገ በኋላ አውራ ጣቶቹ አንድ ላይ ይታሰራሉ። ባቱ፣ ታፋው፣ ሽንጡ፣ ደረቱና አንገቱም በተመሳሳይ ለመገነዣነት በተዘጋጀው የዘሀ ክር ይታሰራሉ።

መጋቢ አእላፍ ጥበቡ የሺታ የተባሉ መረጃ አቀባይ አስከሬኑ ሰባት ቦታዎች ላይ የሚታሰርበትን (የሚገነዝበትን) ምክንያት ተጠይቀው ሲመልሱ፤ ‹‹የሰው ልጅ አራት

ባህርያተ ሥጋ እና ሶስት ባህርያተ ነፍስ በጥቅሉ ሰባት ባህርያትን የያዘ ነው፡፡ ባህርያተ ሥጋ የሚባሉት መሬት፣ ውሃ፣ ነፋስና እሳት ናቸው፡፡ ባህርያተ ነፍስ የሚባሉት ደግሞ ለባዊነት፣ ነባቢነትና ሕያውነት ናቸው፡፡ በነዚህ ባህርያት ተደፋፍሮ የሰራውን ሐጢያት እግዚአብሔር አምላክ ይቅር ይለው ዘንድ ሰባት ቦታ ላይ ይገነዛል›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 23፣ 2004 ዓ.ም)፡፡

ሁለት እጆቹ ብልቱ ላይ እንዲሆኑ የሚደረግበትን ምክንያትም ተጠይቀው ሲመልሱ፤ ‹‹ይሄ የሚሆነው ለህጋውያን ወይም ለህዝባውያን ብቻ ነው፡፡ የሁሉም ሰዎች ሬሳ በተመሳሳይ መንገድ አይገነዝም፡፡ ህጋውያን (ህዝባውያን) እጃቸውን በብልታቸው ላይ ጭነው እንዲገነዙ ይደረጋል፡፡ ዲያቆናት እጃቸውን ከትከሻቸው ላይ ጭነው ይገነዛሉ፡፡ ቀሳውስት እጃቸውን ደረታቸው ላይ አመሳቅለው ይገነዛሉ፡፡ ባህታውያን እና መናኝ ደናግል መነኮሳት ደግሞ እጃቸውን ከአይናቸው ላይ ጥለው ይገነዛሉ›› ብለዋል፡፡ ህጋውያን እጃቸውን ከብልታቸው ላይ ጭነው የሚገነዙት በሠጠኸን ስጋ የሚገባ እንጂ የማይገባ ስራ አልሰራንበትም ሲሉ ነው፡፡ ዲያቆናት እጃቸውን ከትከሻቸው ላይ ጭነው የሚገነዙት ምዕመናንን ለማገልገል በተልዕኮ ሲፈጥኑ መኖራቸውን ለማጠየቅ ነው፡፡ ቀሳውስት እጃቸውን ደረታቸው ላይ አመሳቅለው የሚገነዙት ዘመናቸውን ምእመናንን በመባረክ ማሳለፋቸውን ለማስረዳት ነው፡፡ ባህታውያንም እጃቸውን ከአይናቸው ላይ ጥለው የሚገነዙት የዚህን ዓለም ጣእም እንዳልቀመሱ በዓይናቸውም እንዳላዩ ለማጠየቅ እንደሆነ ነግረውኛል፡፡

ሬሳው ሰባት ቦታዎች ላይ ከታሰረ በኋላ ለመግነዝ በተዘጋጀው ንጹህ ጨርቅ ተጠቅልሎ የሬሳ ሳጥን ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ በሬሳ ሣጥኑ ፋንታ አስከሬኑ በሰሌን ሊጠቀለል ይችላል፡፡ አስከሬኑን በሰሌን ከጠቀለሉ ወይም ደግሞ በሬሳ ሳጥን ውስጥ ካስገቡ በኋላ ቸርንጉርጉር የሆነ ልብስ[7] ያለብሱታል፡፡ የመገነዣው ጨርቅ ንጹህ እንዲሆን የተፈለገበትን ምክንያት የተጠየቁት መሪጌታ ሊባኖስ የተመኘ የተባሉት መረጃ አቀባይ እንደገለጹት አንድም አስከሬኑ ተጓዥ መንገደኛ ነውና ታጥቦ ንፅህናው ሳይጓደል በንጹህ ልብስ ተጠቅልሎ እንዲሄድ በማሰብ ሲሆን አንድም ደግሞ ኒቆዲሞስና ዮሴፍ የኢየሱስን ሥጋ ከመቅበራቸው በፊት በንፁህ በፍታ መከፈናቸውን ለማሰብ እንደሆነ አብራርተውልኛል፡፡ በከተማው አስከሬንን በሬሳ ሳጥን ውስጥ አድርጎ መቅበር የተለመደ

---

7 ይህ ልብስ ብዙ ጊዜ በእድሩ አማካኝነት ተገዝቶ እቃ ቤት ውስጥ የሚቀመጥና ሰው ሲሞት ወጪ ተደርጎ አስከሬኑን ለመሸፈን የሚጠቀሙበት፣ ሬሳው ከተቀበረ በኋላም ተመልሶ በእድሩ እቃ ቤት ውስጥ የሚቀመጥ ጨርቅ ነው፡፡

ነው፡፡ አልፎ አልፎ ግን የአንዳንድ ሰዎች ሬሳ በተለያዩ ምክንያቶች (ምክንያቶቹ ቀደም ሲል መገለፃቸውን ያስታውሷል) በሰሌን ተጠቅልሎ ያለ ሬሳ ሳጥን ሊቀበር ይችላል፡፡ ሰሌን እንዲሆን የተመረጠበትን ምክንያት ቄስ ይትባረክ አለሙ የተባሉት መረጃ አቀባይ ሲያብራሩ ‹‹ሰሌን የሚሰራው ከዘንባባ ቅጠል ነው፡፡ የዘንባባ ቅጠል ደግሞ ኢየሱስ ክርስቶስ በአህያ ውርንጭላ ላይ ተቀምጦ ሲገባ ያዩ ሰዎች በመንገዱ ላይ ያነጥፉለት የነበረው ቅጠል ነው፡፡ እናም አንዳንድ ሰዎች በዚህ ቅጠል በተሰራው ሰሌን የሚከፈኑት ያንን ለማሰብ ነው›› ብለዋል፡፡

የመገነዝ ስነስርአቱ እንደተጠናቀቀ ገናዦቹ በታውን ተጠርተው ለመጡት ካህናት ይለቃሉ፡፡ ካህናቱ ልብሰ ተክህኗቸውን ለብሰው፣ ያመጧቸውን ቅዱሳን መጻህፍት፣ መስቀል፣ ጃንጥላ፣ ከበሮ፣ ማጠንት፣ ጽናጽል ወዘተ. ይዘው አስከሬኑ ወዳለበት ክፍል በመግባት በአስከሬኑ ዙሪያ ክብ ሰርተው ይቆማሉ፤ ለፍታት ይዘጋጃሉ፡፡ ጧፍ ያበራሉ፤ ማጠንቱ ላይ እጣን ጨምረው እንዲጨስ ያደርጋሉ፡፡ አንድ ዲያቆን ከሟቹ የነፍስ አባት ወይም ስርአቱን ከሚመሩት ካህን ፊት ለፊት የሚነበበውን መፅሀፍ ከደረቱ አስጠግቶ ይይዛል፡፡ ካህኑ የሟችን የክርስትና ስም እየጠሩ ያነብባሉ፡፡ ሌሎች ካህናትና ዲያቆናት ደግሞ እየተቀባበሉ ይቀድሳሉ፡፡

ካህናቱ በዚህ ሁኔታ ፍታት እያደረጉ ባሉበት ሰአት በሩቅና በቅርብ የሚገኙ ወዳጅ ዘመዶች ይሰበሰባሉ፡፡ የእድር አባላትም ይታደማሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦችና ዘመዶች የሟቹን ፎቶግራፍ እና አልባሳት (ካፖርት፣ ሱሪ፣ ኮት፣ ጋቢ፣ ቀሚስ፣ ነጠላ ወዘተ.) በመያዝ በእድምተኞቹ[8] ዙሪያ እየተሽከረከሩ ያለቅሳሉ፤ ያስለቅሳሉ፡፡ እድምተኞቹም በአብዛኛው ፍዝ ተመልካች ወይም አድማጭ አይደሉም፡፡ እነርሱም ያለቅሳሉ፤ ያንጎራጉራሉ፡፡ በተለይም ሴት እድምተኞች በሴት ሐዘንተኞች ዙሪያ ክብ ሰርተው በመቆምና ደረታቸውን በእጆቻቸው በመምታት የለቅሶው ተሳታፊ ይሆናሉ፡፡ ሀዘንተኞቹ የሟቹን ፎቶግራፍና አልባሳት የሚይዙት ምስሉን (መልኩን፣ ቁመናውን...) እና መልካም ባህሪያቱን በታዳሚያኑ አእምሮ ውስጥ እንዲከሰት በማድረግ እንዲባቡና በደንብ እንዲያለቅሱ፣ ለቅሶውንም ደማቅ እንዲሆን ለማስቻል ነው፡፡

---

8 እድምተኛ (ታዳሚ) የሚለውን ቃል የሟች ቤተሰቦችን ለማስተዛዘን ወይም ለማጽናናት ከሩቅና ከቅርብ የተሰባሰቡ ሰዎችን (ጎረቤቶችን፣ የአካባቢውን ሰዎች፣ የእድር አባላትን ወዘተ.) ለመግለጽ እጠቀምበታለሁ፡፡ አንዳንድ ጊዜ በዚህ ቃል ፋንታ ለቀስተኛ የሚለውን ቃል የምጠቀምበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡

ለቅሶው በሴት ሐዘንተኞች (በሟች ሴት ቤተሰቦች ወይም ዘመዶች) ይመራል፡፡ እነዚህ ሴት ሀዘንተኞች (አስለቃሾች) መሀል ላይ ቆመው በአንደኛው እጃቸው ደረታቸውን በመምታት ‹‹ዋይ›› ሲሉ በዙሪያው የቆሙት ሴት እድምተኞችም በአንድ እጃቸው ደረታቸውን በመምታት በአስለቃሾቹ ዜማ እና ምት (rhythm) አይነት ‹‹ዋይ›› ይላሉ፡፡ በመቀጠልም አስለቃሾቹ በሌላኛው እጃቸው ደረታቸውን በመምታት ‹‹ዋይ›› ሲሉ እድምተኞቹም እንደዚሁ ያደርጋሉ፤ ‹‹ዋይ›› ይላሉ፡፡ በዚህ አይነት ቅብብሎሽ ‹‹ዋይ ዋይ›› እያሉና ደረታቸውን እየመቱ ያለቅሳሉ፡፡ በዚህ መልክ የሚያለቅሱት ሴቶቹ ናቸው፡፡ ወንዶቹ ከሴቶቹ በመጠኑ ራቅ ብለው በመቆም ጋቢ ለብሰው ከሆነ አፋቸውን በለበሱት ጋቢ ሸፈን በማድረግ፣ ጭራ የያዙ ካሉም አፋቸውን በያዙት ጭራ በመከለል ያለቅሳሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ አንድ እጃቸውን በደረታቸው አንድ እጃቸውን በአፋቸው ላይ አድርገው ወይም ሁለት እጆቻቸውን ወደኋላቸው ሸርበው ወይም ደረታቸው ላይ አጣምረው ወዘተ. ያለቅሳሉ፡፡ ዝም ብለው ቆመው ለቀስተኛውን የሚመለከቱ፣ በቡድን በቡድን ሆነው የግል ጨዋታቸውን የሚጫወቱም አይጠፉም፡፡

ከፊል ሴት ሀዘንተኞች በሴት እድምተኞች መሃል ሆነው እያለቀሱ ሲያስለቅሱ ሌሎቹ (ሴት - ወንድ ሀዘንተኞች) ደግሞ፣ ከፍ ሲል እንደተገለጸው፣ የሟቹን ፎቶግራፍና አልባሳት በመያዝ ክብ ሰርተው በሚያለቅሱት ሴቶች ዙሪያና ፊንጠር ብለው በቆሙት ወንዶች መሀል መለስ ቀለስ እያሉ ያለቅሳሉ፤ ያስለቅሳሉ፡፡

ለቅሶው ከሞላ ጎደል በዚህ መንገድ መጠነኛ ስርአት ይዞ ይካሄዳል፡፡ አልፎ አልፎ ግን ዘግይተው የሚደርሱ የሟች የቅርብ ወዳጆችና ዘመዶች ሲመጡ የአለቃቀሱ ዘይቤ ይቀየራል፤ ድብልቅልቅ ይላል፤ ያዙኝ ልቀቁኝ ይበዛል፡፡ ኡኡታና ጩኸት ይሆናል፡፡ ዘግይተው የሚመጡት የሟች ወዳጅ ዘመዶች እንዲሁ አይቀላቀሉም፡፡ ገና ከሩቅ እያሉ እየወደቁና እየተነሱ፣ እየጮሁና እያለቀሱ ወደ ለቀስተኛው ይጠጋሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦችም እየጮኹና እያለቀሱ ይቀበሏቸዋል፡፡ በዚህ መልክ ከለቀስተኛው ጋር ከተቀላቀሉ በኋላ ከሟች ቤተሰቦች ጋር ትከሻ ለትከሻ ይተቃቀፋሉ፡፡ ከሟች ቤተሰቦች ጋር ትከሻ ለትከሻ የሚተቃቀፉት አን ድም ሰላምታ ለማቅረብ ሲሆን አንድ ም ደግሞ ሐዘናችሁ ሐዘኔ፣ ጉዳታችሁም ጉዳቴ ነው ለማለት ነው፡፡ መተቃቀፍ ለቅሶ መድረስን ማሳወቂያ መንገድም ነው፡፡

ካህናቱ በቤት ውስጥ ለሟች የሚያደርጉትን ፍታት እንደጨረሱ ሁሉም ሰው ሬሳውን ወደ ቤተክርስቲያን ለመሸኘትና ለመቅበር ዝግጅት ያደርጋል፡፡

### 4.2.1.2 የጉዞ ስነስርአት

ካህናቱ በቤት ውስጥ የሚያደርጉትን ፍታት እንዳጠናቀቁ አስተናባሪዎች አራት ጠንከር ጠንከር ያሉ ሰዎችን መርጠው አስከሬኑን እንዲሸከሙ በማድረግ ወደሚቀበርበት ቤተክርስቲያን ጉዞ እንዲጀመር ያደርጋሉ፡፡ አስከሬን የሚሸከሙት ወንዶች ናቸው፡፡ ሁለቱ ከፊት ሁለቱ ደግሞ ከኋላ ሆነው የአስከሬኑን ሳጥን አራት ጠርዞች በመያዝ ይሸከማሉ፡፡ ወይም ደግሞ ሁለት ረጃጅም ሽመሎችን (አጠናዎችን) በሬሳ ሳጥኑ በታች በኩል ግራና ቀኝ ካሰሩ በኋላ የሬሳው ራስ ያለበትን ጫፍ ወደፊት እግሮቹ ያሉበትን ጫፍ ወደኋላ አድርገው በመሸከም ከቤት ያወጡታል፡፡ እነዚህ ወንዶች ከለቀስተኛው መካከል በጥንካሬያቸው ተመርጠው እንዲሸከሙ የሚደረጉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ወይም ደግሞ አንዳንድ ጊዜ እድሩ ለአባላቱ የስራ ክፍፍል የሚያደርግ ከሆነና አባላቱም በተራቸው መሰረት አስከሬን ለመሸከም ስምምነት ያላቸው ከሆኑ በዚሁ መሰረት ተራው የደረሳቸው ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ወንዶች የሚመረጡበትን ምክንያት የተጠየቁት አቶ አንዳርጌ ተረፈ የተባሉ መረጃ አቀባይ ሲጠየቁ፤‹‹ወንዶች የሚመረጡት ከሴቶች በተሻለ ጠንከር ስለሚሉና ጉልበት ስላላቸው ነው እንጂ ሌላ ምክንያት የለውም›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 19፣ 2004 ዓ.ም)፡፡ ይሁን እንጂ ሟች ካህን ከሆኑ አስከሬኑን ከቤት ጀምሮ መቃብር ቦታ ድረስ የሚሸከሙት የክህነት ማእረግ ያላቸው ወይም ዲያቆናት እንደሚሆኑ ቄስ ወልደትንሳኤ አለማየሁ የተባሉት መረጃ አቀባይ ተናግረዋል፡፡

አስከሬኑ ከቤት ሲወጣ ድብልቅልቅ ያለ ጩኸትና ለቅሶ ይሆናል፡፡ ሁሉም በእንባ ይራጫል፡፡ ዋይታና ኡኡታ ይበዛል፡፡ ይህ ለምን እንደሚሆን ያብራሩልኝ ወ/ሮ የትምወርቅ አያሌው የተባሉ መረጃ አቀባይ ‹‹ሟች በህይወት ዘመን እያለ በእግሮቹ እየተንቀሳቀሰ ሲመላለስበት ከነበረው ቤት እና ደጅ በሬሳ ሳጥን ውስጥ ሆኖ ሰዎች ተሸክመው ሲያወጡት ሲታይ ያሳዝናል፣ ያስለቅሳል፡፡ ደንብ ነው፡፡ ቤተክርስቲያንም ትፈቅዳለች፡፡ ቤተክርስቲያናችን የሟች ነፍስ ከስጋው ስትለይ፣ ሟቹ ከቤት ሲወጣ እና ሟች ሲቀበር ሦስት ጊዜ ይለቀስ ትላለች›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 22 2004 ዓ.ም)፡፡

እውነት ነው፤ ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት፣ አንድ ሰው ሲሞት ከፍተኛ ለቅሶ ይሆናል፡፡ በአፀደ ስጋ እያለ ይፈፅማቸው የነበሩ ጥሩ ጥሩ ተግባራት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ መገታታቸው ነውና፣ ዳግም ላይመለስ የምር ተለይቷልና የሟች ነፍስ ከስጋው ስትለይ በጣም ይለቀሳል፤ ዋይታና ጩኸትም ይሆናል፡፡ እንደገና አስከሬኑ በሰዎች ሸክም ከቤት ሲወጣ ለሁለተኛ ጊዜ መሪር ሐዘን፣ ድብልቅልቅ ያለ ለቅሶ ይሆናል፡፡ በመጨረሻም በአፀደ ስጋ ከመሬት በላይ ሲንቀሳቀስ የነበረ ሰው ስጋው ወደ መሬት ውስጥ ሲጨመር (ግብአተ መሬቱ ሲፈፀም) ሌላ ዋይታ፣ ሌላ ጩኸት፣ ሌላ ለቅሶ ይሆናል፡፡

አስከሬኑ በከፍተኛ ጩኸትና ለቅሶ በመታጀብ ከቤት ወጥቶ ጉዞውን እንዲጀምር ይደረጋል፡፡ አንዳንድ ቤተሰቦች ሙታቸውን (በተለይ ሟች ‹‹ትልቅ ሰው›› ከሆነ) እንዲሁ አይለቁም፤ ፍሪዳ ጥለው፣ መንገድህን ጨርቅ ያርግልህ ብለው መርቀው አስመርቀው እንጂ፡፡ ሬሳው ከቤት ከመውጣቱ በፊት በሬ ይታረዳል፡፡ ይህ በቤተሰብ ፍላጎትና አቅም ላይ የሚመሰረት ነው፡፡ የሟች ሬሳ ከቤት ሲወጣ የበሬውን ደም እንዲሻገር ይደረጋል፡፡ ይህ ለሬሳ ሽኝት የሚደረግ የእርድ ሥነስርአት ‹ግንዳብ› ይባላል፡፡ ይህ ስርአት በምን ምክንያት እንደሚደረግ የጠየቅኋቸው አቶ አንዳርጌ ተረፈ የተባሉት መረጃ አቀባይ የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተውኛል፤

> ይሄ ባህል ነው፡፡ በሬ የሚታረደው አንደኛ መስተንግዶውን ለማጠናከር ነው- ለለቅሶ የመጣውን ሕዝብ በጥሩ ሁኔታ አስተናግዶ ለመመለስ እንዲቻል በማሰብ ነው፡፡ ሁለተኛ አንድ ትልቅ ሰው ሲሞት ባይሆን በዚህ እንሸኘው በማለት ነው በሬ የሚታረደው ለቀስተኞቹም ሆኑ ሌሎች የኔ ቢጤዎች ከለቅሶ መልስ የበሬውን ስጋ ከተመገቡ በኋላ ነፍስ ይማር ብለው የሚመርቁት ቀላል ነገር አይደለም(ቃለመጠይቅ፣ ጥር 19፣2004ዓ.ም)፡፡

እንደሌሎች መረጃ አቀባዮች ሁሉ አቶ አንዳርጌም አስከሬን ደም እንዲሻገር የሚደረግበትን ምክንያት ‹‹ባህል ነው›› በማለት ነው ያለፉት፡፡ በኔ እምነት ግን ሟች በህይወት ዘመኑ ሲወጣ ሲገባ ከነበረበት ቤቱ፣ ማረፊያው ከነበረው ጎጆው ወጥቶ የዘላለም ማረፊያው፣ የዘላለም መኖሪያው ወደሆነው የቀብር ጉድጓድ ለመግባት መሄዱን ለማጠየቅ ይመስለኛል አስከሬኑ ያን የደም መስመር፣ ያን ቀይ የደም መስመር እንዲሻገር መደረጉ፡፡ ከቤተሰቦቹ፣ ከወዳጆቹና ከዘመዶቹ የምር መቆራረጡን፣ የምር መለየቱን ለማመልከት ነው ደም ተሻግሮ እንዲሄድ መደረጉ የሚል ግምት አለኝ፡፡

አስከሬኑ የበሬውን ደም እንዲሻገር ከተደረገ በኋላ ጉዞው ይቀጥላል፡፡ ሬሳው ከቤት ሲወጣ ከነበረው መደበላለቅ አንጻር ሲታይ ጉዞው መጠነኛ መረጋጋትና ስነስርአት የሚታይበት ነው፡፡ የራሱ የሆነ ቅደም ተከተላዊ ቅርጽም አለው፡፡ ካህናቱና ዲያቆናቱ ለፍታት ይዘዋቸው የመጡትን መስቀል፣ ፅናፅል፣ ቅዱሳን መጻህፍት፣ ጃንጥላ፣ ከበሮ ወዘተ. ይዘው ልብሰ ተክህኗቸውን እንደለበሱ ከፊት ይቀድማሉ፡፡ አስከሬኑን የተሸከሙት ሰዎች ደግሞ ከኋላ ይከተላሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦች፣ የቅርብ ወዳጆችና ዘመዶችም አስከሬኑን አጅብ አድርገው ይጓዛሉ፤ የሟቹን ፎቶና አልባሳት ይዘው እየሙሁ እያለቀሱ ይከተላሉ፡፡ ለሟች ያላቸውን ፍቅር ወይም ሀዘን ይገልጹልኛል የሚሏቸውን መንገዶች ሁሉ በመጠቀም ወዲያና ወዲህ እየተንቀሳቀሱ፣ እየተንቆራጠጡና እጆቻቸውን እያርገበገቡ ወዘተ. ያጅባሉ፡፡ በመልዕክተኛ፣ በስሚ ስሚ እና በዕድር አባልነት የተሰበሰቡ ሰዎች ወንድ፣ ሴት፣ ትልቅ፣ ትንሽ ሳይለይ ሐዘንተኞቹን ይከተላሉ፡፡ የመቃብር ጉድጓድ ለመቆፈር የተዘጋጁ ወንዶችም አስፈላጊ ቁሳቁሶችን (ዶማ፣ አካፋ፣ ማጭድ፣ ገሶ፣ ገመድ ወዘተ.) በመያዝ አብረው ይጓዛሉ፡፡ የተወሰኑ አስተናባሪዎች ከለቀስተኛው ጋር አብረው የሚሄዱ ሲሆን የተወሰኑት ደግሞ በለቅሶው ቤት ውስጥ በመቅረት ልዩ ልዩ ስራዎችን ይሰራሉ፡፡

በለቅሶ ጊዜ የሀዘንተኞቹ አለባበስ የተለየ ይሆናል፡፡ የሟች ሴት ቤተሰቦችና ወዳጅ ዘመዶች ጸጉራቸውን በጥቁር ሻሽ ይሸፍናሉ፡፡ የእጅ፣ የእግር፣ የጆሮ ጌጦቻቸውን ያወልቃሉ፡፡ ጥቋቁር ቀሚስ ይለብሳሉ፡፡ ነጠላቸውን ወገባቸው ላይ ያደገድጋሉ፡፡ ወንድ ሀዘንተኞችም ጥቁር አልባሳትን ይለብሳሉ፡፡ ጋቢ ወይም ፎጣ ነገር ትከሻቸው ላይ ጣል ያደርጋሉ፡፡ ታዳሚያኑም በሰው ለቅሶ፣ በሰው ሀዘን ደምቀውና ኳለው አይታዩም፡፡ እነርሱም (በተለይ ሴት ታዳሚያን) እንደሀዘንተኞቹ ጸጉራቸውን በጥቁር ሻሽ በማሰር፣ ጌጣጌጦቻቸውን በማውለቅና ነጠላቸውን ዘቅዝቀው በመልበስ አጋርነታቸውን ይገልጻሉ፤ የሀዘን ተካፋይነታቸውንም ያሳያሉ፡፡ አብዛኞቹ ወንድ ታዳሚያንም በተቻለ መጠን ለሀዘን ሊሆኑ የሚችሉ አልባሳትን ይለብሳሉ፤ ጋቢም ይደርባሉ፡፡

በለቅሶው ቤት ውስጥ የቀሩት አስተናባሪዎች ለቀስተኛው ከቀብር ሲመለስ በአግባቡ መስተናገድ ይችል ዘንድ የሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ እንዲሟሉ ያደርጋሉ፡፡ የተወሰኑ ሰዎች ከለቅሶው ቤት ቀርተው ሥራ እንዲሰሩ ያዛሉ፤ ያስተባብራሉ፤ ስራ ያከፋፍላሉ፡፡ በዚሁ መሰረት ከፊሎቹ ውሀ ይቀዳሉ፤ ከፊሎቹ ዕቃ ያጣጥባሉ፤ ከፊሎቹ እንጨት ይፈልጣሉ፤ ከፊሎቹ እንጀራ ይጋግራሉ፤ ከፊሎቹ ቆሎ ይቆላሉ ወይም ንፍሮ ይቀቅላሉ፡፡

በሬ ታርዶ ከሆነም ስጋው ለሚፈለገው የምግብ ዓይነት ዝግጁ እስከሚሆን ድረስ በሚኖሩ ሂደቶች ውስጥ ሁሉም በመተባበርና በመተጋገዝ ይሰራሉ፡፡ ለማስተናገጃ የሚሆኑ ቁሳቁሶች እንደ ሳህን፣ ትሪ፣ ጭልፋ፣ የውሃ መጠጫ ብርጭቆዎች (ኩባያዎች) እና የመሳሰሉ ነገሮች ከዚያም ከዚህም ተብለው እንዲሚሉ ይደረጋል፡፡ በአጠቃላይ አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶች ሁሉ ይጠናቀቃሉ፡፡

ካህናቱ ከፊት ሆነው ለቀስተኛውን የሚመሩበትን ምክንያት የጠየቅኳቸው መጋቢ አዕላፍ ጥበቡ የሽታ የተባሉት መረጃ አቀባይ ሲመልሱ

> ይሄ የመጽሀፍ ቅዱስ ምሳሌነት ያለው ነው፡፡ ከመፅሐፍ ቅዱስ ውስጥ ማንበብ እንደሚቻለው ሙሴና አሮን እስራኤላውያንን ከፊት እየመሩ ከግብጽ ባርነት እንዲወጡ አድርገዋቸዋል፡፡ ከጨለማው ኑሮ ወደ ብርሃን ወስደዋቸዋል፡፡ ዮሴፍም ከመሞቱ አስቀድሞ የግብፅን ምድር ሲለቁ ሬሳውን ይዘውት እንዲወጡ አምላቸው ነበርና የዮሴፍን አፅም ይዘውት ወጥተዋል፡፡ አንድ ሰው ከዚህኛው አለም ወደዛኛው አለም ሲሸጋገር ካህናት እንደነሙሴና አሮን ከፊት እየመሩ ይሸኙታል ብለዋልቃለመጠይቅ፣ ጥር 23፣ 2004ዓ.ም)፡፡

አንዳንድ ጊዜ አስከሬኑ በመኪና የሚሸኝበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ በእንደዚህ ዓይነት አጋጣሚ እንደመኪናው የመጫን አቅም ካህናት፣ የሟች ቤተሰቦችና ወዳጅ ዘመዶች ከሬሳው ጋር አብረው እንዲሄዱ ይደረጋል፡፡ በተለይ የጤና ችግር ያለባቸውና አቅመ ደካማ አዛውንት ቤተሰቦችና የቅርብ ወዳጅ ዘመዶች ቅድሚያ ተሰጥቷቸው ከሬሳው ጋር ይሄዳሉ፡፡ የተቀሩት ቤተሰቦችና ወዳጅ ዘመዶች እንዲሁም ሌሎች ታዳሚያን ሬሳ የያዘውን መኪና ከኋላ እየተከተሉ ይሄዳሉ፡፡ ሬሳ የጫነ መኪና አብዛኛውን ጊዜ ቀስ እያለ በለቀስተኞች የእርምጃ ፍጥነት መሰረት ነው የሚሄደው፡፡



ምስል 1 - የአስከሬን ሽኝት



ምስል 2 - አስከሬኑን ተሸክመው ወደ ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ሲገቡ

አስከሬኑ በዚህ አኳኋን ወደ ቤተክርስቲያን ይሸኛል፡፡ ቤተክርስቲያን እንደደረሰ ፍታት ቤት ውስጥ ካሳረፉት በኋላ ሌላ ፍታት፣ ሌላ ፀሎት ይደረግለታል፡፡ ለሁለተኛ ጊዜ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡ ለነገሩ ለአንዳንድ ሙታን ሰባት ጊዜም ፍታት ሊደረግላቸው ይችላል- አንዱን ፍታት በቤት ውስጥ፣ አምስቱን ፍታት አስከሬኑ በጉዞ ላይ እያለ፣ የመጨረሻውን ደግሞ ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ ውስጥ ከገባ በኋላ፡፡ ይህ የጉዞ ፍታት ይባላል፡፡ የዚህ ዓይነቱ ፍታት ለሁሉም ሟች የሚደረግ አይደለም፡፡ በዕድሜ መግፋትንና በኢኮኖሚ የተሻለ ሆኖ መገኘትን የሚጠይቅ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ ሐሳብ ያካፈሉኝ ቄስ ወልደ ተንሳኤ ሲያብራሩ ‹‹ሟች በዕድሜ ገፋ ያለ ከሆነና ቤተሰቦቹ የጉዞ ፍታት እንዲደረግለት የጠየቁ እንደሆነ ለቤተክርስቲያን አስፈላጊውን ክፍያ ፈፅመው የጉዞ ፍታት ይደረግለታል፡፡ ይሄ በቤተሰቦቹ ጥያቄ መሰረት የሚፈፀም ነው›› ብለዋል፡፡

አቶ ግርማ ተክለሀይማኖት የተባሉ መረጃ አቀባይ ‹‹ሁሉም ሰው የጉዞ ፍታት አይደረግለትም፡፡ የጉዞ ፍታት እንዲደረግ አንደኛ ክፍያ መፈፀም አለበት፡፡ ሁለተኛ ደግሞ ሟች በዕድሜው በሰል ያለ መሆን ይኖርበታል፡፡ እንጂ እኮ ለኩታራው ሁሉ (ለህጻናት ሁሉ ማለታቸው ነው) የጉዞ ፍታት ይደረጋል ማለት አይደለም፡፡ እንዲያውም ህፃናት የጉዞ ፍታት አይደለም ለሌሎች ሰዎች እንደሚደረገው በቤት ውስጥና በቤተክርስቲያን ውስጥ ምንም ዓይነት ፍታት አይደረግላቸውም፡፡ ዝም ብለው ነው የሚቀበሩት›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 18፣ 2004 ዓ.ም)፡፡

መሪ ጌታ ሊባኖስ የተመኘ የተባሉት መረጃ አቀባይም ‹‹ዕድሚያቸው ከ15 ዓመት በታች የሆኑ ሴቶችና ከ18 ዓመት በታች የሆኑ ወንዶች ሐጢያት የለባቸውም ተብሎ ስለሚታመን ምንም ዓይነት ፍታት አይደረግላቸውም፡፡ ይታዘንላቸዋል፤ ይለቀስላቸዋል፣ ይፀለይላቸዋል እንጂ አይፈቱም›› በማለት ከፍ ሲል የተነሳውን ሐሳብ ያጠናክሩታል፡፡

ለሟች የጉዞ ፍታት የሚደረግለት ከሆነ በቤት ውስጥ አንድ ፍታት ይደረግለታል፡፡ ቤተክርስቲያን ከመድረሱ በፊት ደግሞ አምስት የመንገድ ላይ ፍታት ይደረግለታል - የጉዞ ፍታት፡፡ በመጨረሻም ቤተክርስቲያን ውስጥ ሰባተኛው ፍታት ይደረግለታል፡፡ የጉዞ ፍታቱ በመንገድ ላይ የሚደረግ ፍታት ከመሆኑ በስተቀር መጀመሪያ በቤት ውስጥ በኋላም በቤተክርስቲያን ውስጥ ከሚደረገው ፍታት ብዙም የተለየ አይደለም፡፡



ምስል 3 - ካህናት ለሟቹ ፍታት ሲያደርጉ

መጋቢ አፅላፍ ጥበቡ የሽታ የተባሉት መረጃ አቀባይ ‹‹አስከሬኑን መንገድ ላይ በማሳረፍ ካህናቱ ፍታት የሚያደርጉለት እስራኤላውያን በሙሴና በአሮን መሪነት ከምድረ ግብፅ ወጥተው ወደ ርስት ሀገራቸው ሲሄዱ የዮሴፍን አፅም ይዘው ስለነበረና በየቦታው ላይ ያርፉ አጽሙንም ያሳርፉ ስለነበረ ነው፡፡ ያንን ለማጠየቅ ነው አስከሬን በየቦታው እያረፈ ፍታት የሚደረግለት›› በማለት በየመንገዱ ፍታት የሚደረግበትን ምክንያት ያስረዱ ሲሆን

(ቃለመጠይቅ፣ ጥር 23፣2004 ዓ.ም) መሪ ጌታ ሊባኖስ የተመኘ ደግሞ ፍታቱ ሰባት ጊዜ የሆነበትን ምክንያት እንደሚከተለው አስረድተዋል፤

> ሚች ሰባት ጊዜ የሚፈታው አንድም የእያሪኮ ግንብ በሰባት ጊዜ ኡደት እና ፀሎት ፈርሶ እስራኤላውያን ምድረ ርስት እንደገቡ ‹ጌታ ሆይ የሚቹን ቅጽረ ሐጢያት አፍርሰህ ገነት መንግስተ ሰማያት አግባልን› ለማለት ሲሆን አንድም ኤልሳ ሰባት ጊዜ ጸልዮ የሞተውን ብላቴና እንዳስነሳው የእኛንም ፀሎትና ልመና ተቀብለህ የሚችን ነፍስ ከቅጣት አድናት፤ ሰማያዊ ህይወትን ስጣት ለማለት ነው (ቃለመጠይቅ ጥር 21፣2004ዓ.ም)፡፡

ለሚች የጉዞ ፍታት የማይደረግለት ከሆነ አስከሬኑ በቀጥታ ቤተክርስቲያን እንደደረሰ ካህናቱ በቤት ውስጥ ያደረጉትን ዓይነት ፍታት ያደርጉለታል፡፡ ፀሎተ አኮቴት ያደርጋሉ፤ የግንዘት ፀሎት ይጸልያሉ፤ ወዘተ፡፡ ፍታቱ እየተደረገ ባለበት ሰዓት ለሬሳው መቅበሪያ ጉድጓድ የሚቆፈር ከሆነ ቆፋሪዎቹ የሚች የነፍስ አባት በመስቀላቸው ባርከው የሚሰጧቸውን መሬት በምዕራብ - ምስራቅ አቅጣጫ ይቆፍራሉ፡፡ የጉድጓዱን ርዝመት በሬሳው ቁመት ልክ፣ ጥልቀቱን ደግሞ በግምት ከአንድ ሜትር እስከ አንድ ሜትር ከግማሽ እንዲሆን አድርገው ይቆፍሩታል፡፡



ምስል 4 - የመቃብር ጉድጓድ ሲቆፍሩ

በዚሁ ጊዜ ለቀስተኞች (በተለይ ሴቶች) ለአስከሬኑ ፍታት ከሚደረግበት ቤት አካባቢ ገላጣ ቦታ ላይ ቀደም ሲል በተገለፀው አኳኋን ክብ ሰርተው ‹‹ዋይ ዋይ›› የሚለውን እየተቀባበሉና ደረታቸውን እየደቁ ያለቅሳሉ፡፡ አንዳንድ የሚች ዘመዶች ደግሞ የሚቹን አልባሳትና ፎቶ በእጆቻቸው ከፍ አድርገው በመያዝ ወደፊታቸው በማስጠጋትና በመሳም

ወይም ወደ እዛና ወደ እዚህ በመመላለስ ያለቅሳሉ፡፡ ሌሎቹ ደግሞ የሚችን ዝምድና በመጥቀስ (‹‹ልጄ ልጄ››፣ ‹‹አባቴ አባቴ››፣ ‹‹እናቴ እናቴ›› ፣ ‹‹እህቴ እህቴ›› ወዘተ. በማለት)፣ ባህርያቱን በመግለጽ (‹‹ጀግና ነበርክ ጀግና ነበርክ››፣ ‹‹ለጋስ ነበርሽ ለጋስ ነበርሽ››፣ ‹‹ገመናዬ ገመናዬ›› ወዘተ. በማለት) እና በሌሎች ሐዘኔን፣ ፍቅሬንና ቀረቤታዬን ይገልጹልኛል የሚሏቸውን ቃላት በመጠቀም ያለቅሳሉ፤ ያንጎራጉራሉ፡፡ አንዳንድ ወንዶች ደግሞ ክብ ሰርተው ከቆሙት ሴቶች ኋላ ሆነው ጭራ የያዙ ጭራቸውን ፊታቸው አካባቢ ላይ እያወዛወዙና አፋቸውን እየከለሉ ያለቅሳሉ፡፡ አንዳንዶችም አፋቸውን በጋቢያቸው ሸፈን አድርገው ያለቅሳሉ፡፡ ወዘተ፡፡

ካህናት ለሚቱ ፍታት እያደረጉ ባሉበት ጊዜ ሌላም ድርጊት ይከናወናል፡፡ የእድር ሰብሳቢውና ሌሎች ባልደረቦቹ በለቅሶው ላይ የተገኙና ያልተገኙ አባላትን ይለያሉ፡፡ አባላቱ ወደ አንድ ጎን እንዲሰበሰቡ እና ጸጥ እንዲሉ ከተነገራቸው በኋላ የእድሩ ሊቀመንበር ስም ዝርዝሩን በመያዝ ከህዝቡ መሀል ሆኖ ስማቸውን በየተራ ይጣራል፡፡ ከእርሱ ጋር ያሉት ባልደረቦቹ ደግሞ የተጠራውን ስም ሙክ ብለው ያስተጋባሉ፤ አባላቱ እንዲሰሙ አድርገው ይጣራሉ፡፡ በቦታው ላይ የተገኙ አባላትም ‹‹አቤት›› ወይም ‹‹አለሁ›› በማለትና እጃቸውን ወደላይ ከፍ አድርገው በማሳየት መኖራቸውን ያሳውቃሉ፡፡ ምናልባት በሚታወቅ ምክንያት የቀሩ አባላት ካሉ ለቅሶው ቦታ ላይ የተገኙ ጓደኞቻቸው ወይም ጎረቤቶቻቸው ሰዎቹ የቀሩበትን ምክንያት ለህዝቡም ለሊቀመንበሩም ያስረዳሉ፡፡ አስገዳጅ ምክንያት ካልኖረ በስተቀር ከለቅሶ የሚቀር አባል አይኖርም፡፡ አባላቱ ለቅሶ ባለመድረሳቸው ምክንያት ከሚቀጡት የገንዘብ ቅጣት ይልቅ ከሀዘንተኞቹም ጋር ይሁን ከሌላው ህዝብ ጋር ለሚኖራቸው ማህበራዊ ግንኙነት ይጠነቀቃሉ፡፡ ማህበራዊ ግንኙነታቸው እንዳይሻክር ይጥራሉ፡፡

ካህናት ፍታት ማጠናቀቃቸውን፣ ቆፋሪዎችም ቆፍረው መጨረሳቸውን ካረጋገጡ በኋላ አስተናባሪዎቹ ሬሳው በተሸካሚዎች አማካይነት ከፍታት ቤቱ እንዲወጣ ያደርጋሉ፡፡ ተሸካሚዎቹም ሬሳውን በቀጥታ ወደ ቤተክርስቲያን በመውሰድ እንዲሰግድ ያደርጉታል፡፡ የወንድ ሬሳ ከሆነ በወንዶች የመግቢያ በር በኩል፣ የሴት ሬሳ ከሆነ በሴቶች የመግቢያ በር በኩል ሶስት ጊዜ እንዲሰግድ ይደረጋል፡፡ የካህን ሬሳ ደግሞ ከመቅደስ ውስጥ በታቦቱ ፊት እንዲሰግድ ይደረጋል፡፡ በነዚህ ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ የሰጡኝ ቄስ ወልደ ትንሳኤ አለማየሁ እንደገለፁት፤

> አስከሬን ሶስት ጊዜ እንዲሰግድ የሚደረግበት ምክንያት ሐይማኖታዊ ነው -ለአብ፣ ለወልድ፣ ለመንፈስ ቅዱስ የሚጠየቅ ይቅርታና ለሶስቱም የሚደረግ ስግደት ነው፡፡ የካህን ሬሳም በተለየ ሁኔታ እንዲሰግድ የሚደረግበት የራሱ ምክንያት አለው፡፡ ይኸውም ካህናት ከሌሎች ምዕመናን ጋር በተፈጥሮ አንድ ቢሆኑም ካህን በሥልጣን ደረጃ ከፍ ያለ በመሆኑና ከህዝቡ ለየት ብሎ ወደ ቤተመቅደስ በመግባት ታቦተ ህጉን አክብሮ እግዚአብሔርን የሚያገለግልና ስጋ ወደሙን የሚያቀርብ ስለሆነ ነው(ቃለመጠይቅ ጥር 19፡200ዓ.ም)፡፡


የወንድ አስከሬን በወንዶች መግቢያ በር፣ የሴት አስከሬን ደግሞ በሴቶች መግቢያ በር በኩል እንዲሰግድ ከተደረገ በኋላ በነፍስ አባት መሪነት ወደ መቅበሪያ ስፍራ ይወሰዳል፡፡

#### 4.2.1.3 ሥርዓተ ቀብር


ወንዶችም ሴቶችም አስከሬኑን ተከትለው ቀብሩ ወደሚፈጸምበት አካባቢ ይሄዳሉ፡፡ ይሁን እንጂ ሬሳው ከሚቀበርበት ጉድጓድ አጠገብ ሲደርሱ ሴቶቹ ነጠል ብለው እንዲቀሩ ይደረግና ወንዶቹ ብቻ የቀብር ስነስርአቱን ይፈጽማሉ፡፡ ሴቶች ወደጉድጓዱ ተጠግተው ሬሳ እንዲቀብሩ አይፈቀድላቸውም፡፡ የዚህን ምክንያት የጠየቅኋቸው መረጃ አቀባዮች ሀይማኖታዊም ባህላዊም ምክንያቶች እንዳሉት ገልጸዋል፡፡ መጋቢ አእላፍ ጥበቡ የሽታ የተባሉት መረጃ አቀባይ ‹‹በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አንዲትም ሴት የሟችን ሬሳ እንደቀበረች የሚገልጽ ነገር ስለሌለ ነው ሴቶች ሙታንን እንዲቀብሩ የማይፈቀድላቸው›› የሚል መልስ የሰጡኝ ሲሆን፣ ሌሎች መረጃ አቀባዮች ደግሞ ‹‹ሴቶች በተፈጥሮ ሩህሩህ በመሆናቸው ሀዘኑን ስለማይችሉት ነው የማይቀብሩት፣ ሴቶች ቀብሩን ከተመለከቱ ወይም ሬሳ ከቀበሩ መሀን ይሆናሉ፤ አይወልዱም›› የሚሉ ባህላዊ እምነቶች በመኖራቸው ምክንያት መሆኑን ገልጸዋል (ቃለመጠይቅ፣ አቶ ታዬ አንባቸው ጥር 17፣ 2004 ዓ.ም፤ ወ/ሮ አያልነሽ ወርቁ ጥር 20፣ 2004 ዓ.ም፤ ወ/ሮ አበበች መኮንን ጥር 21፣ 2004 ዓ.ም)፡፡

የሟች የነፍስ አባት ወይም ስርአቱን የሚመሩት ካህን ከፊት ቀድመው በመሄድ የተቆፈረውን ጉድጓድ በመስቀላቸው ከባረኩ በኋላ ሰባት ጧፍ ያበራሉ፡፡ ከዚያም አስከሬኑ ሲታጠንበት የነበረውን ዕጣንና ፍም በጉድጓዱ ውስጥ ይጨምራሉ፡፡ ከዚያም ሁለት ሰዎች ጉድጓድ ውስጥ ገብተው በሁለቱ የጉድጓድ ጫፎች ይቆማሉ፡፡ በመቀጠልም ከጉድጓዱ በላይ ያሉ ሰዎች (አስከሬኑን የተሸከሙትም ሆኑ ሌሎች ታዳሚያን) የአስከሬኑ ሳጥን የተሸፈነበትን ጨርቅ ካነሱ በኋላ ራሱን ወደ ምዕራብ እግሮቹን ወደ ምስራቅ አድርገው ጉድጓዱ ውስጥ ለቆሙት ሰዎች ያቀብሏቸዋል፡፡ አንዳንድ ጊዜ የአስከሬኑን ሁለት ጫፎች (የራስጌ እና ግርጌ ጫፎች) በገመድ ካሰሩ በኋላ፣ የሰዎች ጉድጓዱ ውስጥ

መግባት ሳያስፈልግ፣ በገመዱ ቀስ አድርገው በማንሸራተት አስከሬኑን ወደ ጉድጓዱ ውስጥ ሊያስገቡት ይችላሉ፡፡ በእንደዚህ አይነት አኳኋን አስከሬኑን ወደ ጉድጓዱ ውስጥ ካስገቡት በኋላ በአካፋ አፈር ይመልሱበታል፡፡ በአንዳንድ ቦታዎች በተለይም በገጠር አካባቢዎች ከአስከሬኑ በላይ የእንጨት ርብራብ (‹‹ድምድም›› ይሉታል) ከሰሩ በኋላ ነው አፈሩ የሚመለሰው፡፡ ድምድም የሚሰራበት ዋነኛው ምክንያት አስከሬኑን አፈር እንዳይጫነው በሚል ነው፡፡ አፈሩን ከመሬት በላይ እንዲቆለል አድርገው ከመለሱ በኋላ በአካባቢው የተገኘውን ርጥብ ቅጠል ከነቅርንጫፉ ቆርጠው በአስከሬኑ ራስጌ በኩል ይተክላሉ፡፡



ምስል 5 - በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ የአስከሬን ግብአተ መሬት ሲፈጸም



ምስል 6 -የአስከሬኑ ግብአተመሬት በሚፈጸምበት ጊዜ ሴቶቹ በቅርብ ርቀት ሆነው ሲያለቅሱ

ሰባት ጧፍ የሚበራበትን፣ አስከሬኑ ሲታጠንበት የነበረው ዕጣንና ፍም ጉድጓድ ውስጥ የሚጨመርበትን፣ ሬሳው ሲቀበር ራሱ ወደ ምዕራብ እግሮቹ ደግሞ ወደ ምስራቅ እንዲሆኑ የሚደረግበትንና በጀርባው እንደተንጋለለ የሚቀበርበትን ምክንያት የጠየቅኳቸው መረጃ አቀባዮች ሀይማኖታዊ መሰረት እንዳለው ይገልጻሉ፡፡

ሰባት ጧፍ የሚበራበት ምክንያት አንድም፣ ቀደም ሲል እንደተገለፀው፣ ሟች በሰባቱ ባህርያት (በሶስቱ ባህሪያተ ነፍስ እና በአራቱ ባህርያተ ስጋ) ተደፋፍሮ የሰራው ሐጢያት ይቅር እንዲባል ነው፡፡ አንድም ደግሞ ‹‹የሟች ነፍስ በሰባተኛ ቀኗ የሚደነቅ ብርሀን ወዳለበት ሰባተኛው ሰማይ መንበረ ጸባኦት ደርሳ በፈጣሪዋ በእግዚአብሔር ፊት

እንደምትቀርብ የሚያወሳ ተምሳሌት ነው›› (መጋቢ. አእላፍ ጥበቡ የሽታ ቃለመጠይቅ ጥር 23፣2004 ዓ.ም)፡፡

‹‹ካህናት አስከሬኑን በዕጣን ጭስ ማጠናቸው በኋላም ያጠኑበትን ዕጣንና ፍም ጉድጓድ ውስጥ መጨመራቸው የካህኑን የዘካርያስን ጢሰ ዕጣን እንደተቀበልክ የእኛንም ልመና ተቀብለህ ሚችን ሰማያዊ እየሩሳሌምን አውርስልን ሲሉ ነው›› (ቄስ ወልደ ትንሳኤ አለማየሁ ቃለመጠይቅ ጥር 19፣2004 ዓ.ም)፡፡

የአስከሬኑ ራስ ወደምዕራብ፣ እግሮቹ ደግሞ ወደምስራቅ ሆነው ተንጋሎ የሚቀበርበትን ምክንያት አስመልክተው ‹‹መፅሀፍ ‹ ፀሀይ ከምስራቅ ይወጣል› እንዲል ኢየሱስ ክርስቶስ

በምጽአት ቀን በምስራቅ በኩል ይመጣል፡፡ ያን ጊዜ ሙታን ሁሉ በፊቱ ይቆማሉ፡፡ ሚች ሲነሳ በፈጣሪው ፊት ለፊት ሆኖ እንዲነሳ ነው ራሱ ወደ ምዕራብ እግሮቹ ደግሞ ወደ ምስራቅ ሆነው በጀርባው ተንጋሎ እንዲቀበር የሚደረገው›› የሚል ምላሽ የሰጡኝ ደግሞ መሪጌታ ሊባኖስ የተመኝ ናቸው፡፡ አስከሬኑ አፈር ከለበሰ በኋላ በራስጌው በኩል ቅጠል የሚተከልበትን ምክንያት የጠየቅኋቸው መረጃ አቀባዮች በባህል የሚደረግ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ መቃብሩ ላይ ቅጠል መትከል በልማድ የሚደረግ እንጂ ሀይማኖታዊ መሰረት ያለው አይደለም፡፡ ሆኖም ቅጠሉ ትኩስ ሬሳ መኖሩን ለማመልከትና መቃብሩ በሌሎች ሰዎች ለሁለተኛ ጊዜ እንዳይቆፈር በምልክትነት የሚጠቅም እንደሆነ መረጃ አቀባዮቹ ተናግረዋል (ቄስ ይትባረክ አለሙ ቃለመጠይቅ ጥር 20፣2004 ዓ.ም፤ አቶ አንዳርጌ ተረፈ ቃለመጠይቅ ጥር 19፣2004 ዓ.ም)፡፡


በገጠር ባሉት አብያተ ክርስቲያናት ጉድጓድ ቆፍሮ ሬሳን መቅበር የተለመደ ነው፡፡ ቀብር በሚፈጸምባቸው የከተማዋ አብያተ ክርስቲያናትም ለሬሳ መቅበሪያ የተሰጠን ቦታ ወዲያውኑ ቆፍሮ መቅበር በስፋት አለ፡፡ ነገር ግን ይህን ጥናት ለማድረግ በመስክ ጉብኝት ላይ በነበርኩባቸው ጊዜያት ለየት ባለ ሁኔታ ቀብር የሚፈጸምባቸው አጋጣሚዎች ነበሩ፡፡

ለየት ያለ የቀብር ስነስርዓት ሲፈፀምባቸው ከነበሩት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ አንዱ የቅዱስ ማርቆስ ቤተክርስቲያን ነው፡፡ በዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ ምድር ቤት (underground) ያለው አንድ ትልቅ አዳራሽ አለ፡፡ የምድር ቤቱ ወለል ሊሾ ሆኖ ከሊሾው ላይ በግምት አንድ ሜትር ከግማሽ ቁመት ያለው የሲሚንቶ ግንብ አለ፡፡ ይህ


የሲሚንቶ ግንብ ውስጡ ሬሳን ለመቅበር በሚያስችል ሁኔታ በቂ ስፋትና ርዝመት እንዲኖረው ተደርጎ ተከፋፍሏል፡፡ ለእያንዳንዱ ክፍልፋይ ጉድጓድም ከሲሚንቶ የተሰራ ክዳን ተዘጋጅቶለታል፡፡ ይህን የቀብር መፈፀሚያ የአሰራው ‹‹የነጋዴዎች እድር›› የሚባለው እንደሆነና የእድሩ አባላት ወይም የአባላቱ ቤተሰቦች ሲሞቱ በዚህ ቦታ ላይ እንደሚቀበሩ አቶ ሰውነት መኩሪያ የተባሉ መረጃ አቀባይ ገልጸውልኛል ፡፡ ዓላማው ምን እንደሆነ ለጠየቅኋቸው ጥያቄም፤

> አየህ የሬሳ መቅበሪያ ቦታ እየጠፋ ነው፡፡ ከቦታ ጥበት የተነሳ በአንዱ ሬሳ ላይ ሌላ ሬሳ እየተቀበረ ነው ያለው፡፡ በዚህ ቦታ ላይ (በተገነባው) የሚቀበሩ አስከሬኖች ግን በደንቡ መሰረት ለሰባት ዓመት ያህል ይጠበቁና ከዚያ በላይ የሆናቸው አጽማቸው ተሰብስቦ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ እንዲቀበሩ ይደረጋል፡፡ በምትካቸው ሌላ አስከሬን ይቀበራል፡፡ ይሄ የቦታን ችግር ያቃልላል፡፡ እንደገና ደግሞ የአንድ ቤተሰብ ሙታንም በአንዱ ጉድጓድ ውስጥ ስለሚቀበሩ ለችግሩ ጥሩ መፍትሄ ነው

በማለት መልሰዋል (ቃለመጠይቅ፣ ግንቦት 27፣ 2004 ዓ.ም)፡፡



ምስል 7 - አስከሬን ወደምድር ቤት ውስጥ ሲያስገቡ



ምስል 8 - ምድር ቤት ውስጥ በተዘጋጀው ጉድጓድ የአስከሬን ግብአተ መሬት ሲፈጸም

ሌላ ለየት ያለ የቀብር ስነስርአት ሲፈፀም ያስተዋልኩት በ‹አብማ ማርያም› ቤተክርስቲያን ውስጥ ነው፡፡ በዚህ ቤተክርስቲያን ቀደም ሲል ቀብር ሲፈፀምበት የነበረው ቦታ ታርሶ አስከሬኑ ከወጣ በኋላ አፅሙ ተሰብስቦ በአንድ ጉድጓድ ውስጥ እንዲቀበር ተደርጓል፡፡ ከሠው አፅም ነፃ በሆነው ቦታ ላይ ቤተክርስቲያኗ በርካታ ጉድጓዶች በመደዳ

አስቆፍራለች፡፡ ስለዚህ አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ የሚች እድር ለቤተክርስቲያኗ ክፍያ ከፈጸመ በኋላ በተዘጋጀው ጉድጓድ ውስጥ እንዲቀበር ይደረጋል፡፡

### 4.2.2 የእስልምና እምነት ተከታዮች የጊዜ ሞት ክዋኔ

እንደ ክርስትና እምነት ተከታዮች ሁሉ የእስልምና እምነት ተከታዮችም የአንድ ሰው ነፍስ ከስጋው ስትለይ እሪታውን ያቀልጡታል፤ ይጮሃሉ፡፡ ቤተሰቦቹና ወዳጅ ዘመዶቹ መሪር እንባን ያነባሉ፡፡ በቤት ውስጥ ከባድ ለቅሶ ይሆናል፡፡ ጩኸቱንና ለቅሶውን የሰሙ ጎረቤቶችና የአካባቢው ሰዎች ሙስሊም፣ ክርስቲያን፣ ወንድ፣ ሴት፣ ትልቅ፣ ትንሽ ሳይል ይሰበሰባሉ፤ ያዝናሉ፤ ያለቅሳሉ፡፡ ለከተማዋ ህብረተሰብ በተለይ በለቅሶ ጊዜ አለመድረስ፣ አለማስተዛዘን፣ አለማቃበር ነውር ነው፡፡ በሀዘን ጊዜ የማይቀላቀልን ሰው ሕብረተሰቡ ያወግዘዋል፤ አንቅሮ ይተፋዋል፡፡ የተጣሉ ጎረቤታሞች ቢሆኑ እንኳን የሚታረቁበት አጋጣሚ ነው ማለት ይቻላል - ለቅሶ፡፡ በመሆኑም አንድ ሰው ሲሞት የአካባቢው ሰው ይሰበሰባል፤ ያዝናል፤ ያስተዛዝናል፡፡ ለሚች ቤተሰብ በልዩ ልዩ መንገድ አጋርነቱን ይገልጻል፡፡ የደረሰብህን መከራ ለብቻህ ተወጣው ብሎ ሜዳ ላይ አይጥልም፡፡ አለሁልህ ይላል፡፡ በተግባርም ይገልጣል፡፡ ይረዳል፤ ይደግፋል፡፡

ሰው ሲሞት በአጠገቡ ያሉ አሚሚቾች ወዲያውኑ የአይኖቹን ቆቦች ይዘጋሉ፤ ጥርሶቹን ይገጥማሉ፤ አፉን ይከድናሉ፡፡ ሀፍረተ ስጋውን እንዳያዩ በመጠንቀቅ ለብሶት የነበረውን ልብስ ካወለቁለት በኋላ ለጊዜው ቀለል ባለ ልብስ ይሸፍኑታል፡፡ በእስልምና የሚችን ሀፍረተ ስጋ ማየት ሀራም(ክልክል) ነው፡፡ የእጆቹና የእግሮቹ መገጣጠሚያዎች ደርቀው እንዳይቀሩና በኋላ እንዳያስቸግሩ ያለሰልሷቸዋል፡፡ መጠነኛ ክብደት ያለው ነገርም ሆዱ ላይ ይጭኑበታል፡፡ እነዚህ በሙሉ የሚቹ ነፍስ ከስጋው እንደተለየች ወዲያውኑ በፍጥነት የሚፈጸሙ ተግባራት ናቸው፡፡ በእስልምና እምነት የሚች ነፍስ ከስጋው ተለይታ ሰውነቱ ከቀዘቀዘ በኋላ ሬሳውን ማንገላታት ክልክል ነው፡፡ አቶ አህመድ ኑር ያሲን የተባሉ መረጃ አቀባይ ‹‹ሰው የተወደደና የተከበረ ፍጡር ነው፡፡ በሕይወት እያለ አስፈላጊው ክብር ሊሰጠው ይገባል፡፡ በሞተም ጊዜ በተቻለ መጠን ጀናዛውን[9] በጨዋነትና ርህራሄ በተሞላበት አኳኋን እንድንይዝ አላህ(ሱ.ወ) ያዛል›› ብለዋል፡፡ የሚች ሆድ ላይ ቀላል ነገር የሚቀመጥበትንም ምክንያት ተጠይቀው ሲመልሱ ሆዱ እንዳይነፋና የሚወጡ ፈሳሽ

[9] ጀናዛ፡- የሞተ ሰው፣ ለመቀበር የተዘጋጀ ሬሳ ወይም አስከሬን ማለት ነው፡፡

ነገሮች (ነጃሳዎች) ካሉ እንዲወጡ ለማድረግ ሲባል የሚከናወን መሆኑን ገልጸዋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 17፣ 2004 ዓ.ም)፡፡

የተወሰኑ ሰዎች የማስተናበሩን ድርሻ በመውሰድ ወደ ኡለማዎች ዘንድ መልእክተኛ ይልካሉ፡፡ መርዶው እንዲነገራቸውና እንዲመጡ ያደርጋሉ፡፡ የተወሰኑ ሰዎችንም ወደገበያ በመላክ ለመግነዝ የሚሆን ሰባት ሜትር አቡጀዲ ጨርቅ እና ለለቅሶ ስነስርአቱ ማስፈጸሚያ የሚሆኑ እንደ ስንዴ ወይም ሽንብራ፣ ቡና፣ ስኳር እና የመሳሰሉ ነገሮች እንዲገዙ ያደርጋሉ፡፡ ወደእድሩ ሊቀመንበርም ሰው በመላክ (ሟች ወይም ቤተሰቡ የእድር አባል ከሆኑ) ጉዳዩን እንዲያውቅ ካደረጉ በኋላ አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶች ሁሉ ይከናወናሉ፡፡ መቀመጫ ወንበሮች ይጓጓዛሉ፤ ድንኳን ይተከላል፤ እንደሳህን፣ ብረትድስት፣ ጭልፋ ወዘተ. ያሉ ነገሮች ይመጣሉ፡፡ የተወሰነው ጀማ ደግሞ ዶማ፣ አካፋ፣ ማጭድ ገሶና የመሳሰሉ ነገሮችን ይዞ ወደቀብር ቦታ በመሄድ ጉድጓድ ይቆፍራል፡፡

ሰው ሲሞት ኡለማዎች የሚጠሩበትንና ሰባት ሜትር የመግነዝ ጨርቅ የሚገዛበትን ምክንያት የተጠየቁት ሀጂ ጁሃር ሳሊሀ የተባሉ መረጃ አቀባይ የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል፤ ‹‹አንድ ሰው በሚሞትበት ጊዜ ሟቹ በተወደደና ባመረ ሁኔታ ላይ ሆኖ ጌታውን እንዲገናኝ ለማዘጋጀት ከመቀበሩ በፊት የጀናዛ ሶላትና ዱዓ (ጸሎት) ይደረግለታል፡፡ ኡለማዎች የሚጠሩት ለዚሁ ነው - ሶላትና ዱዓ እንዲያደርጉለት ነው የሚጠሩት›› ብለዋል፡፡ የመግነዙን ጨርቅ በሚመለከትም የሚከተለውን ምላሽ ሰጥተዋል፤ ‹‹ሰባት ሜትር ጨርቅ የሚገዛው ለጀናዛው መጠቅለያ ነው፡፡ ሰባቱ ሜትር ጨርቅ ለሦስት ከተቆራረጠ በኋላ ጀናዛው ይከፈናል›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 19፣ 2004 ዓ.ም)፡፡

ሟች ከመሞቱ በፊት ለሰደቃዬ ብሎ ገንዘብ ወስኖ ከሆነ አስተባባሪዎቹ ሰዎችን መርጠው ወደገበያ በመላክ በሬ እንዲገዛ ያደርጋሉ፡፡ ለሰዶቃ ተብሎ የተወሰነ ነገር ሳይኖር እንዲሁ ገንዘብ ወጪ አድርጎ በሬ መግዛት፣ ሰደቃም ማድረግ እንደማይቻል ሼህ ሰይድ ቢላል በሚከተለው መንገድ አስረግጠው ገልፀዋል፤ ‹‹የሰደቃ ገንዘብ ንጹህ ገንዘብ መሆን አለበት፤ ሟች በኑዛዜው ውስጥ የወሰነው ገንዘብ ሊሆን ይገባዋል፡፡ ሟች ካልተናዘዘ ከእድሩም ቢሆን ሰደቃ ይደረግለታል እንጂ ከቲሞች (የሙት ልጆች) ገንዘብ ላይ ማንሳት አይፈቀድም፡፡

ሁሉም ሰው በየፊናው የሚጠበቅበትን ስራ ይሰራል፤ ሀላፊነቱን ይወጣል፡፡ ጀናዛውን የመከፈን ስራም ይቀጥላል፡፡

### 4.2.2.1 ስርአተ ግንዘት

ሟች በኑዛዜው ላይ የጠቀሳቸው ሰዎች ካሉ በእነርሱ አማካኝነት፣ አለበለዚያ ደግሞ ለሟች የቅርብ ዘመድ የሆኑ ሰዎች (ቢቻል የሟች አባት፣ አያት፣ ወንድ ልጅ ወዘተ.) አስቀድመው ራሳቸው ውዱእ በማድረግ ጀናዛውን አልጋ መሠል በሆነና ከፍ ባለ ነገር ላይ አስተኝተው የእጅና የእግር ጣቶቹን ጥፍር ይቆርጡለታል፤ የብብቱን ፀጉር ይነጩለታል ወይም ይላጩለታል፡፡ ከሆዱ ውስጥ የሚወጣ ቆሻሻ (ነጃሳ) ካለ ሆዱን በቀስታ ጫን ጫን እያሉ ቆሻሻው በደንብ እንዲወጣ በማድረግ ያጥቡታል፡፡ ጀናዛውን እንዳስፈላጊነቱ ሁለት ሶስት ጊዜ ሊያጥቡት ይችላሉ፡፡ ሼህ መሐመድ ሙሔ የተባሉ መረጃ አቀባይ እነዚህ ሁሉ ዝግጅቶች የሚደረጉት ጀናዛው በፈጣሪው ፊት ንፁህ ሆኖ በመቅረብ ውዱእ እንዲያደርግ በሚል መሆኑን ጠቅሰው ‹‹የወንድ ጀናዛ በወንዶች፣ የሴት ጀናዛ ደግሞ በሴቶች ይታጠባል፤ እንክብካቤ ይደረግለታል፡፡ ከሰባት ዓመት በታች ያሉ ልጆች በሚሞቱበት ጊዜ ደግሞ ነውር እንዳለባቸው ሆነው ስለማይቆጠሩ ማንኛውም ሰው ወንድ ሴት ሳይል ውዱእ ሳያደርግ ሊያጥባቸው ይችላል፡፡ በተጨማሪም ሚስት የባሏን፣ ባልም የሚስቱን ጀናዛ ማጠብ ይፈቀድላቸዋል›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 19 2004 ዓ.ም)፡፡

አቶ መሀመድ ሀሰን የተባሉ መረጃ አቀባይ ደግሞ ‹‹ጀናዛው በተቻለ መጠን በሟች የቅርብ ዘመድ ሊታጠብ ይገባዋል፡፡ ይህም የሚደረግበት ዋነኛ ምክንያት ዘመድ ከሆነ የሟቹን ሬሳ ሳይጠየፍ በደንብ ያጥበዋል፤ ምናልባት ጉድለቶች ካሉበትም እነዚያን ጉድለቶች በምስጢር ይጠብቅለታል ተብሎ ስለሚታመን ነው›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 19 2004 ዓ.ም)፡፡

ጀናዛው ንፁህ መሆኑን ካረጋገጡ በኋላ ውዱእ እንዲያደርግ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ መሰረት ሁለቱንም እጆቹን ሶስት ሶስት ጊዜ ያጥቧቸዋል፡፡ አፍንጫውንና አፉን ሶስት ሶስት ጊዜ ይወለውሏቸዋል፡፡ ፊቱንም ሶስት ጊዜ ያጥቡታል፡፡ ከዚያም መጀመሪያ የቀኝ ክንዱን ቀጥሎ የግራ ክንዱን ሶስት ሶስት ጊዜ ያጥቧቸዋል፡፡ በመቀጠል ጭንቅላቱንና ጆሮዎቹን ያብሷቸዋል፡፡ በመጨረሻም የቀኝ እግሩንና የግራ እግሩን በማከታተል ሶስት ሶስት ጊዜ ያጥቧቸዋል፡፡

በዚህ አኳኋን ውዱእ ካደረጉለት በኋላ ፊቱን ወደ ቂብላ በማዞር በቀኝ ጎኑ ያስተኙታል፡፡ ክንዶቹንም ጎኖቹ ላይ ያሳርፏቸዋል፡፡ አንዱን ረጅም ጨርቅ (ባለ ሰባት ሜትር ጨርቅ) ለሶስት በመክፈል ጀናዛውን ይከፍኑታል፡፡ በአንደኛው ጨርቅ በጭንቅላቱ በኩል ተረፍ እንዲል አድርገው ከወገብ በላይ ያለውን የሰውነት ክፍል ይጠቀልላሉ፡፡ በሁለተኛው ጨርቅ በእግሮቹ በኩል ተረፍ እንዲል አድርገው ከወገቡ በታች ያለውን የሰውነት ክፍል ይጠቀልላሉ፡፡ በሦስተኛው ጨርቅ ደግሞ መላ ሰውነቱን ይጠቀልላሉ፡፡ የመጠቅለያ ጨርቆችን ጫፍ በጀናዛው ግራ ጎን በኩል እንዲሆኑ ካደረጉ በኋላ ይቋጥሩታል ወይም በጨርቅ ያስሩታል፡፡ በጭንቅላቱ በኩል የሚኖረውን ትርፍ ጨርቅ ይቋጥሩታል ወይም ደግሞ ከአቡጀዲው በተተለተለ ጨርቅ ያስሩታል፡፡ በእግሮቹ በኩል የሚኖረውንም ትርፍ ጨርቅ በተመሳሳይ መንገድ ይቋጥሩታል ወይም በተተለተለው ጨርቅ ያስሩታል፡፡

ጀናዛው በሦስት ጨርቆች የሚከፈንበትን ምክንያት የተጠየቁት አቶ ጌታቸው ኢሳ የተባሉ መረጃ አቀባይ ሲመልሱ፤ ‹‹የአላህ መልእክተኛ አስቀድመው እንዲህ እንዲሆን ስላዘዙንና እርሳቸውንም (ነብዩ መሀመድን (ሶ.ዐ.ወ[10]) ) በሚመለከት በሀዲሱ ላይ ‹በሶስት ነጫጭ የጥጥ ጨርቆች ተከፈኑ (ተሸፈኑ)› የሚል ጽሁፍ ስላለ በነዚህ ሁለት ምክንያቶች ነው ጀናዛ በሦስት ጨርቆች የሚጠቀለለው›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 21፣ 2004 ዓ.ም)፡፡

ሼህ ሰይድ ቢላል ለተባሉት መረጃ አቀባይ ‹‹በጾታ፣ በእድሜ፣ በማህበራዊ ደረጃ ወዘተ. ሳቢያ የአከፋፈን ልዩነት ካለ ቢነግሩኝ›› ብዬ ላነሳሁላቸው ጥያቄ ሲመልሱ፤ ‹‹ወንዶች፣ ሴቶች፣ የሀይማኖት አባቶች ሁሉም በሶስት ጨርቆች ይከፈናሉ፡፡ ምናልባት ሰባት አመት ላልሞላቸው ልጆች አንድ ጨርቅ ብቻ የሚበቃቸው ከሆነ በአንድ ጨርቅ ሊከፈኑ ይችላሉ እንጂ ሁሉም በሦስት ጨርቅ ነው የሚከፈነው›› ብለዋል፡፡ ቋጠሮዎቹ በግራ በኩል እንዲሆኑ ለምን እንደተፈለገም ሲመልሱ፤ ‹‹ጀናዛ ጉድጓድ ውስጥ ሲቀበር በቀኝ ጎኑ በኩል እንዲተኛ ነው የሚደረገው፡፡ በቀኝ ጎኑ ከተኛ በኋላ የተጠቀለለባቸው ጨርቆች ቋጠሮዎቹ እንዲፈቱ ይደረጋሉ፡፡ ጀናዛውን ማገላበጥ ሳያስፈልግ የተቋጠሩትን ቋጠሮዎች በቀላሉ መፍታት እንዲቻል ነው በግራ በኩል የሚታሰሩት›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 17፣2004 ዓ.ም)፡፡

---

[10] ሶ.ዐ.ወ “ሶለሏ አለይሂ ወሰለም” ማለት ነው፣ ትርጉሙም ሰላም በእርሳቸው ላይ ይሁን እንደማለት ነው፡፡

ጀናዛውን ከጠቀለሉ በኋላ ሽቶ ይረጩበታል፤ ከዚያም ወደ መስጊድ በመውሰድ ጀናዛው ላይ ይሰግዳሉ፤ ሶላት ያደርጋሉ፡፡ ቁርአን ይቀራሉ፡፡ በሟች መኖሪያ ቤት አቅራቢያ መስጊድ ካለ ግን መጀመሪያውኑም ጀናዛውን የማጠብና የመከፈን ስራ በመስጊድ ውስጥ እንዲጠናቀቅ ነው የሚደረገው፡፡ በሟች መኖሪያ ቤት አካባቢ ከነአካቴው መስጊድ ከሌለ ደግሞ ጀናዛውን በቤት ውስጥ ከከፈኑ በኋላ ወደቀብሩ ቦታ በመውሰድ ሶላት ያደርጉለታል፡፡ ለጀናዛ የሚደረገው ሶላት ‹ሶላተል ጀናዛ› ይባላል፡፡ ሼህ ሙስጠፋ የተባሉ መረጃ አቀባይ ‹‹የሶላተል ጀናዛ (የጀናዛ ሶላት) አፈጻጸም ከመደበኛው ሶላት አፈጻጸም ብዙ የተለየ አይደለም፡፡ ለመደበኛው ሶላት የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎች - ውዱእ ማድረግ፣ ወደቂልባ መዞርና የመሳሰሉ ነገሮች ከተደረጉ በኋላ የሚሰገድ ስግደት ነው›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 21 2004 ዓ.ም)፡፡

በሶላተል ጀናዛ ጊዜ ኢማሙ በሬሳው ጭንቅላት በኩል ሆኖ (የሴት ሬሳ ከሆነ ደግሞ በመቀመጫዋ በኩል ሆኖ) ወደ ቂልባ ዞሮ በመቆም ይሰግዳል፡፡ ሌሎቹም በተመሳሳይ ረድፍ ሆነው ይሰግዳሉ፡፡ አራት ጊዜም ‹‹አላሁ አክበር›› ይላሉ፡፡ ከሶላት ስግደቱ በኋላ ዱዓ (ፀሎት) ያደርጋሉ፡፡ ሟች ተጓዥ መንገደኛ ነውና በሄደበት መልካሙ ሁሉ እንዲገጥመው ይማጸኑለታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) የሟቹን ሀጢያት ይቅር እንዲለው፣ በእሳት ከመቀጣት እንዲያድነው ወደ ጀነትም እንዲያስገባው ይለምኑለታል፡፡ ጥሩ ቦታና ሰፊ ማረፊያ እንዲያገኝ ይጸልዩለታል፡፡ በዚህ ምድር ላይ ከነበረው ቤት የተሻለ ሰፊና ምቹ ቤት እንዲያጋጥመው፣ በዚህ ምድር ላይ ከነበረችው ሚስት የተሻለችና ጥሩ የሆነች ሚስት እንዲያገኝ፣ በዚህ ምድር ላይ ከነበረው ቤተሰብ የበለጠ ቤተሰብ እንዲያፈራ አጥብቀው ይጸልዩለታል፤ ይማጸኑለታል፡፡

ዱዓው ለሞተው ብቻ ሳይሆን በህይወት ላሉ ሰዎችም የሚደረግ ጸሎት ነው፡፡ ሠዎች የበደሉትን በደል አላህ ይቅር ይላቸው ዘንድ ይለምናሉ፡፡ ሙስሊሞች በህይወት ዘመናቸው ሁሉ በእምነታቸው (በሀይማኖታቸው) ጸንተው እንዲኖሩ ይማጸናሉ፡፡ የእነርሱን (የራሳቸውን) ዋጋም እንዳያጠፉባቸው ይለምኑታል፤ ለጸለዩት ጸሎት፣ ለሰገዱት ስግደት ምንዳቸውን ይጠይቁታል፡፡

ጀናዛው እየተገነዘና ሶላት እየተሰገደለት ባለበት ሰዓት ሁሉ ቤተሰቡና ወዳጅ ዘመዶቹ በታዳሚው መ ሀል መለስ ቀለስ እያሉ ያለ ቅሳሉ፡፡ ታዳሚያንም ለሟች እንዳላቸው ቅርበትና ወዳጅነት በመጮህና በማንጎራጎር ሃዘናቸውን ይገልጻሉ፤ ያለቅሳሉ፤ ያነባሉ፡፡

ይሁን እንጂ ደረት እየደቁ እየወደቁና እየተነሱ ማልቀስ የተፈቀደ አይደለም፡፡ ይህ በሙስሊሞች ዘንድ የተከለከለ ነው፡፡ በዚህ ዙሪያ ሀሳብ ያካፈሉኝ አቶ ኢብራሂም አደም የተባሉ መረጃ አቀባይ ‹‹በእስልምና ደረት እየደቁ፣ ፊት እየነጩ፣ እየወደቁና እየተነሱ ማልቀስ የተከለከለ ነው፤ አይፈቀድም፡፡ የሟችን ፎቶና ልብስ ይዞ ግጥም እየገጠሙ ማልቀስም አይቻልም›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ ጥር 20፣ 2004 ዓ.ም)፡፡

ሀዘንተኞቹ ረጋ ባለ ሁኔታ እየጮኹ ያለቅሳሉ እንጂ እንደ ክርስትና እምነት ተከታዮች ክብ ሰርተው ‹‹ዋይ ዋይ›› አይሉም፤ ደረታቸውን አይደቁም፡፡ አይወድቁም አይነሱምም፡፡ ዘግይተው የሚደርሱ ወዳጅ ዘመዶች ካሉም በተለይም ሴቶች በዚሁ አግባብ ከቤተሰቡ ጋር ትከሻ ለትከሻ በመተቃቀፍ ወይም እጅ ለእጅ ተጨባብጠው በመሳሳም (እጃቻቸውን ነው የሚሳሳሙት - ከተጨባበጡ በኋላ አንደኛው የሌላኛውን እጅ ይስማል) በማልቀስና በማንባት ሀዘናቸውን ሊገልጹ ይችላሉ እንጂ አብዝቶ በመጮኽ፣ ልብስን በመቅደድና በመሳሰሉት መንገዶች ማልቀስ አይፈቀድላቸውም፤ አያለቅሱም፡፡ ‹‹አላህ ፈቅዶ ፈጠረው፤ አላህ ወዶ ወሰደው›› ጽኑ እምነታቸው ይመስላል፡፡ ‹‹የራሱን ፍጡር ለምን ወሰድከው ብሎ ፈቃዱን መጋፋት አይቻልም›› ነው ያሉኝ ሼህ መሀመድ ሙሄ የተባሉት መረጃ አቀባይ፡፡

ለጀናዛው የሚደረገው ሰላትና ዱዓ እንዳበቃ ወደ ቀብር ቦታ ጉዞ ይደረጋል፡፡ አብዛኞቹ ወንዶች ከሬሳው ጋር ወደቀብር ቦታ ሲሄዱ የተወሰኑ ወንዶች ከሴቶች ጋር በቤት ውስጥ የሚሰሩ ስራዎችን ይሰራሉ፡፡ በሬ ተገዝቶ ከሆነ ልምድ ያላቸው ወንዶች በመረዳዳት በሬውን ያርዳሉ፡፡ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ እንደተመለከትነው ጀናዛው የበሬውን ደም እንዲሻገር አይደረግም፡፡ ይልቁንም ሁሉም በመረዳዳትና በመተባበር ለለቀስተኛው የሚሆን ምግብ ያዘጋጃሉ፡፡ እንጀራው፣ ስጋው፣ ቆሎው ወይም ንፍሮው፣ ቡናው ወዘተ. ይዘገጃጃል፡፡

### 4.2.2.2 የጉዞ ስነስርአት

ሟች በሞተበት ቤት አቅራቢያ መስጊድ ካለ ሰላት መስገዱ፣ ዐሎት (ዱዓ) መጸለዩ እና ቁርዓን መቅራቱ እንደተጠናቀቀ ጀናዛው ወደ መቃብር ቦታ ይወሰዳል፡፡ በሟች መኖሪያ ቤት አቅራቢያ መ ስጊድ ከሌለ ደግሞ የ ማጠቡንና የመከፈኑን ሥራ በቤት ውስጥ ከአጠናቀቁ በኋላ ወደ መቃብር ቦታ ይወስዱታል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ከቀብር በፊት መከናወን ያለባቸው ነገሮች ከተከናወኑ በኋላ ጀናዛው እንዲቆይ አይደረግም፤ በፍጥነት ተወስዶ ይቀበራል፡፡ ሼህ ሰይድ ቢላል የተባሉት መረጃ አቀባይ

አንዴ ሀመምተኛው መሞቱ ከተረጋገጠ በኋላ በተቻለ መጠን ሬሳው በቶሎ ይታጠባል፣ ይከፈናል፤ ይቀበራል፡፡ ሬሳው ቤት ውስጥ ብዙ እንዲቆይ አይደረግም፡፡ የአላህ መልእክተኛ (ሰ.0.ወ) ‹ሟች መልካም ሰው ከሆነ ለርሱ መልካም ወደሆነው ነገር ማቻኮል አለባችሁ፡፡ ሟች ክፉ ሰው ከሆነም ከራሳችሁ ላይ መገላገል ያለባቸው ክፉ ሸክም ስለሆነ ሬሳውን ቶሎ ቅበሩ› ብለው ስላዘዙን ሬሳን በተቻለ መጠን ወዲያውኑ ነው የምንቀብረው ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 17፣2004 ዓ.ም)፡፡

ጀናዛውን በጨርቅ ከጠቀለሉና በአልጋ መሰል ነገር ላይ ካደረጉ በኋላ ከስር ለሸክም አመቺ የሆኑ ሁለት እንጨቶችን በማድረግ ለአራት ተሸክመው ይወስዱታል፡፡ ሙስሊሞች እንደ ክርስቲያኖች ጀናዛን በሬሳ ሳጥን ውስጥ አይከቱም፤ በሬሳ ሳጥን አይቀብሩም፡፡ ጀናዛን መሸከም ከአላህ ዘንድ ምንዳን ያስገኛል የሚል እምነት ስላለ ታዳሚያን በመረባረብ ይሸከማሉ፤ ይተጋገዛሉ፡፡ መኪና ካለም በመኪና ይወስዱታል፡፡

ጀናዛውን የሚሸከሙትም ሆኑ አጅበው የሚወስዱት ወንዶች ናቸው፡፡ ጀናዛውን የተሸከሙት ሰዎች ከፊት ቀደም ብለው በእርጋታ ይሄዳሉ፡፡ የሟች ቤተሰብ፣ ወዳጆችና ዘመዶች ከጀናዛው በኋላ ይሆናሉ፡፡ የሀይማኖት አባቶችና ሌሎች ታዳሚያንም ከኋላ ሆነው ጀናዛውን አጅበው ይሄዳሉ፡፡ ጀናዛ ከፊት እንዲሆን የሚደረግበትን ምክንያት የተጠየቁት አቶ አህመድ ኑር ያሲን የተባሉት መረጃ አቀባይ ሲመልሱ፤‹‹ሌሎች ሰዎች በሙሉ ከኋላ ሆነው ጀናዛው ከፊት እንዲሆን የሚደረገው ከፊታችን ሞት እንዳለ፣ እኛንም ሞት እንደሚጠብቀን ለማመላከት ነው›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 17፣2004 ዓ.ም)፡፡ ሴቶቹ ከለቅሶው ቤት የተወሰነ ርቀት ያህል (በግምት እስከ መቶ ሜትር ርቀት) በማልቀስ ከሸኙ በኋላ ይመለሳሉ እንጂ ወደ ቀብር ቦታ አብረው ሄደው አይቀብሩም፤አያቃብሩም፡፡ ሴቶች ወደ መቃብር ቦታ ለምን እንደማይሄዱና እንደማይቀብሩ የተጠየቁት አቶ አህመድ ኑር ያሲን የተባሉት መረጃ አቀባይ ሲመልሱ ‹‹ሴቶች በተፈጥሮ ሩህሩህ ስለሆኑና በሐዘን ብዛት ራሳቸውን ስተው ወደ መቀበሪያ ጉድጓድ ውስጥ ልግባ ስለሚሉ እንዲዘይሩ አይፈቀድላቸውም›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 17፣2004 ዓ.ም)፡፡

ጀናዛው መቃብር ቦታ ላይ ከደረሰ በኋላ በቅርብ ቦታ መስጊድ ባለመኖሩ ምክንያት ሶላት ካልተሰገደለት ከመቀበሩ በፊት ሶላት ይሰገድለታል፤ ቁርዓን ይቀራለታል፡፡ በሟች አቅራቢያ መስጊድ በመኖሩ ምክንያት ሰላት ተሰግዶለት ከሆነም እንደ ሁኔታው መቃብር ቦታ ላይም እንደገና ሶላት ሊሰገድለት ይችላል፡፡ ከሶላት በኋላ ዱዓ ይደረግለታል፡፡ ቁርአን ይቀራለታል፤ ይፀለይለታል፡፡ ሟች በመቃብር ውስጥ ለሚጠየቃቸው ጥያቄዎች

ትክክለኛና የማያወላውሉ ምላሾችን ይሥጥ ዘንድ ይለምኑለታል፡፡ አላህ (ሱ.ወ) ለሟች ይቅርታ እንዲያደርግለት ይማጸኑለታል፡፡

ሐጂ ጁሐር ሳሊህ እና ሌሎችም እንደገለጹት አንድ ሰው ሞቶ ተቀበረ ማለት ከሁሉ ነገር አረፈ ወይም እረፍት አገኘ ማለት አይደለም፡፡ ገና ወደ መቃብር እንደገባ መላዕክት ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን ይጠይቁታል፡፡ በመቃብር ውስጥ ከሚጠየቃቸው ጥያቄዎች መካከል ‹‹ጌታህ ማነው?››፣ ‹‹ዲንህ[11] ምንድን ነው?››፣ ‹‹ወደ እናንተ የተላከው ሰውዬ ማነው?›› የሚሉት ይገኙበታል፡፡ ሟቹ በመቃብር ውስጥ ለሚጠየቃቸው ለነዚህና እነዚህን ለመሳሰሉት ጥያቄዎች ትክክለኛና የማያወላውል ምላሽ እንዲሰጥና አላህ (ሱ.ወ) ወደ ጀነት እንዲያስገባው አጥብቀው ይለምኑለታል፤ አጥብቀው ይፀልዩለታል፡፡ ዱዓው ከተጠናቀቀ በኋላ የቀብር ስነስርአት ይፈፀማል፡፡

### 4.2.2.3 ስርዓተ ቀብር

ሶላቱና ዱዓው እንደተጠናቀቀ የሟች ቤተሰቦችና ወዳጅ ዘመዶች (ወንዶች ብቻ መሆናቸውን ያስታውሷል) ተላቅሰው ጀናዛው እንዲቀበር ይደረጋል፡፡ ጀናዛው የሚቀበርበት ጉድጓድ አቆፋፈሩ ለየት ያለ ነው፡፡ በግምት ከአንድ ሜትር እስከ አንድ ሜትር ከግማሽ የሚደርስ ጥልቀት ያለው ጉድጓድ ወደ ታች ይቆፈራል፡፡ ከዚያም ከጉድጓዱ ወለል ትንሽ ከፍ በማለት ወደ ጎን በሰሜን አቅጣጫ አስከሬኑን ሊያስተኛ የሚችል ዋሻ መሰል ነገር ይቆፈራል፡፡ ይህ ወደ ጎን የሚቆፈር ዋሻ መሰል ጉድጓድ ‹ለሃድ› ይባላል፡፡ ለሃዱ ጀናዛውን ቁጭ ለማለት የሚያስችል እንዲሆን ተደርጎ ይቆፈራል፡፡ የመቃብሩ ጉድጓድ (ቀደም ብዬ እንደጠቆምኩት) ጀናዛው ወደ ቀብር ቦታ ከመምጣቱ አስቀድሞ የሚዘጋጅ ነው፡፡

ጀናዛውን ለመቅበር በቅድሚያ የተወሰኑ ሠዎች (አንድ ሁለት ሰዎች) ከጉድጓዱ ወለል ላይ እንዲቆሙ ይደረጋል፡፡ ከዚያም ከላይ ያሉ ሰዎች ጀናዛውን ከአልጋው ላይ አንስተው ‹‹ቢስሚ- ላሂ ወዐላ ሱን ነቲ ረሱሊ ላህ››[12] በማለት ጉድጓዱ ውስጥ ላሉት ሰዎች

---

[11] ዲን የሚለው የአረብኛ ቃል ሲሆን ትርጉሙም ሀይማኖት ማለት እንደሆነ ሼህ ሰይድ ቢላል ተናግረዋል፡፡

[12] ትርጉሙ ‹‹በአላህ (ሱ.ወ) ስም እጀምራለሁ፣ በመልዕክተኛውም ሱንና መሰረት እፈፅማለሁ›› ማለት እንደሆነ ሼህ ሰይድ ቢላል ተናግረዋል፡፡

ያቀብሏቸዋል፡፡ ጉድጓድ ውስጥ ያሉ ሰዎችም ፊቱን ወደ ሰሜን (ወደ ቂልባ) በማዞር ለሃዱ ውስጥ ያስገቡታል፡፡ ከዚያም በቀኝ ጎኑ እንዲተኛ ካደረጉ በኋላ ሲከፈን የታሰሩትን ቋጠሮዎች ይፈቷቸዋል፡፡ በዚህ አኳኋን ከቀበሩት በኋላ የለሃዱን አፍ በእንጨትና በድንጋይ ደፍነው በጭቃ ይመርጉታል፡፡ ከዚያም ከጉድጓዱ ውስጥ ወጥተው አፈሩን ወደነበረበት በመመለስ ጉድጓዱን ይሞሉታል፣ ይደፍኑታል፡፡ በመጨረሻም ርጥብ ቅጠል ከነቅርንጫፉ ቆርጠው በተመለሰው አፈር ላይ ይተክላሉ፡፡ ዙሪያውንም ድንጋይ ይደረድራሉ፡፡

ለሃድ የሚቆፈርበትን፣ ጀናዛው ከተቀበረ በኋላም ለሀዱ በእንጨትና በድንጋይ ተደፍኖ በጭቃ የሚመረግበትን፣ ጀናዛው ሲቀበር ወደ ሰሜን (ወደ ቂልባ) እንዲዞር የሚደረግበትን እንዲሁም ሲከፈን የታሰሩት ቋጠሮዎች ሲቀበር የሚፈቱበትን ምክንያት የጠየቅኋቸው መረጃ አቀባዮች የሚከተሉትን ምላሾች ሰጥተውኛል፡፡

ሼህ ሰይድ ቢላል የተባሉት መረጃ አቀባይ ‹‹ለሃድ የሚቆፈረው ጀናዛው ከተቀበረ በኋላም በእንጨትና በድንጋይ የሚደፈነውና በጭቃ የሚመረገው ጀናዛው አፈር እንዳያገኘው ነው፡፡ የሞተን ሰው በጨዋነትና በርህራሄ እንድንይዝ አላህ (ሱ.ወ) ስለሚያዘን ነው›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 17፣2004 ዓ.ም)፡፡ አቶ አህመድ ኑር ያሲን የተባሉት መረጃ አቀባይ ደግሞ ‹‹ጀናዛ ሲቀበር ወደ ሰሜን (ወደቂልባ) ዞሮ መሆን አለበት፡፡ ወደ ሰሜን ዞሮ የሚቀበርበትም ምክንያት ካዕባ (መካ መዲና) በሰሜን በኩል ስላለች ነው›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 17፣2004 ዓ.ም)፡፡ ሀጂ ጁሀር ሳሊህ የተባሉት መረጃ አቀባይ ደግሞ ለሃድ የሚዘጋጅበትን እና ጀናዛው ሲከፈን የተቋጠሩ ቋጠሮዎች ሲቀበር የሚፈቱበትን ምክንያት አንድ ላይ በማስተሳሰር የሚከተለውን መልስ ሰጥተዋል፣ ‹‹ለሃድ የሚዘጋጀው ለጀናዛው ጥንቃቄና ለክብሩ ሲባል ነው፡፡ ጀናዛው እንደተቀበረ በመላኢኮች ጥያቄ ይጠየቃል፡፡ የሚጠየቃቸውን ጥያቄዎች ቁጭ ብሎ መመለስ እንዲችል ነው እነዚህ ነገሮች የሚደረጉት፡፡ ቋጠሮዎቹ የሚፈቱትም ጀናዛው ዘና እንዲል ነው›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 19፣2004 ዓ.ም)፡፡

መቃብሩ ላይ ዕፅዋት የሚተከልበትን ምክንያት የተጠየቁት ሼህ መሀመድ ሙሂ የተባሉት መረጃ አቀባይ ሲመልሱ ‹‹ምናልባት ሟቹ በህይወት ዘመኑ ብዙ ሐጢያት ያለበት እንደሆነ፣ በፀሎት ጊዜም የስነስርዓት ግድፈት ከነበረበት ለምሳሌ ጡሃራ ሳይሆን (ሳይታጠብ - ሳይፀዳ ማለት እንደሆነ ነግረውኛል) ሶላት ሰግዶ ከነበረ፣ ሱሪውን ሽንት

ነክቶት እያለ ሰግዶ ከነበረ ወዘተ. በነዚህ ስህተቶች ጥያቄ ስለሚቀርብለት በተተከለው ዛፍ ራህመት እዝነት ያደርግለታል ተብሎ ስለሚታመን ነው ዕፅዋት የሚተከለው›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 19፣2004 ዓ.ም)፡፡ እኒሁ መረጃ አቀባይ መቃብር ላይ ሐውልት እንደማይሰራና በዚያ ፋንታ በመቃብሩ ዙሪያ ድንጋይ የሚደረገውም ጎርፍ በቀላሉ አፈሩን አጥቦ እንዳይወስደው መሆኑን ገልፀዋል፡፡

## 4.3. ድህረ ቀብር ክዋኔ

‹‹ጊዜ ሞት ክዋኔ›› የሚል ርዕስ በተሰጠው በቀደመው ክፍል የአንድ ሰው ነፍስ ከስጋው ከተለየችበት ቅጽበት ጀምሮ ግብዓተ መሬቱ እስከሚፈፀምበት ጊዜ ድረስ የሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች የሚያከናውኗቸውን ክንውኖች ተመልክተናል፡፡ በዚህኛው ክፍል ከግብዓተ መሬት መጠናቀቅ በኋላ የሚኖሩ ስነስርዓቶችን እንመለከታለን፡፡ የአንድን ሰው የቀብር ስነስርአት ፍጻሜ ተከትሎ የሁለቱም ሐይማኖት ተከታዮች የሚያከናውኗቸው ስነስርአቶች አሉ፡፡ እነዚህ ስነስርአቶች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፡፡

### 4.3.1 የክርስትና እምነት ተከታዮች ድህረ ቀብር ክዋኔ

የሟቹ ግብዓተ መሬት እንደተጠናቀቀ ካህናትና አንዳንድ ሽማግሌዎች ለቀስተኞቹን በመምከር፣ በመቆጣትና በመገሰጽ ዝም እንዲሉ ካደረጉ በኋላ ወደ አውደ ምህረቱ እንዲሄዱ ያደርጓቸዋል፡፡ ለቀስተኞቹ በሙሉ በአውደ ምህረቱ ፊት ለፊት ይሰበሰባሉ፡፡ ካህናቱ ከአውደ ምህረቱ ላይ ይቆማሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦችና የቅርብ ዘመዶች ደግሞ ከአውደ ምህረቱ ታች በካህናቱ ፊት ለፊት ይሆናሉ፡፡ ሌሎች ታዳሚያንም ለሐዘንተኞች እንዳላቸው ቅርበት ከጎንና ጎን እንዲሁም ከኋላ ሆነው ይቆማሉ፡፡ በዚህ መልክ ሰብሰብ ብለው ከቆሙ በኋላ ካህናቱ ለቀስተኞችን ዝም እንዲሉ በመጠየቅ የሟች የህይወት ታሪክ የሚነበብለት ከሆነ የህይወት ታሪኩን የሚያነበው ሰው ወደ አውደ ምህረቱ ወጥቶ እንዲያነብ ይጠይቃሉ፡፡ የሟችን የህይወት ታሪክ የሚያነበውም ሰው ካህናቱ ወደቆሙበት አውደ ምህረት በመሄድና ፊቱን ወደ ሕዝቡ በማድረግ የሟቹን የህይወት ታሪክ ጮኽ ብሎ ያነብባል፡፡ የሚያነበው የህይወት ታሪክ ሟች ከማን፣ የት እና መቼ እንደተወለደ፣ እንዴት እንዳደገ፣ የሥንት ልጆች አባት እንደሆነ፣ ምን ምን መልካም ሥራዎችን እንደሰራ፣ ምን ያህል አመት እንደኖረ፣ መቼ እንደሞተ የሚያትት ነው የሚሆነው፡፡



ምስል 9 - ለቀስተኞች የሚችን የህይወት ታሪክ ሲያዳምጡ

የሚች የህይወት ታሪክ እንደተነበበ ከካህናቱ መካከል አንዳቸው ሀዘንተኞቹን የሚያጽናናና የሚያረጋጋ ትምህርት ይሰጣሉ፡፡ ሀዘንተኞቹ አብዝተው በማልቀስ ራሳቸውን መጉዳት እንደሌለባቸው ይመክራሉ፣ ይገስጻሉ፡፡ ከሞት በኋላ ሌላ ህይወት እንዳለም ይሰብካሉ፡፡ሰው በህይወት ዘመኑ መልካም ከሰራ ‹ገነት› ከምትባለው መልካም ቦታ እንደሚገባ፣ መጥፎ ከሰራ ደግሞ ‹ገሀነም› ወደሚባለው መጥፎ ቦታ እንደሚጣል በማስታወስ እድምተኞቹ ለሚች ነፍስ እንዲማጸኑ ይጠይቃሉ፣ ‹‹ ‹ነፍስ ይማር› በሉ›› ይላሉ፡፡ እድምተኞችም ሦስት ጊዜ ‹‹ነፍስ ይማር›› በማለት ፈጣሪ የሚችን ነፍስ እንዲምራት ይማጸናሉ፡፡ በመጨረሻም ካህናቱ የማሳረጊያ ጸሎት ያደርጋሉ፡፡ ከጸሎት በኋላ ሀዘንተኞቹ ከታዳሚው ትንሽ ወደፊት ለየት ብለው ፊታቸውን ወደህዝቡ አድርገው በመቆም ተሰናብተው መሄድ የሚፈልጉ ሰዎችን ያሰናብታሉ፡፡ መሄድ የሚፈልግ ግለሰብ ወደሀዘንተኞቹ ፊት ለፊት በመምጣትና ከአንገቱ ጎንበስ በማለት ‹‹እግዚያብሔር ያጽናችሁ›› እያለ ይሄዳል፡፡ ይህ ስነስርአት ለሁለቱም ወገኖች ትርጉም ያለው ነው፡፡ ግለሰቡ አንድም ሀዘንተኞቹን ያጽናናበታል፣ አንድም በለቅሶው ስነስርአት ላይ መገኘቱን ያሳውቅበታል፡፡ ሀዘንተኞቹ ደግሞ በለቅሶአቸው ላይ የተገኙ ሰዎችን ያውቁበታል፡፡


ሀዘንተኞቹ የሚሰናበቱትን ሰዎች ካሰናበቱ በኋላ ወደቤታቸው ጉዞ ይጀምራሉ፡፡ ጉዞው የራሱ ስነስርአት ያለው ነው፡፡ ሴቶችና ወንዶች ተቀላቅለው አይሄዱም፡፡ ሴት

ለቀስተኞች በሴት ሀዘንተኞች መሪነት ከፊት ቀድመው ሲሄዱ ወንድ ለቀስተኞች ደግሞ በወንድ ሀዘንተኞች መሪነት ከኋላ ይከተላሉ፡፡ ይህ የመልስ ጉዞ ከሞላ ጎደል የተረጋጋ ነው፡፡ ከውይይት በስተቀር ለቅሶና ጩኸት አይኖርም፡፡ ለምን ቢሉ ብዙዎች ሸክማቸው ይቀልላቸዋል፤ በፈሰሰ እንባቸው ምትክም ሰላምና መረጋጋት ይሰማቸዋልና ነው፡፡

ሴት ለቀስተኞች ከፊት፣ ወንድ ለቀስተኞች ደግሞ ከኋላ የሚሆኑበትን ምክንያት የጠየቅኋቸው መረጃ አቀባዮች ‹‹ባህል ነው›› የሚል ቁርጥ ያለ መልስ ሰጥተውኛል (አቶ አንዳርጌ ተረፈ፤ ወ/ሮ አበበች መኮንን) ፡፡

ሀዘንተኞቹ ከታዳሚያን ፊት ሆነው የሚሄዱበትን ምክንያት የጠየቅኋቸው መረጃ አቀባዮች ደግሞ የሚከተሉትን ምላሾች ሰጥተውኛል፡፡ ለምሳሌ አቶ ዳኛቸው ቢልልኝ የተባሉት መረጃ አቀባይ ‹‹እንደሙሽራ እነሱ ከፊት ሆነው ሌሎች ለቀስተኞች ከኋላ ሆነው ማጀብ ስላለባቸው ነው›› ሲሉ፣ ወ/ሮ የትምወርቅ አያሌው የተባሉት መረጃ አቀባይ ደግሞ ‹‹በየመንገዱ ላይ የሚሰናበቱ ሰዎች በቀላሉ እንዲያገኟቸውና መሰናበት እንዲችሉ ነው›› ብለዋል፡፡

ሀዘንተኞች በየተወሰነ ርቀት ላይ ወይም መስቀለኛ መንገድ ላይ በደረሱ ቁጥር (መስቀለኛ መንገድ ካለ) እየቆሙ ወደየጉዳያቸው መሄድ የሚፈልጉ ሰዎችን ያሰናብታሉ፡፡ እቤት ድረስ አብረው መሄድ የማይችሉ (የማይፈልጉ) ወይም ጉዳይ ያላቸው ሰዎች ወደሀዘንተኞቹ ፊት እየቀረቡና ‹‹እግዚአብሔር ያጽናችሁ እያሉ›› ከለቀስተኛው ይለያሉ፤ ወደየጉዳያቸው ይሄዳሉ፡፡



ምስል 10 - ወንዶች ከሴቶች ነጠል ብለው ለብቻቸው በመሆን ወደቤት ሲመለሱ

ለቀስተኞቹ በዚህ አኳኋን ወደ ለቅሶው ቤት ተመልሰው ድንኳን ውስጥ ከመግባታቸው በፊት እጆቻቸውን ይታጠባሉ፡፡ ለማስታጠብ የተመደቡ ሰዎች ከድንኳኑ ውጭ ውሃ አዘጋጅተው በመጠበቅ እጅ ያስታጥባሉ፡፡ ለቀስተኞቹ እጆቻቸውን ከታጠቡ በኋላ ጣቶቻቸው ላይ የቀሩትን የውሃ እንጥፍጣፊዎች በጆሮዎቻቸው በኩል ወደ ኋላቸው ይረጫሉ፡፡ የዚህን ስነስርአት ትርጉም የጠየቅኋቸው ወ/ሮ አበበች መኮንን የተባሉት መረጃ አቀባይ ሲመልሱ፤ ‹‹የመታጠቡ ስነስርአት ለንጽህና ነው፡፡ እንኳን በለቅሶ ጊዜ በሌላም ጊዜ ቢሆን እጃችን ብዙ ነገሮችን ስለሚነካካ መታጠብ አለብን፡፡ ሰዎች ከታጠቡ በኋላ ውሃውን ወደኋላቸው የሚረጩት ሐዘንን ያርቀው ለማለት ነው›› ብለዋል፡፡ መጋቢ አእላፍ ጥበቡ የሽታ የተባሉት መረጃ አቀባይ ደግሞ የመታጠቡ ስነስርአት መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሰረት እንዳለው ይገልጻሉ፤ ‹‹በኦሪት ዘሌዋውያን ‹በድን የነካ ሰው እስከማታ የረከሰ ነው፤ ገላውን በውሀ ይታጠብ› የሚለውን ለማስታወስ ነው ሬሳውን የቀበሩትም ሆኑ ሌሎች ለቀስተኞችም በውሀ የሚታጠቡት›› ብለዋል፡፡ ውሀን ወደኋላ የመርጨት ጉዳይ ግን በባህል የሚደረግ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡



ምስል 11 - የእጅ መታጠብ ስነስርአት

ሴቶቹም ወንዶቹም እጆቻቸውን እየታጠቡ ወደ ድንኳኑ ውስጥ ገብተው ይቀመጣሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦች በተለይም ሴቶቹ ከድንኳኑ ውስጥ በአንደኛው ጥግ ለነሱ ተብሎ በተነጠፈ ፍራሽ ላይ ይቀመጣሉ፡፡ የቅርብ ወዳጆቻቸውና ዘመዶቻቸው ደግሞ በእነርሱ ዙሪያ ይሆናሉ፡፡ ሌሎች ሴቶችም እዚያው አካባቢ እጅብ ብለው ይቀመጣሉ፡፡ ወንዶችም እንደዚሁ ለብቻቸው ይሆናሉ፡፡ ይሄ በጾታ መሳሳብ ምክንያት የሚፈጠር እንጂ ግዴታ አይደለም፡፡ እንደሁኔታው ወንዶችና ሴቶች ተቀላቅለው የሚቀመጡበት አጋጣሚ ሊኖር ይችላል፡፡

ለቀስተኞቹ ቦታ ቦታቸውን ከያዙ በኋላ ቡና ይፈላላቸዋል፡፡ ቤት ውስጥ የተዘጋጀው ምግብ ይቀርብላቸዋል፡፡ የሚቀርብላቸው ምግብ እንደሟቹ ቤተሰብ አቅምና እንደተቀበረበት ቀን የሚለያይ ነው፡፡ ሟቹ የተቀበረው በፆም ቀን ከሆነ የሚቀርበውም ምግብ የጾም(የእንስሳት ተዋጽኦ የሌለበት) ነው የሚሆነው፡፡ እንደ ቤተሰቡ አቅም ቆሎ ወይም ንፍሮ ብቻ ወይም ደግሞ እንጀራ በፆም ወጥ ሊቀርብ ይችላል፡፡ ለቀስተኞች ወደ ቤት የተመለሱት ከ6 ሰዓት በፊት ከሆነ ምንም ዓይነት ምግብ ላይቀርብም ይችላል፡፡ በአብዛኛው ምግብ የሚቀርበው ከዚህ ሰዓት በኋላ ነው፡፡ ቀብሩ በፍስክ ቀን የተከናወነ ከሆነ ደግሞ ንፍሮው ወይም ቆሎው እንደተጠበቀ ሆኖ እንጀራና ሥጋም በተጨማሪነት ሊቀርብ ይችላል፡፡ የሚቀርበው ንፍሮ ወይም ቆሎ ከሆነ የሚያስተናብሩ ሰዎች በሳህን በሳህን ይዘው እየዞሩ ለሁሉም ካስዘገኑ በኋላ አልፎ አልፎ በታዳሚዎች ፊት ያስቀምጣሉ፡፡

ምግብ እንዲቀርብ የሚደረገው በተለያዩ ምክንያቶች ነው፡፡ አንደኛው ምክንያት ምግብ የሃዘን ማብረጃ ወይም እርም ማውጫ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡ ሌላኛው ምክንያት ደግሞ ለቀስተኛው ከተመገበ በኋላ ‹‹የሟችን ነፍስ ይማር›› እያለ በሚያደርገው ምርቃት ‹‹የሟች ነፍስ ገነት ትገባለች›› ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ በቀብር እለት የሚቀርበው ምግብ ማህበራዊ መልዕክትም አለው፡፡ ይኸውም የሟች ቤተሰቦች በኢኮኖሚ የተሻሉ መሆናቸውን ለማሳየት የሚጠቀሙበት መንገድ መሆኑ ነው፡፡ በተለይ ከብት አርደው ሥጋ ያበሉ ከሆነ ‹‹ከብት አርደው ያበሉ፤ የለጋስ ዘሮች›› ተብለው ስማቸው እንዲጠራና እንዲወደሱ የሚያደርጉበት መንገድ ነው፡፡ አንዳንዴ ደግሞ ማህበራዊ ተጽዕኖን በመፍራት የሚደረግ ሊሆን ይችላል፡፡ ይኸውም የሟች ቤተሰቦች አቅም የሚፈቅድ ሆኖ እያለ በቀብር ስነስርአቱ እለት አርደው ባያበሉ በማህበረሰቡ ነቀፌታ ሊደርስብን ይችላል ብለው በመስጋት ከብት አርደው ሊያበሉ ይችላሉ፡፡

ለቅሶው በሐዘንተኞቹ ላይ የሚፈጥረውን ኢኮኖሚያዊ ጫና ለማቃለል ዕድሮች የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይደለም፡፡ በተለይ ‹‹የሰፈር እድር›› ወይም ‹‹የሴት ዕድር›› እየተባሉ የሚጠሩ ዕድሮች ኢኮኖሚያዊ ድጋፍ በማድረግና ማህበራዊ ግንኙነትን በማጠናከር ረገድ ያላቸው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ እነዚህኛዎቹ እድሮች በአብዛኛው በሰፈር በሰፈር ተከፋፍለው የሚቋቋሙና ሴቶች ብቻ የሚሳተፉባቸው ናቸው፡፡ አንድ ሰው ሐዘን ሲደርስበት ለወጥ የሚሆኑ ነገሮችን (ሽሮ፣ ዘይት፣ በርበሬ ወዘተ.)፣ እንጀራ፣ የማብሰያ እንጨትና የመሳሰሉ ነገሮችን በማዋጣትና ምግብ በማዘጋጀት ለቅሶ የሚደርሱ ሰዎችን እስከ ሦስት ቀን ያበላሉ፡፡ የሰፈር ሰዎችና ጎረቤቶች እስከ ሦስት ቀን ድረስ በለቅሶው ቤት በመገኘት ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን ይጫወታሉ፤ ሐዘንተኞችን ያጽናናሉ፤ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ይወያያሉ፤ ለችግሮቻቸው መፍትሄ ይሻሉ፤ ወዘተ፡፡

በሦስተኛው ቀን ቡና ተፈልቶ፣ ቆሎ ተቆልቶ ወይም ንፍሮ ተቀቅሎ ድንኳን ይፈርሳል፡፡ አሁንም እንደ ሟች ቤተሰብ አቅምና ድንኳኑ እንደሚፈርስበት ቀን የሚለያይ ሆኖ እርድ ሊፈፀም ይችላል፡፡ በዚህ ቀን የሚታረደው እርድ ‹‹ፍራጅ›› ይባላል፡፡ የሟቹ ቤተሰቦች እንደ አቅማቸው በግ አርደው ምግብ በማዘጋጀት በእለቱ የተገኙትን፣ ድንኳን በማፍረስ ያገዙትን እና ነዳያንን ይመግባሉ፡፡


በቀጣዮቹ ጊዜያት የሟች ቤተሰቦችና ዘመዶች ሀዘናቸውን በልዩ ልዩ መንገዶች ይገልፃሉ፡፡ ወንዶች ሙሉ ጥቁር ልብስ በመልበስ፣ ፂማቸውን በማሳደግ፣ ፀጉራቸውን በመላጨትና ጥቁር ኮፍያ በማድረግ ወዘተ. ሐዘናቸውን የሚገልጹ ሲሆን ሴቶቹ ደግሞ ፀጉራቸውን ተላጭተው ጥቁር ሻሽ በማሰር፣ ጥቁር ቀሚስና ነጠላ (ኩታ) በመልበስ ወዘተ. ሀዘናቸውን ይገልጻሉ፡፡ ሐዘናቸው በዚህ ብቻ የሚገታ አይደለም፤ በተለይ የሟች አርባ እስከሚወጣ ድረስ በተለያዩ መንገዶች ይቀጥላል፡፡

የሟቹ አርባ (ተዝካር) እስከሚወጣበት ቀን ድረስ ባሉት ተከታታይ እሁዶች የሟች ቤተሰብ፣ወዳጆችና ዘመዶች ቤተክርስቲያን በመሄድ ያለቅሳሉ፡፡ እስከ አርባኛው ቀን ድረስ በየሳምንቱ እሁድ እሁድ ወደ ቤተክርስቲያን እየሄዱ የሚያለቅሱት ለቅሶ የራሱ ሥርዓት ያለው ነው፡፡ በጠዋት ተነስተው የሀዘን ልብሳቸውን በመልበስና የሟቹን ፎቶና አልባሳት በመያዝ ቀብሩ ቦታ ሄደው ያለቅሳሉ፡፡ ከዚያም ሥርአተ ቅዳሴ እስከሚጠናቀቅ

ድረስ ከቤተክርስቲያኑ ቅጥር ግቢ ውጭ ጥላ ባለበት ቦታ ላይ ሰብሰብ ብለው ይቀመጣሉ፡፡ ስርአተ ቅዳሴው ከተጠናቀቀ በኋላ ባሉበት ሆነው እንደገና ይላቀሳሉ፡፡



ምስል12 - ሀዘንተኞቹ በአንደኛው እሁድ ሚች በተቀበረበት ቦታ ላይ ሲያለቅሱ



ምስል 13 - ስርአተ ቅዳሴ እስኪጠናቀቅ ድረስ ሀዘንተኞቹና ለቀስተኞቹ ዛፍ ጥላ ስር ተቀምጠው ሲጠብቁ

ይህ ዓይነቱ ለቅሶ ሐዘንተኞቹን የሚጎዳ መሆኑ ባያጠያይቅም ለአካባቢው ህብረተሰብ የተለያዩ ማህበራዊ ሙያዎች አሉት፡፡ ከነዚህም መካከል አንዱ በተለያዩ ምክንያቶች በቀብር ስነስርአት ላይ ላልተገኙ ሰዎች ለቅሶ እንዲደርሱ ምቹ አጋጣሚ የሚፈጥር መሆኑ ነው፡፡ አንድ የህብረተሰቡ አባል ቢችል በቀብር ስነስርአቱና ሐዘንተኞቹ እስከ ሶስት ቀን ድረስ ድንኳን ውስጥ በሚቀመጡባቸው ጊዜያት እየተገኘ ቢያስተዛዝንና ቢያፅናና ይመረጣል፡፡ ይህን ማድረግ ካልቻለ ግን እስከ አርባኛው ቀን ድረስ ካሉት እሁዶች ቢያንስ በአንደኛው እሁድ ለቅሶ የመድረስ ማህበራዊ ግዴታ አለበት፡፡ ከነዚህ ምርጫዎች በአንዱ ተጠቅሞ ለቅሶ የማይደርስ የህብረተሰቡ አባል ቢኖር ‹‹እርሙ-ቢስ፣ እርሙ-በላ›› እየተባለ ማህበራዊ ውግዘት ይገጥመዋል፤ ከማህበራዊ ህይወት ይገለላል፡፡

የዚህ ዓይነቱ ለቅሶ ሌላኛው ማህበራዊ ሙያ በቀብር ስነስርአት ወቅት ያልተገኘው ሰው ሁሉ በየጊዜው ወደ ሚች ቤተሰቦች ቤት እየሄደ ሃዘንተኞችን በየጊዜው በመስተንግዶና በለቅሶ እንዳይጎዳቸው የሚያደርግ መሆኑ ነው፡፡

በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ከሚከናወኑ የድህረ ቀብር ክዋኔዎች መካከል ለሚች የሚደረጉ የመታሰቢያ ስነስርአቶች ጉልህ ሥፍራ ያላቸው ናቸው፡፡ መሪጌታ ሊባኖስ

የተመኙ የተባሉት መረጃ አቀባይ እንደገለጹት የመታሰቢያ ስነስርአቶች የሚደረጉት ቅዱሳን መፃህፍት «ስለሞቱ ሰዎች መታሰቢያ አድርጉላቸው» ብለው ስለሚያዙ እንደሆነና መጻህፍቱ ላይ በተደነገጉ ቀናት መሰረት እንደሚፈፀም ተናግረዋል፡፡ ከጠቆሙኝ መፃህፍት መካከል በአንደኛው ላይ የሚከተሉት የመታሰቢያ ቀናት ሰፍረው ይገኛሉ፤ እለት፣ ሳልስት፣ ሰባት፣ ዘጠኝ፣ አስራ ሁለት፣አስራ አራት፣ ሰላሳ፣አርባ፣ ስልሳ(ሰማኒያ)፣መንፈቅ፣ ዓመት (ፍትሀ ነገስት፣ 1958፣ 273)፡፡ ከእነዚህ ቀናት መካከል አብዛኛውን ጊዜ የመታሰቢያ ስነስርአት የሚደረግባቸው ቀናት ሳልስት፣ አስራ ሁለት፣አርባ እና ዓመት ናቸው፡፡ እነዚህ ቀናት የተመረጡበትን ምክንያት ተጠይቀው ሲመልሱም፤ «በሦስተኛው ቀን መታሰቢያ የሚደረገው ኢየሱስ ክርስቶስ ሦስት መአልትና ሦስት ሌሊት በከርሰ መቃብር አድሮ በሦስተኛው ቀን መነሳቱን ለማጠየቅ ነው፡፡ አስራ ሁለተኛው ቀን አስራ ሁለቱን ሀዋርያት ለማስታወስ ነው፡፡ በአርባኛውም ቀን መታሰቢያ የሚደረገው በአርባ ቀን ያገኘውን ልጅነት በማሳደፉ እዳ አታድርግበት ለማለት ነው» ብለዋል፡፡በእነዚህ ቀናት ካህናት ስለሟች ነፍስ ይጸልያሉ፤ ምህረትን ይለምናሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦችም እንደ አቅማቸው ምግብና መጠጥ በማዘጋጀትና ወደ ቤተክርስቲያን በመውሰድ ለሐይማኖት አባቶችና ለነዳያን ያበላሉ፤ ያጠጣሉ፡፡

ለሟች ሐውልት ማሰራት ከድህረ ቀብር ክዋኔዎች መካከል አንዱ ሆኖ ይጠቀሳል፡፡ የሟች ቤተሰቦች አቅማቸው የሚፈቅድ ከሆነ በሟች መቃብር ላይ ሐውልት ያስገነባሉ፡፡ በአስገነቡት ሐውልት ላይም የሟቹን ፎቶግራፍ እንዲቀመጥ በማድረግ ከፎቶው ስር ልዩ ልዩ ጽሁፎች እንዲጻፍ ያደርጋሉ፡፡ ከፎቶው ስር የሚጻፉት ጽሁፎች አብዛኛውን ጊዜ የሟቹን ስም፤ የትውልድ ቦታ እና በህይወት የኖረበትን እድሜ (ዘመን) የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ አንዳንድ ጊዜ ግን የተለያዩ ጥቅሶችም (ለምሳሌ «ሩጫዬን ጨርሻለሁ») የሚጻፉበት አጋጣሚ ይኖራል፡፡ በሟች መቃብር ላይ ቤት የሚያሰሩም ቤተሰቦች አሉ፡፡ አንዳንዶቹ ደግሞ መቃብሩን በሳጠራ እንዲከለል ያደርጋሉ፡፡

ሳጠራው፣ ቤቱ ወይም ደግሞ ሐውልቱ ሁሉም መቃብርን ቆፍረው አስከሬንን ከሚበሉ አራዊት ለመከላከል ታስበው የሚሰሩ ናቸው፡፡ ከዚህም በቀር በጊዜ ብዛት ቦታው እንዳይጠፋ እና ለሌላ መቃብርነት ዳግመኛ እንዳይቆፈር ለማድረግ ሲባል የሚሰሩ ናቸው፡፡ አንዳንድ ቤተሰቦች መቃብር ላይ ቤት የሚያሰሩት ለሌሎች በመጠለያነት

እንዲያገለግል በማሰብ እንደሆነ ወ/ሮ አበበች መኮንን የተባሉት መረጃ አቀባይ ተናግረዋል፡፡

### 4.3.2 የእስልምና እምነት ተከታዮች ድህረ ቀብር ክዋኔ

በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ የአንድ ሟች ግብአተ መሬት ከተጠናቀቀ በኋላ ወዲያውኑ ዱዓ ማድረግ የግድ ነው፤ ዱዓ ያደርጋሉ፡፡ ቀብሩ በተጠናቀቀ ቅጽበት መላኢኮች ለሟች ልዩ ልዩ ጥያቄዎችን ያቀርቡለታል፣ ይጠይቁታል ተብሎ ይታመናል፡፡ ስለዚህ መቃብር ውስጥ ከመላኢኮች ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ሟች ትክክለኛና የማያወላውሉ ምላሾችን ይሰጥ ዘንድ፣ አላህ (ሱ.ወ) ሟቹን ያነሳሳውና ያሳውቀው ዘንድ ዱዓ ያደርጉለታል፤ ይለምኑለታል፡፡

የዱአው ወይም የጸሎቱ ስነስርአት ከተጠናቀቀ በኋላ የሟች የህይወት ታሪክ የሚነበብ ከሆነ በኡለማዎችና በአስተናባሪዎች አማካይነት ሁሉም ለቀስተኞች ወደ አንድ አካባቢ ሰብሰብ ብለው የህይወት ታሪኩ ይነበብለታል፡፡ በቀደመው ክፍል እንደተመለከትነው የሚነበበው የህይወት ታሪክ በአብዛኛው የሚያተኩረው ሟቹ ከማን፣ የት እና መቼ እንደተወለደ፣ እንዴት እንዳደገ፣ የስንት ልጆች አባት እንደሆነ፣ ምን ምን መልካም ስራዎችን እንደሰራ፣ ምን ያህል አመት እንደኖረና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ ነው፡፡ የህይወት ታሪኩ ተነቦ እንዳበቃ ኡለማዎቹ ይመርቃሉ፡፡ ከዚያም፣ በተለይም ከብት ታርዶ ከሆነ የሟች ቤተሰቦች ወይም ዘመዶች ለታዳሚያን በሙሉ ‹‹እባካችሁ እቤት ድረሱልን›› የሚል መልእክት ያስተላልፋሉ፡፡

ከዚህ በኋላ ወደ ቤት ይመለሳሉ፡፡ ሲመለሱ በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ እንደተመለከትነው ሐዘንተኞቹ ከፊት ይሆናሉ፤ ሌሎቹ ታዳሚያን ደግሞ ከኋላ ይከተላሉ፡፡ ምናልባት በተለያዩ ምክንያቶች ከመንገድ ላይ ተሰናብተው መሄድ የሚፈልጉ ሰዎች ከአሉ ወደሀዘንተኞቹ ፊት ቀረብ በማለት እየዘየሩ፣ የተወሰነ ብር ደበቅ አድርገው እየሰጡ እና ‹‹አላህ ይሶብራችሁ›› (አላህ ያጽናችሁ) እያሉ ይሄዳሉ፡፡ ሰዎች ብር የሚሰጡት ለቅሶ ለመድረሳቸው ምልክት ይሆን ዘንድ እንደሆነና ማንኛውም ሰው የአቅሙን ያህል መስጠት እንደሚችል አቶ አህመድ ኑር ያሲን የተባሉት መረጃ አቀባይ ተናግረዋል፡፡

ቤት እንደደረሱ ከድንኳኑ ውጪ ተዘጋጅቶ በሚጠብቃቸው ውሃ እጆቻቸውን እየታጠቡና ጣቶቻቸው ላይ የሚቀሩትን የውሃ እንጥፍጣፊዎች በጆሮአቸው በኩል ወደኋላቸው እየረጩ ወደ ድንኳኑ ውስጥ በመግባት በተዘጋጀላቸው ቦታ ላይ ይቀመጣሉ፡፡ ወንዶችና ሴቶች ተቀላቅለው አይቀመጡም፡፡ ቢቻል ሁለት ድንኳኖች ይተከሉና በአንደኛው ድንኳን ወንዶች ብቻ በሁለተኛው ድንኳን ደግሞ ሴቶች ብቻ ይቀመጣሉ፡፡ ካልሆነም ደግሞ አንዱን ድንኳን በመጋረጃ ለሁለት ከከፈሉ በኋላ በአንደኛው ክፍል ወንዶች በሌላኛው ክፍል ሴቶች ይቀመጣሉ፡፡

እጆቻቸውን የሚታጠቡበትን፣ ጣቶቻቸው ላይ የቀሩ የውሃ እንጥፍጣፊዎችን ወደኋላቸው የሚረጩበትንና ወንዶችና ሴቶች ድንኳን ውስጥ ተቀላቅለው የማይቀመጡበትን ምክንያት የተጠየቁት መረጃ አቀባዮች የሚከተሉትን ምላሾች ሰጥተዋል፡፡ ሼህ ሰይድ የተባሉት መረጃ አቀባይ ‹‹እጅ የመታጠቡ ስርአት ለንጽህና ነው፡፡ በእጆቻችን ብዙ ነገር ስለምንነካካ መታጠብ ስላለብን ነው የምንታጠበው፡፡ ውሀ ወደኋላ የምንረጨውም ሀዘንን ያርቀው ለማለት ነው›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 17፣2004 ዓ.ም) ፡፡ አቶ አህመድ ኑር ሀሰን የተባሉት መረጃ አቀባይ ደግሞ ወንዶችና ሴቶች ተቀላቅለው የማይቀመጡበትን ምክንያት አስመልክተው ‹‹በአይን አይቶ ላለመመኘት (ላለማመንዘር) እና የሞላሁት ውዱእዬ እንዳይፈርስ በሚል ምክንያት ነው ወንዶችና ሴቶች ተቀላቅለው የማይቀመጡት›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 17፣2004 ዓ./) ፡፡

ወንዶቹ በተዘጋጀላቸው ቦታ ከተቀመጡ በኋላ መስተንግዶው ይቀጥላል፡፡ ቡና ይፈላል፤ በሬ ታርዶ ምግብ የተዘጋጀ እንደሆነም ምግብ ይቀርባል፤ ይበላል፤ ይጠጣል፡፡ ስጋ ለማይበሉ የክርስትና እምነት ተከታዮች ደግሞ ቆሎ ወይም ንፍሮ ይቀርብላቸዋል፡፡ ለለቀስተኞች የሚቀርበውን ምግብ አዘገጃጀት በሚመለከት ወ/ሮ ሶፊያ አህመዲን የተባሉት መረጃ አቀባይ እንደሚከተለው ገልጸዋል፤ ‹‹በሬው ከታረደ በኋላ ስጋው በትንሽ በትንሹ ይቆራረጣል፡፡ በትንሽ በትንሹ የተቆራረጠው ስጋ ሸርጥ ይባላል፡፡ ይሄ ስጋ ከተቆራረጠ በኋላ በሳህን በሳህን እየተደረገ ከዳቦ ወይም ከእንጀራ ጋር ለለቀስተኞቹ ይሰጣል ብለዋል (ቃለመጠይቅ፣ ግንቦት 29፣ 2004 ዓ.ም)፡፡

ለቀስተኞቹ የቀረበላቸውን ምግብ ከበሉ በኋላ ልዩ ልዩ ጨዋታዎችን ይጨዋወታሉ፡፡ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና የመሳሰሉ ጉዳዮችን እያነሱ ይወያያሉ፡፡ ሀዘንተኞቹን ሀዘን እንዳይጠናባቸው ያጽናናሉ፤ ያረጋጋሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ከሩቅ ቦታ

የመጡና የሚቸኩሉ ሰዎች ሀዘንተኞቹን እየዘየሩ፣ ያቅማቸውን ያህል ብር እየሰጡና ‹‹አላህ ይሶብራችሁ›› እያሉ ይሰናበታሉ፡፡ ጎረቤቶችና የአካባቢው ሰዎች ግን ድንኳን እስከሚፈርስበት ቀን ድረስ ሀዘንተኞቹን እያጽናኑ ይሰነብታሉ፡፡

በሦስተኛው ቀን፣ በሰባተኛው፣ በሁለት ሰባቱ፣ በአራት ወር ከአስረኛው ቀን ከዚያም በየአመቱ የሟች ቤተሰቦች የመታሰቢያ ስነስርአት ያደርጋሉ፡፡ አቅማቸው እንደፈቀደላቸው ከብት ወይም ፍየል አርደው ሰዶቃ ያደርጋሉ፡፡ ነዳያንን ይመግባሉ፡፡ እነርሱም ይበላሉ ይጠጣሉ፡፡ ኡለማዎቹ ለሟች ቁርአን ይቀሩለታል፤ ዱአ ያደርጉለታል ቡና ይፈላል፤ ጨዋታውም ይቀጥላል፡፡

እነዚህ የመታሰቢያ ጊዜያት የተመረጡበትን ምክንያት የጠየቅኋቸው ሼህ ሰይድ የተባሉት መረጃ አቀባይ ሲመልሱ፤ ‹‹በተለምዶ በእነዚህ ቀናት ሰደቃ ተደርጎ ቁርአን ይቀራል፤ ዱአም ይደረጋል እንጂ የሞተን ሰው ዚያራ ለማድረግ (ቁርአን ለመቅራትም ሆነ ዱአ ለማድረግ) ጊዜ አይገድበውም፡፡ በማንኛውም ጊዜ ዱአ ማድረግ ይቻላል›› ብለዋል፡፡ በአራት ወር ከአስረኛው ቀን የሚደረገው ስነስርአት ግን የተለየ ምክንያት እንዳለው ነግረውኛል፡፡ አንዲት ሴት አባወራዋ ከሞተባት ቀን ጀምሮ እስከ አራት ወር ከአስር ቀናት ድረስ ጸጉሯ ተሸፍኖ ይቆያል፡፡ ሽቶ መነስነስ፣ የሚሸት ቅባት መቀባት፣ የሚያማምሩና አይን የሚስቡ ልብሶችን መልበስ አትችልም፡፡ በጣም አስፈላጊ ለሆኑ ጉዳዮች ካልሆነ በስተቀር ከቤትም አትወጣም፡፡ ልብሷን ሳትቀይር ‹ጉልባብ› እንደለበሰች ቤቷ ውስጥ ትቆያለች፡፡ ባል ማግባትም አትችልም፡፡ በአራት ወር ከአስረኛው ቀን ሰዶቃ ከተደረገ በኋላ ግን ልብሷን መቀየር፣ ጸጉሯን መሰራት፣ ቅባት መቀባት ወዘተ. ትችላለች፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ይህ ቀን የሀዘን መቋጫ፣ የሀዘን መደምደሚያ ቀን ሆኖ ይወሰዳል፡፡ ሴቷ አራት ወር ከአስር ቀን ድረስ እንድትቆይ የሚደረገው መጽሀፉ ስለሚያዝ እንደሆነና ዋነኛ ምክንያቱም ከሟቹ የጸነሰችው ልጅ መኖር አለመኖሩ እንዲታወቅ መሆኑን መረጃ አቀባዩ ተናግረዋል፡፡ እማወራዋ ብትሞት ወንዱ ምን ያህል ጊዜ መቆየት ይጠበቅበታል? በማለት ያነሳሁላቸውን ጥያቄም ሲመልሱ፤ ‹‹ቀድሞውኑ ወንድ እስከ አራት ሴት ማግባት ይችላል፡፡ አንዷ ብትሞትበት ከሌላኛዋ ጋር መኖር ይችላል፡፡ ለክበሬታዬ ብሎ በራሱ ጊዜ ለመቆየት ካላሰበ በስተቀር በሞተችዋ ምትክ ወዲያውኑ ሌላ ሴት ማግባት ይችላል፡፡ እንደ ሴቷ አራት ወር ከአስር ቀን እንዲጠብቅ አይገደድም›› ብለዋል (ቃለመጠይቅ ጥር 17፤2004 ዓ.ም) ፡፡

# 5. በሁለቱ የሐይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔ ውስጥ የታዩ አንድነቶች (ተመሳሳይነቶች) እና ልዩነቶች

በዚህ ክፍል በሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርዓት ክዋኔ ውስጥ በጉልህ የተስተዋሉ አንድነቶች (ተመሳሳይነቶች) እና ልዩነቶች ጠቅለል ተደርገው ቀርበዋል፡፡

## 5.1. አንድነቶች (ተመሳሳይነቶች)

በዚህ ንኡስ ክፍል በሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች ውስጥ ጎላ ጎላ ብለው የታዩ ተመሳሳይነቶች (አንድነቶች) እንደሚከተለው ቀርበዋል::

- የሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች አንድ ሰው በጠና ታሞ እማይድንበት ደረጃ ላይ መድረሱን ሲገምቱ ቀጣይ ህይወቱ የተደላደለ እንዲሆን ለማዘጋጀት ከፍተኛ ግምት ይሰጣሉ፡፡ በክርስትናው እምነት ህመምተኛው የሰራውን ሐጢያት ሁሉ ለካህን እንዲናገር ይደረጋል፡፡ በእስልምናው እምነት ደግሞ ከሊማን እንዲያነብ ይደረጋል፡፡ የእነዚህ ሁነቶች ዋና ዓላማ የሟች ቀጣይ ዕጣ ፋንታ ጥሩ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ የሁለቱም ሐይማኖት ተከታዮች ህመምተኛው ሲሞት ለሚያስፈልጉ ነገሮችና ከሞት በኋላ ለሚኖሩ ጉዳዮችም ቅድመ ዝግጅቶችን ያደርጋሉ፡፡ ከሚያደርጓቸው ቅድመ ዝግጅቶች መካከል አንዱና ዋነኛው ታማሚውን እንዲናዘዝ ማድረግ ነው፡፡ በዚህ መሰረት የሐይማኖት አባቶችና የአካባቢው ሽማግሌዎች ታማሚውን ያናዝዙታል፡፡ ኑዛዜው በአብዛኛው በሐብት ንብረት ክፍፍል ላይ የሚያተኩር ነው የሚሆነው፡፡
- የሁለቱም ሐይማኖት ተከታዮች የሟችን አስከሬን ይንከባከባሉ፤ የሟቹን አይኖች ይከድናሉ፤ ጥርሶቹን ይገጥማሉ፤ አፉን ይዘጋሉ፡፡ ከዚያም አስከሬኑን ከአጠቡ በኋላ በጀርባው ተንጋሎ ቀጥ ብሎ እንዲተኛ ያደርጋሉ፡፡
- በሁለቱም ሐይማኖት ተከታዮች ዘንድ እንደሟች ቤተሰብ የኢኮኖሚ አቅም ሁኔታ አስከሬን (ጀናዛ) ከቤት ሲወጣ በሬ ይታረዳል፡፡
- የሁለቱም ሐይማኖት ተከታዮች ሙታቸውን ከቀበሩ በኋላ ወዲያውኑ መቃብሩ ላይ ርጥብ ቅጠል ከነቅርንጫፉ ይተክላሉ፡፡

- የሟች ግብዓተ መሬት ከተጠናቀቀ በኋላ እንደሁኔታው (እንዳስፈላጊነቱ) የህይወት ታሪኩ ይነበባል፡፡ በሁለቱም የሐይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚነበበው የህይወት ታሪክ ሟች ከማን፣ የት እና መቼ እንደተወለደ፣ እንዴት እንዳደገ፣ የስንት ልጆች አባት እንደሆነ፣ ምን ምን መልካም ስራዎችን እንደሰራ፣ ምን ያህል ዓመት እንደኖረ፣ መቼ እንደሞተ የሚያትት ነው፡፡
- የሁለቱም ሐይማኖት ተከታዮች የሚቹን ስርአተ ቀብር አጠናቅቀው ወደ ቤት ከተመለሱ በኋላ ድንኳን ውስጥ ከመግባታቸው በፊት እጆቻቸውን ይታጠባሉ፡፡ ከታጠቡ በኋላም ጣቶቻቸው ላይ የሚቀሩ የውሃ እንጥፍጣፊዎችን በጆሮዎቻቸው በኩል ወደኋላቸው ይረጫሉ፡፡
- እንደሟች ቤተሰብ የኢኮኖሚ አቅም የሚለያይ ሆኖ በሁለቱም ሐይማኖት ተከታዮች ዘንድ በሬ አርዶ ታዳሚያንን መግቦ መሸኘት የተለመደ ነው፡፡ በቀጣይ ጊዜያትም ለሟች የመታሰቢያ ስነስርአት ማድረግ በሁለቱም ሐይማኖት ተከታዮች ዘንድ የሚስተዋሉ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች ናቸው፡፡

## 5.2. ልዩነቶች

በዚህኛው ንኡስ ክፍል በሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎች ውስጥ በጉልህ የታዩ ልዩነቶች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

- በክርስትናው እምነት የሟች አስከሬን በሁለተኛው ቀን፣ በሶስተኛው ቀን ወዘተ. የሚቀበርባቸው አጋጣሚዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ግን ጀናዛው (ሬሳው) ቤት ውስጥ ብዙ እንዲቆይ አይደረግም፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ከቀብር በፊት መከናወን ያለባቸው ነገሮች ከተከናወኑ በኋላ ሙትን በፍጥነት ወደ ቀብር ቦታ ወስዶ መቅበር የተለመደ ነው፤ ግዴታም ነው፡፡
- የክርስትና እምነት ተከታዮች የግንዘት ስርአት የሚያከናውኑት የእያንዳንዱን ሟች ምድራዊ ማእረግ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ሟች አንድ ማዕረግ ካለው የሚገንዘው እንደሱ የሆነ ሰው ነው፡፡ ካህኑን ካህን እንጂ ምእመን አይገንዘውም፡፡ በዚህ መሠረት የሟች አስከሬን ሰባት ቦታዎች ላይ በክር ይታሰራል፤ ይገነዛል፡፡ የሟቹን ምድራዊ ማዕረግ መሠረት በማድረግ እጆቹ ብልቱ ላይ ወይም ደረቱ ላይ ወይም ትከሻዎቹ ላይ ወይም አይኖቹ ላይ እንዲሆኑ ይደረጋሉ፡፡ በእስልምና እምነት

ተከታዮች ዘንድ የምድራዊ ማዕረግን መሠረት ያደረገ የአገናነዘ ልዩነት የለም፡፡ ሟች ከመሞቱ አስቀድሞ እንዲገንዙት የመረጣቸው ሰዎች ካሉ በእነርሱ አማካይነት፣ አለበለዚያ ደግሞ ለሟች የቅርብ ዘመድ የሆነ ማንኛውም ሰው አስከሬኑን ወደቂልባ አዙሮ በቀኝ ጎኑ በማስተኛትና ክንዶቹንም ጎኖቹ ላይ በማድረግ ይገንዘዋል፡፡

- የክርስትና እምነት ተከታዮች አስከሬኑን በአንድ ንፁህ ጨርቅ ከጠቀለሉ በኋላ እንደሁኔታው በሰሌን ብቻ ሸፍነው ወይም ደግሞ በሬሳ ሳጥን ውስጥ አስገብተው ለቀብር ያዘጋጃሉ፡፡ የእስልምና እምነት ተከታዮች ደግሞ አንዱን ባለሰባት ሜትር ጨርቅ ለሶስት ከቆራረጡ በኋላ ጀናዛውን ይከፍናሉ፡፡ ሙስሊሞች እንደ ክርስቲያኖች ጀናዛን በሬሳ ሳጥን ውስጥ አይከቱም፤ በሬሳ ሳጥን አይቀብሩም፡፡
- የክርስትና እምነት ተከታዮች የሟችን ፎቶግራፍና አልባሳት በመያዝ ክብ ሰርተው ደረታቸውን በእጆቻቸው በመምታት "ዋይ ዋይ" እያሉ ያለቅሳሉ፤ እድምተኞችንም ያስለቅሳሉ፡፡ በእስልምና እምነት ደረት እየደቁ፣ ፊት እየነጩ፣ እየወደቁና እየተነሱ ማልቀስ የተከለከለ ነው፤ አይፈቀድም፡፡ የሟችን ፎቶና አልባሳት ይዞ ግጥም እየገጠሙ ማልቀስም አይቻልም፡፡ ሀዘንተኞች ረጋ ባለ ሁኔታ እየሳጉ ያለቅሳሉ እንጂ እንደክርስትና እምነት ተከታዮች ክብ ሰርተው "ዋይ ዋይ" አይሉም፤ ደረታቸውን አይደቁም፤ አይወድቁም አይነሱምም፡፡
- በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ወንዶችም ሴቶችም አስከሬኑን ወደሚቀበርበት ቦታ መሸኘት የተለመደ ነው፡፡ ሴቶቹ አስከሬኑ ከሚቀበርበት ጉድጓድ አጠገብ እንዳይደርሱ፣ ሬሳው ሲቀበርም እንዳይመለከቱ ይደረጋል እንጂ ወደ ቀብር ቦታ አብረው እንዳይሄዱ አይከለከሉም፡፡ በእስልምና ሐይማኖት ሴቶች በፍፁም ጀናዛውን ተከትለው ወደ ቀብር ቦታ እንዲሄዱ አይፈቀድላቸውም፡፡
- የክርስትና እምነት ተከታዮች ለሬሳ መቅበሪያ የሚሆነውን ጉድጓድ በምዕራብ-ምስራቅ አቅጣጫ ቁልቁል በመቆፈር የአስከሬኑን ራስ ወደ ምዕራብ እግሮቹን ደግሞ ወደ ምስራቅ አድርገው በጀርባው አንጋለው ይቀብራሉ፡፡ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ጀናዛ የሚቀበርበት ጉድጓድ አቆፋፈሩ ለየት ያለ ነው፡፡ በግምት ከአንድ ሜትር እስከ አንድ ሜትር ከግማሽ የሚደርስ ጥልቀት ያለው ጉድጓድ ወደ ታች ይቆፈራል፡፡ ከዚያም ከጉድጓዱ ወለል ትንሽ ከፍ በማለት ወደ ጎን በሰሜን አቅጣጫ አስከሬኑን ሊያስተኛ የሚችል ዋሻ መሰል ነገር (ለሃድ) ይቆፈራል፡፡ በዚህ

መልክ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ የጀናዛውን ወደ ሰሜን (ወደ ቂልባ) በማዞር ለሃዱ ውስጥ ያስገቡታል፡፡ ከዚያም በቀኝ ጎኑ እንዲተኛ ካደረጉ በኋላ ሲከፈን የታሰሩትን ቋጠሮዎች ይፈቷቸዋል፡፡ ጀናዛውን በዚህ አኳኋን ከቀበሩ በኋላ የለሃዱን አፍ በእንጨትና በድንጋይ ደፍነው በጭቃ ይመርጉታል፡፡

- የክርስትና እምነት ተከታዮች ሙታቸውን በሚሸኙበት ጊዜ የሐይማኖት አባቶች (ካህናትና ዲያቆናት) ከፊት ይቀድማሉ፡፡ አስከሬኑን የተሸከሙ ሰዎች ደግሞ ከኋላ ይከተላሉ፡፡ የሟች ቤተሰቦች፣ የቅርብ ወዳጆችና ዘመዶች ወንድ ሴት ሳይል አስከሬኑን አጅበው ይጓዛሉ፡፡ በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ደግሞ ጀናዛ የተሸከሙ ሰዎች ከፊት ቀደም ብለው በእርጋታ ይሄዳሉ፡፡ የሐይማኖት አባቶች፣ የሟች ቤተሰቦች፣ ወዳጆችና ዘመዶች እንዲሁም ሌሎች ታዳሚያን (ሁሉም ወንዶች ብቻ መሆናቸውን ልብ ይሏል) ከጀናዛው በኋላ ሆነው አጅበው ይሄዳሉ፡፡
- የክርስትና እምነት ተከታዮች የሟች አርባ (ተዝካር) እስከሚወጣበት ቀን ድረስ ባሉት ተከታታይ እሁዶች (በየሳምንቱ እሁድ እሁድ) ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ያለቅሳሉ፡፡ በእስልምና እምነት ተከታዮች ይህ አይደረግም፤ በየሳምንቱ እሁድ እሁድ በመቃብር ቦታ ላይ እየተሰበሰቡ አያለቅሱም፡፡
- ከቀብር መልስ ወንዶችም ሴቶችም በተዘጋጀው አንድ ድንኳን ውስጥ ይቀመጣሉ፡፡ እንደሁኔታው ወንዶችና ሴቶች ተቀላቅለው የሚቀመጡባቸው አጋጣሚዎች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ በእስልምና እምነት ግን ወንዶችና ሴቶች ተቀላቅለው አይቀመጡም፡፡ ቢቻል ሁለት ድንኳኖች ይተከሉና በአንደኛው ድንኳን ወንዶች ብቻ በሁለተኛው ድንኳን ደግሞ ሴቶች ብቻ ይቀመጣሉ፡፡ ካልሆነም ደግሞ አንዱን ድንኳን በመጋረጃ ለሁለት ከከፈሉ በኋላ በአንደኛው ክፍል ወንዶች ብቻ በሌላኛው ክፍል ሴቶች ብቻ ይቀመጣሉ፡፡

# 6. ማጠቃለያ እና ይሁንታ

## 6.1 ማጠቃለያ

በዚህ የጥናት ጽሁፍ ውስጥ በደብረ ማርቆስ ከተማ እና አካባቢዋ የሚገኙ የኦርቶዶክስ ክርስቲያኖችና ሙስሊሞች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎቻቸው ምን እንደሚመስሉ ተመልክተናል፡፡ በሁለቱም ሀይማኖት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ሂደት ውስጥ በእድሜ፣ በጾታ ወይም በማህበራዊ ደረጃ ልዩነት ምክንያት የተለያዩ ክዋኔዎች የሚከውኑባቸው አጋጣሚዎች እንዳሉ ለመረዳት ተችሏል፡፡ የለቅሶ ስነስርአት ክንዋኔዎቻቸው ከሚመሩባቸው ሀይማኖታዊ መጻህፍት (መጽሐፍ ቅዱስ /ቅዱስ ቁርአን) ጋር ያላቸው ግንኙነት እምን ድረስ እንደሆነም ተገንዝበናል፡፡ የትኞቹን ድርጊቶች በልማድ ወይም በባህል እንደሚያከናውኑም ተመልክተናል፡፡ የለቅሶ ስነስርአቶቻቸውን ሂደት ለማሳየት ክዋኔዎቹ የቅድመ ሞት ክዋኔ፣ ጊዜ ሞት ክዋኔ እና ድህረ ቀብር ክዋኔ ተብለው በሦስት ክፍሎች ተከፍለው ነው የቀረቡት፡፡ በእያንዳንዱ ክፍል ውስጥ የሁለቱ ሀይማኖት ተከታዮች የሚያከናውኗቸው ክንውኖች በንጽጽር ቀርበዋል፡፡

በቅድመ ሞት ክዋኔ ውስጥ አንድ ሰው በጠና ታሞ የማይድንበት ደረጃ ላይ መድረሱ ሲገመት የሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች የሚያከናውኗቸውን ድርጊቶች ተመልክተናል፡፡ በዚህም መሰረት የሁለቱም ሐይማኖት ተከታዮች ህመምተኛውን ከመሞቱ በፊት እንዲናዘዝ የሚያደርጉት ለሁለት ዋና ዋና ዓላማዎች እንደሆነ ተረድተናል፡፡ የመጀመሪያው ዓላማ የሁለቱም ሐይማኖት ተከታዮች ከሞት በኋላ ሌላ ህይወት አለ ብለው ከማመናቸው ጋር የሚያያዝ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በመሆኑም የኑዛዜው ተቀዳሚ ተግባር ህመምተኛው ከዚህ አለም በሞት ተለይቶ ወደ ሌላኛው ህይወት ሲሸጋገር መልካም ነገር እንዲያጋጥመው ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው፡፡ ሁለተኛው ዓላማ ወይም ተግባር ደግሞ የቀሪ ሰዎችን ቀጣይ ዕጣ ፋንታ ለመወሰን ምቹ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ነው፡፡ ህመምተኛው ማን ምን ማድረግ እንዳለበትና የትኛው ንብረት ለማንኛው ሰው እንደሚገባ የሚወስንበትና አንዳንድ ሁኔታዎችን ቀደም ብሎ ፊርማ የሚያሲዝበት መልካም አጋጣሚ ነው፡፡

‹‹ጊዜ ሞት ክዋኔ›› በሚለው ክፍል የአንድ ሰው ነፍስ ከስጋው ከተለየችበት ቅጽበት አንስቶ እስከ ስርአተ ቀብሩ ፍጻሜ ድረስ የሚከናወኑ ድርጊቶችን በሶስት ንኡሳን ርዕሶች ከፋፍለን

ተመልክተናል፡፡ ሥርዓተ ግንዘታቸው ምን እንደሚመስል በተመለከትንበት ንኡስ ክፍል የክርስትና እምነት ተከታዮች በማህበራዊ ደረጃ ልዩነት ምክንያት ልዩ ልዩ የግንዘት ስርአቶች እንዳሏቸው አስተውለናል፡፡ የባህታውያን ስርአተ ግንዘት ከካህናት፣ የካህናቱ ከዲያቆናት፣ የዲያቆናቱ ከህጋውያን የተለያየ እንደሆነ ታውቋል፡፡ የክርስትና እምነት ተከታዮች የግንዘት ሥርዓት ከእስልምና እምነት ተከታዮች የግንዘት ሥርዓት ጋር አንዳንድ ልዩነቶች እንዳሉም በጥናቱ ተደርሶበታል፡፡ በጉዞ ስርዓቶቻቸውም ያታን መሰረት ያደረጉ ልዩነቶች እንዳሏቸው ታውቋል፡፡ የቀብር ስነስርአቶቻቸውን በቃኘንበት ንዑስ ክፍልም የሁለቱን ሐይማኖት ተከታዮች የሚያመሳስሉ አንዳንድ ክንውኖች (ለምሳሌ መቃብር ቦታ ላይ ቅጠል መትከል) ያሉ ቢሆንም ጎልተው የሚታዩ በርካታ ልዩነቶች እንዳሉ አስተውለናል፡፡ ከአስከሬን አገናነዝ (አከፋፈን)፣ ከመጠቅለያ ጨርቅ ብዛት፣ አስከሬኑን አጅቦ ወደ ቀብር ቦታ ከመሄድ፣ ለሟች ከሚደረግ የጉዞ ፍታት፣ ከአስከሬን የቀብር አቅጣጫ ምርጫ ወዘተ. ዙሪያ ያሉ ልዩነቶችን ተመልክተናል፡፡

‹‹ድህረ ቀብር ክዋኔ›› በሚለው ክፍል ውስጥ ደግሞ የሟች ግብዓተ መሬት ከተፈፀመ በኋላ የሁለቱ ሐይማኖት ተከታዮች የሚያከናውኗቸውን ክንውኖች አይተናል፡፡ ለሟች ፀሎት የማድረግ፣ የህይወት ታሪክን የማንበብ፣ እጅን ታጥቦ ወደ ኋላ የመርጨት፣ ምግብ የማዘጋጀትና መታሰቢያ የማድረግ ስነስርዓቶች በሙሉ የሁለቱን ሐይማኖት ተከታዮች የሚያመሳስሏቸው ተግባራት እንደሆኑ ሁሉ በአንጻሩ ልዩነቶች እንዳሉም አስተውለናል፡፡

## 6.2 ይሁንታ

ይህን ጥናታዊ ፅሁፍ ለማዘጋጀት የመስክ ሥራ ማካሄድ ግድም አስፈላጊም ነበር፡፡ በዚህ መሰረት በሁለት ዙር የተከፈለ የመስክ ጉዞ በማድረግ ከተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች፣ ከግለሰቦችና ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ልዩ ልዩ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር መረጃ ለመሰብሰብ ጥረት አድርጌአለሁ፡፡ መረጃዎቹን በምሰበስብበት ወቅት ይበል የሚያሰኙ በጎ ተግባራት እና ቢስተካከሉ መልካም ነው የምላቸው አንዳንድ እንከኖች አጋጥመውኛል፡፡

ወደ አካባቢው ሄጄ የምርምር ሥራውን ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ የሚመለከታቸው አካላት ተገቢውን ድጋፍ አድርገውልኛል፡፡ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔውን ለመመልከት ፈቃድ የምጠይቃቸው የሟች ቤተሰቦችና ዘመዶች ሰዎች በአብዛኛው ፍቃደኞች ነበሩ፡፡

ቃለመጠይቅ ለማድረግ የማናግራቸው ሰዎችም አብዛኞቹ በአካባቢው እንግዳን የመቀበል ወግ መሰረት በአክብሮት በመቀበልና ፈቃደኛነታቸውን በመግለጽ ያደርጉልኝ የነበረው ትብብር ደስ የሚያሰኝና የሚያበረታታ ነው፡፡ በዚህ ረገድ ከጥናቴ ርዕስ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸውንና ሌሎች መረጃዎችን አገኝባቸዋለሁ ያልኳቸውን የልዩ ልዩ መስሪያ ቤት ቢሮዎችን በማንኳኳበት ጊዜ በሚመለከታቸው የቢሮ ኃላፊዎች ይደረግልኝ የነበረው አቀባበልም በጣም ጥሩ ነበር፡፡ ብዙዎቹ መረጃዎቹን የት፣ ከማን እና እንዴት ማግኘት እንደምችል በመጠቆም ድጋፍ አድርገውልኛል፡፡ ይህ የተባባሪነት መንፈስ የሚያስመሰግንና ሊቀጥል የሚገባው ነው፡፡

መስሪያ ቤቶቹም ሆኑ ሌሎች ጉዳዩ የሚመለከታቸው አካላት ቢያደርጓቸው ይበጃሉ የምላቸው አንዳንድ ጉዳዮችም አሉ፡፡ በዚህ ጥናት የመረጃ ስብሰባ ወቅት ስለ አካባቢው አጠቃላይ ገፅታ ዳራ ለመስጠት የሚያስችሉ መረጃዎችን ለማግኘት ወደ ደብረማርቆስ ከተማ አስተዳደር ባህልና ማስታወቂያ ቢሮ ሄጄ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ከቢሮው ያገኘኋቸው መረጃዎች በጣም ጥቂትና ከተለያዩ ጽህፈት ቤቶች የተገኙ ልዩ ልዩ የሥራ ሂደት ዘገባዎች (ሪፖርቶች) ናቸው፡፡ እነዚህ ዘገባዎች (ሪፖርቶች) ያልታተሙ በመሆናቸው እንደመረጃ ለመጠቀም አስተማማኝነታቸው ላይ ጥያቄ ማስነሳቱ አይቀሬ ነው፡፡ በመሆኑም ቢሮው ዘገባዎቹን (ሪፖርቶቹን) በተገቢው መንገድ በመመርመርና በማጠናቀር ለተጠቃሚው አሻሚ በማይሆኑበት መንገድ ቢያቀርባቸው መልካም ነው፡፡

በሌላ በኩል የምስራቅ ጎጃም ዞን አስተዳደር የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የደብረማርቆስ ከተማንና የአጎራባች ወረዳዎችን የሰርግ፣ የለቅሶ፣ የአለባበስ፣ የአመጋገብ፣ የአክብሮት መግለጫ… ስነስርአቶችን በጽሁፍና በምስል አጠናቅሮ ለተጠቃሚዎች ለማድረስ እንቅስቃሴዎችን ጀምሮ እንደነበረና ጥረቱ በልዩ ልዩ ምክንያቶች እንዳልተሳካ ለመረዳት ችያለሁ፡፡ የአካባቢውን ባህላዊ እሴቶች ጠብቆ ለተተኪው ትውልድ ከማስተላለፍ አንፃር የጽህፈት ቤቱ እንቅስቃሴ መልካም ጅምር በመሆኑ የሚመለከታቸው አካላት የሙያና የበጀት ድጋፍ በማድረግ የተጀመሩትን እንቅስቃሴዎች ማጠናከርና ለውጤት ማብቃት ይኖርባቸዋል የሚል እምነት አለኝ፡፡

የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎችን ፎቶ ሳነሳና ቪዲዮ ስቀርጽ አንዳንድ እክሎች አጋጥመውኝ እንደነበር ቀደም ሲል ገልጫለሁ፡፡ የክርስትና እምነት ተከታዮች የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔዎቻቸውን ፎቶ ሳነሳ ወይም ቪዲዮ ስቀርጽ አንዳንድ ጥያቄዎችን ያነሱ የነበረ

ቢሆንም ዓላማውን ካስረዳኋቸው በኋላ ግን እንድቀርፅ ይፈቅዱልኝ ነበር፡፡የእስልምና እምነት ተከታዮች ግን የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔያቸውን ፎቶ እንዳነሳም ይሁን ቪዲዮ እንድቀርጽ ፍፁም ፈቃደኛ አልሆኑም፡፡ የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔያቸው በቪዲዮ ተቀርጾ፣ ፎቶም ተነስቶ በአግባቡ ተሰንዶ ቢቀመጥ ባህሉን ለቀጣይ ትውልድ ከማስተላለፍ አንጻር የሚኖረው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡ በመሆኑም ይሄን ጉዳይ ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚመለከተው አካል የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራ ቢሰራና ለውጥ ቢያመጣ መልካም ይመስለኛል፡፡

# ዋቢ ጽሁፎች


ሀብተማሪያም አሰፋ፡፡ *የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባህሎች፤* አዲስ አበባ ፡፡ (ማተሚያ ቤቱ አልተጠቀሰም)፣ 1986 ፡፡

ሐረገወይን ድፋባቸው፡፡ ‹‹የክስታንኛ የለቅሶ ግጥሞች››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲግሪ፣ 1974፡፡

ሕይወት አበሩ፡፡ ‹‹የመኢኒት ብሄረሰብ ባህላዊ የለቅሶ ስርአት ክዋኔ››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የሁ.ዲግሪ፣ 2003፡፡

መአዛ ተስፋይ፡፡ ‹‹በአጋመ አውራጃ የቀብር ስርአት አፈጻጸምና የለቅሶ ግጥሞች የይዘት ትንተና››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ዲግሪ፣ 1982፡፡

ሙሉጌታ በላይ፡፡ ‹‹የሚጫ ወረዳ የለቅሶ ስነስርአት እና የሙሾ ግጥም ይዘት ትንተና ፎክሎራዊጥናት››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲግሪ፣ 2002፡፡

ሞገስ ሚካኤል፡፡ ‹‹በላይ አርማጭሆ ወረዳ የሚደረግ የቀብር ስነስርአት፣ በስርአቱ ላይ የሚካሄድ ቀረርቶ፣ ፉከራና ክዋኔው››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የሁ.ዲግሪ፣ 2002፡፡

ሽመልስ አክሊሉ፡፡ ‹‹የቋሪት ወረዳ የለቅሶ ስነስርአትና የግጥሞች ይዘት ትንተና››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲግሪ፣ 1997፡፡

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የባህልና ቱሪዝም ቢሮ፡፡ *የአማራ ህዝብ ባህልና ቋንቋ፤* አዲስ አበባ፡፡ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት፣ 2001፡፡

ተሾመ ሙሉጌታ፡፡ ‹‹በቤንሻንጉል ጉሙዝ በድባጤ ወረዳ የለቅሶ ስነስርአት››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲግሪ፣ 1998፡፡

አለም እሸቱ፡፡ *መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ፡፡* አዲስ አበባ፤ የቅድስተ ማርያም

ኮሌጅ የሊበራል አርትስ ፋክልቲ ህትመት፣ 1994 ፡፡

አስቴር አንጀሎ፡፡ ‹‹የጋሞ ብሄረሰብ የለቅሶ ስርአት››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣ 1997፡፡

አቡበከር ሀሰን፡፡ ‹‹የሺናሻ ብሄረሰብ የሀዘንና የተዝካር ስርአት ክዋኔ››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣ 1998፡፡

አባተ አሰፋ፡፡ ‹‹የአሚባራ ወረዳ አፋሮች የለቅሶ ስርአት (አርካ) እና የምሳሌያዊ ንግግሮች ትንታኔ››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣ 2000፡፡

አየለ መሎሪ፡፡ ‹‹የሀዲያ ህብረተሰብ የለቅሶ ስነስርአት››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣ 1986፡፡

ኪዳነወልድ ክፍሌ፡፡ *መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ* ፡፡ አዲስ አበባ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1948፡፡

ወርቁ ማንደፍሮ፡፡ ‹‹በሊቦ ከምከም ወረዳ የለቅሶ ስነስርአትና የሙሾ ግጥሞች››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣ 1987፡፡

ወርቁ ወጌ፡፡ ‹‹በቸሀ ጉራጌ የልደትና የሞት ስርዓት››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣ 1982፡፡

ወርቃየሁ አረጋ፡፡ ‹‹የአዊ ሕብረተሰብ ሴንቲ (የለቅሶ ስርአት) እና የአውኚ ዚንዚምኚ (የሙሾ) ግጥሞች ይዘት ትንተና››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣ 1995፡፡

ዘላለም ኢዮብ፡፡ ‹‹በጎፋ ብሄረሰብ ባህላዊ ለቅሶ (ዬሆ) ግጥሞች ክዋኔና ስነግጥማዊ ገጽታ››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲማጽ፣ 1995፡፡

ዘላለም ፋንቱ፡፡ ‹‹የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔ በበና ፀማይ ወረዳ››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ስነጽሁፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት፣ የሁዲማጽ፣ 2004፡፡

ዘሪሁን አስፋው፡፡ *የስነጽሁፍ መሰረታውያን*፡፡ አዲስ አበባ፤ ንግድ ማተሚያ ቤት፣ 1996፡፡
የምስራቅ ጎጃም ዞን ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የ2003 ዓ.ም ሪፖርት፣ ደብረ ማርቆስ፣ 2003፡፡
የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፡፡ *አማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ 1993፡፡
የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ጽ/ቤት የ2004 ዓ.ም የ3ኛው ሩብ አመት የእቅድ ክንውን ሪፖርት፣ ደብረ ማርቆስ፣ 2004፡፡
የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር የመንግስት ኮሚዩኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት የ2004 ዓ.ም የ3ኛው ሩብ አመት ሪፖርት፣ ደብረማርቆስ፣ 2004፡፡
የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ የ2003 ዓ.ም አመታዊ ሪፖርት፣ ደብረ ማርቆስ ፣2003፡፡
የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ግብርና ጽ/ቤት የ2003 ዓ.ም አመታዊ ሪፖርት፣ ደብረ ማርቆስ፣ 2003፡፡
የደብረ ማርቆስ አስተዳደር ግብርና ጽ/ቤት የ2004 ዓ.ም የ3ኛው ሩብ አመት ሪፖርት፣ ደብረ ማርቆስ፣ 2004፡፡
የደብረ ማርቆስ ከተማ አስተዳደር ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት የ2004 ዓ.ም የ3ኛው ሩብ አመት እቅድ ክንውን አፈጻጸም ሪፖርት፣ ደብረማርቆስ፣ 2004፡፡
ድጋፌ ፈይሳ፡፡ ‹‹የሲዳማ ብሄረሰብ የለቅሶ ስነስርአት››፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲግሪ፣ 1975፡፡
ጌታመሳይ ግዛው፡፡ ‹‹የሺናሻ ብሄረሰብ የቀብር ስርአት ክዋኔ ከፎክሎር ዘውጎች አንጻር››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲግሪ፣ 2002፡፡
ጌጡ ታደሰ፡፡ ‹‹ክዋኔ በጎንደር ከተማ የለቅሶ ስነስርአት››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲግሪ፣ 1989፡፡
ጥላሁን ኢቢዶ፡፡ ‹‹የጌዲኦ ሕብረተሰብ የለቅሶ ስርአት››፡፡አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲግሪ፣ 1982፡፡

ፈለገሕይወት ዘገዩ፡፡ ‹‹በባንጃ ሽኩዳድ ወረዳ የቀብር ሥነሥርዓትና የለቅሶ ግጥሞች ስብስብ ይዘት ትንተና››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ ክፍለ ትምህርት፣ ዲ.ማጽ፣ 1997፡፡

ፈቃደ አዘዘ፡፡ *የስነ ቃል መምሪያ*፡፡ አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት፣ 1991፡፡

__________ ፡፡‹‹የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች አፋዊ ኪነተቃል ጥናት››፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ለሴሚናር የቀረበ፣ 1970 (ያልታተመ)፡፡

ፍትሐ ነገስት ንባብና ትርጓሜው፡፡ አዲስ አበባ፤ ብርሀንና ሰላም ማተሚያ ቤት፣ 1958፡፡

Abdulla Abdurahman. “Harriri Funeral customs.” *Ethnological society Bulletin.* Ed. Alula Pankhurst vol. 1. No. 1. Addis Ababa, Addis Ababa University press, 2002.

Abebe Ambachew (etal). “Funeral and Burial” *Ethnological Society Bulletin.* Ed. Alula Pankhurst. Vol. 1, No. 7. Addis Ababa, Addis Ababa University press, 2002.

Andargatchew Tesfaye. “The Funeral customs of the Kottu of Harar.” *Ethnological society Bulletin.* Ed. Alula Pankhurst. Vol. 1, No 7. Addis Ababa, Addis Ababa University, 2002.

Bauman, Richard. *Verbal Art as performance.* Waveland: Waveland University press. 1977.

*Encyclopedia of Religion and Ethics.* Vol. IV. Morrison and Gibb Limited, Great Britain.

Fassika Bellete. “The death Customs Among the Amharas of Šäwa”.” *Ethnological society Bulletin.* Ed Alula Pankhurst Vol. 1 No 7, Addis Ababa, Addis Ababa University press. 2002.

Finnegan, Ruth. *Oral Tradition and the verbal Arts: a Guide to Research practices.* New York: Thomson Publishing Company, 1992.

Martha C sims and Martine Stephens. *Living Folklore: An Introduction to the Study of people and their traditions.* Ohio: Utah state University press. 2005.

Negga Tessema. "The Death Customs in the province of Tigre" *Ethnological society Bulletin.* Ed. Alula Pankhurst Vol. 1 No 5. Addis Ababa, Addis Ababa University press. 2002.

*The Encyclopedia Americana.* International Edition. Grolier Incorporated, 1983.

*The world Book Encyclopedia.* World Book,Inc.a scott Fetzer company Vol. 5, USA: 1992.

*The world Book Encyclopedia.* World book- Child craft International, Inc. Vol, 7. USA. 1978.

Vansina, Jan. *Oral Tradition as History.* USA: The university of Wisconsin press. 1985.

## አባሪዎች

### አባሪ አንድ፡- የመረጃ አቀባዮች ዝርዝር ሁኔታ (ፕሮፋይል)

| ተ.ቁ | የዋና መረጃ አቀባይ ስም | ዕድሜ | ጾታ | ሐይማኖት | ሥራ | መረጃ የተሰበሰበበት ቀን | መረጃ የተሰበሰበበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ሼህ ሰይድ ቢላል | 49 | ወ | እስልምና | የደ/ማ ሸሪአ ፍ/ቤት ዳኛ (ቃዲ) | ሀሙስ ጥር 17/2004 ዓ.ም | መስጊድ ግቢ ውስጥ |
| 2 | ቄስ ወልደትንሳኤ አለማየሁ | 52 | ወ | ክርስትና | የቤተክርስቲያን አገልጋይ | ቅዳሜ ጥር 19/2004 ዓ.ም | ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ |
| 3 | መሪጌታ ሊባኖስ የተመኝ | 64 | ወ | ክርስትና | በደ/ማ ከተማ ቤተ ክህነት ሰባኪ ወንጌል | ሰኞ ጥር 21/2004 ዓ.ም | በመኖሪያ ቤታቸው ግቢ ውስጥ |
| 4 | መጋቢ አእላፍ ጥበቡ የሽታ | 69 | ወ | ክርስትና | የምስ/ ጎጃም ዞን ሀገረ ስብከት የስብከተ ወንጌል ሀላፊ | ረቡዕ ጥር 23/2004 ዓ.ም | በቢሮአቸው |
| 5 | አቶ አንዳርጌ ተረፈ | 65 | ወ | ክርስትና | ጡረተኛ | ቅዳሜ ጥር 19/2004 ዓ.ም | ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ |
| 6 | አቶ አህመድ ኑር ያሲን | 61 | ወ | እስልምና | በደ/ማ/ከ/ እስልምና ጉዳይ ስራ አስፈጻሚ | ሐሙስ ጥር 17/2004 ዓ.ም | መስጊድ ግቢ ውስጥ |
| 7 | ሼህ መሀመድ ሙሂ | 70 | ወ | እስልምና | የግል | ቅዳሜ ጥር 19/2004 ዓ.ም | መስጊድ ግቢ ውስጥ |
| 8 | አቶ ጌታቸው ኢሳ | 44 | ወ | እስልምና | ነጋዴ | ሰኞ ጥር 21/2004 ዓ.ም | ለቅሶ ቤት |

| ተ.ቁ | የንኡስ መረጃ አቀባይ ስም | ዕድሜ | ጾታ | ሐይማኖት | ሥራ | መረጃ የተሰበሰበበት ቀን | መረጃ የተሰበሰበበት ቦታ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | አቶ ዳኛቸው ቢልልኝ | 46 | ወ | ክርስትና | ግብርና | ሰኞ ጥር 21/2004 ዓ.ም | ለቅሶ ቤት |
| 2 | ሌቴናል ኮሎኔል ያደሳ | 67 | ወ | ክርስትና | የአድር ሊቀመንበር | ማክሰኞ ጥር 22/2004 ዓ.ም | ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ |
| 3 | ቄስ ይትባረክ አለሙ | 50 | ወ | ክርስትና | የቤተክርስቲያን አገልጋይ | እሁድ ጥር 20/2004 ዓ.ም | ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ |
| 4 | ወ/ሮ የትምወርቅ አያሌው | 38 | ሴ | ክርስትና | የቤት እመቤት | ማክሰኞ ጥር 22/2004 ዓ.ም | ለቅሶ ቤት |
| 5 | አቶ ግርማ ተክለሃይማኖት | 42 | ወ | ክርስትና | ነጋዴ | አርብ ጥር 18/2004 ዓ.ም | ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ |
| 6 | ወ/ሮ አበበች መኮንን | 48 | ሴ | ክርስትና | መምህርት | ሰኞ ጥር 21/2004 ዓ.ም | በመኖሪያ ቤታቸው ውስጥ |
| 7 | ወ/ሮ አያልነሽ ወርቁ | 39 | ሴ | ክርስትና | የቤት እመቤት | እሁድ ጥር 20/2004 ዓ.ም | ለቅሶ ቤት |
| 8 | አቶ ታዬ አምባቸው | 69 | ወ | ክርስትና | ጡረተኛ | ሐሙስ ጥር 17/2004 ዓ.ም | ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ |
| 9 | አቶ ሰውነት መኩሪያ | 56 | ወ | ክርስትና | ነጋዴ | አርብ ግንቦት 27/2004 ዓ.ም | ቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ |
| 10 | ሐጂ ጁሐር ሳሊህ | 72 | ወ | እስልምና | ጡረተኛ | ቅዳሜ ጥር 19/2004 ዓ.ም | ለቅሶ ቤት |
| 11 | አቶ መሐመድ ሐሰን | 45 | ወ | እስልምና | ነጋዴ | ቅዳሜ ጥር 19/2004 ዓ.ም | ለቅሶ ቤት |
| 12 | ሼህ ሙስጠፋ | 54 | ወ | እስልምና | የግል | ሰኞ ጥር 21/2004 ዓ.ም | መስጊድ ግቢ ውስጥ |
| 13 | አቶ ኢብራሂም አደም | 39 | ወ | እስልምና | ነጋዴ | እሁድ ጥር 20/2004 ዓ.ም መስኪድ ግቢ ውስጥ | መስጊድ ግቢ ውስጥ |
| 14 | ወ/ሮ ሶፊያ አህመዲን | 41 | ሴ | እስልምና | የቤት እመቤት | ረቡዕ ግንቦት 29/2004 ዓ.ም | ለቅሶ ቤት |

## አባሪ ሁለት

ለመረጃ አቀባዮች የቀረቡ መንደርደሪያ ጥያቄዎች

- ሞት ምንድነው? ከመጽሐፍ ቅዱስ/ ከቅዱስ ቁርዓን ጋር በተያያዘ እንዴት ይገለጻል?
- ሰው ሲሞት በቅደም ተከተል የሚደረጉ የለቅሶ ስነስርአቶች ምን ምን ናቸው?
- የተለየ ክዋኔ የሚደረግላቸው አሉ? ለምሳሌ ህጻን/አዛውንት፣ ወንድ/ሴት፣ ሀብታም/ደሃ፣ የሀይማኖት አባት/ ተራ ሰው ወዘተ. ሲሞት የሚደረግ የተለየ ስነስርአት አለ? ለምን?
- ክዋኔዎቹ ለምንድን ነው የሚደረጉት? ትርጉማቸው ምንድነው?
- የማህበረሰቡ የስራ ክፍፍል ድርሻ ምን ይመስላል?
- የለቅሶ ስነስርአት ክዋኔው ለምን ያህል ጊዜ ይቆያል? ለምን?
- ቀሪ ዘመድ ወይም ቤተሰብ ለሟች ሀዘኑን የሚገልጽባቸው ምን ምን መንገዶች አሉ?
- ለሟች መታሰቢያ ይደረጋል? መታሰቢያ የሚደረግላቸው እነማን ናቸው?
- መታሰቢያ የሚደረገው መቼ መቼ ነው? ለምን?

# ማረጋገጫ

ይህ የጥናት ጽሁፍ የእኔ የግል ስራ መሆኑንና በፅሁፉ ውስጥ የተጠቀምኩባቸውን ተዛማጅ ፅሁፎችንና መረጃዎችን በሙሉ በትክክል የጠቀስኩ መሆኔን አረጋግጣለሁ፡፡

ስም:- መንናዬ እንግዳወርቅ

ፊርማ:-

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝምና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ የአማርኛ ቋንቋ፣ ስነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

መስከረም፣2005 ዓ.ም

አዲስ አበባ